# አ ገ ቱ ኒ

## ተምረን ወጣን

መስፍን ወልደ ማርያም

አዲስ አበባ 2002

አገቱኒ

Copyright © 2010 by Mesfin Wolde-Mariam
የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው
መጋቢት 2002 ዓ.ም.

All rights reserved. No part of this book may be reproduced or transmitted in any form or by any means without written permission from the author.

ISBN
Printed in USA by 48HrBooks (www.48HrBooks.com)



# ኢትዮጵያ የሁላችንም አገር ናት።

በ1997 ዓ.ም. የነጻነት ጮራን ለማድመቅ ሲጥሩ
የመጨረሻውን መስዋዕትነት ለከፈሉ፣
ለቆሰሉና ለተጎዱ፤
ለታሰሩትና ከነቤተሰቦቻቸው ለተጉላሉ፣
ለታሰሩት የከፉ ቀን አለኝታና አጋር ሆነው ለለፉት፣
በውጭ አገር በብርድና በጸሐይ ድምፅ ለሌላቸው ለጮሁት፣
ከሚወዷት አገራቸውና ከሚወዱት ወገናቸው ተለይተው በስደትና በናፍቆት
ለሚጨነቁት፣
ሁሉ በአክብሮት እጅ እነሣለሁ፤
ብርሃኑን ብልጭ አድርገው ድርግም ላደረጉት ቅን መንፈስና ወኔ
እንዲሰጣቸው አምላክን እለምናለሁ
የብርቱካን ሚደቅሳን እናትና የብርቱካን ሚደቅሳን ልጅ የመረረ ሐዘን
የሚያዳምጥ ኅሊና እንዲሰጣቸውም እለምናለሁ

## ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደእግዚአብሔር ታደርሳለች

እርስበርችሁ ከመዋደድ በቀር ለማንም ዕዳ
አይኑርባችሁ፤
ሌላውን የሚወድ ሕግን ፈጽሞታልና፤

## ስለዚህ ፍቅር የሕግ ፍጻሜ ነው።

ሮሜ 13/8

## ማውጫ

### ክፍል አንድ


፩ እንደመቅድም- እኔና ሥልጣን ........................................ 5
፪. ከፉ ቀን ጥሩ ነው........................................ 24
፫. የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት አንዳንድ አንቀጾች ........................................ 30
፬. የቅድመ ቅንጅት የፖሊቲካ ሁኔታ ........................................ 34
፭. የቅንጅት ዓላማ ........................................ 43
፮. ምርጫ 97 ........................................ 49
፯. ቅንጅት ተሸነፈ ተባለ ........................................ 58
፰. እስር ቤት፡-ማእከላዊና ቃሊቲ ........................................ 68
፱. ክስና ፍርድ ቤት ........................................ 78
፲. ሽምግልናና እርቅ ........................................ 105
፲፩. ፖሊቲካና የሥልጣን ጥም በኢትዮጵያ ........................................ 123
መደምደሚያ ........................................ 141


### ክፍል ሁለት


መግቢያ ........................................ 151
አንድ፡-ራእይ ኢትዮጵያ በ2020 -- ከየት ወዴት
........................................ 154
ሁለት፡- የሞት ቅጣትአገዛዝና የባለሥልጣኖች ወንጀል
........................................ 169
ሦስት፡-መግደልና ማስገደል፤ ተንጋሎ የተፋ፣ ለራሱ ከፋ
........................................ 174
አራት፡-መላ ወይስ ዱላ
........................................ 183
አባሪ፡-ለቅንጅት ምክር ቤት የስንብት ደብዳቤ ........................................ 194




# ፩
# እኔና ሥልጣን

## *መንደርደሪያ*

ብዙ ሰዎች ስለእኔ «ታሪክ» ለመጻፍ ይፈልጋሉ፤ ወይም እንድጽፍ ይገፋፉኛል፤ እኔ በበኩሌ ታሪክ የሚባል ነገር የለኝም፤ የቃሊቲ ጓደኛዬ ዓባይነህ ብርሃን ለጋዜጠኞች ሲናገር «መስፍን ምን ሥራ ሠርቶ ያውቃል ወሬ ነው እንጂ» አለ ብሎ አንድ ጋዜጠኛ የእኔን መልስ ለማወቅ ደወለልኝ፤ ለእኔ ዓባይነህ በተናገረው «ሥራ»ና «ወሬ» በተባሉት ቃላት ትርጉም ላይ ከተስማማን ምንም ስሕተት አላገኘሁበትም፤ ይህንን ስነግረው ጋዜጠኛው ግር አለው፤ እንደተሰደብሁ ቆጥሬው የምናደድ መስሎት ነበረ፤ አብዛኛውን ሕይወቴን ያሳለፍሁት በማስተማር ነው፤ ዓባይነህ ወሬ የሚለው! ማስተማር ታሪክ የሚሠራበት ተግባር አይደለም፤ እያንዳንዱ ተማሪ የትምህርቱ ዘመን ሲያበቃ ከአስተማሪዎቹና ከትምህርት ቤቱ ጋር ያለው ግንኙነት እየተቋረጠ ይሄዳል፤ አንዳንዴ በአጋጣሚ አንዳንድ ተማሪዎችን ከተስፋ መቁረጥ ለማውጣት ይቻል ይሆናል፤ ሁለት ምሳሌዎችን ልስጥ፡፡

አንድ ቀን የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ የአራተኛ ዓመት ተማሪ ቢሮዬ መጣና ትምህርቱን ለማቋረጥ መወሰኑንና ከዲኑም ጋር ተነጋግሮ መጨረሱን ነገረኝ፤ በዕድሜ ከኔ የሚያንስ አልነበረም፤ በንግዱ ዓለም ቆይቶ በትምህርት ናፍቆት ተገፍቶ በራሱ ጥረት ለዩኒቨርሲቲ የበቃ ሰው ነው፤ የቀረው ስድስት ወር ብቻ ነው፤ የሚሰጠኝ ምክንያት ሁሉ አላጠግብህ አለኝ፤ ስለዚህም ውሳኔውን ተቃውሜ ለሦስት ሰዓት ያህል በክርክር ወጥሬ ያዝሁትና ሀሳቡን አስለወጥሁት፤ ፈተናውን አልፎ ተመረቀ፤ የተመረቀ ዕለት የተጠቀለለውን ዲፕሎማ አመጣና «እንካ ያንተ ነው፤» አለኝ፤ የራስህ የልፋትህ ውጤት ነው ብዬው ተለየኝ፤ይህንን ተማሪ ከራሱ ፍርሃት ማዳኔ እርካታ ሰጥቶኛል፡፡

*ሁለተኛ* አንዲት ቆንጆ ልጅ እኔ ክፍል እንዳለች ባውቅም አብዛኛውን ጊዜ በር ላይ ብቻዋን ቆማ ክፍል ሳትገባ ትቀራለች፤ አንድ ቀን ቢሮ እንድትመጣ ነገርኋትና ስትመጣ ለምን ክፍል እንደማትገባ ስጠይቃት እንደማትፈልግ ነገረችኝ፤ ታዲያ ለምን ትመጫለሽ? በወላጆችዋ አስገዳጅነት፤ ለዚች ተማሪ ትምህርት ለእንጀራ የሚያስፈልጋት አልነበረም፤ ስለዚህ ትምህርት ለጌጥ እንደሚሆንም አሳመንኋትና ተለያየን፤ አሜሪካ ሄዳ ትምህርት ለእንጀራን ተማረች፡፡

በተረፈ ከአፄ ኃይለ ሥላሴ ጋር ተጋፍጠን ኢየሱስ ወርቅ ዛፉ ከዩኒቨርሲቲ ሲመረቅ የለፋበትንና ያገኘውን ውጤት በይፋ እንዲታወቅለት ዲፕሎማውን ከጃንሆይ ባይቀበልም ስሙ እንዲጠራ ማድረጋችን ደስ ያሰኛል፤ በአጠቃላይ ሲታይ ግን ትውልድ ሲመጣና ትውልድ ሲሄድ እያስተናገደ አስተማሪ ታሪክን ለመሥራት ዕድል የለውም።

እያንዳንዳችን ከልጅነታችን ጀምሮ ጠመዝማዛ፣ ወይም መንታ፣ ወይም ኮረኮንችና እሾሃማ መንገዶች ይጋረጡብናል፤ ከእነዚህ የትኛውን መንገድ ይዘን እንደምንጓዝ አብዛኛውን ጊዜ የምንወስነው እያንዳንዳችን ራሳችን ቢሆንም አንዳንዴ አስገዳጅና ከአቅም በላይ የሆኑ ኃይሎችም ይወስኑልናል፤ ሌሎች ኃይሎች ቢወስኑልንም ያንን መንገድ እስከመጨረሻው ለመከተል፣ ወይም ላለመከተል ኃላፊነቱ የእያንዳንዳችን ብቻ ነው፤ በሌላ አነጋገር ኑሮአችንን የምናንጸው እያንዳንዳችን ነን፤ ስለዚህም በአጠቃላይ ባለንበት ሁኔታ ቢከፋንም ቢደላንም ተጠያቂዎቹ ራሳችን እንጂ ሌላ ሰበብ አይኖረንም፤ ለኑሮአችን አለመሳካት ሰበብ መፈለግ ራሳችንን ይበልጥ ከማዳከም ሌላ ጥቅም የለውም፤ በምመርጣቸው መንገዶች ኑሮዬን የማንጸው እኔ ነኝ፤ ሌሎች ሰዎች በበጎም በከፋም አስተዋጽኦ እንዳላቸው ሳይታለም የተፈታ ነው፤ በጎውን አስተዋጽኦ እየተቀበልሁና እየቀረብሁ፣ ከከፋው ደግሞ ለመሸሽና ለመራቅ እየሞከርሁ ኑሮዬን መምራት የምችለው እኔው ነኝ፤ ለራስ ኑሮ ኃላፊነትን መቀበል ለእኔ ዋናውና የመጀመሪያው መመሪያ ነው፤የኔን የኑሮ ሁኔታ በማንም ሌላ ሰው ላሳብበው አልችልም።

እኔ በኃላፊነት የማልጠየቅባቸውና ሌሎች ሰዎችም በኃላፊነት የማይጠየቁባቸው ብዙ ነገሮች አሉ፤ ለምሳሌ ቁመቴ፣ የቆዳዬ ቀለም፣ የእናት ቋንቋ የሚባለው፤ ሃይማኖትም ቢሆን የወረስሁት ነው (ከቡዲስቶች፣ ከሂንዱዎች፣ ጀምሮ ሌሎችንም ሃይማኖቶች ለማጥናት ሞከሬ እግዚአብሔር በአፍአዊ ቲያትር የማይገኝ መሆኑን ተገንዝቤ የወረስሁትን ለመጠበቅ ወሰንሁ)፤ አንድ ሰው ኃላፊነት እንዲቀበል የሚገደደው እሱ ራሱ ላደረገው ወይም ለተናገረው ብቻ ነው፤ በኑሮ ጠመዝማዛ መንገድ የሚያጋጥሙኝን ጉዳዮች ሁሉ እንዴት እንደተወጣኋቸው፣ ወይም እንዴት እንዳሸነፍኋቸው፤ ወይም እንዴት እንዳሸነፉኝ የእኔ ኃላፊነትና ተጠያቂነት ይሆናል፤ የአንድ ሰው ኑሮው የከፋም ይሁን የለማ ራሱ የካበው ወይም ያፈረሰው ውጤት ነው፤ ሰው ኑሮውን ይመስላል የሚባለውም ለዚህ ይመስለኛል።

ሁለተኛው የኑሮ መመሪያ ብዬ የያዝሁት በማኅበረሰብ ውስጥ ስለምኖር፣ ማኅበረሰቡ ለእኔ እድገት ያደረገውን ትልቅና ወሳኝ አስተዋጽኦ ነፍሴ ድረስ ይሰማኛል፤ ስለዚህም የሕዝቡ ኑሮ፣ ደህንቱ፣ ጉስቁልናው፣ ችጋሩ፣ ጥቃቱ ያንገበግበኛል፤ በአገኘሁት አጋጣሚ ሁሉ፣ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ



እጮህለታለሁ፤ ለሰውም፣ ለእግዚአብሔርም እነግርለታለሁ፤ ከዚህ ቃል ኪዳን በገንዘብ ገዝቶም ይሁን በጉልበት አስፈራርቶ የሚያስወጣኝ የለም።

## ልጅነት

የማስታውሰው የመጀመሪያው ጠምዛዛ መንገድ ያጋጠመኝ አምስት ዓመት ግድም ሲሆነኝ ነው፤ እኅቴና እኔ ከአባታችን ጋር ነበርን፤ አባታችን ወደማይጨው ሲዘምቱ ግርግሩና ዝግጅቱ ሁሉ ይታየኛል፤ እናታችን እየመጡ ይጠይቁን ነበር፤ እሳቸው ሲሄዱ ሁልጊዜም እኔ በጣም እየጮህኩ አለቅሳለሁ፤ አንድ ቀን እንዲያውም አብሬ ካልሄድሁ ብዬ ድርቅ ስላልሁ ከእናቴ ጋር ሄድሁ፤ አባቴ ከማይጨው ሲመለሱ እኔን እቤት አላገኙኝም፤ በጣም እንዳሳዘናቸውና ልክ እንደትልቅ ሰው አድርገው እንደተቀየሙኝ ብረዳም እስካሁን አልገባኝም።

ለንግዲህ የመጀመሪያው በደመ-ነፍስ «የመረጥሁት» መንገድ ከእናቴ ጋር መኖርን ነው፤ እናቴ ደግሞ ሌላ መንገድ ውስጥ አስገድደው አስገቡኝ፤ ትምህርት ቤት የገባሁት በእግር ብረት ታስሬ ነው፤ እግር ብረቱ እግሬን እንዳይፍቀኝ መሀሉ ላይ ገመድ አስሬ፣ ገመዱን በእጄ ወደላይ ይዤ በቅምቡርስ ጉዞ ወደትምህርት ቤት ለሁለት ወር ያህል ተመላልሻለሁ፤ በትምህርት ፈጠንሁና አስተማሪዬ (አለቃ ታምራት የሚባሉ ጎንደሬ ነበሩ) ከአለቆቹ አንዱ አደረጉኝ፤ መጀመሪያ ሥልጣን የቀመስሁት በዚህ ነው፤ ጣመኝ፤ አንድ ተማሪ «ጸ» ስለው «ሰ» ያለ እንደሆነ ጆሮው እስቲቀላ ማሸት አንዱ የሥልጣን መግለጫ ነበረ፤ በዚያ ላይ አለንጋም ወይም እርጬሜ አለ፤ የመጀመሪያው ደረጃ በሥልጣን የመባለግ ትምህርት ነበር! እግር ብረቱ ከወለቀም በኋላ የአለቃነት ጣሙ እየገፋፋኝ ጥሩ ተማሪ ወጣኝ፤ አለቃ ታምራት ከሊቅነታቸው በተጨማሪ ስዕልና ሐረግ መሥራት ይችላሉ፤ ነፍሱን ይማረውና ለይገዙ ብሥራት ሐረግ መጀመሪያ ያሳየሁት እኔ ከአለቃ ታምራት የተማርሁትን ነበር፤ እሱ ግን እጅግ በጣም ሠለጠነበትና ዛሬ ስሙ የሚጠራበት ሆኖአል።

በአለቃ ታምራት ትምህርት ቤት እንዳለሁ አንድ እሙን የሚባል ጓደኛ ነበረኝ፤ እሱና ሁለት ሌሎች ልጆች ሆነን የዚህን ዓለም ከንቱነት ስናወራ ቆየንና እንመንን ብለን ወዲያውኑ ወስነን ቀበናን ተሻግረን ራስ ካሣ ጫካ ገባን፤ አውጡን፣ ቀጋውን፣ አጋሙን ስንበላ አመሸንና ጀምበር ቆልቆል ማለት ስትጀምር አንዱ «እናቴ ናፈቀችኝ!» ሲል ወዲያው ሁላችንም እኔም! እኔም! እያልን ቁልቁለቱን ወርደን በየቤታችን ገባን፤ ስለዚህ ለአንድ ቀን ያህል መንኘለሁ! በኋላም ቅዳሴ ስንማር ከእሙን ጋር ቀጨኔ እንቀፍፍ ነበር።

በዚህ ትምህርት ቤት እያለሁ ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ተከፈተና አባቴ እዚያ እንድገባ ፈለጉ፤ ነገር ግን ያኮተልካሉ ስለተባለ እምቢ ብዬ ሌላ መንገድ መረጥሁና ወደቤተ ክርስቲያኑ ትምህርት አደላሁ፤ ቅዳሴን ከመምሬ

አስፋው ከሚባሉ ቄስ ተማርሁ፤ የውዳሴ ማርያምና ከዚያም አለፍ ያለ ዜማ አለቃ አካሉ ወልደ ማርያም ቤት ልጃቸውን ዘውገ ወልደ ማርያምን (ሁሉንም ነፍሳቸውን ይማረው) የሚያስተምሩላቸው መምህር ስለነበሩ እኔም ተፈቅዶልኝ እዚያ እያደርሁ ተማርሁ፡፡

ሌላ ያልታሰበ ጠምዛዛ መንገድ አጋጠመኝ፤ ለጥምቀት በኪዳነ ምሕረት ታቦቶችን አጅበን ሄደን ማታ ጫካው ዳር እሳት እያነደድን ስንሞቅ ከአንድ ልጅ ጋር ተጣላን፤ የተለኳኮሰ ጭራሮ ወረወረብኝ፤ እሱ ተለቅ ያለ ሰውነቱም ደንዳና ነበረ፤ ድብድቡን ስንጀምር በያዘው ዱላ ጭኔ ላይ ዠለጠኝ፤ ዱላ ስላልያዝሁ ሥጋ ለመብያ የያዝሁትን ሰንጢ አወጣሁ፤ ፈራና ሲሮጥ ወደቀ፤ የወደቀበት ሄጄ አንዴ ወጋሁት፤ እሱን ወደሀኪም ቤት ወሰዱት፤ እኔን ፖሊሶች እጆቼን በገመድ አስረው አሳደሩኝ፤ ጠዋት ወደፖሊስ ጣቢያ በገመድ እየጎተቱ ሲወስዱኝ እናቴ ወደጥምቀተ ባሕሩ ሲመጡ ተገናኘን፤በጭራሽ አልደነገጡም፤«ምንድን ነው ነገሩ?» ሲሉ ፖሊሱ አስረዳቸው፤ «እሱስ ግድ የለም» ብለው የት እንደሚወስደኝ ከጠየቁ በኋላ መንገዳቸውን ቀጠሉ፤ በሳቸው ሚዛን ከዚያ የከፋ ወንጀል አለ ማለት ነው፡፡

ገና ከልጅነቴ ጀምሮ ሰዎች ሁለት ተጻራሪ ጠባዮች እንዳሉብኝ ይነግሩኛል፤ እኔም ይታወቀኝ ነበር፤ ለምሳሌ አንድ ዓይነ ስውር ወይም በሌላ በሽታ የተያዘ ለማኝ መንገድ ዳር ተቀምጦ የሚያለቅስ በሚመስል ድምፅ ሲለምን እናቴ መጥተው እስቲወስዱኝ ድረስ አጠገቡ ቁጭ ብዬ አለቅስ ነበር፤

በሌላ ጊዜ ደግሞ ልጃገረዶች በገምቦ ውሀ ቀድተው ሲመለሱ ገምቦውን በድንጋይ ሳፈነዳው ደስ ይለኝ ነበር፤ ማታ ፍዳዬን እቀበላለሁ፤ ተናዳጅና ጠበኛነቱን በኳስ ጨዋታና በጸሎት ለመግራት የቻልሁ ይመስለኛል፤ በሌሎች ስቃይ መጨነቁ ግን እስካሁንም የለቀቀኝ አይመስለኝም፤

በዊንጌት በነበርሁባቸው ወሮች ቅዳሜ ወይም እሑድ ወደ ጴጥሮስ ወጳውሎስ መቃብር ውስጥ እየገባሁ ከሙታን ጋር አወራ ነበር፤ በተለይ የቆንጆ ሴቶችና የሕፃናት መቃብር ላይ በጣም እያሳዘኑኝ «ምን ነካችሁ? ምን አገኛችሁ?» እያልሁ እጠይቅ ነበር፤ የአንዲት ሴትን ስም እስካሁን አስታውሰዋለሁ፤ -ጥሩነሽ ሽምጥር፡፡

አሥራ ሁለት ዓመት ግድም ሲሆነኝ ሦስት ጠምዛዛ መንገዶች አጋጥመውኛል፤ ሁለት ጊዜ ታስሬአለሁ ማለት ነው፤ አንዴ በእግር ብረት፣ አንዴ በገመድ፤ ሁለቱንም ጊዜ መታሰሬ ረድቶኛል፤ አስተምሮኛል፤ በተለይም ሁለተኛው እስር የመጣው ብዙ ሰዎች «ይኸ ልጅ አንድ ቀን ክንፍ አውጥቶ ይሄዳል» የሚል አስተያየት በነበራቸው ጊዜ መሆኑ ሰይጣን ምን ጊዜም ቢሆን ሩቅ እንዳልሆነ አረጋግጦልኛል፡፡

በተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት በተመላላሽነት ስገባ ሦስተኛውን ጠመዝማዛ መንገድ ጀመርሁ፤ ጥቂት ወራት ያህል ከተማርሁ በኋላ በአዲስ



አበባ ውስጥ ከባድ ችግር ገብቶ ስለነበረ ያለኝን ጥሩ የእጅ ጽሑፍ ችሎታ በመጠቀም እናቴን ለመርዳት ማዘጋጃ ቤት በር ላይ ማመልከቻ ጸሐፊ ሆንሁ፤ ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች ትምህርቴን እንድቀጥል ስለፈለጉ በአዳሪነት እንድገባ ለትምህርት ሚኒስቴር ማመልከቻ እንድጽፍ ገፋፉኝና ማመልከቻውን ለአቶ መኮንን ዘውዴ ሰጠሁ፤ ስለትምህርቴ ከምክትል ዲሬክተሩ የምስክር ወረቀት እንዳመጣ ጠይቀውኝ ወሰድሁላቸው፤ ወዲያው ደብዳቤ ጽፈው እንድገባ ሆነ፤ ከብዙ ዓመታት በኋላ አቶ መኮንን በሕይወት እያሉ አጋጣሚውን አግኝቼ አዳሪነት እንዳስገቡኝና ትልቅ እርዳታ እንዳደረጉልኝ ስለነገርኋቸው በጣም ደስ ይለኛል፤ እንዲህ ያለ አጋጣሚ ሳላገኝ ሌሎች አምልጠውኛል፡፡

አዳሪነት አዲስ ዓለም! ደብተሩ፣ እርሳሱ፣ መጽሐፉ፣ ልብሱ፣ አልጋው፣ ምግቡ፣ ትምህርቱ እንደልብ! ጨዋታው እንደልብ! ጂምናስቲክ መሥሪያው እንደልብ! አስተማሪዎቻችን የካናዳ የካቶሊክ ቄሶች ነበሩ፤ የተመሰከረላቸው አስተማሪዎች ናቸው፤ በተለይ ጠንክሮ መሥራትና የኃላፊነትን ስሜት በተማሪዎች ላይ ለማሳደር ትልቅ ጥረት ያደርጉ ነበር፤ ተሳክቶልኝ እንደሆነ ባላውቅም እኔም በአስተማሪነቴ የእነሱን አርአያ ተከትዬ ነበር፡፡

በተፈሪ መኮንን ገና አምስተኛ ክፍል ሆኜ እናቴ በጠና መታመማቸው ተነግሮኝ አስፈቅጄ ሄድሁ፤ ስደርስ ምንም አይሰሙም ነበር፤ በበነጋታው ዓረፉ፤ ቀብሩ ላይ ሳለቅስ «እንግዲህ ማን ይችለኛል!» እያልሁ እጮህ ነበር፤ ነገር ግን እኔን ትተው ይሄዳሉ ብዬ አላመንሁም፤ ስለዚህም አንድ ሳምንት ሙሉ በየቀኑ ሌሊት በአሥራ አንድ ሰዓት እየተነሣሁ መቃብራቸውን ትኩር ብዬ እየተመለከትሁ የተነቃነቀ እንደሆነ ለመቆፈር እዘጋጅ ነበር፤ ከሳምንት በኋላ ቁርጤን አወቅሁት፤ ስለዚህም ለመቃብራቸው እሳቸውን የማላሳፍር ጨዋ ሰው ለመሆን ቃል ኪዳን ገባሁ፤ ከልቤ የማይወጣው ሐዘን ግን ለልፋታቸው ሁሉ ትንሽም ውለታቸውን ሳልመልስና ከችግር ሳላወጣቸው መቅረቴ ነው፤ የእናቴ መሞት ጠባዬን በቁርጠኛነት እንድገራ ከጸሎት ጋር ረድቶኛል፤ አንድ በአለቃ ታምራት ትምህርት ቤት የነበረና ዛሬም ያለ አብሮ-አደጌ አንድ ቀን በመንገድ ላይ አቆመኝና ባለፈው ማታ ስለእኔ ትልቅ ክርክር ተነሥቶ እንደነበረ ነገረኝ፤ በግብዣው ላይ ከነበሩት አንዱ እኔ ከመስፍን የተማርሁት አንዱ ነገር ትእግሥት ነው በማለቱ አብሮ-አደጌ ግራ ይገባውና ስለሌላ ሰው ነው ወይስ እኔ ስለማውቀው መስፍን ነው የምታወራው? በማለት ጠይቆ ካረጋገጠ በኋላ እኔ የማውቀው መስፍን ወልደ ማርያም ትእግሥት ሊያስተምርህ አይችልም፤ ጠብ ያለሽ በዳቦ የሚል ሰው ነው ብዬው በጣም ተከራከርን ብሎ አጫወተኝ፤ ሁለቱም አልተሳሳቱም፤ የሚያውቁኝ በተለያየ ጊዜና በተለያየ ሁኔታ ነው፤ ሰው ራሱን መለወጥ ይችላል፤ ለሞቱት እናቴ የገባሁት ቃል ኪዳን ነው፡፡

ሰይጣን በተፈሪ መኮንንም ገባ፤ አንድ አስተማሪ በክፍሉ ተማሪዎች ተናዶ ከነዘርማንዘራቸው ሙልጭ አድርጎ ሰደባቸው፤ ከክፍል ሲወጡ ያለቅሱ ነበር፤

ሲነግሩን ሁላችንም ተናደድን፤ ቀስ እያለ በጣም ከባድ የሆነ ረብሻ ተነሣ፤ እኔ ተገፍቼ ከቀደሙት መሀል ተገኘሁ፤ አንማርም በማለታችን ብቻ ሳይሆን የመጣውን ባለሥልጣን ሁሉ አንሰማም እያልን በመመለሳችን አገር ተረበሸ፤ ትምህርት ቤቱ በክብር ዘበኛ ተከበበና ጃንሆይ ከነልጆቻቸውና ከነሚኒስትሮቻቸው መጡ፤«ከየትም ለቃቅመን አምጥተን» ያሉት ያን ዕለት ነው፤ ነገሩ እውነት ቢሆንም ማቴዎስ ጥግነህ የሚባል ተማሪ «ጃንሆይ! አባቶቻችን ግብር ይከፍላሉኮ!» ብሎ የመለሰላቸውም እውነት ነው፡፡
በዚህ ረብሻ ምክንያት ሀያ ሁለት የምንሆን ልጆች ከተፈሪ መኮንን ወደሌሎች ትምህርት ቤቶች ተዛወርን፤ እኔ ወደዊንጌት ተዛውሬ ከሦስት ወራት በኋላ የለንደን ማትሪኪዩሌሽን ተፈትኜ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ሲከፈት እዚያ ገባሁ፤ እግዚአብሔር ይመስገንና በጠመዝማዛው መንገድ እዚህ ደረስሁ!
በትምህርት ቤት የጉርምስና ዘመን ከትምህርት ውጭ የነበረኝ ምኞት ጡንቻ ማፈርጠም ነበር፤ ጂምናስቲክ እሠራለሁ፤ ኳስ እጫወታለሁ፤ በተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት እነታደሰ ላቀው፣ (ነፍሳቸውን ይማረውና) ተሰማ ኃይሉ፣ ኃይሉ አፈወርቅ የኔው ቢጤ ነበሩ፤ ጡንቻ ማፈርጠም በጣም ትልቅ ነገር መስሎ ይታየኝ ነበር፤ በዊንጌትና በዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ እንደኔ ያለ የጡንቻ ፍቅር ያደረበት የማውቀው (ነፍሱን ይማረውና) ገብረ ክርስቶስ ደስታን ነው፤ ገብረ ክርስቶስ ቻርልስ አትላስ ከሚባል የታወቀ የጡንቻ አሠልጣኝ ጋር እየተጻጻፈ ይሠለጥን ነበር፤ በትምህርት ቤት የሚያገኘው ወተትም ስለማይበቃው በቀን አንድ ሊትር በኮንትራት ይመጣለት ነበር፤ በዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ውስጥ በሆድ አንደኛ እኔ፣ ገብሬ ሁለተኛ ነበርን፤ እንዲያውም እኔ መጥገብ ሳይሆን ጥርሴን ሲደክመኝ ነበር መብላት የማቆመው!
እስጢፋኖስ የሚባል የታወቀ ቦቅሰኛ ካላሠለጠንሁህ ብሎኝ ጡንቻዬን በቦቅሰኛነት ለመሞከር ጀምሬ ነበር፤ ነስር አቋረጠልኝና ተገላገልሁ፤ የጡንቻም ነገር ቀስ እያለ በመንፈሳዊነት ደበዘዘ፡፡

## ከልጅነት በኋላ — በሥራ ዓለም

### የመጀመሪያ ሥራ

ራስ ምታትና ነስር በጣም ስላስቸገረኝ ከዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ትምህርቴን አቋርጬ የመጀመሪያ ሥራዬ በእቴጌ መነን ትምህርት ቤት አስተማሪነት ነበር፤ የለበስሁት ኮሌጁ የሰጠኝን ልብስ፣ ጫማውም ከዚያው ነበር፤ ጠዋት ወደእቴጌ መነን ትምህርት ቤት ለመሄድ ስዘጋጅ ትልቅ አንጀባ ነበር፤ ነፍሳቸውን ይማርና ወርቁ ተፈራ ሰዓቱን ሰጠኝ፤ ንጉሤ ፍትሕአወቀ ክራቫት አሰረልኝና ጨዋ መስዬ አስተማሪነቴን ጀመርሁ፤ ገና ሃያ አንድ ዓመት ያልሞላኝ ጎረምሳ ነበርሁ፤



እንዳጋጣሚ ሥራ በጀመርሁ በጥቂት ወራት ውስጥ የትምህርት ቤቱ ዲሬክተር የነበሩት ወይዘሮ ስንዱ ገብሩ (ነፍሳቸውን ይማረውና) አዲስ ባል አግብተው ለመጀመሪያ ጊዜ ዕድሜያቸው ከገፋ በኋላ አረገዙ፤ እርግዝናው ችግር ብማስከተሉ ወደእንግሊዝ አገር ለህክምና ሄደው ለብዙ ወራት ቆዩ፤በቦታቸው ሌላ ሰው አልተመደበም፤ እንደሚመስለኝ እሳቸው በቀጥታ በንጉሠ ነገሥቱ የተሾሙ በመሆናቸው ትምህርት ሚኒስቴር እጁን ለማስገባት አልፈለገም፤ የማየው ችግር ገፍቶኝ በዚህ ከፍት የኃላፊነት ቦታ ላይ እኔ በየዋህነት ጥልቅ አልሁበት፡፡

በትምህርት ቤቱ የመጻሕፍት ችግር፣የስፖርት ዕቃዎች ችግር፣ የአስተዳደር ችግር በጉልህ ይታይ ነበር፤ እኔ ተማሪዎቹ ስላሳዘኑኝ ለትምህርት ሚኒስቴር ደብዳቤ እየጻፍሁ ወስጄ ለአቶ ሥዩም ያዕቆብ (የግምጃ ቤት ኃላፊ ነበሩ) እሰጣቸዋለሁ፤ ይስቁና እኔ ተራ አስተማሪ በመሆኔ እንዲህ ያለ ሥልጣን እንደሌለኝና እሳቸውም ሊያስተናግዱኝ እንደማይችሉ ያስረዱኛል፤ አይገባኝም፤ እኔ የጠየቅሁት ለተማሪዎቹ አስፈላጊ የሆኑ መጻሕፍትን ወይም የስፖርት ዕቃዎችን ነው፤ የሥልጣንን ነገር ምን አመጣው? ደብዳቤዬን ይዤ ወደአቶ በለጢ ገብረ ጻድቅ (ዋና ዲሬክተር) ዘንድ እሄዳለሁ፤ እሳቸው ይበልጥ ይስቁብኛል፤ ያስረዱኛል፤ አሁንም አይገባኝም፤ አቶ አካለ ወርቅ ቢሮ በር ላይ እቆምና ሲገቡ ጠብቄ ደብዳቤዬን እሰጣቸዋለሁ፤ አቶ ሥዩምም፣ አቶ በለጢም ያሉኝን እነግራቸዋለሁ፤ ስልካቸውን ያነሱና «ይሄ ልጅ ደመወዝ አልጠየቀ፤ ሹመት አልጠየቀ፤ ልሥራ ሲል እናሠራሀም እንበለው እንዴ? የጠየቀውን ስጡት እባካችሁ፤» ብለው ደብዳቤው ላይ ያዝዙና ይፈርሙልኛል፤ እየፈነጠዝሁ ወደአቶ ሥዩም ዘንድ ሄጄ እሰጣቸዋለሁ፤ እየሳቁ ደስ ብሏቸው የተጠየቀውን ያስረክቡኛል፤ ብዙ ከሆነ ወይ ጋሼ ክብረትን ወይ ጋሼ ሞገስን (የትምህርት ሚኒስቴር ሹፌሮች) ለምኜ ይወስዱልኛል፤ ትንሽ ከሆነ በጋሪ ጭኜ አወስዳለሁ፤ የልብ ልብ አገኘሁና የፒንግ ፖንግ ጠረጴዛና መጫወቻውን ጠየቅሁ፤ እንደለመድሁት ደረጃውን ሁሉ አዳርሼ አቶ አካለ ወርቅ ዘንድ ደረስሁ፤ ስልክ አንሥተው ወደተግባረ ዕድ ትምህርት ቤት ደወሉና የፒንግ ፖንግ ጠረጴዛው አስፈላጊ ከሆኑት ነገሮች ጋር ተሠርቶ ለእኔ እንዲያስረክቡ አዘዙልኝ እነጋሼ ክብረትን ለምኜ እጭንና ወደእቴጌ መነን!

እንደሌሎቹ ሁሉ አቶ አካለ ወርቅም በወጉ መሠረት ትክክል የሆነውን መልስ ቢሰጡኝ ኖሮ የእኔ ጥረት ሁሉ መክኖ ይቀር ነበር፤ ተማሪዎቹም ይጎዱ ነበር፤ እሳቸው ግን ወጉን ሁሉ ተሻግረው፣ የጥያቄዬን ተገቢነት ተገንዝበው ለጥረቴ ፍሬ አስገኙለት፤ አቶ አካለ ወርቅን የማመሰግናቸው በዚህ ብቻ አይደለም፤ አንድም ጊዜ ጥረቴ ከሥራ ፍላጎት ያላለፈና እንደባህላችን ወደደጅ ጥናት ያዘነበለ ሆኖ ሳይታያቸውና ሳያጎድፉብኝ በንጹሕነቱ በመመልከታቸው ነው፡፡

በአጭሩ የእቴጌ መነን ትምህርት ቤት ታሪኬ ብዙ ቁም ነገሮች ይታዩበታል፤ የሥልጣን ተዋረድ ጉዳይ፣ የሥልጣን አጠቃቀም ከወግና (ፎርማሊቲ ማለቴ ነው) ከመሠረታዊ ዓላማ ጋር መያያዝ ወይም አለመያያዝ፣ ሥልጣንና ወግ ሲቆራኙ ምን ያህል ለሥራ እንቅፋት እንደሚሆኑ፣ ሥልጣንና በጎ ፈቃድ ሲገናኙ ደግሞ ምን ያህል ሥራን በቀላሉና በርካሽ እንደሚያራምዱ፣ ሥልጣን ለሌለውና መሥራት ለሚፈልግ የሚገጥሙት እልህ አስጨራሽ እንቅፋቶች በግልጽ የሚታዩ ይመስለኛል፤ በሙሉ ነጻነት የሚሠራ ልበ-ሙሉ ባለሥልጣንና ቁጣን እየፈራ የሚጨነቅ ባለሥልጣን ኃላፊነታቸውን እኩል አይወጡም፡፡

ወይዘሮ ስንዱ ወልደውና አርፈው ከእንግሊዝ አገር ሲመለሱ የእኔን ሥራ ይሰማሉ፤ በአገዛዝ ሥርዓት ሥልጣን ያለው ሰው ፈሪ ነውና ጠርተው ያነጋግሩኛል፤ መናደዳቸውን የገለጹት እርስዎ ሲሉኝ የነበሩት አንተ በማለትና ለወንበራቸው የነበራቸውን ስጋት በመግለጽ ነበር፤ እኔ ገና የሃያ ዓመት ጎረምሳ ነኝ «እርስዎ አለቃዬ ከመሆንዎ ሌላ እናቴም ሊሆኑ የሚችሉ ነዎ፤ ስለዚህም አንተ በማለትዎ አልዋረድም፤ የእርስዎን ሥራ ስለሠራሁልዎ ያመሰግኑኛል እንጂ ይቀየማሉ ብዬ አልገመትሁም ነበር፤ ከአሁን ወዲያም ከእርስዎ ጋር አልሠራም፤» ብያቸው ተለያየን፤ ሙሉ እውነቱን መናገር ስለሚያስፈልግ በኋላ ግን ተመልሼ ሥራዬን እንድቀጥል በአቶ አካለ ወርቅ በኩል እንድታዘዝላቸው ሞከሩ፤ ካልተማመንን አብሮ መሥራት አይቻልም ብዬ በውሳኔዬ ጸናሁ፤ ጭራሽ አስፈላጊ ባልሆነበት ሁኔታም ቢሆን የሥልጣን ፍቅር ሥጋት ውስጥ እንደሚጨምር ተረዳሁ፡፡

## ሁለተኛ ሥራ

ሁለተኛው ሥራዬ በካርታና ጂኦግራፊ ኢንስቲትዩት በተባባሪ ዲሬክተርነት ነበር፤ ዲሬክተሩ አንድ አሜሪካን (እንደምጠረጥረውም ሲአይኤ) ነበር፤ በዚያን ጊዜ አሜሪካኖች የዓባይን ተፋሰስ በአውሮጵላን ፎቶግራፍ እያነሱ በተፋሰሱ ላይ ዝርዝር ጥናት ያካሂዱ ነበር፤ በዚህ ጥናት የተሳተፉ ኢትዮጵያውያን ወጣት መሀንዲሶች (ኃይሉ ሻውል፤ ደመቀ መታፈሪያና ሌሎችም...) ብዙ ነበሩ፤ የተነሣው ፎቶግራፍ በሙሉ በካርታና በጂኦግራፊ ድርጅት ይከማች ነበር፤ የዓየር ፎቶግራፉ ከመነሣቱ በፊት በጽሕፈት ሚኒስቴር በታዘዘ ደብዳቤ በአገር አስተዳደር ሚኒስቴር ውስጥ በአቶ ክብረት አስታጥቄ በሚመራ ኮሚቴ ውስጥ እንዳገለግል ታዘዝሁ፤ ኮሚቴው ሥራውን ሲጀምር «ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት አሜሪካኖች በዓየር ፎቶግራፍ እንዲያነሱ ስለፈቀዱ የሚያስከትለውን ጉዳት እንድታጠኑ» የሚል መመሪያ ተነበበ፤ ግራ ገባኝ፤ በቃለ ጉባኤው እንዲያዝልኝ ጠይቄ የሚከተለውን ተናገርሁ፤ «ፎቶግራፉ እንዲነሣ



በመፈቀዱ አልስማማም፤ ሁለተኛ እንዲያነሡ ከተፈቀደ በኋላ የሚያደርሰውን ጉዳት አጥኑ ማለት ዋጋ የለውም፤ ጉዳት መኖሩ ከተጠረጠረ መጠናት የነበረበት ሳይፈቀድ ነበር፤ አሁን ማድረግ የሚቻለው በዚህ የአሜሪካኖች ሥራ ኢትዮጵያ ልታገኝ የምትችለውን ያህል ጥቅም እንድታገኝ ማድረግ ነው፤ አንዱና ዋናው ጥቅም የካርታ ድርጅቱን በተለያዩ የካርታ ሥራ መሣሪያዎችና በሰው ኃይል ሥልጠና ማጠናከር ነው፤» በመጠቀም በኩል ያቀረብሁት ሀሳብ ከሞላ ጎደል ተቀባይነትን አገኘ፡፡

አንድ የተለየ ሹመት ይሁን ምን የማላውቀው ነፍሱን ይማረውና ሻለቃ ወርቅነህ ገበየሁ ያመጣብኝ ጣጣ ነበር፤ በጠረፍ ጉዳዮች የሚጠና ነገር ሲኖር እየነገረኝ እተባበረው ነበር፤ ይህንን ይዞ ለእኔ ሳይነግረኝ ከጃንሆይ አስፈቅዶ ከካርታ ሥራ ድርጅት ወደጸጥታ መሥሪያ ቤት መዛወሬን ከዚያው መሥሪያ ቤት ሰማሁ፤ ስገሰግስ ቢሮው ሄድሁና ጠየቅሁት፤ ማስፈቀዱን ነገረኝ፤ «የምትፈልገው ሬሳዬን ከሆነ አሁኑኑ አድርገው፤ እንኳን ከጃንሆይ ከእግዚአብሔርም ብታስፈቅድ በምንም ዓይነት መንገድ እዚህ መሥሪያ ቤት እንድሠራ አታደርገኝም፤» አልሁት፤ የተማራችሁት ሰዎችም ስለዚህ መሥሪያ ቤት ያላችሁ አመለካከት ያሳዝናል ብሎኝ ተለያየን፡፡

በአሜሪካኑ አለቃዬና በእኔ መሀከል የአይጥና የድመት ጨዋታ ሆነ፤ በትምህርት ሚኒስቴርም (ሚኒስትሩ ልጅ እንዳልካቸው መኮንን ነበሩ) ሆነ በአገር ግዛት ሚኒስቴር በእኔ በኩል ያለውን አመለካከት ችላ እያሉ ወደአሜሪካኖቹ ያዘነበሉ ሆኑ፤ በዚህ ጊዜ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ፕሬዚደንት የነበሩት ዶር. ማት በዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ አስተማሪ እንድሆን ጠይቀውኝ ከካርታ ሥራ ድርጅት ለመልቀቅ እያሰብሁ ባለሁበት ጊዜ ልጅ እንዳልካቸው ቀድመው ከሥልጣናቸው ያለፈ ደብዳቤ «ወደዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ተዛውረህ እንድትሠራ» ብለው ጻፉልኝ፤ ትምህርት ሚኒስቴር በዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ላይ፣ ያውም ዶር. ማት ባሉበት ምንም ሥልጣን አልነበረውም፡፡

## ሦስተኛ ሥራ

በዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ አስተማሪ ስሆን ስለኢትዮጵያ መልክአ ምድር ምንም አላውቅም ነበር፤ መረጃዎችን የምሰበስበው ከኢጣልያን መጻሕፍትና ካርታዎች ነበር፤ በጣም አድካሚ ነበር፤ ሌላ ቀርቶ የቦታ ስሞችን እንኳን ‹ቸ›ንና ‹ጨ›ን መለየት አልቻልም ነበር፤ ለፈረንጅ ቸና ጨ ያው ነው፤ በዚህ በኩል ተማሪዎች ብዙ አስተምረውኛል፤ ነገር ግን እየዞርሁ አገሩን ማየትና ማጥናት ነበረብኝ፤ በእግሬም፣ በበቅሎም በላንድሮቨርም ዞርሁ፤ የስሜንን፣ የመቅደላን፣ የወጨጫን ተራራዎች ወጣሁ፤ አጋዴንንና ባሌን፣ ወለጋንና ከፋን፣ ኢሉባቦርንና ሌሎችንም እየዞርሁ አጠናሁ፤ የገጠሬውን መራራ ኑሮ አየሁ፤ ከገበሬውና ከአርብቶ አደሩ ጋር እየተነጋገርሁ እውቀቴን አዳበርሁ፤ ቀስ በቀስ የእኔም ስሜት ወደገጠሬው

እያዘነበለ መጣ፤ «የመሬት ለአራሹ» መፈክር ከዚህ የፈለቀ ነው፤ ጊዜው ጥሩ ነበር፤ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በዶር. ማት ዘመን ለመሥራት ለፈለገ እንቅፋት የሚሆን አልነበረም፤ እንዲህ ራሴን እያስተማርሁ አስተምር ጀመር፤ ለመማሪያ የሚያገለግል የኢትዮጵያ ካርታዎች ስብስብ (አትላስ) ሠርቼ አሳተምሁ፤ ቆይቼም ለመማሪያ የሚሆን የኢትዮጵያ ጂኦግራፊ መጽሐፍ አሳተምሁ።
በዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ የክፍል ኃላፊ የሆንሁት በመከራ ሰው ጠፍቶ ነው፤ ገፋፍቶ የክፍል ኃላፊ እንድሆን ያደረገኝ ዝቪ ያቬትዝ የሚባል እሥራኤላዊ ዲን ነበረ፤ ወደአገሩ ለእረፍት ሲሄድ ተጠባባቂ ሆኜ በሱ ቦታ እንድሠራም አግባባኝ፤ በመጨረሻም ኮንትራቱን ጨርሶ ወደአገሩ ሊመለስ ሲል እኔ ቦታውን እንድይዝ ወትውቶኝ አልተቀበልሁትም፤ አብርሃም ደመወዝን አደረገው፤ እኔ የጂኦግራፊ የክፍል ኃላፊነቱን ብቀበልም ቆይቼ ጊዜው ሲመቻች ሹመትን አስቀርቼ በዴሞክራሲያዊ መንገድ ተገላገልሁት፤ የክፍሉ መምህራን ተሰብስበን ባቀጣጠር ቅደም ተከተል ሦስት ሰዎችን፣ አሰፋ ምሕረቱን፣ መኮተ በላቸውንና እሱላ አባተን ደርድረን እያንዳንዳቸው በተከታታይ ለሁለት ዓመት ኃላፊ እንዲሆኑ ተስማምተን ለፕሬዚደንቱ ለአክሊሉ ሀብቴ ውሳኔያችንን አስተላለፍንለት፤ ለሌሎች የዩኒቨርሲቲው ክፍሎች አርአያ እንሆናለን ብዬ ነበር፤ ግን አልሆንንም፤ ሹም-ሽሩ በሌሎች ክፍሎች ቀጠለ።

ከዩኒቨርሲቲው ውጭ ለሥልጣን የሚያሳጩ ብዙ ዕድሎች ነበሩኝ፤ ብዙ ታላላቅ ባለሥልጣኖችን አውቅ ነበር፤ በተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ረብሻ የተነሣ ጊዜ ከአቶ አካለ ወርቅና ከኮሎኔል ታምራት ይገዙ ጋር ተዋውቄ ነበር፤ ህንድ አገር ተማሪ ሆኜ ከልዑል ራስ እምሩ ጋር በጣም የጠበቀ ግንኙነት መሥርቼ ነበር፤ በአሜሪካ ተማሪ ሆኜ ከአቶ ይልማ ዴሬሳ ጋር በጣም ከመቀራረቤ የተነሣ ቤተሰብ እመስል ነበር፤ ራስ አንዳርጋቸው መሳይ የባለቤቴ የወይዘሮ የወይን እሸት በሻህውረድ ዘመድ በመሆናቸውና ልዕልት ተናኘ ወርቅም የክርስትና እናትዋ ስለሆኑ እተዋወቃቸው ነበር፤ ልዑል አልጋ ወራሽንና ልዕልት መድፈሪያሽ ወርቅም ጋር እተዋወቅ ነበር፤ ከነዚህ ሁሉ ይበልጥ የረዱኝ አቶ አካለ ወርቅ ነበሩ፤ ግን ቤታቸው ሄጄ አላውቅም፤ ራስ አንዳርጋቸው የአገር ግዛት ሚኒስትር በነበሩ ጊዜ ምክትል ይሁን ረዳት ሚኒስትር እንድሆንላቸው ጠይቀውኝ ለሰጡኋቸው መልስ እሳቸው የተናገሩኝ በመልሴ በጣም እንዳፍር አደረገኝ፤ «የለም እንጣላለን» አልኋቸውና ትኩር ብለው አይተውኝ «ለምን ጠብ ታስባለህ? እኔ የምፈልግህ ለሥራ ነው» ሲሉኝ ለማለት የፈለግሁትን ባስረዳም መልሴ አሳፈረኝ።

በዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ባለሁበት ጊዜም ሆነ ከዚያም በኋላ ዕድል ባገኘሁበት ጊዜ ሁሉ አገሩን በእግሬም፣ በበቅሎም፣ በመኪናም እየዞርሁ አጠና ነበር፤ የማስተምረውን ሁሉ አብዛኛውን እኔው እየዞርሁ መቃረም ነበረብኝ! በምዘዋወርበት ጊዜ የገጠሩን ሕዝብ ኑሮና የገበሬውን ስቃይ ለመካፈል ቻልሁ፤



ስለዚህም ይመስለኛል ተወልጄ ያደግሁት በአዲስ አበባ ከተማ ቢሆንም ልቤና ስሜቴ የገጠር ሆነ።

በዩኒቨርሲቲ ባለሁበት ጊዜ ለመጀመሪያም ለመጨረሻም ሴራ ሊባል የሚችል ድብቅ ሥራ የፈጸምሁት የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበርን ለማቋቋም ነበር፤ የብዙ ሰዎችን ምክር አልሰማም ብዬ በረከተ አብ ሀብተ ሥላሴን መርጬ ከሱ ጋር ሴራውን ጀመርን፤ ከወንጂ ስኳር ፋብሪካ አብርሃምና አንድ ስሙን የማላስታውሰው ሰው፣ ከምድር ባቡር አቶ ደመና ይመስለኛል፣ ከቃጫ ፋብሪካ አንድ ልዩ የመንፈስ ኃይል ያላቸውና ጫማ የማያደርጉ ሽማግሌ ... ሌሎችም ሆነን በጥብቅ ምሥጢር ተያያዝነው፤ አሜሪካኖችም ለመርዳት ተዘጋጅተው ስለነበረ መነጋገር ጀመርን፤ አንድ ጊዜ እኔ ለጥናት በየክፍለ ሀገሩ በምዘዋወርበት ጊዜ አንድ አሜሪካን መጥቶ ለበረከት ገንዘብ ሰጥቶት ነበረ ማለትን ሰምቼ አረጋገጥሁ፤ ገንዘቡንም በመቋቋም ላይ ለነበረው ማኅበር ሳይሰጥ መቅረቱ ብቻ ሳይበቃው አብርሃም መኮንንን ተቀብያለሁ ብለህ ፈርም ብሎታል፤ ከዚያ በኋላ ከእኔ ጋር እንዳበቃው ነገርሁት፤ ለሌሎችም ነግሬ ከጉዳዩ ተለየሁ፤ በረከት ግን መስፍንና ተክለ ጽዮን የሚባሉ ወጣቶችንም፣ በየነንም ጨምሮ የሠራተኛውን ማኅበር ወደመቆጣጠሩ ተጠጉ፤ በኋላ እንደተረዳሁት ከአሜሪካኑ በተቀበለው ገንዘብ መሬት ገዛበት፤ ማኅበሩ ሲቋቋም ለወንበርና ለስልክ ማስገቢያ ተበድሬ ገንዘብ ሰጠሁ፤ እንደማስታውሰው ግማሹ አልተመለሰልኝም፤ የኢትዮጵያ ሠራኞች ማኅበርን አርማ ሀሳቡን ነግሬው የሠራልኝ ነፍሱን ይማረውና ገብረ ክርስቶስ ደስታ ነው፤ ገብረ ክርስቶስ የሳለው (አሪጂናሉ) አሁንም አለኝ፤ የሠራተኞች ማኅበርን አመሠራረት ታሪክ አብርሃም ይጽፈዋል ብዬ ስጠብቅ አንድ ሰሞን ጀመር አደረገና ተወው፤ እውነቱን መናገር ችግር ውስጥ እንደሚያስገባው ገምቶ ይመስለኛል፤ የኤርትራው የሠራተኞች ማኅበር ችግር ስለነበረበት እኔ አስመራ ሄጄ ከመሪዎቹ ጋር ዘዴውን ከተወያየን በኋላ በልዑል ራስ ዓሥራት በኩል ደግሞ ሌላ ሥራ ተሠርቶ እንዲፈቀድላቸው ሆነ፤ ከዚያ በኋላ ሴራ የሚባል ነገር ውስጥ እንዳልገባ በቁርጠኛነት ወሰንሁ።

በረከተ አብ እንደተጣላሁት ሲያውቅ በርካሽ ሸጠኝ፤ የጊሚራ አውራጃ ገዢ ተብዬ «ተሾምሁ»! ወህኒ አልከተቱኝም!

ስለዩኒቨርሲቲው ከመጨረሴ በፊት ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅንና የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲን ለማያውቁ ሰዎች አንድ ነገር ማለት እገደዳለሁ፤ እነዚህን አድባራት ከዛሬው ነፍስ የሌለው ነገር ጋር እንዳያመሳስሏቸው፤ በተግባርም፣ በባሕርይም፣ በተልእኮም በፍጹም የተለዩ ነበሩ።

## ሹመት-ግዞት

ለበጎ ነው ባይባልም እንደተናገርሁት አንዴ የጊሚራ አውራጃ ገዢ ተብያለሁ (1957)፤ አንዴ ደግሞ የጊምቢ አውራጃ አስተዳዳሪ ተብያለሁ (1965)፤ ከመጀመሪያው ልጅ ካሣ ወልደ ማርያም መከተልኝና አዳነኝ፤ ሁለተኛው ላይ እንደካሣ ወልደ ማርያም የሚመክትልኝ ሳይሆን አሳልፎ የሰጠኝ አክሊሉ ሀብቴ ነበር፤ አክሊሉ ሀብቴ በዩኒቨርሲቲው ምክር ቤት ውሳኔ በራሱ ፊርማ በዩኒቨርሲቲው የሕይወት መምህር እንደተባልሁ የጻፈልኝ ፕሬዚደንት በዚያው ፊርማው ወደግምቢ ከመሄድ ሌላ አማራጭ የለህም ብሎ ጻፈልኝ፤ በዚያን ጊዜ በዩኒቨርሲቲው ምክር ቤት ውስጥ በተነሣ ክርክር ላይ መስፍን ጊሚራ የተሾመው አገሩን እንዲያውቅ ነው ሲባል ነፍሱን ይማረውና አብርሃም ደሞዝ «መስፍን በያለበት እየዞረ እያንዳንዷን ሜትር ካሬ አጥንቶታል» ሲል የአክሊሉ ሀብቴ ምክትል የነበረውና በቃላት ጨዋታ ልዩ ስጦታ ያለው ሙሉጌታ ወዳጆ «ይበልጥ እንዲያውቅ እያንዳንዷን ስንዝር እንዲያጠና ነው» ብሎ መመለሱን በኋላ ሰምቻለሁ።

በግምቢ የተሾምሁት በአፍሪካ አዳራሽ የዩኒቨርሲቲ የቀድሞ ተማሪዎች ገጠሪቱ ኢትዮጵያ በሚል ርእስ ባዘጋጁት ውይይት ላይ በአደረግሁት ንግግር ውስጥ በኢትዮጵያ ኃላፊነቱ ያልተወሰነ የአክሰዮን ማኅበር እንጂ መንግሥት የለም በማለቴ አስቆጥቼ ስለነበር ነው፤ ሹመቱ እኔን ከዩኒቨርሲቲውና ከአዲስ አበባ ለማስወጣት እንደነበር ግልጽ ነው፤ ግን እኔ እምቢ በማለቴ የጃንሆይን ትእዛዝ ባለመቀበል ተብሎ አንድ ሳምንት ታሰርሁ፤ እንግዲህ ለሦስተኛ ጊዜ መታሰሬ ነው፤ በአቶ ጌታሁን፣ የአገር ግዛት ሚኒስትሩ ቢሮ የፖሊሱ አዛዥ ጄኔራል ይልማ ሺበሺና ዶር. አክሊሉ ሀብቴ ባሉበት ከማእከላዊ ተይዤ ቀረብሁ፤ ወደመርሀቤቴ የሚወስደኝ ሄሊኮፕተር መዘጋጀቱን (እሳቸው መርሀቤቴን የማላውቀው መስሏቸዋል)፣ በጀቱ ከየት እንደሆነ ባይታወቅም በወር አንድ መቶ ብር እንደተቆረጠልኝ፣ ጃንሆይ እሺ አይላችሁም ደረቅ ነው ማለታቸውን ነገሩኝ፤ የምታቀርቡልኝ ምርጫ ሰፊ ከሆነው ግምቢና ከመርሀቤቴ፣ ከመቶ ብርና ከአንድ ሺህ አምስት መቶ ብር ደመወዝ በእስር ቤት ነው፤ እኔ ደረቅም አይደለሁም፤ ቂልም አይደለሁም፤ የተሻለውን እስር ቤት እመርጣለሁ፤ ሆኖም ይህንን ለማያውቀው ለግምቢ ሕዝብ ግን አዝናለሁ፤ ብዬ ወዲያው ተፈትቼ ወደቤቴ ወሰዱኝ።

የግምቢን አሥራ አንድ ወረዳዎች ጎበኘሁ፤ ለብዙ ዓመታት አንድም ሀኪም ያልነበረው ሀኪም ቤት ሀኪም እንዲመጣለት አስደረግሁ፤ ለዓመታት ከተማው በውሀ ችግር ላይ ስለነበረ አንድ አዲስ ሞተር ተገዝቶና አሮጌው ተጠግኖ ውሀ እንዲያገኙ አደረግሁ፤ ሌላ ከሥልጣን ጋር የተገናኘ ነገር ለወረዳዎች ደብዳቤ ተጽፎ ለፊርማ ሲያመጡልኝ «ትሑት አገልጋይዎ» ብለው እንዲጨምሩበት ትእዛዝ ስሰጥ «ወደታች» ሲጻፍ እንዲህ አይባልም ብለው



ተከራከረውኝ ነበር፤ የኔን ትእዛዝ እንዲቀበሉ አሳመንኳቸው፤ አንድ ሌላ ውሳኔም ሰጥቻለሁ፤ በለቀምት የባለሥልጣኖች ስብሰባ ላይ ከመንግሥት ሠራተኛ ደመወዝ ምን ያህል በመቶ እንደሆነ አላስታውስም ለልማት እየተቀነሰ ገቢ እንዲሆን የሚል ትእዛዝ ከደጃዝማች ወልደ ሰማዕት የተጻፈ ደብዳቤ አሳዩኝ፤ የደመወዙ ባለቤት ራሱ በፊርማው እንዲቆረጥ ካላረጋገጠ በቀር የማንም ደመወዝ እንዳይነካ ብዬ ቅነሳውን አገድሁት፤ ገና ዕቃዬን ሁሉ አጓጉዤ ሳልጨርስ አብዮት የሚባል ነገር መጣና ገላገለኝ!

## መርማሪ ኮሚስዮን

ግምቢን ተከትሎ ያጋጠመኝም ሥራ በግዴታ የተጫነብኝ ነበር፤ አንዳንድ ሰዎች በማወቅም ባለማወቅም መርማሪ ኮሚስዮንን ደርግ እንዳቋቋመው አድርገው ይናገራሉ፤ ይጽፋሉም፤ መርማሪ ኮሚስዮን በአዋጅ ሲቋቋም ደርግ አልነበረም፤ ማንበብ ለሚችል ሰው አዋጁን ማየት ብቻ በቂ ነው፤ ለማናቸውም በጊዜው በነበረው ብሔራዊ ምክር ቤት በከፍተኛ ድምፅ ተመረጥሁ፤ በጭራሽ አልፈለግሁትም፤ ምክንያቱም የአፄ ኃይለ ሥላሴን አገዛዝ ሳብጠለጥለው ኖሬ አስቀድሜ በፈረድሁበት ላይ መርማሪ መሆን ትክክል አልመሰለኝም፤ መውጫ ይሆነኛል ብዬ ያሰብሁት መሐላው ነበር፤ ታማኝነትን ለአንድ ሰው የሚያደርገው ከሆነ ከመሐላው ሥርዓት ለመውጣት ቆርጬ ነበር፤ መሐላው ለኅሊናዬ ያጋደለ ስለነበረ ትንሽ ድንጋጤ ፈጥሬ አለፈ፤ ቃለ መሐላ የፈጸምነው በጃንሆይ ፊት፣ በአቶ ሰሎሞን ገብረ ማርያም አስተናጋጅነት ነው፤ አሥራ አምስት ሰዎች የነበሩበት ኮሚስዮን ሊቀ መንበር አድርጎ መረጠኝ (አንዳንዶች እንደጻፉት በሹመት አልነበረም፤)።

ስለመርማሪ ኮሚስዮን ለመጀመሪያ ጊዜ ያየሁት መጠነኛ ሙከራ አንድ የሕግ ሰው ይመስለኛል (በዛወርቅ ከሚል ስሙ ጸታውን መለየት አልቻልሁም) በወንበር ውስጥ «ምርምር» ተብሎ የታተመውን ነው (ነሐሴ 2001)፤ ምርምር የሚለው በጣም ይበዛበታል እንጂ ጥሩ ሙከራ ነው፤ ጸሐፊው በግል ስሜት ተነሣስቶ እንደጻፈው በግልጽ ይታያል፤ በዚያው መጽሔት ላይ በጊዜው የነበረውን ሁኔታ አንድ የውጭ አገር ሰው ማብራራት ሲችል ኢትዮጵያዊው ይህንን እንኳን ለመገንዘብ አለመቻሉ ይገርማል፤ ከውስጥ በስሜት ተጭኖ የሚመጣውን እውነት እድርጎ መቀበል ተምረዋል ለተባሉትም አዳጋች እየሆነ ይታያል፤ በዛወርቅ ያነሣቸው ጥያቄዎች ሁሉ ጥቃቅንና ቁም ነገሩን የሚያስገነዝቡ ባይሆኑም ተገቢ ናቸው፤ ቁም ነገሩ ያለው መርማሪ ኮሚስዮን እንዴት እንደተቋቋመና እንዴት እንደተበተነ የሚሉ ጥያቄዎች ላይ ነበር፤ ከጋዜጣ መግለጫዎች አለመውጣቱ ጽሑፉን ጎድቶታል፤ በተለይ የመጨረሻው ዓረፍተ ነገር የጸሐፊውን የስሜት ውሳኔ ያጋልጥበታል፤ «የተቋቋመው ኮሚስዮን ላቋቋመው ሳይሆን ለሌላ ላላቋቋመው አካል ሪፖርት

አድርጎ ያው የሆነው እንደሆነ አይተናል፤» ይላል! አይ የሕግ ምሑር! ራሱ ጸሐፊው የማያውቀውንና ያልደረሰበትን ነገር እኛንም ከሱ ጋር የመደናበሩ ተካፋይ ያደርገናል።

አሥር ብዙወርቆች አሥር ዓመት የዚህን ዓይነት «ምርምር» ቢያደርጉ በመርማሪ ኮሚስዮን ሥራ ላይ ትንሽም ጉድፍ እንደማያገኙ እርግጠኛ ነኝ፤ ከወሬ ደረጃ ያልወጣ ጽሑፍ መሆኑን የሚያረጋግጠው የመርማሪ ኮሚስዮን ዋና ጸሐፊ የነበረው ሠይፉ ተከለ ማርያም ከመጽሔቱ ደጋፊዎች አንዱ ተብሎ ስሙ መጠቀሱ ነው፤ ነገር ግን ከሠይፉ ምንም መረጃ «ተመራማሪው» እንዳላገኘ ለእኔ ግልጽ ነው፤ ሠይፉ ከማንም የኮሚስዮኑ አባል እኩል ወይም ይበልጥ ስለመርማሪ ኮሚስዮን ያውቃል፤ ከዚያም በላይ አንድ ቃለ ጉባኤ ለማንበብ አልሞከረም፤ ድንገት ወደፊት እውነተኛ ምርምር የሚያደርጉ ሰዎች ይመጡ ይሆናል በማለት ስለመርማሪ ኮሚስዮን በእኔ ዘንድ የነበረውን ሰነድና ማስታወሻ በሙሉ ለኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ማእከል ከሰጠሁ ዘመናት አልፈዋል፤ በተጨማሪም እንደመሀመድ ኢድሪስ ጉዳዩን ሲከታተሉ የነበሩ ጋዜጠኞችን አልደረሰባቸውም፤ አንድ ቀን እውነቱ ያነቃዋል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ፤ ምርምር የሚባለው እውነትን ፍለጋ ነው እንጂ ወሬን ማግበስበስ አይደለም፤ ስለልዑል መኮንን አሟሟት እኔ የተሻለ «ምርምር» ሠርቻለሁ።

የመርማሪ ኮሚስዮኑ ተግባር ክሶችንና ጉዳዮችን እየመረመረ ያስከስሳል፣ ወይም እያስከሰስም ብሎ ለልዩ ዓቃቤ ሕግ ማስተላለፍ ብቻ ነበር፤ ከዚህ በላይ የሆነ ኃላፊነትም ተግባርም አልነበረውም፤ ገና ደርግ በአራተኛ ክፍለ ጦር ውስጥ እያለ መርማሪ ኮሚስዮኑ ከደርግ ጋር በአራተኛ ክፍለ ጦር ውስጥ እንዲሠራ ሻለቃ (በዚያን ጊዜ) መንግሥቱ ጠየቀኝና በበኩሌ ቃለ መሐላ ፈጽመናልና እንደማይቻል ነገርሁት፤ ቆይቶ ወደምኒልክ ግቢ ከገቡም በኋላ ጉዳዩን እንደገና አንሥቶ ጠየቀኝ፤ የግሌን ውሳኔ አለመቀበሉን ስለተገነዘብሁ በአጀንዳ ተይዞ ለኮሚስዮኑ አቀረብሁት፤ አብዛኛዎቹ አባላት ተቃወሙት፤ ይህንኑ ለኮሎኔል መንግሥቱ አሳወቅሁት፤ ከዚያ በኋላ ነው የሕዝብ ድርጅት የተባለው የደርግ ረዳት ሆኖ የተቋቋመው።

በኅዳር 14/67 ሰድሳዎቹ ከተገደሉበት ዕለት ጀምሮ ወደመርማሪ ኮሚስዮን መሄድ አቆምሁ፤ የስንብት ደብዳቤ ለኮሚስዮኑ አቀረብሁ፤ ብዙ ወሬና ማስፈራሪያ ነበረና እንደገባኝ የኮሚስዮኑ አባሎች እኔን ላለማጋለጥ ስንብቴን አልተቀበሉትም፤ ስለማስፈራሪያው ሠይፉ ተክለ ማርያም ይበልጥ ያውቃል፤ እኔም ቆርጬ ስለነበረ እንደገና የስንብት ደብዳቤ አስገባሁ፤ ከዚያ በኋላ ከሊቀ መንበርነት እንድወርድ፤ ነገር ግን በአባልነት እንድቀጥል ተስማማንና ሥራ ጀመርሁ፤ በረከተ አብ ሀብተ ሥላሴ ወንበሩን ለመያዝ በጣም ቋምጦ ነበር፤ እንደምንም ታግዬ አሥራ አምስት ከሚሆኑት የኮሚስዮኑ አባሎች ውስጥ ለማ ጉተማ ሊቀ መንበር እንዲሆን ተመረጠ።



አሥራ አምስት ከሚሆኑት የኮሚስዮኑ አባሎች ውስጥ በትክክለኛነታቸውና በኅሊናቸው ንጽሕና ብርቅ የሆኑ ሰዎች ነበሩ፤ ከሕግ ውጭ መግደል ሲጀመር የኮሚስዮኑ ሥራ ዓላማ-ቢስ መሆኑን ሁላችንም ተረዳነው፤ ስለዚህም እንዲፈርስ ጥረት ማድረግ ጀመርን፤ በመጨረሻም በቴሌቪዥን በአደባባይ እንደተገለጸው በአስተዳደርም ሆነ በፍርድ በደል የተመረመረው ጉዳይ ዘጠና ስምንት በመቶ ያህሉ ዋጋ-ቢስ ሆኖ ተገኘ።

በመጨረሻም ኮሚስዮኑ የራሱን መሻሪያ አዋጅ አርቅቆ ሥራውን አበቃ።

በሕይወቴ በሥልጣን ላይ ላሉ ሰዎች ቅርብ የሆንሁት የመርማሪ ኮሚስዮን ሊቀ መንበር በነበርሁበት አጭር ጊዜ ውስጥ ነው፤ከማናቸውም ጊዜ የበለጠ ሥልጣን በጥፍሩ ይዞ ሊጎትተኝ የሞከረበት ወቅት ነበር፤በማምለጤ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ።

## የሹመት ጥያቄዎች

ከዚያ በኋላ የአስመራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚደንት እንድሆን ተጠይቄ ነበር፤ መምህራን ከየትም መቅጠር እንድችልና ማናቸውንም እርዳታ ከየትም ማግኘት እንድችል፣ ማርክሲስታዊና ሌኒናዊ ፍልስፍና እንደአንድ ትምህርት እንዲሰጥ እንጂ በሌሎች ትምህርቶች እንዳይገባ በማለት እነዚህን ሦስት ቅድመ ሁኔታዎች በጽሑፍ አቅርቤ እቀበላለሁ አልሁ፤በሳምንቱ ሁሴን ኢስማኢል መሾሙን ሰማሁ! ከዚያ በኋላም የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚደንት እንድሆን ተጠይቄ ነበር፤ አልተቀበልሁም፤ በብሔረሰብ ኢንስቲትዩት ውስጥ እንድገባ ኮሎኔል መንግሥቱ ራሱ ጠይቆኝ አልፈልግም ብዬው ትቶኛል።

የዩኒቨርሲቲው ሠላሳኛ ዓመት ሲከበር የአገልግሎት ሽልማት ስለሚሰጠኝ በበዓሉ እንድገኝ ፕሬዚደንቱ ዱሪ መሀመድ ነግሮኝ ነበር፤ በዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ አንዲት ኤሊ. አለችና እሰዋ ትቀድመኛለች፤ ለሰዋ ስጣት፤ አልመጣም፤ ስሜን አትጥራ ብዬው ነበር፤ ግን ባልነበርሁበት ስሜ ተጠራ፤ የደርግ አሥረኛ ዓመት ሲከበርም ልሻን እንደሚሰጠኝ ሰምቼ የጥሪ ካርዱ ላይ ባለ ስልክ ደውዬ እንደማልገኝ አስታውቄ ቀረሁ፤ በሌለሁበት አሁንም ስሜ ተጠራ፤ በጃንሆይ ዘመንም ወደጽሕፈት ሚኒስቴር ሄጄ ልሻን እንድቀበል ተነግሮኝ አልሄድሁም።

[1] ዶር. መኮንን ወልደ አምላክ ከዩኒቨርሲቲ፣ በዚያን ጊዜ ሻለቃ ዓለማየሁ ከክብር ዘበኛ፣ ሻለቃ ምትኩ ከዓየር ኃይል፣ አቶ ጌታቸው ከኦዲተር መሥሪያ ቤት፣ ኮማንደር ለማ ጉተማ በኋላ ተለወጠ እንጂ በመርማሪ ኮሚስዮን አባልነቱ ለእውነት የቆመ ነበር፤ ሌሎችም ነበሩ።

ጡረታ በወጣሁ ጊዜ ኮሎኔል መንግሥቱ አንድ አሁንም በሕይወት ያለ ባለሥልጣን ልኮብኝ ወደዩኒቨርሲቲ እንድመለስ ተጠይቄ ሊሆን እንደማይችል በቁርጠኛነት መልሼለታለሁ፤ ዳግመኛ በሻምበል ፍቅረ ሥላሴ በኩል ተጠይቄ ጡረታዬን ለማስከበር እንደምፈልግ አስረድቼ በሰላም ከዩኒቨርሲቲ ወጥቼ በወያኔ ከመባረር አምልጫለሁ።

በቅርቡ ሁለት የምክር ቤት አባላት አቶ ተመስገንና አቶ መሀመድ አሊ ስለእኔ የሹመት ምኞት የጻፉትን ከየት እንዳገኙት አላውቅም፤ ግን አቶ ተመስገን «ዛፍ ያጣ ጉሬዛ» ያላትን በጣም ወድጃታለሁ! ጉሬዛው ከየት መጥቶ ዛፍ የሌለበት አገር ገብቶ የቸገረው?

## የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ)

ወደሰብአዊ መብቶች ጉዳይ የገፋኝ በችጋር ላይ ያደረግሁት ጥናት ነው፤ በድርጅት የተደገፈ አይሁን እንጂ በደርግም ዘመን በሰዎች ጉዳይ ደጅ እጠና ነበር።

ወያኔ የመጣው ጡረታ ላይ ሆኜ ነው፤ በወያኔ/ኢሕአዴግ አገዛዝ ገና ከመጀመሪያው ኢሰመጉን ለማቋቋም አስፈላጊ ዝግጅት ከአደረግሁ በኋላ ነፍሱን ይማረውና ወርቁ ተፈራንና ዓሥራት ገብሬን (ሁለቱም የሕግ ሰዎች) ሳማክራቸው ዋና ሆነው ብዙ ነገሮችን አከናወኑልኝ፤ በኋላም አበበ ወርቄ ረድቶናል፤ ወዲያውም ዓሥራት ገብሬ ጊዜያዊ ጽሕፈት ቤትና ጸሐፊ በመለገስ የኢሰመጉ ሥራ ተጀመረ፤ ያለዓሥራት ገብሬ እርዳታ ኢሰመጉን ለማቋቋም በጣም ብዙ ጊዜ ይፈጅ ነበር፤ በሊቀ መንበርነት ተመርጬ ስሠራ ለብዙ ዓመታት ቆየሁ፤ በመሀል ፕሮፌሰር እንዳርጋቸው ተሰፋዬ ከመግባቱ በቀር እኔው በወንበሩ ላይ ቆየሁበት፤ በዚያም ጊዜ ውስጥ ለጡረታ ዕደሜዬ መደጎሚያ ይሆነኛል ያልሁትን ከአገር አገር ስዞርበት ጨረስሁት፤ ሌሎች ሰዎች እንዲገቡበት ለማድረግ ያደረግሁት ሙከራ ሁሉ አልተሳካም፤ ያለኝ አንድ አማራጭ ብቻ ነበር፤ የኢሰመጉ ደንብ የፖሊቲካ ፓርቲ አባል የሆነ ሰው በሥራ አስፈጻሚ ውስጥ አይገባም የሚለውን ተመርኩዤ በፖሊቲካ ፓርቲውስጥ በመግባት ተገላገልሁ! ችጋር ወደሰብአዊ መብቶች፣ ሰብአዊ መብቶች ደግሞ ወደፖሊቲካ ገፍቶ ቃሊቲ ከተተኝ!

የሆነ ሆኖ ለእኔ በኢሰመጉ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሰጠሁት አገልግሎት ሕይወቴን በሙሉ ከኖርሁበትና ከምኖርበት የማስተማር አገልግሎት ጋር የሚጣጣምና ከፍተኛ የመንፈስ እርካታ ያገኘሁበት ነበር፤ የኢሰመጉ ጽኑ አባሎች ከሆኑ ሽማግሌዎችም ሆኑ ወጣቶች ጋር ለኢትዮጵያ ሕዝብ እኩልነት፣ ፍትሕ፣ ነጻነትና መብቶች ያላቸውን ቆራጥ አቅዋም በአደባባይ ለመግለጽ



ከሚችሉ ሰዎች ጋር መሥራት ትልቅ ትምህርትና ኩራት ሆኖኛል፤ ሌላውን የሚመዝነው ሕዝብና የወያኔ/ኢሕአዴግ ባለሥልጣኖች ናቸው፤ ምናልባት አንድ መናገር ያለብኝ ነገር የኢሰመጉ ዓላማ የወያኔን የሰብአዊ መብቶች ረገጣ ለማሳጣት ሳይሆን፣ ወያኔ የሚታረምበትን መንገድ በማመልከት ለመርዳትና የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለመብቶቹ እንዲያውቅ ለማድረግ ነበር፤ ሁለተኛው በመጠኑም ቢሆን ተሳክቶአል ለማለት ይቻላል፤ የመጀመሪያው ግን ዛሬም ችግር ነው።

## የፖሊቲካ ፓርቲ

በፖሊቲካ ፓርቲም ውስጥ ከምክር ቤት አባልነት ውጭ ምንም የሥልጣን ቦታ ውስጥ አልገባሁም፤ ከቅንጅት ምክር ቤትም ቢሆን የስንብት ደብዳቤ አቅርቤ ወጥቼ ነበር፤ ለምርጫም አልተሰለፍሁም፤ ግን አመራር ውስጥ አለህበት ተብዬ ሁለት ዓመታት ያህል ታሰርሁበት፤ ዕድሜ ልክ እስራት ተፈረደብኝ!

ዛሬም በአንድነት ውስጥ የምክር ቤት አባል ብሆንም የአንድነት ፕሬዚደንት ብርቱካን ሚዴቅሳ ከታሰረችና ግዛቸው ሽፈራው ተጠባባቂ ሲሆን ከሎሌዎቹ ጋር ሆኖ አንገብርም ያልነውን ሁሉ ከምክር ቤቱ አስወጣን፤ «ዝምአንልም» ብለን የማንሸጥ፣ የማንለወጥ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ሕዝብ እኩልነት፣ ፍትሕና ነጻነት እየታገልን ነው።

## መደምደሚያ

ማኅበረሰብ ባለበት ሁሉ አስተዳደር አለ፤ አስተዳደር ባለበት ሁሉ ሕግና እኩልነት አለ፤ ሕግና እኩልነት ባለበት ሁሉ ነጻነት አለ፤ አስተዳደርና ሕግ ባለበት ሁሉ ሥልጣን አለ፤ ሕግ አስከባሪዎች አሉ፤ ሕግ አስከባሪዎች ባሉበት ዳኞች አሉ፤ ነጻነት የእያንዳንዱ ሰው፣ የእያንዳንዱ የማኅበረሰብ አባል መሠረታዊ የተፈጥሮ ሀብት ነው፤ ነጻነት የእያንዳንዱ ሰውና በድምሩም የጠቅላላው ማኅበረሰብ ሀብት ሲሆን፣ ሕግ ደግሞ እያንዳንዱ ሰው በማኅበረሰቡ ውስጥ በደኅንነትና በነጻነት መኖር የሚያስችለው ዋስትና ነው፤ ሥልጣን ለነጻነትና ለሕግ መሣሪያ ሆኖ የኅብረተሰቡን ደኅንነትና አብሮ የመኖርን ፍላጎት የሚያሳካ ሕጋዊ ጉልበት ነው።

ስለዚህም ሥልጣን መሣሪያ ነው፤ የአንድ ሰው ወይም የጥቂት ሰዎች መሣሪያ ሳይሆን የማኅበረሰቡ በሙሉ መሣሪያ ነው፤ የሥልጣን ትክክለኛ ተግባሩ የግለሰቡንና የማኅበረሰቡን ደኅንነት በማጣጣም የሁለቱንም መብቶች ለማስከበር ነው፤ ሥልጣንን በሕገ አራዊት ደረጃ ከሚገኘው ጉልበት ለይተን ማየት ያስፈልጋል፤ ሰዎች ለጉልበት ሲገብሩና ሲገዙ ገና ከአራዊትና ከእንስሳት

ደረጃ አለመውጣታቸውን የሚያመለክት ነው፤ ሥልጣንን ከጉልበት የሚለየው ሕጋዊነት ነው፤ ሕጋዊነት ስንል ማኅበረሰቡ በሙሉ ነጻነትና በቀጥታም ሆነ በትክክለኛ ወኪሎቹ ያወጧቸውን ሕጎች የተከተለ ማለት ነው፤ ስለዚህም ሥልጣን በሕግ የተሰጠና በሕጋዊ ሥርዓት አገልግሎት ላይ የሚውል ጉልበት ነው፤ በዚህ ምክንያት የፈረጠመ ጡንቻ ያለው ጎበዝና ኮሳሳው ደካማ፣ ያናጠጠው ሀብታምና መናጢው ደሀ በሕግ ስር በእኩልነት ይተዳደራሉ፤ በሥልጣንና በጉልበት መሀከል ያለው መሠረታዊው ልዩነት ሥልጣን በሕዝብ ቁጥጥር ስር መሆኑና ተጠያቂነት ያለበት መሆኑ ነው፡፡

በዚህ አመለካከት እኔ በሕይወቴ እውነተኛ ሥልጣን አይቼ አላውቅም ማለት ነው፤ ከፋሺስት ኢጣልያ አገዛዝ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ያየሁት ጉልበትን እንጂ ሥልጣንን አይደለም፤ እኔ የማውቀው ጉልበት ሥልጣን የሚባል ስም እየተሰጠው እያሰረ፣ እየረገጠና እየገደለ ሲገዛ ነው፤ ይህ በልጅነቴ ከነበረኝ ጠባይ ጋር በከፊል ይስማማ ይሆናል፤ ከአደግሁ በኋላ ከኮተኮትሁት ጠባይ ጋር ግን በጭራሽ አብሮ አይሄድም፤ ታዲያ እንዴት ብዬ ልውደደው?

እንዴት ሥልጣንን በጣም እየቀረብሁት አመለጥሁት? ሙሉ በሙሉ አስቤውና አቅጄው ነው ለማለት አልችልም፤ በጥሞና ወደኋላ ተመልሼ ሳስበው ሁልጊዜም የኔ ባሕርይ አካል ሆነው የቆዩ ሁለት ነገሮች አሉ፤ አንዱ ትናንትን አልረሳም፤ ከአደግሁበት ደሀነት ብወጣም ደሀነትን አልረሳም፤ ለምሳሌ ቤት ስከራይ እኔ ያደግሁበት ዓይነት ትንሽ ቤት በእጠገቡ መኖር አለበት፤ ወደአሁኑ «የጌትነት» ቤቴ ስገባ ያደግሁበትን ማስታወስና ትዕቢትን ማስተንፈስ አስፈላጊ ሆኖ ይታየኛል፤ ችላ ካሉት እንደደሀነት ቶሎ የሚረሳ ነገር የለም፤ ሁለተኛው ነገን አስባለሁ፤ ዛሬ የተናገርሁት ወይም ዛሬ ያደረግሁት ነገ እንዲያሳፍረኝ አልፈልግም፤ የዛሬ ምኞት የነገ ዕዳ መሆኑን እገነዘባለሁ፤ አንድ ምኞት ሲያድርብኝ አዝሎ የሚመጣውን ብዙ ቅራቅንቦ አስቀድሜ አስበዋለሁ፤ ነጻነቴ የምኞት ሎሌ እንዳይሆንብኝ በጣም እጠነቀቃለሁ፤ መቸገርን የማልወደውን ያህል መንደላቀቅንም አልወድም፤ሥልጣንና እኔ ያልተገጣጠምነው በዚህ ምክንያት ይመስለኛል፤ ሌላ ምሥጢር የለውም፡፡

በተለይ ለወጣቶች በሆነ ነገር ማስረዳቱ በቀላሉ ለመገንዘብ ይረዳ ይሆናል፤ የእኔ ትውልድ ለትምህርት ውጭ አገር ደርሶ ሲመለስ አንደኛ መንግሥት ሦስት ሺህ ብር ለዕቃ መግዣ ብድር ይሰጥ ነበር፤ ሁለተኛ አንድ ሬድዮግራም የሚሉት ነገርና የሞዝቮልድ የቤት ዕቃ የኑሮ ደረጃ መለኪያ ሆነው ይታዩ ነበር፤ ሁሉንም ጠላኋቸው፤ ብድር ደግሞ ጭራሽ አልወድድም፤ አንዳንዴ የሰዎች ግፊት ኃይለኛ ነው፤ ሳልፈልግ አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር ብቻ ተበደርሁ፤ እነዚያ ሁለቱ ዕቃዎች ግን በቤቴ አልገቡም፡፡

መሬት መግዛትና ቤት መሥራት ሌላው ትልቁ የሕይወት ዓላማ ነበረ፤ ፈተናውን ተቋቁሜ ብዙ ጊዜ ከቆየሁ በኋላ አንድ ቀን አንድ ጓደኛዬ መሬት



ልገዛ ነውና አብረን እንሂድ ሀሳብ ትሰጠኛለህ ስላለኝ ወደአቧሬ ሄድን፤ የልዑል ራስ ዓሥራት ካሣ ወይም የባለቤታቸው መሬት ነው፤ ጓደኛዬ ከወኪሉ ጋር ሲነጋገር እኔ አንድ ረዢም ግራር ከንፉን በሰፊው ዘርግቶ አየሁ፤ እስሩ እኔ ቤት ሠርቼ ጥላው ስር ተቀምጬ ራሴን አየሁት፤ መሬቱ የሚሸጥ መሆኑን ካረጋገጥሁ በኋላ እኔ እገዛዋለሁ ብዬ በድንገት ቃል ገባሁ፤ ባንክ ሄጄ ብድር ጠይቄ ተፈቀደልኝ፤ ሌሊት እንቅልፍ አጣሁ፤ እባንንና ስነቃ ላብ በላብ ነኝ፤ ሰባት ሺህ ብር እንዴት አድርጌ ልከፍል ነው? ቤቱስ በምን ሊሠራ ነው? ልዑል ራስ አስመራ ስለነበሩ የውሉ ወረቀት ተፈርሞ መምጣት ስለነበረበት ዘገየብኝ፤ አንድ ቀን እንደተለመደው ወኪሉ እንዲያጣድፍልኝ ለመቀስቀስ ራስ ካሣ ሰፈር ሄድሁ፤ መርዶ ነገረኝ፤ እኔ የያዝሁት መሬት ለደጃዝማች አሉላ መሸጡን ነገረኝ፤ እኔ ይገፔው እንደነበረ መናገሩን አረጋገጥሁ፤ አረርሁ! ተቃጠልሁ!

መለስ ሲልልኝ ውርደቱን ያመጣብኝ እጉል ምኞት መሆኑን ተረዳሁና ለልዑል ራስ ደብዳቤ ጻፍሁ፤ -- የደብዳቤው አጠቃላይ ይዘት መሬቱን ከወኪሉ ጋር ተዋውለን እንደነበረ፣ ገንዘብ እንደተበደርሁ፣ ለፍቼ ባገኘሁት ገንዘብ «የልዑል ጌታዬን መሬት ለመግዛት ብቁ አለመሆኔን መረዳቴን» የምጽፍላቸው ያንንም ሆነ ሌላ መሬት ፈልጌ ሳይሆን የደረሰብኝን በደል ለመግለጽ ብቻ መሆኑን፣ እንዲያውም ከእጉል ምኞት እንዳዳኑኝ ምስጋና ማቅረቤን -- በፖስታ ብልከው አልደረሰም ይባላል ብዬ አስመራ የትምህርት ሚኒስቴር ወኪል በነበረ ጓደኛዬ (ጳውሎስ ዓሥራት) በኩል በእጅ እንዲደርሳቸው አደረግሁ፡፡

ግን እስካሁን ድረስ ፍቅረ ንዋይ በግራር በኩል ገብቶ እንዴት አድርጎ ነፍሴን ሰንጎ ሊይዛት እንደሞከረ ይደንቀኛል፡፡

## ፪
# ከፉ ቀን ጥሩ ነው

የፈጸምነውን ወንጀል ሳናውቅ፣ የበደልነው ሰው ሳይኖር በታጠቁ ወታደሮች ከየቤታችን ተይዘን ታሰርን፤ በመጨረሻም ቃሊቲ ገባን፤ በቃሊ ቲ ቆርቆሮ-በቆርቆሮ ቤት ውስጥ ሌሊት ሌሊት በመቀርቀሪያ ተቸንክሮ በብረት ቁልፍ ከውጭ ተቆልፎብን እያደርን፣ ቀን ቀን ደግሞ ከአንድ መቶ ሜትር ካሬ በማይበልጥ ግቢ ውስጥ ከዘጠና እስከአንድ መቶ የምንሆን ሰዎች እየተተራመስን ስንኖር ቅዳሜና እሁድ ለአንድ ሰዓት ያህል ከፉ ቀን ያመጣልንን የዘመድና የወገን ፍቅርና ድጋፍ የምናይባቸው ቀኖች ነበሩ፤ የቃሊቲ ርቀት መንፈሳቸውን ሳያዳክመው፣ የቃሊቲ ፖሊሶችን ማዋከብና ማንገላታት ችለው፣ ጸሐዩንና ዝናቡን ተቋቁመው ሲጠይቁን የነበሩት ሁሉ የከፉ ቀን በጎዎች፣ የጨለማ ቀን ብርሃኖች ናቸው፤ ከፉውን ቀን ጥሩ ያደርጉታል፤ እነሱን ከፉ ቀን አያጋጥማቸውና::

በቃሊቲ ኑሮ ማለት በሁለትና በሦስት ፌስታል ውስጥ በሚካተት ንብረት መወሰን ነው፤ በዚህ ሁኔታ እያለን በፌስታሉ ውስጥ ያለው ንብረታችን ሳይሟጠጥ እንደገና የሚሞላው ቅዳሜና እሁድ ነው፤ የሚያስፈልጉንን ነገሮች ሁሉ ከጥርስ ሳሙና እስከጢም መላጫ አስበው የሚያመጡልን ሰዎች አሉ፤ ልብሳችንን የሚያሳጥቡልን አሉ፤ እንዳይበርደን ጋቢ የሚያመጡልን አሉ፤ እነዚህ ከፉ ቀን የቀሰቀሳቸውና በትሩፋት ተግባራቸው ከፉ ቀንን የሚገፉ የቅዱስ መንፈስ መልእክተኞች ናቸው፤ ከፉ ቀን ጥሩ ነው፤ ለቅዱስ መንፈስ መልእክተኞች መንገዱን ይጠርጋል፤ አምላክ እነዚህን የቅዱስ መንፈስ መልእክተኞች ይጠብቃቸውና::

የቃሊቲ ኑሮ ተስፋ የጨለመበት ነው፤ ከፉ ቀን ጥሩ ነው፤ በውጭ አገሮች በአሜሪካ፣ በአውሮፓ፣ በአውስትራልያና በደቡብ አፍሪካ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በወገኖቻቸው ላይ የተፈጸመው ግፍ እንሣስቷቸው በበረዶና በዝናብ፣ በጸሐይ ሐሩርና በሙቀት ሳይሸነፉ ተደጋጋሚ ሰላማዊ ሰልፎችን በማድረግ የየአገሩን መንግሥታትወጥረው በማስጨነቅ በአገራቸው ያለውን ሁኔታ አሳውቀዋል፤ በኢትዮጵያ አገዛዝ ላይ ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ጫና እንዲደረግ ያስመዘገቡት አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፤ በኢትዮጵያዊነት ብቻ መተባበርን ያመጣው ከፉ ቀን ነው፤ የትብብሩን መግለጫ እያጠነከረውና በጎ እልህ ውስጥ ያስገባው ከፉ ቀን ነው፤ ከፉ ቀን ጥሩ ነው ያስተባብራልና::

ከፉ ቀን እንደየአውሮፓው ምክር ቤት አባል ወይዘሮ አና ጎሜዝ ያሉ፣ እንደየአሜሪካው ምክር ቤት አባል ዶናልድ ፔይን ያሉ ለእውነት የቆሙ



ትልልቅ ሰዎች የኢትዮጵያ ወዳጆች እንዲሆኑ አደረገ፤ ከፉ ቀን ጥሩ ነው በጊዜው በአሜሪካ የነበረው መንግሥት ለእውነት ያለውን መለኪያና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያለውን ግምት አሳየን፤ ኢትዮጵያ የእግዚብሔር አገር ስለሆነች አለቃ አያሌው (ነፍሳቸውን ይማርና) እንዳሉት «ኢትዮጵያን የነካ» መቅኖ እንደማያገኝ እንደወትሮው እያየን ነው፤ ከፉ ቀን ጥሩ ነው መማር የፈለገውን ያስተምራል፤ እግዚአብሔር ኃያላንንም ያስተምራል::

የቃሊቲ ከፉ ቀኖች በርኅራኄአቸው፣ በቸርነታቸው፣ በፍቅራቸውና በወዳጅነታቸው፣ በአሳቢነታቸው፣ በመንፈሳዊ ወኔያቸውና በመንፈሳዊ ልዕልናቸው በጽድቅ ተራራ ላይ የወጡ ሰዎችን አሳይቶኛል፤ እነዚህን ሰዎች አንጥሮ ያወጣቸው ከፉ ቀን ነው:: ልቤ የእነዚህን ሰዎች ስም ለመዘርዘር ይፈልጋል፤ አእምሮዬ ግን ደግ የዋለልህን ለከፋት አታጋፍጠው ይለኛል፤ ከፉ ቀን ጥሩ ነው የበጎ አድራጊዎችን ስም እግዚአብሔር በጽድቅ መዝገቡ እንዲገቡ ለመጻለይ ያስገድዳል፤ በአገር ውስጥ ከቅዳሜና እሁድ ውጭ በሳምንት ቢያንስ ሁለት ቀን በያይነቱ ምግብ ሲልኩልኝ የነበሩ ሰዎች አሉ፤ እግዚአብሔር ሁልጊዜም ለትሩፋታቸው የሚበቃውን አብዝቶ ይስጣቸው፤ ሌሎች ደግሞ የአመሌን ግዴታ እንድወጣ በየሳምንቱ ሲጃራ የሚያመጡልኝ ነበሩ፤ ከኢትዮጵያ ውጭ የሚኖሩትም ቸኮላቱን፣ ልብሱን፣ከዘራውን፣ መድኃኒቱንና ቅባቱን ሁሉ ይልኩልኝ ነበረ፤ ከፉ ቀን ጥሩ ነው ያስተዛዝናል፤ ከፉ ቀን ጥሩ ነው ደጋግ ሰዎችን ይቀሰቅስና የግፍን መራራነት እንዲቀንሱት ያደርጋል::

ከፉ ቀን ጥሩ ነው፤ ምንም ዓይነት ውለታ የሌለበት ሰው የእስረኛ ሞግዚት ሆኖ የቤቱን ጣጣ ሁሉ እንዲችልለትና ማናቸውንም አስፈላጊ ነገሮች ሁሉ ሥራዬ ብሎ እንዲያቀርብ ያደርገዋል፤ ለታሰሩት አባትና እናት፣ ወንድምና እኅት ይሰጣቸዋል፤ ከፉ ቀን ጥሩ ነው ምንም ውለታ የሌለባቸው ሰዎች ከባድና የማይከፈል የውለታ ጭነት እንዲያስሸክሙ ግብረ ሠናይ ይገፋፋቸዋል::

በጣም በዝቅተኛ ገቢ የሚተዳደሩ ሰዎች ማኅበር ገብተው ለመመላለሻና ለሙዝ የሚሆን ገንዘብ እያዋጡ በየሳምንቱ በዕጣ በተራ እየመጡ የሚጠይቁን ነበሩ፤ ከፉ ቀን ጥሩ ነው በተለያየ የኑሮ ደረጃ የተከፋፈሉትን በዓላማ ያያይዛቸዋል፤ ከፉ ቀን ጥሩ ነው የግፍን ጥርስ ሁሉም እንዲያየውና እንዲንቀው ያደርጋል::

እኅቴ ወይዘሮ ዘለቃ ወልደ ማርያም ከልጅዋ ከወይዘሮ መዓዛ መኮንን ጋር ሁለት ዓመታት ያህል በሳምንት ሁለት ቀናት የሚያስፈልገኝን ሁሉ እያመጣች፣ በየፍርድ ቤቱ ቀጠሮ እየተገኘች በመጉላላት ሃያ ኪሎ ያህል እንድትቀንስ ሊያደርጋት የሚችል ግዴታም ሆነ ውለታ አልነበረባትም፤ ከፉ ቀን የጫነባት ከአንድ ማኅፀን የመውጣት ግዴታ ነው፤ ከኢትዮጵያ ማኅፀን የወጡትን ሁሉ ከፉ ቀን በግዴታ ያስተሳሰራቸውም በዚሁ ምክንያት ነው፤ ወደድንም፣ ጠላንም ሁላችንም፣ ወያኔንም ጨምሮ የአንድ እናት ልጆች ነን፤ እኔ እቴሜቴ የምላትን

እኅቴን የወያኔ ፖሊሶች በአክብሮት «እማማ» ይሏት ነበር፤ ክፉ ቀን ያሳየን የእናት ሆድ ዥጉርጉር መሆኑን ነው።

የክፉ ቀን የውሰታ ሸክም ከቃሊቲ ስንወጣ አላበቃም፤ ለህክምና ወደሕንድ አገር እሄዳለሁ ብዬ ስዘጋጅ ብዙ ወዳጆቼ ብዙ ሺህ ብር አዋጥተውም ሆነ ለየብቻቸው ለመንገዴ እንዲሆን ሰጡኝ፤ ሌሎችም በግላቸው እርዳታ ያደረጉልኝ ብዙ ናቸው፤ ስማቸውን ለመግለጽ ባለመቻሌ አዝናለሁ፤ በአሜሪካና በአውሮፓ የሚኖሩ ወዳጆች ደግሞ ብዙ ገንዘብ አዋጥተው ሕንድ ድረስ ላኩልኝ፤ ደጎች እስካሉ ክፉ ቀን ጥሩ ነው።

አንዳንድ ጊዜም የሚያስገርምና በጥልቀቱም በክብደቱም የማይረሳ ነገር ያጋጥማል፤ አንድ ጊዜ ለውሀ አንድ ሺህ ስድስት መቶ አሥራ ሰባት ብር ያህል ከፈልሁ ብዬ በጋዜጣ ጽፌ ነበረ፤ አንድ የማላውቀው ሰው መንገድ ላይ ሰላም አለኝና ሰለምታ ተለዋወጥን፤ በጋዜጣ ስለጻፍሁት የውሀ ዋጋ አንሥቶ «አባክዎን ትንሽ ልርዳ» አለኝ፤ እኔም ጉዳዩ ያለቀና የተዘጋ ነገር መሆኑንና እርዳታም እንደማያስፈልገኝ ኮስተር ብዬ አስረዳሁት፤ እሱ ግን አጥብቆ የእግዚአብሔርን ስም እየጠራ ለመነኝ፤ አመስግኜው እግዚአብሔር ይስጥልኝ ብዬ ሰላምታ ሰጥቼ ልሄድ ዘወር ስል «በኢትዮጰያ አምላክ!» አለኝ፤ ደነገጥሁ፤ እጄን ዘርግቼ ገንዘቡን ተቀበልሁና አመስግኜው ሄድሁ፤ ከመደንገጤ የተነሣ ስሙንም አልጠየቅሁትም፤ አሁን መንገድ ላይ ባየው አላውቀውም፤ ሁሌም ይቆረቁረኛል፤እቤቴ ከገባሁ በኋላ ሳየው ጥቅልል አድርጎ የሰጠኝ አምስት መቶ ብር ነበር፤ ክፉ ቀን ጥሩ ነው ትሕትና ያስተምራል፤ ቸር አድራጊ ለምኖ፣ ተቀባይ ተለምኖ! ምን ሠርቼ ለዚህ በቃሁ?

ክፉ ቀን ጥሩ ነው ብዙ ጉድም ያሳያል፤ ጓደኛ ወይም ወዳጅ የነበረው ሲርቅና ሲረሳ፣ ስንቱ የተማረውና የተመራመረው አእምሮውን በኦሞ ሙልጭ አድርጎ አጥቦ፣ ኅሊናውን በጨጓራው አፍኖ የሆነውን አልሆነም፤ ያልሆነውን ሆኗል እያለ ለወዳጆቹ ባላጋራ፣ ሆኖ ሲሟገት፣ ለልጆቹ ሐፍረት ሲሆን አየን፤ ዱሮ አባቶቻችን ባለጌን ሀብቱ አያኮራውም ይሉ ነበር! አየነው በክፉ ቀን ዘንድሮ! አበሻ ሲበደልም ያንጎራጉራል፤ በኢጣልያን የወረራ ዘመን

*አርኩም ይሄድና ንኬሉም ያልቅና*
*ያስተዛዝበናል ይኸ ቀን ያልፍና!*

እየተባለ ይዘፈን ነበር፤ በደርግ ዘመንም

*ደርግ በነገሡ ባሥራ ሦስት ዓመቱ*
*ቤት ያፈርስ ጀመር እንደልጅነቱ!*

ሲባል ነበር፤ ባይዘፈንም።

ክፉ ቀን ጥሩ ነው ታሪክን ያስታውሰናል፤ ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ ለፍርድ ቤት በልበ ሙሉነትና በነጻነት ለመናገር መቻላቸውን እኛ በፍርድ ቤት ከአጋጠመን የግዴታ አርምሞ ጋር እንድናነጻጽረው እንገደዳለን፤ ክፉ ቀን ጥሩ



ነው ያለፈውን ከአለው ጋር በእውነት እንድናወዳድረው ያስገድደናል፤ ክፉ ቀን ጥሩ ነው ሕጋዊ ሥርዓትን እንድንናፍቅ ያደርገናል፤ ክፉ ቀን ጥሩ ነው ክብርን ወደውርደት፣ ውርደትን ወደክብር ይለውጣል፤ ክፉ ቀን ጥሩ ነው ያበጠውን ያፈነዳል፤ የፈነዳውን ያሳብጣል፤ ክፉ ቀን ጥሩ ነው ትዕቢተኛውንና ሐሰተኛውን ወዳጆቹ እስኪታዘቡት ያጋልጠዋል፤ ክፉ ቀን ጥሩ ነው የእውነትንና የሐሰትን ድንበር፣ የግፍንና የሕጋዊ ሥርዓትን ድንበር ቁልጭ አድርጎ ያሳያል፤ክፉ ቀን ጥሩ ነው የጉልበተኛውን ልብ ያደነድናል፤ አእምሮውንም ደርግሞ ይዘጋዋል፤የጭካኔውን ወሰንየለሽነት ያወጣዋል።

ክፉ ቀን ጥሩ ነው ጥሩ ቀንን እየጮኸ ይጣራል፤ ክፉ ቀን ጥሩ ነው ያለፋል እንጂ ያልፋል፤ ክፉ ቀን የመጪው ጥሩ ቀን ምልክት ነው፤ ክፉ ቀን እንደሌሊት ጨለማ ነው፤ የሌሊቱ ጨለማ ለእንቅልፍ እንደሚጠቅም የቀኑ ብርሃንም ለሥራ ይበጃል፤ ለሕይወት እንቅልፍም ሥራም በግድ አስፈላጊዎች ናቸው፤ ስለዚህም ይፈራረቃሉ፤ ጨለማው በብርሃን መወገዱ የተፈጥሮ ሕግ ነው፤ ክፉ ቀንም ለጥሩ ቀን ቦታውን መልቀቁ የተፈጥሮ ሕግ ነው፤ በጨለማ ሕይወት ሊቀጥል እንደማይችለው ሁሉ በክፉ ቀንም ሕይወት ሊቀጥል አይችልም፡

ጥሩ ቀን በግድ ክፉ ቀንን ለማስወገድ ይመጣል፤ ክፉ ቀን ጥሩ ነው እንደሰንሰለት የተያያዙ ትውልዶችን ለያይቶ አያጠቃም፤ አንዱን ሲነካ ሁሉንም ይነካል፤ ክፉ ቀን ጥሩ ነው ቀድሞ የሚጣላው ከነገው ባለቤት ከሚያድገው ልጅ ጋር ነው፤ ክፉ ቀን ጥሩ ነው ቀኖችን ሁሉ ሳይለይ ዛሬ ያደርጋቸዋል፤ ትናንትን ወደዛሬ ለውጦ ነገንም ዛሬ ለማድረግ ይመኛል፤ ክፉ ቀን ጥሩ ነው ጊዜ ወደፊት እንጂ ወደኋላ እንደማይሄድ ስለማያውቅ ጊዜ እያሳሳቀ እንደጎርፍ ይወስደዋል፤ ክፉ ቀን ጥሩ ነው መታደስ ስለማይችል ይሻግታል፤ ክፉ ቀን ጥሩ ነው ስለሚሻግት የክፉ ቀን ብል ይበላዋል፤ ራሱን በራሱ ጨርሶ ለጥሩ ቀን መንበሩን ያመቻቻል፤ ክፉ ቀን ጥሩ ነው ተስፋን የሚያስቆርጥ ሳይሆን ተስፋን በምጥ የሚያስወልድ ነው፤ ሕይወት በምጥና በስቃይ ይጀምራል፤ የሕይወት ጣዕም ምጡንና ስቃዩን ያስረሳል፤ ሕይወት ሕይወትን፣ ፍቅርን፣ እድገትንና ተስፋን ያወርሳል።

ሕይወት ክቡር ነው፤ ያማጠች እናት ብቻ የምታውቀው ድል ነው፤ ሕይወት ኃይል ነው፤ የእውቀት፣ የጥበብና የሥልጣኔ ሁሉ ምንጭ ነው፤ ሕይወት ፋታ የማይሰጥና የማያቋርጥ የተከታታይ ትውልዶች ጉዞ ነው፤ በዚህ ጉዞ እጅ ለእጅ ካልተያያዙ በየመታጠፊያውና በየገደላገደሉ የመለያየት አደጋ ያጋጥማል፤ ሕይወት ጊዜ ነው፤ ጊዜ ካልሠሩበት ማስረጃቱን አያቆምም፤ ሕይወት ታሪክ ነው፤ ታሪክ ነገ እንጂ ዛሬ አይጻፍም፤ ነገ ከዛሬ የተለየ ጊዜ እንደሚሆን ማስታወሱ የሚጠቅመው ለዚህ ነው፤ ሕይወት ምስክርነት ነው፤ የትናንቱንና የዛሬውን የምንመዘግብበት ትምህርት ነው፤ ሕይወት ተስፋ ነው፤

ነገን ከትናንቱና ከዛሬው የተለየ አድርገን በአዲስ መልክ የምንቀርጽበት ውሳኔ ነው፡፡

የሁላችንም ሕይወት በአንድ ላይ ክቡር ሆኖ ኃይልን ካላገኘ የእያንዳንዳችን ሕይወት በተናጠል ዛሬም ሆነ ነገ ዋጋ ሊኖረው አይችልም፤ ለሌላው ሰው ሕይወት ዋጋ ስንሰጥ ለራሳችንም ሕይወት ዋጋ መስጠታችን ነው፤ የሌላውን ሰው ሕይወት ስናራክስ የራሳችንንም ሕይወት ማራከሳችን ነው፤ እያንዳንዳችንን አምጣ የወለደችንና ተጨንቃ ያሳደገችን እናት አለችን፤ ለእያንዳንዳችን እናት የእያንዳንዳችን ሕይወት መለወጫ የሌለውና በምንም የማይመነዘር የነጠረ ንጹሕ ፍቅር ነው፤ ግፍ ማለት በዚህ በማይመነዘር የነጠረ ንጹሕ ፍቅር ላይ ጉዳት ማድረስ ነው፤ በአንዲት እናት ላይ የደረሰ መሪር ሐዘን እናቶች ሁሉ የሚሰማቸው መሪር ሐዘን ነው፤ የአንድ እናት እንባ አገርን የሚያጥለቀልቅ የእንባ ጎርፍ ሊሆን ይችላል፡፡

የእያንዳንዱ ሰው ሕይወት ውሱን ነው ቢባልም ከኋላውም ከፊቱም ከሌሎች ሰዎች ሕይወት ጋር የሚቆራኝበትና ሞት የማይበጥሰው ጠንካራ ሰንሰለት አለ፤ ትንሽም ይሁን ትልቅ፣ በጎም ይሁን ክፉ የተረከበው አለ፤ የሚያስረክበውም አለው፤ ተረካቢም አለ፤ ታሪክ የምንለው ይህንን ነው፤ የእያንዳንዱ ሰው ሕይወት ሰፊና ብርሃናማ ሲሆን የሌሎችንም ሰዎች ሕይወት ያዳብራል፤ የጋራና የኅብረት ጥረት ታሪክን እያደሰና ወደፊት እየገፋ ያራምዳል፤ ታሪክ የሚያኮራውና የሚያስከብረው ዛሬ ከትናንት ወዲያው፣ ነገ ከዛሬው ሲሻል ብቻ ነው፤ «ባለህበት ሂድ!» የሕይወት ጸር ነው፤ በጊዜ መቀለድ ነው፤ የትም የማያደርስ መነቃነቅ ጉልበትን መጨረስ ብቻ ነው!

ክፉ ቀን ጥሩ ነው የሕይወት ጣዕሙ በግል ሳይሆን በጋራ መሆኑን ያስተምራል፤ አንኳን የአንድ አገር ሕዝብና የዓለም ሕዝቦች ሁሉ በጣም ተቀራርበዋል፤ በጣም ተሳስረዋል፤ አያገባኝም፤ አያገባውም የሚባል ፈሊጥ ጊዜው እያለፈበት ነው፤ ሁሉም በሁሉም ነገር ያገባዋል፤ የአንዱ ችግር የሁሉም ችግር ነው፤ ክፉ ቀን ጥሩ ነው ይህንን እውነት ያሳያል፡፡

ክፉ ቀን ጥሩ ነው የወደቀውን ለድል፣ የጣለውን ለውድቀት ያዘጋጃል፤ በመግደል የሚተማመነውን ጊዜያዊ ድል ለሞት ዕጣ ይዳርገዋል፤ ገድሎ የሚያሸንፍ በሞት ይሸነፋል፤ ተገድሎ የሚያሸንፍ ድሉ የዘለዓለም ነው፤ ክፉ ቀን ጥሩ ነው፤ ከፋት በጎነትን አሸንፎ እንደማይዘልቅ ያሳያል፤ ሕግ ቀልቡን ሲገፈፍ፣ ዳኝነት ሚዛን ሲያጣ፣ ጉልበት ሁሉን ዳምጦ ሲወጣ፣ የሰውነት ባሕርይ ከፉና በጎው ነጥሮ ገሃድ ሲወጣ  ያሳያል፤ ክፉ ቀን የጠራ መስተዋት ነው፤ መልካችንን ብቻ ሳይሆን ባሕርያችንንም፣ ጤናችንን ብቻ ሳይሆን ሕመማችንንም፣ ውበታችንን ብቻ ሳይሆን አስከፊነታችንንም ቁልጭ አድርጎ ያሳየናል፤ ክፉ ቀን ጥሩ ነው የሕዝብነትን ጥሪ እንድናዳምጥ፣ ከራስ በላይ ነፋስ



በሚል እምነት ላይ የቆመውን የግል ኑሮን ማነቆ እንድንበጥስ እንድንተሳሰብ፣ የእድገትን ጉዞ እንቅፋቶች እንድናስወግድ ያሳስበናል፡፡

ክፉ ቀን ጥሩ ነው፤ ክፉ ቀን የነጻነት ነጋሪት፣ የሕጋዊ ሥርዓት ዋዜማ፣ የሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነት መለከት ነው፤ ክፉ ቀን ሕዝብን ለድል አክሊል የሚያዘጋጅ ነው፤ ኢትዮጵያ የእግዚአብሔርን እጆች ይዛ ትነሣለች፤ የእግዚአብሔርን እጆች ይዛ ታብባለች፤ የእግዚአብሔርን እጆች ይዛ ታፈራለች፤ ትታፈራለች፡፡

# ፫

# አንዳንድ

# የሕገ መንግሥት አንቀጾች

**አንቀጽ** 9(1) ሕገ መንግሥቱ የሀገሪቱ የበላይ ሕግ ነው:: ማንኛውም ሕግ ልማዳዊ አሠራር እንዲሁም የመንግሥት አካል ወይም ባለሥልጣን ውሳኔ ከዚህ ሕገ መንግሥት ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈጻሚነት አይኖረውም::

4) ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የሀገሪቱ ሕገ አካል ናቸው::

**አንቀጽ 13**

(1) በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የፌዴራል መንግሥትና የክልል ሕግ አውጪ ሕግ አስፈጻሚና የዳኝነት አካሎች በዚህ ምዕራፍ · ድንጋጌዎች የማክበርና የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታ አለባቸው::

**አንቀጽ 20**

(3) በፍርድ ሂደት ባሉበት ጊዜ በተከሰሱበት ወንጀል እንደጥፋተኛ ያለመቆጠር በምስክርነት እንዲቀርቡም ያለመገደድ መብት አላቸው::

**አንቀጽ 26**

(2) ማንኛውም ሰው በግል የሚጽፋቸውና በፖስታ የሚልካቸው ደብዳቤዎች እንዲሁም በቴሌፎን በቴሌኮሙኒኬሽንና በኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎች የሚያደርጋቸው ግንኙነቶች አይደፈሩም:

**አንቀጽ 29**

(1) ማንኛውም ሰው ያለምንም ጣልቃ ገብነት የመሰለውን አመለካከት ለመያዝ ይችላል::

(2) ማንኛውም ሰው ያለምንም ጣልቃ ገብነት ሀሳቡን የመግለጽ ነጻነት አለው:: ይህ ነጻነት በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ወሰን ሳይደረግበት በቃልም ሆነ በጽሑፍ ወይም በሕትመት በሥነ ጥበብ መልክ ወይም በመረጠው በማንኛውም የማሰራጫ ዘዴ ማንኛውንም ዓይነት መረጃና ሀሳብ የመሰብሰብ የመቀበልና የማሰራጨት ነጻነቶችን ያጠቃልላል::

[2] በዚህ ምዕራፍ የተባለው ምዕራፍ ሦስት፤ መሠረታዊ መብቶችና ነጻነቶች የሚመለከት ነው፡



(5) በመንግሥት ገንዘብ የሚካሄድ ወይም በመንግሥት ቁጥጥር ስር ያለ መገናኛ ብዙሃን የተለያዩ አስተያየቶችን ለማስተናገድ በሚያስችለው ሁኔታ እንዲመራ ይደረጋል::

**አንቀጽ 30**

(1) ማንኛውም ሰው ከሌሎች ጋር በመሆን መሣሪያ ሳይዝ በሰላም የመሰብሰብ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነጻነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው::...

**አንቀጽ 31**

ማንኛውም ሰው ለማንኛውም ዓላማ በማኅበር የመደራጀት መብት አለው::...

**አንቀጽ 60**

(1) ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሥልጣን ዘመኑ ከማለቁ በፊት አዲስ ምርጫ ለማካሄድ በምክር ቤቱ ፈቃድ ምክር ቤቱ እንዲበተን ለማድረግ ይችላል::

(2) በጣምራ የመንግሥት ሥልጣን የያዙ የፖለቲካ ድርጅቶች ጣምራነታቸው ፈርሶ በምክር ቤቱ የነበራቸውን አብላጫነት ያጡ እንደሆነ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ተበትኖ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ሌላ ጣምራ መንግሥት በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ለመመስረት እንዲቻል ፕሬዚዳንቱ የፖለቲካ ድርጅቶችን ይጋብዛል:: የፖለቲካ ድርጅቶቹ አዲስ መንግሥት ለመፍጠር ወይም የነበረውን ጣምራነት ለመቀጠል ካልቻሉ ምክር ቤቱ ተበትኖ አዲስ ምርጫ ይደረጋል::

**አንቀጽ 73**

(2) በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አብላጫ መቀመጫ ያገኘው የፖለቲካ ድርጅት ወይም ያገኙት የፖለቲካ ድርጅቶች የመንግሥት ሥልጣን ይረከባል/ይረከባሉ::

**አንቀጽ 79**

(2) በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ የዳኝነት አካል ከማንኛውም የመንግሥት አካል ከማንኛውም ባለሥልጣን ሆነ ከማንኛውም ሌላ ተጽዕኖ ነጻ ነው::

(3) ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸውን በሙሉ ነጻነት ያከናውናሉ:: ከሕግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ አይመሩም::

**አንቀጽ 112**

(1) በፌዴራልና በክልል የምርጫ ከልሎች ነጻና ትክክለኛ ምርጫ በገለልተኝነት እንዲካሄድ ከማንኛውም ተጽዕኖ ነጻ የሆነ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ይቋቋማል::

ከዚህ በላይ ተመርጠው የወጡትን የሕገ መንግሥቱን አንቀጾች ሕገ መንግሥቱን እንደየጥቃት መሣሪያ አድርገው የሚጠቀሙበት የተለያዩ ባለሥልጣኖች ትክክለኛ ግንዛቤ እስቲአገኙ ድረስ ደጋግመው ሊያነብቡአቸው ይገባቸዋል፤ ከዚህ በላይ ተመርጠው የወጡትን የሕገ መንግሥቱ አንቀጾች በተለይ ፖሊሶች፣ ዓቃብያነ ሕጎች፣ ዳኞችና የምርጫ ቦርድ ሰዎች የኃላፊነታቸውን መጠን በትክክል የሚያስገነዝቡ በመሆናቸው እነዚህን አንቀጾች በጥሞና ሊያጠኑአቸው ይገባል፤ ሕጉን አላውቅም በማለት ከወንጀል ክስ ለማምለጥም የማይቻል መሆኑን ሊረሱት አይገባቸውም።

ወደፊት ክስም ሆነ የታሪክ ወቀሳ የሚመሠረተው በነዚህ አንቀጾች ላይ ሊሆን ይችላል፤ በልጆችና በልጅ ልጆች ላይ የኀሊና ጫናና የመንፈስ መናወጥ እንደሚያስከትል ልንጠራጠር የምንችል አይመስለኝም፤ እነዚህን ሕገ መንግሥታዊ አንቀጾች ለመጠበቅና ለማስጠበቅ ግልጽ የሆነ አደራና ኃላፊነት የተቀበሉና ያልተወጡት ሰዎች ሁሉ ሌላው ቢቀር በልጆቻቸውና በልጅ ልጆቻቸው ይወቀሳሉ።

እነዚህ የሕገ መንግሥቱ አንቀጾች አለኝታና መከታ ሳይሆኑአቸው ቀርተው የግፍና የጥቃት ሰለባ የሆኑ ሰዎችም ከነወንድሞቻቸውና እኅቶቻቸው፣ ከነልጆቻቸውና የልጅ ልጆቻቸው የጥቃት ቁስላቸውን የሚያሽርላቸው አጥተው እያረሩ አብረው ይኖራሉ፤ ለሕገ መንግሥቱ ሊኖራቸው የሚገባውን አደራና ኃላፊነት ያልተወጡት ባለሥልጣኖች ልጆችና የልጅ ልጆች በማያውቁትና በማይነካቸው ጥፋት ጉዳዩ በተነካ ቁጥር እነሱም ይታመማሉ፤ይሸማቀቃሉ፤ ለምን? ሊኮሩባቸው በሚፈልጉአቸው ሰዎች እንዲያፍሩ ይገደዳሉና፤ ማንም ሰው ምን ጊዜም ብቻውን አይደለም፤ የሚወዱትና የሚያስቡለት፣ የሚጨነቁለት ሰዎች አሉት፤ እነዚያ ሰዎች ያንን ሰው የሚወዱትን ያህል ሊያከብሩት ይፈልጋሉ፤ ፍቅሩ የሚመጣው በተፈጥሮ ግንኙነት፣ ወይም አብሮ ለብዙ ዘመናት በመኖር፣ ወይም በውለታ ይሆናል፤ ማክበሩ ግን በነዚህ መንገዶች አይመጣም፤ በዚያ ሰው መኩራቱም በነዚህ መንገዶች አይመጣም፤ አንድ ሰው የሚከበረውና ዘመዶቹን የሚያኮራው ሌሎች፣ ዘመድ ወይም ወዳጅ ያልሆኑ ሰዎች በሚሰጡት ግምት ነው።

በሌላ አነጋገር ፍቅር ዕድሜው አጭር ነው፤ ክብር ዕድሜው ረዢም ነው፤ ፍቅር ቢበዛ ከአንድ ትውልድ አያልፍም፤ ክብር ከብዙ ትውልዶች የሚመጣ ነው። እኔ ከሞትሁ የሚል ካለ አያነጋግርም! በሕግ አይቀለድም፤ ደርግን ልዩ ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ በሕግ አለመቀለዱ ነበር፤ በመደበኛ ፍርድ ቤቶች ውስጥ ጣልቃ አይገባም ነበር፤ ዳኞቹ በተደጋጋሚ በመንግሥት ላይ ሲፈርዱ ታይቷል፤ በፍርድ ቤት ከቀጥተኛ ጣልቃ ገብነት ያለፈ ጭካኔ የታየው ስዒረ መንግሥት ሞክረዋል በተባሉት አሥራ ሁለት ጀኔራሎች ላይ ኮሎኔል መንግሥቱ በንዴት የፈጸመው አረመኔያዊ ግፍ ነው፤ ከዚህ በቀር ደርግ



ያስራል፤ ይገድላል፤ ነገር ግን ፍርድ ቤቶችን መሣሪያ በማድረግ ሳይሆን ከሕግ ሥርዓቱ ውጭ ነበር፤ ደርግ የፖሊቲካ ውሳኔ በማለት እየገደለ የፍየል ወጠጤ የሚያስዘፍነው ከሕጉ ሥርዓት ውጭ ነበር።

ማኅበረሰባዊ ኑሮ ያለሕግ አይሠምርም፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ በዳኝነት በኩል የሚያኮራ ባህል አለው፤ ያንን ልናዳብረው ሲገባን መጠበቅ እንኳን አለመቻላችን አንዱና ዋነኛው የውድቀታችን ምልክት ነው፤ ሕግ እንደተፈለገ የማጥቂያ መሣሪያ ከተደረገ፣ ፖሊሶች ሕጋዊ ሥርዓትን ጠብቀው የማይመረምሩ ከሆነ፣ ዓቃብያነ ሕጎች የሕጉን መንፈስ ተከትለው ክስን በትክክል የማይመሠርቱ ከሆነ፣ ዳኞች በትእዛዝ ሳይሆን በሕጉና በኅሊናቸው የማይዳኙ ከሆነ ማኅበረሰቡን የሚያስተማምነውና የሚያስተሳስረው ነገር ይጠፋል፤ የሚያስከትለውም የኅሊና ቁስል በአንድ ትውልድ የሚሽር አይሆንም፤ ይህ ቁስል የሚያብሰለስለው አሁን በአጥቂነትና በተጠቂነት ያለውን ትውልድ ብቻ ሳይሆን የእነሱን ልጆችና የልጅ ልጆችም ነው፤ የሚያሳዝነውም ይህ ነው፤ እውነቱን እየተናገርን ኅሊናችንን ማጠብና ማፅዳት ያስፈልገናል።

# ፬
# የቅድመ-ቅንጅት የፖለቲካ ሁኔታ

## 1. የፖለቲካ ቡድኖች ሁኔታ

ወያኔ/ኢሕአዴግ የፖለቲካ በሩን ገርበብ አድርጎ ከከፈተው በብዙ ዓመታት ከ1997 ይቀድማል፤ ነገር ግን ተቀናቃኝ የፖለቲካ ቡድኖች ሆነው አደባባይ የወጡት አብዛኛዎቹ ወያኔ/ኢሕአዴግ የቀየሰላቸውን ቅርጽ ይዘው ነበር፤ የሁሉም ቡድኖች መሠረት ቋንቋ ወይም ጎሣ ነበር፤ በእኔ አስተሳሰብ እነዚህን የጎሣ ቡድኖች የፖለቲካ ቡድኖች ማለት ስሕተት ነው፤ ዋናው ምክንያት የተቋቋሙት በፖለቲካ ሀሳብ ወይም እምነት ላይ ሳይሆን በአንድ ጎሣ ላይ ነው፤ ፖሊቲካ ቋንቋውን ብቻ ሳይሆን የሃይማኖቱንም፤ የጤናን፣ የትምህርትን፣ የሀብት ድልድሉንም፣ በአጠቃላይ የኑሮን ጣጣ በሙሉ የሚነካና ከሁሉም በላይ በሕጋዊ ሥርዓት ላይ የሚያተኩር ነው፤ አንድ ዓይነት ቋንቋ የሚናገሩ ወይም በአንድ ሃይማኖት የሚያምኑ ሰዎች የሚያቀራርባቸውና የሚያያይዛቸው ነገር መኖሩ አያጠራጥርም፤ ነገር ግን ቋንቋውንም ሆነ ሃይማኖቱን አብዛኛው ሰው አስቦና ፈልጎ የመረጠው ስላልሆነ በኃላፊነት የሚጠየቅበት አይደለም፤ እንዲሁም የተለያዩ ቋንቋዎችን የሚነጋገሩና በተለያዩ ሃይማኖቶች የሚያምኑ ገበሬዎች፣ የፋብሪካ ሠራተኞች፣ ነጋዴዎች፣ ባለሀብቶች፣ አስተማሪዎች፣ ወታደሮችና ፖሊሶች በየፊናቸው በአንድ ዓይነት ተግባር ላይ በመጠመዳቸውና ተመሳሳይ ችግሮችን በማየታቸው አብረው በአንድነት ቆመው እንዲታገሉ የሚያደርጓቸው ብዙ ነገሮች አሉ፤ ፖሊቲካ የሚሆነው ይህ ዓይነቱ እያንዳንዱ ሰው በተናጠል ቆሞ የጋራ ኃላፊነትን የሚቀበለውና አስፈላጊም መስሎ ሲታየው ከሌሎች ጋር ተባብሮ ሊለውጠው የሚችለው የኑሮ ጣጣ የሚወልደው ችግር ነው።

ኑሮ የሚወልዳቸው የጋራ ችግሮች የቋንቋንና የሃይማኖትን ድንበር ጥሰው ሰዎችን አስተሳስረው ለአንድ ዓላማ እንዲቆሙ ያደርጋሉ፤ ስለዚህም የጎሣ ቡድኖች በተፈጥሮ ይዘትና በመንደር ችግር ብቻ የታጠሩ በመሆናቸው ሊያድጉ አይችሉም፤ እንዲያውም የማይቀር የኑሮ ጣጣ የሚወልደው የፖለቲካ አስተሳሰብ እየገባባቸው ያያይዘናል ብለው ያሰቡት የጎሣ ክር እየተበጣጠሰባቸው የተለያየ አመለካከት ያላቸው ሰዎች አንድን ጎሣ ሲከፋፍሉት እያየን ነው።

በአንድ ሰው ላይ ጥቃት ወይም በደል ሲፈጸም የእኔ ጎሣ አባል አይደለም ብሎ አያገባኝም የሚል ገና ወደሰውነት ደረጃ ቀርቶ ወደዜግነት ደረጃ



ያልደረሰ ነው፤ የራሱን ሰውነት ገና ሰላላወቀ የሌላውን ሰውነት ለመገንዘብ ያዳግተዋል፤ በራሱ ላይ ቢደርስም የጠራ ሰውነቱን የሚያመለክት አስተያየት አይኖረውም፤ ጥቃትንና በደልን፣ አድልዎንም የምንቃወመው ግፍ በራሳችን ላይ ሲፈጸምብን እንደማንወደው ሁሉ በሌላ በማንም ሰው ላይ ሲፈጸም ትክክል አይደለም ከሚል አጠቃላይ ቁም ነገር ተነሥተን ነው፤ ስለዚህም የሰውነት ግንዛቤ ከአለን አንድ ጎሣ ከማንም ምንም ዓይነት ጥቃት ወይም በደል እንዳይደርስበት ለመከላከል የጎሣ ድርጅት በግድ አስፈላጊ አይደለም፤ በጎሣ የሚያምኑ ሰዎች ጥቃት የሚሉት በራሳቸው ጎሣ ላይ ብቻ፣ ያውም በሌላ ጎሣ አባል ግፍ ሲፈጸም ነው፤ የጎሣ ድርጅት ጥቃት የሚለው ከጎሣው ውጭ በሆነ ሰው የሚሰነዘረውን ብቻ ነው ከተባለ የሚቃወመው ጥቃትን ሳይሆን የአጥቂውን ማንነት ብቻ ነው፤ የአንድ ጎሣ አባሎች በጥቃት ቢጣመዱ ችግር አይታይም ማለት ይመስላል፤ በዚያው በጎሣው ውስጥ ያሉት በደህውና በደካማው ላይ የሚያደርሱትን ጥቃት በአጥቂዎቹ ማንነት የሚታለፍ ከሆነ የግንዛቤ ችግርን ያመለክታል፤ ጥቃትን ከማናቸውም አቅጣጫ ለመታገል ሰው መሆን ይበቃል፤ እውነተኛ ዜጋ መሆን ይበቃል፤ የሚያስፈልገው ማንም የጎሣ አባል ወይም ዜጋ ብቻ ሳይሆን ማንም ሰው ለጥቃት ወይም ለበደል መዳረግ የለበትም የሚል እምነትና አቅዋም ነው፤ ወደ ፖለቲካ የሚያመራው መንገድ ይህኛው ነው።

ብዙዎቹ የፖለቲካ ቡድኖች የጠራ የፖለቲካ አመለካከትና አቅዋም ስለሌላቸው ከገዢው ቡድን ጋር ከሚያደርጉት ትግል ይልቅ እርስበርሳቸው የሚያደርጉት ትግል ይበልጥ ነበር፤ እንደአነግና እንደእስላማዊው የኦሮሞ ነጻ አውጪ ድርጅት ያሉት እስከ መገዳደልም ደርሰው ነበር፤ ወያኔ/ኢሕአዴግ በሩን ገርበብ አድርጎ ቢከፍትም ተቀናቃኝ የፖሊቲካ ቡድኖች የሚባሉት ራሳቸውን አጠናክረውና ተደራጅተው በልበ ሙሉነት ገዢውን ቡድን በምርጫ ሊገጥሙት ቆራጥ አቅዋም አልነበራቸውም፤ እንዲያውም ብዙ ጊዜ በምርጫ ላለመሳተፍ ሰበቦችን ይደረድሩ ነበር።

ጥቂት የፖሊቲካ ቡድኖች በሕጋዊነት በኢትዮጵያ ውስጥ ይንቀሳቀሱ ነበር፤ መላ ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረት (ኢዴኅ) የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ፓርቲ (ኢዴአፓ) የመላ ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ፓርቲ (መኢዴአፓ)፣ የኅብረት ኃይሎች ዋናዎቹ ነበሩ፤ ከነዚህም መሀከል በውስጥ ንትርክና መከፋፈል ኢዴኅ ከጠንካራ ህልውና ውጭ ሆነ፤ ሁሉም በውስጣቸው ችግሮች ነበሩባቸው፤ እርስበርሳቸውም ችግሮች ነበሩአቸው። ነገሩ ያሰጋን ጥቂት ሰዎች ተነጋገርንና በኢትዮጵያ ውስጥ የፖለቲካ ባህልን ለማዳበር የእነዚህ የፖለቲካ ቡድኖች መተባበር አስፈላጊ ነው ብለን የአቀራራቢ ወይም የአስታራቂ ቡድን ፈጠርንና በ1995ና በ1996 ግድም ሥራ ጀመርን፤ ዶር. ብርሃኑ ነጋ፣ ዶር. በፈቃዱ ደግፌ፣

አቶ አበበ ወርቄና እኔ ከየቡድኖቹ መሪዎች ጋር ብዙ ተከታታይ ስብሰባዎችን አካሄድን፤ ያነጋገርናቸው የፖሊቲካ ቡድኖች መሪዎች ኤንጂነር ኃይሉ ሻውል፣ ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ፣ ዶር. መረራ ጉዲና፣ አቶ ልደቱ ኢያሰውና ሌሎችም ነበሩ።

በመሀከላቸው ምንም የፖሊቲካ አስተሳሰብ ልዩነት ሳይኖርባቸው ጥቃቅን አለመተማመንን የሚያመለክቱ ነገሮች ብቻ እያነሡ ለማቀራረብ የተደረገው ጥረት ሳይሳካ ቀረ፤ እኛም በጣም ተስፋ ቆረጥንና አቋረጥነው፤፡ ምናልባት አንድ ዓመት ያህል ከቆየን በኋላ ብዙ ሰዎች እንደገና ጥረቱን እንድንቀጥል ገፋፉን፤ በበኩሌ በአለፈው ጥረታችን አለመሳካት በጣም አዝኜ ስለነበረ ለሁለተኛ ጊዜ ለማዘን ፈቃደኛ አልነበርሁም፤ ግን ብርሃኑ ነጋ በጣም ስለገፋፋኝ ጀመርነው፤ ብዙ ስብሰባዎችን ከአደረግን በኋላ በመጀመሪያው ዙር አብረው የነበሩ የመሰሉን ሰዎች በሁለተኛው ዙር ቦታ ተለዋውጠው አገኘናቸው፤ የማይበገሩ ስለሆኑብን እንድናቋርጠው ተገደድን፡

ስለዚህም በ1997 ይህንን የፖለቲካ ቡድኖቹን የፈዘዘ ሁኔታ ለመለወጥ ሕዝቡ ለምርጫ ተሳትፎ እንዲመዘገብ የማያቋርጥ ቅስቀሳ በጋዜጣዎች ሁሉ ተጀመረ፤ በእንጻሩም ምርጫው ዋጋ የለውም፤ የወያኔ/ኢሕአዴግን የዴሞክራሲ አስመሳይነት ለማረጋገጥ ካልሆነ በቀር ፋይዳ የለውም የሚሉም በየጋዜጣዎቹ ላይ ይጽፉ ነበር፤ ሆኖም የምርጫ ምዝገባ ቅስቀሳው እየለና የሕዝቡ መንፈስ ለምርጫ ተነሣሣ፤ ወያኔ/ኢሕአዴግን ለመፈተን ቆረጠ፤ ቅንጅት ያመጣው የመንፈስ ለውጥ ይህ ነው፤ ቅንጅት እንዴት ተፈጠረ; ይህንን ዋና ጥያቄ ለመመለስ በቀስተ ደመና ምሥረታ መጀመር አለብን።

## 2. የቀስተ ደመና መመሥረት

ሌሎቹን የፖሊቲካ ቡድኖች ማቀራረብ ያቃተን ሰዎች ተስፋ አልቆረጥንም ነበር፤ ከዚህ በኋላ ብርሃኑ ነጋ፣ በፈቃዱ ደግፌ፣ ሽመልስ ተከለ ጻድቅና እኔ ሌሎች ሰዎችንም ጨምረን ቀደም ሲል ስናደርገው እንደነበረው ስለፖሊቲካ ፓርቲ መነጋገር ጀመርን፤ በዚህ ጊዜ ብርሃኑ በኢኮኖሚስቶች ማኅበር መካነ ጥናት የነበረውን ኃላፊነት ጨርሶ ስለነበረ እራታችን በቁርጠኛነት አዲስና የተለየ የፖለቲካ ቡድን ለማቋቋም ተነሣን፤ የተለየ የሚያደርገውም ሙሉ በሙሉ በፖሊቲካ እምነት ላይ እንጂ ምንም ሌላ ነገር ያልተበረዘበት እንዲሆንና ትልቁ ተልእኮውም ያሉትን የፖሊቲካ ቡድኖች እንደሙጫ ሆኖ ለማያያዝ የሚችል የመንፈስና የአእምሮ ጉልበት ያለው ቡድን ለመመሥረት ውሳኔ ላይ ደረስን፤ በፖሊቲካ እምነታችን አንዳንዶቻችን በጣም ጠንካራ የማኅበረሰባዊ ወይም ሶሽያል ዴሞክራሲ ዝንባሌ የነበረን ቢሆንም



ለጊዜው ሁሉንም የሚያያይዝ ሰፋ ያለ መሠረት ያለውን የፖለቲካ እምነት መረጥን፤ ደርግ በአጉል አመራር ሶሽያሊዝም ወይም ማኅበረሰባዊነት የሚባለውን የፖለቲካ ፍልስፍና በሕዝብ እንዲጠላ ስላደረገው ብዙ ሰዎች ሊሰሙትም አይፈልጉም፤ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መልክ እንዳለው አያውቁም፤ ወይም ለማወቅ አይፈልጉም፤ ዴሞክራሲያዊ ሶሽያሊዝም ዛሬ በብዙ የአውሮፓ አገሮች የሚሠራበት ነው፤ አብዛኛውን ጊዜ የዚህ ፖለቲካ እምነት አቀንቃኞችና ደጋፊዎች የሚሆኑት የሠራተኛው ክፍል ናቸው፤ እንደኛ አገር ላለው ደግሞ ደሀው ገበሬም ደጋፊ ይሆነው ነበር፤ እነዚህ በኢትዮጵያ ገና አልነቁም፤ ስለዚህም ጊዜው ገና ይመስላል፡

እንግዲህ ቀስተ ደመና በዚህ ሁኔታ ተጀመረና ወጉንና ሥርዓቱን ሁሉ አሟልቶ ሕጋዊ የፖሊቲካ ቡድን ሆነ፤ የመጀመሪያው ተግባሩ ያደረገውም ከተለያዩ የፖለቲካ ቡድኖች ጋር እየተገናኘ ስለመተባበር መነጋገር ነበር፤ የቀስተ ደመና አንዱና ዋናው ዓላማ ሌሎቹን በኑሣ ያልተደራጁትን ቡድኖች ማያያዝና ማጠናከር ነበር። ከቀሩት ተቀናቃኝ ቡድኖች ጋር ለመወዳደር ሳይሆን ለእነሱ ሲሚንቶ ለመሆንና አንድነትን ለመፍጠር ነበር።

## 3. የቅንጅት አመሠራረት

ቀደም ሲል የፖሊቲካ ቡድኖቹን ለማግባባት ሲጥሩ የነበሩት (ከአቶ አበበ በቀር) አሁን የቀስተ ደመና ቡድን አባሎች ሆነው የመቀናጀቱን ዓላማ በትጋት ጀመሩ፤ የተነሡት ሁለት ዋና ቁም ነገሮችን ይዘው ነበር፤ አንደኛ በቅንጅቱ ውስጥ እንዲገቡ የሚጋበዙት ለማንም ያልተዘጉና ለዜጎች ሁሉ ክፍት የሆኑ የፖሊቲካ ቡድኖች ብቻ እንዲሆኑ፣ ሁለተኛ የፖሊቲካ ቡድኖቹ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉና ሕጋዊ ሰውነትን ያገኙ እንዲሆኑ በመወሰን ነበር፤ በዚህ መሠረት የቀስተ ደመና ቡድን አባሎች የተመረጡትን አምስት የፖለቲካ መሪዎች ተራ በተራ ማነጋገር ጀመሩ፤ የቀስተ ደመና አቅዋም በደንብ የተጠና ስለነበረ ከቡድኖቹ ጋር መሠረታዊ ስምምነት ለማግኘት ብዙ ጊዜም አልወሰደም፤ ጥሪው ባቡሩ ሊነሣ ነው፤ መንቀሳቀስ የምትፈልጉ ተሳፈሩ የሚል ነበር።

የመረጥናቸውና ያነጋገርናቸው የፖለቲካ ቡድኖች የሚከተሉት ነበሩ፡-

- መኢአድ፣ መላ ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ተለዋዋጭ ታሪክ ያለው ነው፤ በመጀመሪያ ሲቋቋም መላ አማራ ሕዝባዊ ድርጅት ነበረ፤ በኋላ ወደመላ ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ተለወጠ፤ በቅንጅት ውስጥ በኋላ ከተካተቱት ድርጅቶች ሁሉ ረጂም ታሪክ ያለውና በአብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ክፍሎች ይንቀሳቀስ የነበረ ነው፤ በአመራርም በኩል በፕሮፌሰር ዓሥራት የመላ አማራ ሕዝባዊ ድርጅት ተብሎ ተቋቁሞ በኋላም በቀኛዝማች ነቅዓ ጥበብ ሲመራ የቆየ ድርጅት ነው፤ቀደም ሲል በዚሁ ድርጅት ውስጥ የፕሮፌሰር ዓሥራት ምክትል

ሆኖ ሲሠራ የነበረው ኤንጂነር ኃይሉ ሻውል ነበር፤ በኋላ በፈቃዱ ለቀቀና በይፋ ፖሊቲካ መድረኩ ወጣ፤ ድርጅቱ ዓላማውንና ስሙን ለውጦ መኢአድ ከሆነ በኋላ ኤንጂነር ኃይሉ ሻውል በፕሬዚደንትነት ተመርጦ ገባ።

ኢዴአፓ፣ በመጀመሪያ የተቋቋመው መላው አማራ ውስጥ በነበሩ ወጣቶች ነው፤ እነዚህ ወጣቶች በመላ አማራ ድርጅት ውስጥ የነበረው ሁኔታ የሚያሳድጋቸው መስሎ ሳይታያቸው ቀረና ከደቡብ ኅብረት ጋር ተቀላቀሉ፤ እዚያም ደስ ስላላቸው የራሳቸውን ፓርቲ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ፓርቲ ብለው አቋቋሙ፤ ሁሉም ገና ወጣቶች ስለነበሩ በሰል ያሉ ሰዎችን ለማስገባት በጣም ጥረው ዶር. አድማሱ ገበየሁንና ዶር. ኃይሉ አርአያን አገኙ፤ እነዚህን ሰዎች ለወጉ በከፍተኛ ወንበር ላይ አስቀምጦ ባለሙሉ ሥልጣን ሆኖ ፓርቲውን እንደኮሚዩኒስት ፓርቲ በዋና ጸሐፊነት የሚመራው ልደቱ አያሌው ነበረ፤ ምናልባትም ቀድሞ በመላ አማራ ድርጅት ውስጥ አንድ ላይ ስለነበሩና ስለሚተዋወቁ፣ በዚህም የተነሣ በመሀከላቸው የቆየና የሻከረ ግንኙነት ከመኢአድ ጋር ነበራቸው፤ በኋላ የቅንጅት መበታተኛ ምክንያቶች አንዱ ይህ በመኢአድና በኢዴአፓ መሀከል ሊበርድና ሊሽር ያልቻለ መቆሳሰል ነበር።
ሌላው እጩ ፓርቲ መኢዴአፓ ነበር፤ የተቋቋመው ከኢዴአፓ በወጣ ሰው ስለነበረ በመኢአድና በኢዴአፓ መሀከል ከመአሕድ (መላው አማራ) ግንኙነታቸው የተፈጠረውን ዓይነት የሻከረ ስሜት በኢዴአፓና በመኢዴአፓ መሀከልም ተፈጥሮ ነበረ፤ ይህንን ሁሉ ችግር በግልጽ ተነጋግሮና ተወያይቶ ወደስምምነት ለመድረስ ቀላል አልነበረም፤ ግን የሚቻለው ተደረገ።

የሚቀጥለው እጩ ፓርቲ ኢዴሊ (የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሊግ) ነበረ፤ ይህ ፓርቲ ከብርሃኑ ነጋና ከእኔ ጋር የተያያዘ ታሪክ አለው፤ በ1992 ኢሰመጉ (የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ) ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ባዘጋጀው አውደ ትምህርት ላይ ባደረግነው ንግግር በማእከላዊ ታስረን በነበረበት ጊዜ እንደልማዳቸው ቤት ሲበረብሩ ከሁለታችንም ቤት የኢዴሊን ፕሮግራም አገኙ፤ እንደሚመስለኝ ሰዎቹ አንብበን ሀሳብ ወይም አስተያየት እንድንሰጣቸው የላኩልን ነው፤ ምንም ከሕግ ውጭ ነው የሚባል ነገር የለበትም፤ ለማእከላዊ ወንጀል ፈጣሪዎች ግን መንግሥትን ለመገልበጥ በሰውር የተቋቋመ ድርጅት አስመስለው ከባድ ክስ ተመሠረተብን፤ ከኢዴሊ የምዝገባ ማመልከቻ ጋር ይህ ሰነድ ለምርጫ ቦርድም ደርሶ እንደነበረ ሰምተናል፤ ኀሊና ያላቸው ዳኞች አጋጥሞን ከአንድ ወር እስር በኋላ በዋስ ብንለቀቅም ነጻ የወጣነው ከሰባት ዓመታት በኋላ ነው፤ ዋስ ባይፈቀድልን ኖሮ ቃሊቲ እንቆይ ነበር! ከሁለተኛው እስርም እናመልጥ ነበር! ነበር! ለማናቸውም ቅንጅትን በተመለከተ የኢዴሊ ጉዳይ ምንም ችግር አላጋጠመንም።



ኢዴኅ (የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረት ወይም በተለምዶ ኢዲዩ የሚባለው) በትርምስ ላይ ስለነበረ ሊካተት አልቻለም።

ከኢዴአፓ ጋር መጀመሪያ በጥቅምት 2/97 ባደረግነው ንግግር «እነማን ናችሁ?» በማለት ጀምረው «ምን አነሣሣችሁ?» እያሉ አግባብ ያላቸውን ጥያቄዎች ከሰነዘሩና ከተወያየን በኋላ ወደሌሎች ፓርቲዎች ዞሩ፤ በአጠቃላይ ለሌሎች ፓርቲዎች ቀና አመለካከት አልነበራቸውም፤እናንተ አዲሶች ናችሁ፤ እኛ ቆይተንበታል፤ እስከዛሬ የነበረው ችግር ለወደፊት መሰናከል ሊሆን ይችላል፤ በማለት በተለይ የመኢአድን «አምባገነን አመራር» እያወገዙ ተናገሩ፤ ዶር. አድማሱ ወደዋናው ጉዳያችን እንድንገባ ገፋፍቶን ጀመርን፤ በሚያግባቡን ነጥቦች ላይ ተወያይተን ተለያየን።

ጥቅምት 7 ቀን በተደረገው የሁሉም ፓርቲዎች ስብሰባ ላይ ልደቱ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በጣም የከረረ አቅዋም እንዳለው አመለከተ፤ ለምሳሌ የአባል ድርጅትን ህልውና የሚነካ ጉዳይ በድምፅ ብልጫ ሊወሰን አይገባም አለ፤ በዚህ ጉዳይ ላይ የህልውና ጉዳይ የምትለውን ዘርዝርልን በማለት ብርሃኑ ወጥሮ ሲይዘው ስለገንዘብ ማሰባሰብና አዲስ ድርጅትን ስለማስገባት አነሣ፤ ከዚህ ጋር ተያይዞ የመኢዴአፓ ቅንጅትን በመቀላቀሉ ጉዳይ የጠነከረ ተቃውሞ ከኢዴአፓ በኩል ቀረበ፤ ሌሎቻችን መኢዴአፓን ለመቀበል ዝግጁዎች ብንሆንም የኢዴአፓ ተቃውሞ የከረረ ስለነበረ የጊዜው የፖለቲካ ሚዛን ለኢዴአፓ በማጋደሉ መኢዴአፓን ሳንቀበለው ቀረን፤ በበኩሌ ትክክል አልነበርንም ባይ ነኝ፤ ምናልባትም የመጀመሪያው ስሕተት (የልደቱም የሌሎቻችንም) ይህ ነበር ለማለት ይቻላል።

የፖሊቲካ ዓላማ በግል ስሜትና በቂም በርን መዝጋት ሳይሆን መሠረታዊ አቅዋማቸው አንድ ለሆነ ሁሉ በርን መክፈት ነው፤ ነገር ግን በጊዜው ኢዴአፓን ከማጣት የተሻለ የፖለቲካ ትርፍ መስሎ ታየን፤ የቀሩት አራት ቡድኖች እየተገናኙ መነጋገር ቀጠሉ; የአራቱ ፓርቲዎች ባሕርይ የተለያየ ነበር፤ ኢዴአፓ ፕሬዚደንትና ምክትል ፕሬዚደንት ቢኖሩትም የሚመራው በዋና ጸሐፊው ነበር፤ መኢአድ ሌሎች ወንበሮች ቢኖሩትም የሚመራው በፕሬዚደንቱ ነበር፤ ኢዴሊ እንዴት ሲመራ እንደነበረም ለማወቅ አልተቻለም፤ እንደሚመስለኝ በስተጀርባ ሆኖ በሚመራ ፕሬዚደንት ስር ነበር፤ቀስተ ደመና ሲጀምር በተቻለ መጠን በዴሞክራሲያዊ መንፈስ በእኩልነትና በነጻነት በፕሬዚደንቱ ይመራ ነበር።

ውይይቱ ሠመረና ከአራቱ ቡድኖች አራት አራት ተወካዮች እየተገናኙ በቋሚነት መነጋገር ጀመሩ፤ ምናልባት አንድ ነገር ለእኔ ግልጽ ባልሆነልኝ ምክንያት የኢዴሊ ፕሬዚዳንት በማናቸውም ስብሰባ ላይ አለመገኘቱ ካልሆነ በቀር ሁሉም ቡድኖች በዋና መሪዎቻቸው ተወክለው ነበር፤ የቅንጅት ጥንስስ ይህ ነበር፤ አንዳንድ ሰዎች እንደሚገምቱት ቅንጅት በድንገት ብቅ ያለ ድርጅት

አይደለም፤ ታሪክ አለው፡፡ገብረ ክርስቶስ በጻፈው *ቅንጅት ከየት ወዴት* በሚለው መጽሐፍ ቅንጅት በጥድፊያ የተቀነባበረ አስመስሎ ጽፎአል፤ በእርግጥ ገብረ ክርስቶስ እንደገለጸው እንኳን በቀስተደመና በኩል የተደረገውን ዝግጅትና የራሱ ድርጅት በሆነው በመኢአድ ውስጥ የሆነውን እያውቅ እንደነበር ስለገለጸ አይፈረድበትም፤ መኢአድ፣ (መላ ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት) ኢዴአፓ-መድኅን (የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ፓርቲ)፣ ቀስተ ደመናና ኢዴሊ (የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሊግ) በአንድ ላይ ሆነው ቅንጅት የሚባል አዲስ ድርጅት መሥርተው ደንብ አወጡ፤ ሹሞቹን መረጡ፡፡

ከየቡድኑ ወደቅንጅት የገቡት ሰዎች አብዛኛዎቹ ቅንጅት ለመሆን ጊዜ ፈጀባቸው፤ አስተያየት ሲሰጡም ሆነ ድምፅ ሲሰጡ በግል እምነታቸው ላይ የተመሠረተ ሳይሆን በቡድናቸው ፍላጎት የሚመሩ ነበሩ፤ እራቱ የቀስተ ደመና አባሎች (ብርሃኑ፣ በፈቃዱ፣ ሽመልስና እኔ የተለያዩ ሀሳቦችን እናቀርባለን፤ ድምፅ ስንሰጥም ነጻ ሆነን በየራሳችን አቅዋም ነበር፤ በሌሎቹ ዘንድ በተለይ በመኢአድና በኢዴአፓ ተወካዮች በኩል መቀናጀቱ ገና አልጠለቀም ነበር፤ ግን ቀስ እያለ አቅጣጫ መያዝ ጀምሮ ነበር፡፡

በእኔ ግምት የብርሃኑ ነጋ አስተዋጽኦ የጎላ ነበር፤ አንዱም ዋና ምክንያት የብርሃኑ ጠባይ ነው፤ ብርሃኑ አንድ ነገር ከያዘ በእልህ ነው የሚከታተለው፤ ለራሱም ቢሆን ፋታ አይሰጥም፤ ልማቱም ሆነ ጥፋቱ ከችኮላ ጋር የተያያዘ ነው፤ ስለዚህም የተለያዩትን ቡድኖች ሰንጎ የያዛቸው በይበልጥ እሱ ነበር፤ በመጀመሪያው ላይ የሌሎች ቡድኖች መሪዎችም ቢሆኑ ከብርሃኑ ነጋ ጋር ይበልጥ የመቀራረብና የመተማመን ዝንባሌ ነበራቸው፤ ይህ እውነት በመጨረሻ ላይ ወደከፋ መልኩ የተለወጠው ሌሎች በብርሃኑ ላይ ያላቸው እምነት እየመነመነ መሄድ ሲጀምር ነው፡፡

እራቱ የፖለቲካ ቡድኖች እንዲቀናጁ ለማድረግ የቀረበውን ሀሳብ ለመቀበል በሁሉም ዘንድ ችግር አልነበረም፤ ችግር መከሰት የጀመረው የሹመት ድልድል ሲመጣ ነበረ፤ በድርጅት ደረጃ እየተያዩና እየተጠባበቁ የሚፎካከሩት መኢአድና ኢዴአፓ ነበሩ፤ በግለሰብ ደረጃ ደግሞ ኤንጂኒር ኃይሉ ሻውልና አቶ ልደቱ አያሌው ገና ከመጀመሪያው የሚጠባበቁ ነበሩ፤ በመጀመሪያው ላይ በብርሃኑና በልደቱ መሀከል ደህና መግባባት ያለ ይመስል ነበር፤ በኋላ ግን በብርሃኑና በልደቱ መሀከል ቅራኔ እየሰፋ መጣ፤ እነዚህን ሦስት የቅንጅት ምሰሶዎች የሆኑ ግለሰቦች በአእምሮችሁ ያዙአቸው፡፡

የቅንጅትን መዋቅር ለማጠናቀቅ ሹማምንቱን መምረጥ ሲጀመር ማን ፕሬዚደንት ይሁን ከባድ ጥያቄ ሆነ፤ ኢንጂነር ኃይሉ ሻውልና ዶር. ብርሃኑ ነጋ ተጠቆሙ፤ ብርሃኑ አልፈለገምና ለኃይሉ ይሙዋገት ነበረ፤ (በመጨረሻ ቅንጅት

---

[3] ገብረ ክርስቶስ ኃይለ ሥላሴ፣ ***ቅንጅት ከየት ወዴት*** 2000 ዓ.ም.፤ አ.አ. ገ.66-67.



ሲከፋፈል የሆነውን ያስተዋለ ቅንጅት በአጭር ዕድሜው ውስጥ የሄደበትን ጠመዝማዛና ተለዋዋጭ መንገድ ለመገንዘብ አያዳግተውም፤) ልደቱ በበኩሉ ለብርሃኑ ይሙዋገት ነበር፤ ልደቱ የራሱን የፖለቲካ ልምድና ዘዴኛነቱን ከሁሉም ሰው አብልጦ በማቅረብ ብርሃኑን እንዲቀበሉለት ጠንካራ ሙከራ ሲያደርግ ከባድ ግጭት ተከሰተ፤ ልደቱ ሽፋፍኖ ቢያቀርበውም አስተሳሰቡ በጎሣ ላይ የተመሠረተ መሆኑ ለሁላችንም አልተሰወረም፤ ልደቱ የፖለቲካ ብልጠት ወይም ስልት አስመስሎ ያቀረበው በኃይሉና በብርሃኑ መሀከል ያለውን የትውልድ ልዩነት በመሆኑ ብዙዎቻችን፣ ብርሃኑም ጭምር በጣም ተቃወምነው፤ ሆኖም ለተለዋወጥናቸው የሻከሩ ቃላት እኔ በበኩሌ ከመቀመጫዬ ተነሥቼ ልደቱን ይቅርታ ጠይቄያለሁ፤ ይቅርታ በመባባል ታለፈና የኃይሉ ፕሬዚደንትነት ጸደቀ፡፡

ቅንጅት ሲመሠረት የታሰበው የቀድሞዎቹ የፖለቲካ ቡድኖች ሞተው ፍጹም አዲስ በሆነ ቡድን ይተካሉ የሚል ነበር፤ ነገር ግን የአራቱ የፖሊቲካ ቡድኖች ታሪክና አመሠራረት በተዋኅዶ ለመሥራት የሚያስችል አልሆነም፤ ኢዴሊና ቀስተ ደመና የታወቀ ታሪክ አልነበራቸውም፤ አዲሶችና በፖሊቲካ ንቃታቸው ባበሰሉ ሰዎች የሚመሩ ነበሩ፤ መኢአድና ኢዴአፓ ታሪክ ያላቸው ቢሆኑም ልጓሙን ከጨበጡት መሪዎች ውስጥ ብዙዎቹ በዕድሜ እንጂ በትምህርት ከቀስተ ደመናና ከኢዴሊ ጋር የሚወዳደሩ አልነበሩም፤ ምናልባትም በዚህ ምክንያትም ከቀድሞ ቡድናቸው ለመላቀቅ አስቸጋሪ የሆነባቸው ሰዎች ነበሩ፤ በቀድሞው ቡድን ውስጥ ጎላ ያለ ሥልጣን የነበራቸው የመኢአድና የኢዴአፓ ሰዎች በቅንጅት ውስጥ ካሉት ጋር ለመወዳደር አቀበትና ተሰፋ የሚያስቆርጥ መስሎ እንደታያቸው መገመት ይቻላል፤

ሌሎች ይህ ስሜት አልነበራቸውም ባይባልም በተለይ በመኢአድና በኢዴአፓ መድኅን መሪዎች መሀከል የባሰ ነበር፤ በተጨማሪም በመኢአድና በኢዴአፓ የተለመደው አሠራር ዋናዎቹ መሪዎችን እንደብቸኛ ወሳኝ የሚያደርግ ስለነበረ ይህ ልምድ በቅንጅት ውስጥ የማይሠራ መሆኑ ሥልጣናቸውን ያሳነሰባቸው መስሎ እንደታያቸው መገመት ይቻላል፤ በሁለቱም በኩል የችሎታ ምትክ ሆኖ የሚቀርበው መስዋዕትነት ከፍለን፣ ተገድለን፣ ታስረን፣ ተደብድበን የሚል መከራከሪያ ነበር፤ ሁለቱም የሞቱትንና የተጎዱትን ሰዎች በመጋለብ የየራሳቸውን ጥቅም ለማስፋት ይሞክሩ ነበር፤ ሁለቱም የሞት ዋጋ ወይም ካሣ ይከፈለን የሚሉ ነበሩ፤ በድርጅቶች ፉክክር በኩል ሲታይ ገና ቅንጅት ሲጠነሰስ የነበረው ችግር ይህን ይመስል ነበር፡፡

አብዛኛዎቹ የመኢአድና የኢዴአፓ መሪዎች በትንንሾቹ ድርጅቶች የነበራቸው ሥልጣንና ክብር በአዲሱ ትልቅ ድርጅት ውስጥ ተበርዞ ያነሰ መስሎ ታያቸው፤ በትንንሾቹ ውስጥ ትልቅ ከመሆን በትልቅ ውስጥ ትንሽ መሆን መሻሉን አውቀው የሚመርጡ ከራሳቸው ውጭና ከራሳቸው በላይ ሌላ

ዓላማ መኖሩንና የማኅበረሰብ እድገትም በአንድ ሰው ቁመትና ወርድ ብቻ የማይለካ መሆኑን የተገነዘቡ ሲሆኑ ነው፤ መለኪያው ራስ ብቻ ሲሆን ከራስ በላይ ነፋስ በሚሉት አስተሳሰብ መነጣጠልና አጉል ፉክክር ይነግሣሉ፤ ይህንንን ተንተርሶ ደግሞ የግል የሥልጣን ጥም ያቆጠቁጣል፤ ላስተዋለው ገና ከመጀመሪያው በቅንጅት ውስጥ ይታይ የነበረው ችግር ይኸው ነበር።

አንድ ኮሚቴ ይቋቋም ሲባል አባሎቹን ለመምረጥ የሚቀርበው መመዘኛ ለመጣበት የቀድሞ ፓርቲ ውክልና እንጂ ችሎታ ወይም ለተፈለገው ሥራ ያለው ብቃት አልነበረም፤ ለምሳሌ የውጭ ግንኙነት ኃላፊ ለመሆን በአማርኛና በእንግሊዝኛ ንግግርም ሆነ ጽሑፍ የተካነ ሰው መሆን ያስፈልገዋል፤ በተጨማሪም የቅንጅትን አቅዋም ከራሱ እምነት ለይቶ የማየት ችሎታ ይጠበቅበታል፤ በተሰጣቸው የኃላፊነት ክልል ውስጥ ታጥረው መሥራት የሚያስቸግራቸው የቅንጅት አመራር አባሎች እንደነበሩ የታወቀ ነው፤ በአደባባይ ንግግር ሲያደርጉም ሆነ ለጋዜጦች መግለጫ ሲሰጡ፣ ወይም በየኤምባሲው ከዲፕሎማቶች ጋር ሲነጋገሩ ራሳቸውን ለመካብ ባላቸው ጉጉት የቅንጅትን አቅዋም የሚያደፈርሱ ነበሩ፤ ሁሉም በየፊናው አድራጊ ፈጣሪ መስሎ ለመታየት ባለው ምኞት ሲንቀሳቀስ በግድ ግጭት ይፈጠራል፤ በኋላ በቅንጅት ውስጥ የተከሰተው መከፋፈል (ከልደቱ ጀምሮ) ቀድሞ የተፈጠረውን ስንጥቅ የሚያመለክት ነው፤ ልደቱ ከቅንጅት ሲወጣ ሰው ሁሉ ዓይንህ ላፈር ስላለው የተናገረውን ያዳመጠው ያለ አይመስለኝም፤ በግል ዝናና በበላይነት ምኞት ተገፍቶ ቅንጅትን አቁስሎ ከመውጣት ይልቅ ውስጥ ሆኖ መታገል ነበረበት ተብሎ ይወቀስ እንደሆን እንጂ ምክንያቶች አልነበሩትም ለማለት አይቻልም።



# ፩
# የቅንጅት ዓላማ

## 1. የቅንጅት ባሕርይ

ቅንጅት የኢትዮጵያ ሕዝብ አበሳ፣ ግፍ ጭቆና አስከነፍሳቸው ጠልቆ የሚሰማቸው ሰዎች በጭንቀት አምጠው የወለዱት ድርጅት ነው፤ የምጡ ጭንቀት ያስለቀሳቸው ሰዎች አሉ፤ የምጡ ጭንቀት ከአለፈና እንባውም ከደረቀ በኋላ የመፈንደቅ ስሜት፣ የተስፋ ሙቀትና የዓላማ ጥንካሬ በግልጽ መታየት ጀመረ፤ የዓላማው ግልጽነት የኢትዮጵያን ሕዝብ ቀልብ ሳበ።

ዓላማው ምን ነበር? የኢትዮጵያ ሕዝብ የአገሩ ባለቤትና የመንግሥት የሥልጣን ባለቤት እንዲሆን ለማድረግ ነበር፤ ማንም ኢትዮጵያዊ በዕድሜ፣ በጾታ፣ በጎሣ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖትም ሆነ በማናቸውም ልዩነት ምክንያት ከፍና ዝቅ ሳይል እኩልነቱንና ነጻነቱን ጠብቆ በልበ ሙሉነት የአገሩ ባለቤትና ባለሥልጣን መሆኑን ተገንዝቦና አምኖ በ97 ዓ.ም. ምርጫ ነቅቶ እንዲሳተፍ ለማድረግ ነበር፤ ይህ ዓላማ አጠቃላይ ነው፤ ሁሉንም የሚያቅፍ ነው፤ ማንም ነጻነትን ተቃውሞ የሚቆም የለም፤ ማንም እኩልነትን ተቃውሞ የሚቆም የለም፤ ማንም ፍትሕን ተቃውሞ የሚቆም የለም፤ ማንም የእያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ ችሎታ በማዳበር አብሮ መበልጸግን የሚቃወም የለም።

የቅንጅትን ዓላማ የሚቃወሙ ነጻነትን፣ እኩልነትን፣ ፍትሕንና አብሮ መበልጸግን አይቃወሙም፤ የሚሉት ለሕዝቡ የሚበጀውን ነጻነት፣ እኩልነትና ፍትሕ፣ አብሮ ለመበልጸግ የሚሻለውን መንገድ የምናውቀው እኛ ብቻ ነን፤ ለሕዝቡ የሚጠቅመውን የምናውቀው እኛ ነን፤ የሕዝብ ሥልጣን ማለት እኛ የምንነግረውን መፈጸም ነው፤ በሌላ አነጋገር የሚሉት የሕዝቡ ሞግዚት እኛ ነን፤ ስለዚህም የሕዝቡን ሥልጣን በግድ ተረክበን በፈለግነው መንገድ ሕግ እያወጣን፣ ሲያስፈልግም እየሻርን እናስተዳድረዋለን ነው።

የቅንጅት መንፈስ ፊት ለፊት የተጋፈጠው ከዚህ «እኛ እናውቅልሃለን» የሞግዚትነት የአገዛዝ ሥርዓት ጋር ነው፤ የቅንጅት መንፈስ የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ/ኢትዮጵያዊትም ማለት ነው፤ የነጻነት አዋጅ ነው፤ የቅንጅት መንፈስ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በሕግ ሊኖራቸው የሚገባቸውን እኩልነት የሚያበስር አዋጅ ነው፤ የቅንጅት መንፈስ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ/ት/ በነጻነትና በእኩልነት የአገር ባለቤት ሆኖ በልበ ሙሉነት ኑሮውን የሚያሻሽልበትን መንገድ ለመቀየስ የሚያስችለው አዋጅ ነው፤ በአጭሩ የቅንጅት መንፈስ የእልፍ ዓመታትን የአገዛዝ ሽክም ጥሎ ሁሉም በሕግ የሚተዳደርበትን ሥርዓት የሚመሠርት

አዋጅ ነው፤ የሙሴ ቡራኬ፣ የክርስቶስ ረድኤት፣ የመሐመድ ምርቃት ያደረበት መንፈስ ነው፤ የቅንጅት መንፈስ።

ይህንን የአለፋ ዓመታት የጭቆና ሸክም የነቀነቀ መንፈስ በቅንጅት መሪዎች ሁሉ እኩል ግንዛቤን አላገኘም ነበር፤ ለአንዳንዶቹ መንፈስ የሚለው ቃል ተጨባጭ ትርጉም የሌለው ከተረት ያልተሻለ መስሎ ታያቸው፤ ይህንን ለማስረዳት የጻፉም ነበሩ፤ መንፈስ በሚባል ነገር እምኔታ አልነበራቸውም፤ ሁለት ተጨባጭ ማስረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል፤ አንዳንዶቻችን በቅንጅት መንፈስ የምናምነው በምርጫው ማሸነፍ እንደሚቻል ስንናገር አምኔታው የሌላቸው ከሃያ በመቶ የበለጠ አናገኝም ይሉ ነበር፤ ሁለተኛ የሚያዝያ 30 ቀን 1997 ዓ/ም ሕዝባዊ ስብሰባ በወያኔ ከተጠራው የሚያዝያ 29 ስብሰባ በጣም ያንሳል ብለው የሰጉ ነበሩ፤ ብርሃኑ ነጋ አስቀድሞ ወደደቡብ ሄዶ ስለነበረ የሚያዝያ ሠላሳን ሙሉ ተአምር አላየም፤ ልደቱ እያሴው ዘግይቶ በመምጣቱ ከሌሎቹ ተለይቶ ለብቻው እንደሰርገኛ በመኪና ላይ ሆኖ ገባ! በዚያን ዕለት በመስቀል አደባባይ በመኪና ለመንቀሳቀስ ፍላጎቱ ከየት መነጨ? የብርሃኑ አለመኖር፣ የልደቱ ለብቻው በመኪና ላይ ሆኖ እጆቹን ማውለብለብ፣ ሌሎቹ በኃይሉ ሻውል ዙሪያ መሰባሰብ የቀንጅትን የወደፊት አካሄድ አመልካቾች ነበሩ።

ሚያዝያ 30 የኢትዮጵያ ሕዝብ በታሪኩ ለመጀመሪያ ጊዜ በሙሉ ነጻነትና በሙሉ ልብ በራሱ ፈቃድ በነቂስ በአደባባይ በመውጣት ለነጻነትና ለለውጥ ያደረበትን ናፍቆት በገሀድ ለዓለም አሳየ፤ ከላይ እንደገለጽሁት ዛሬ ከተገነጠሉት ውስጥ በዚህ የረጋ የሕዝብ ውቅያኖስ መሀከል የነበረው ኤንጂነር ኃይሉ ብቻ ነበር፤ ልደቱ በኋላ በመኪና ተጭኖ ወደዳር ዘለቀ፤ ዶክተር ብርሃኑ እንዲያውም አልነበረም፤ ይህንን  ሰላማዊ የሕዝብ ውቅያኖስ ያላየ፣ ይህንን የኢትዮጵያ ሕዝብ ጨዋነት ያልተገነዘበ፣ ይህንን የኢትዮጵያን ሕዝብ ሕግና ሥርዓት አክባሪነት ያላስተዋለ፣ ይህንን የኢትዮጵያ ሕዝብ ለነጻነት ያለውን ናፍቆት ያልተረዳ ከራሱ በላይ ለሆነ የሕዝብ የፖለቲካ ትግል ቃል ኪዳን ለመግባት ያዳግተዋል።

የቅንጅትን ዓላማ በትክክል አለመገንዘብ ለግል የሥልጣን ምኞት በርን ከፍቶአል፤ የቅንጅት ዓላማ የኢትዮጵያን ሕዝብ የአገሩና በአገሩ ላይ የሥልጣን ባለቤት ለማድረግ ነው ስንል ምን ማለታችን ነው? በተደላደለ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ በሚደረግ ትክክለኛ ምርጫ የድምፅ ብልጫ ያገኘው የፖሊቲካ ቡድን የመንግሥት ሥልጣንን ተረክቦ አገሩን እንዲያስተዳድር ይደረጋል፤ እንደኛ አገር የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ገና ባልተዘረጋበትና ሕዝቡም በሕግ የተሰጠውን የሥልጣን ባለቤትነት ገና በወጉ ባልተረዳበት ሁኔታ በትክክለኛ የዴሞክራሲያዊ ምርጫ የሚገኝ ሥልጣን ለአሸናፊው የፖሊቲካ ቡድን



የሚተላለፍና ለግለሰቦች የሚከፋፈል ከመሆኑ በፊት የሕዝቡን ሥልጣን በውክልና የተቀበለው ሕግ አውጪው ክፍል በጣም ተጠናክሮና የበላይነትን ጨብጦ ሕዝቡ የሥልጣን ባለቤት መሆኑን የሚያስገነዝቡትና የሚያስጨብጡት ሥራዎችን መሥራት ይጠበቅበታል የሚል ነበር።

እያንዳንዱ ዜጋ ያሉትን ሕጋዊ መብቶች በሙሉ አውቆና ተረድቶ የራሱ በመሆናቸው ላለማስደፈርና ላለማስነጠቅ ነቅቶ እንዲጠብቅ ማመቻቸት አስፈላጊ ይሆናል፤ ሕዝቡ የሥልጣን ባለቤትነቱን ነቅቶና ተደራጅቶ ለመጠበቅ በማይችልበት ሁኔታ የሕዝቡን ውክልና በምርጫ የሚይዙ የፖለቲካ ቡድኖች በግለሰቦች የሥልጣን ጥም እየተማረኩ ወደ አምባ ገነንነት ሲያመሩ ተደጋግሞ ታይቶአል፤ ለዚህ ነው በማናቸውም የፖሊቲካ ቡድን ውስጥ በሕዝቡ ላይ ጋልበው ወደ አምባገነንነት ለመሸጋገር የሚያኮበኩቡትን የሥልጣን ጥመኞች መጠባበቅና መቆጣጠር ዋና የመጀመሪያ ደረጃ ተግባር መሆን የሚያስፈልገው፤ ሕዝቡ የሥልጣን ባለቤትነቱን ካወቀና ካረጋገጠ፣ በኅብረት ተነሥቶ በትግሉ መብቱን ለማስከበር ከቆረጠና በልበ-ሙሉነትና በነጻነት የመሰብሰብ፣ የመደራጀትና ሀሳቡን የመግለጽ ብቃቱን ከአረጋገጠ በኋላ ሥልጣንን የመቆጣጠር ቻሎታው ሲዳብር የሥልጣን ጥመኞች እንደልባቸው ሊፎካከሩ ይችላሉ።

የሥልጣን ጥመኞች የምላቸውን ሥልጣንን ለሕዝብ አገልግሎት ከሚጠቀሙበት ሰዎች ለይተን ማየት ያስፈልጋል፤ ለሥልጣን ጥመኞች ሥልጣን የራሳቸውን የግል ጥቅምና ክብር፣ ዝናም ማዳበሪያ ነው፤ የሥልጣን ጥመኞች ሥልጣን የሕዝቡ ሀብት መሆኑን እየዘነጉ የራሳቸው የግል ሀብትና የሀብት ሁሉ ምንጭ አድርገው ይጠቀሙበታል፤ ሥልጣንን ለሕዝብ አገልግሎት የሚያውሉ ሰዎች ግን የሥልጣን ባለአደራነታቸው በጥልቅ የሚሰማቸውና የሕዝቡን ጥቅም ዋና ዓላማቸው ያደረጉ ናቸው፤ የሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነት የሚረጋገጠው በመጀመሪያው ላይ ለሕዝብ ባለአደራነታቸው በጥልቅ የተሰማቸው ሰዎች በቃል ኪዳን ከሕዝቡ ጋር ሲተሳሰሩ ነው።

ምርጫ የተለያዩ የፖለቲካ ቡድኖች ተፎካክረው አሸናፊው የመንግሥትን ሥልጣን የሚይዝበት መንገድ ወይም ዘዴ ብቻ አይደለም፤ ትክክለኛው አገላለጽ አሸናፊው የፖሊቲካ ቡድን በሕዝብ ስም ለተወሰነ ጊዜ በአደራ ሥልጣን የሚረከብበት ነው ማለቱ ነው፤ የፖሊቲካ ቡድኖቹ የሕዝብ ሥልጣንን በአደራ የሚረከቡ መሆናቸው በጥልቅ ሳይገባቸው፣ ሕዝቡም የሥልጣን ባለቤት ራሱ እንደሆነ በሚገባ ሳይገነዘብ ምርጫ ሲደረግ በአፍሪካ አገሮች በተደጋጋሚ እንደምናየው የሕዝብ ድምፅ ሳይሆን ጠመንጃ የያዘው በወንበሩ ላይ ይወጣል፤ ይህ የአፍሪካ ሁኔታ የሚያሳየው ጠመንጃ የያዘው ክፍል ገና ጠመንጃ የያዘበትንም ምክንያት እንዳላወቀና በዜግነት ተግባርና በሎሌነት መሀከል ያለውን ልዩነት እንዳልተገነዘበ በግልጽ የሚያሳይ ነው።

በቅርቡ በታይላንድ ከተመረጠ ገና አንድ ዓመት ያልሞላውን ጠቅላይ ሚኒስትር ከሥልጣኑ እንዲወርድ ሕዝቡ አደባባይ ወጥቶ ጠየቀ፤ ጥያቄው ሕጋዊ ስላልሆነ አልወርድም አለ፤ ሕዝቡም ካልወረድህ ቢሮህ አትገባም ብሎ ግቢውን ወረረበት፤ ከሁለት ሳምንት በላይ ከቢሮው የተለየው ጠቅላይ ሚኒስትር ጊዜያዊ አዋጅ አወጣ፤ የጦር ሠራዊቱ የሚጣሉ ሰዎችን ከመገላገል ውጭ ሰላማዊ ሰልፉን አንበትንም፤ ሥራችን አይደለም አለ፤ ፍጥጫው ተባባሰና ኢኮኖሚውን በጣም የሚጎዳ ሲሆን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወንበሩን ለቀቀና ሌላ ተሰየመ፤ የሥልጣን ባለቤትነቱን የሚያውቅ ሕዝብና የአንድ ቡድን ሎሌ ሳይሆን የአገር አገልጋይ መሆኑን የተገነዘበ የጦር ሠራዊት ባለበት ሕዝብ በልበ-ሙሉነት መብቱን ለማስከበር ይደፍራል፡፡ ሚያዝያ  ሠላሳ በአሥራ ስምንት ዓመታት የማታለልና የባዶ ተስፋ ውርጅብኝ ውስጥ ማንም ያላሰበውና ማንም ያልጠበቀው ጥሩ ፍሬ በቀለ! ቅንጅት የተለፈፈውን እንከን የሌለበት የሚል ውሸት አመነና ተቀበለ፤ ይህንን ውሸት ሕዝቡም እንዲያምን አደረገ፤ «ይታያል ጉዱ!» ብሎ በሙሉ ልብ ተነሣ፤ ውሸቱን በቅን መንፈስ እንደእውነት ተቀበለው፤ ሚያዝያ 30 የዚህ በቅን መንፈስ የመታለል ብሥራት ነው፤ ለሰላም፣ ለፍትሕ፣ ለነጻነት፣ ለሥልጣን ባለቤትነትና ለአገር ኩራት የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለውን ጽኑ እምነት የወያኔን የማታለል ልማድ ፊት-ለፊት በገሀድ የገጠመበት ነው፤ ስለዚህም የወያኔን አታላይነት እርቃኑን ያወጣበት ታሪካዊ ቀን ነው፡፡

ቀደም ብሎ ቅንጅት ለሚያዝያ 30 ሕዝባዊ ስብሰባ በመስቀል አደባባይ እንደሚደረግ አሳውቆ ነበር፤ ስለዚህም ሚያዝያ 29 ቀን 1997 ወያኔ/ኢሕአዴግ በመስቀል አደባባይ ሕዝባዊ ስብሰባ ጠራ፤ በሺህ የሚቆጠሩ የንብ ምልክት ያለባቸው ሹራቦችና ቆቦች ተሰፍተው ለሕዝብ በገፍ ታደሉ፤ ጥሬ ገንዘብም ታድሏል ተብሎ ተወራ፤ የመንግሥት መኪናዎችና አውቶቡሶች በፈቃደኝነትም ይሁን በመደለል ወይም በግዴታ ወደ መስቀል አደባባይ የሚሄደውን ሕዝብ ያመላልሱ ጀመር፤ በአውቶቡሶች ወደመስቀል አደባባይ ከሚጓዙት ውስጥ አብዛኞዎቹ የወያኔ/ኢሕአዴግን ሹራብ ለብሰው የቅንጅትን ምልክት ያሳዩ ነበር፤ለማናቸውም የመስቀል አደባባይ በሕዝብ ሞላ፤ አቶ መለስ ዜናዊም በአሥራ አምስት ዓመታት ውስጥ  ምናልባትም ለሦስተኛ ጊዜ በዚያ አደባባይ ተገኝቶ ንግግር አደረገ፤ በጣም ደስ ብሎት ስለነበረ «ሕዝባዊ ማዕበል» የሚል ስያሜ ሰጠው፤ የአብዛኛውን ሕዝብ ልባዊ ድጋፍ እንዳገኘ ማረጋገጫ መስሎ ታየው፤ በገንዘብ የተደለለንና በጉልበት የተገደደን ሕዝብ ስሜት ለማወቅ ረቀቅ ያለ አስተሳሰብን ይጠይቃል፤ ስለዚህም  በግርድፉ ብዛትን ብቻ መመዘኛ



በማድረግ ሚያዝያ 29 አስጨፈረ፡፡•

በነጋታው በሚያዝያ 30 የቅንጅት ሕዝባዊ ስብሰባ በዚያው በመስቀል አደባባይ ከሰዓት በኋላ በስምንት ሰዓት ተጠርቶ ነበር፤ በአምስት ሰዓት ግድም አደባባዩ ብቻ ሳይሆን ከየአቅጣጫው የሚመጡት መንገዶች ሞሉ፤ ከአካባቢው ከተሞች አውቶቡስና መኪና እየተከራዩ መጥተው አዲስ አበባን አጥለቀለቋት፤ አቶ መለስ ቸኩሎ ሕዝባዊ ማዕበል ካለው ከአራት አምስት ጊዜ እጥፍ የሆነ የሕዝብ ቁጥር ነበር፤ ወጣት፣ ሽማግሌ፣ ወንድ፣ ሴት ሳይባል የአዲስ አበባና የአካባቢው ሕዝብ ቤቱን ዘግቶ በነቂስ የወጣ ይመስል ነበር፤ በአዲስ አበባ ዙሪያ ከሚገኙ ከተሞች በአውቶቡስና በሚኒባሶች የሚመጡ ብዙ ሰዎች መንገዶቹ ሁሉ ተዘግተው ስለነበረ አልደረሱም፤ የሚያዝያ ሠላሳው ሕዝባዊ ስብሰባ ዋናው አስደናቂነቱ የሕዝብ ብዛት ብቻ አልነበረም፤ ሰላማዊነቱና ጨዋነቱም የሚያኮራ ነበር፤ በዚህ ረገድ በየትም ቢሆን ታይቶ የማይታወቅ ነበር፤ በሚልዮን የሚቆጠር ሕዝብ ወጥቶ አንድ ቅጠል ሳይበጠስና ምንም ዓይነት ረብሻ ሳይነሣ በሰላምና በፍቅር መበተኑ የማይረሳ ኢትዮጵያዊ ታሪክ ነው፤ ይህ እንዲሆን ቅንጅት ያደረገው ዝግጅትና አስተዋጽኦ ከባድ ነበር፤ በፖሊሶች በኩል የታየው ሥርዓትም በጣም አስደናቂ ነበር፤ ፖሊሶችም እንደ ቅንጅት ሳይታለሉ አልቀሩም ይመስለኛል፤ ሆኖም ልክ እንደሕዝቡ ፖሊሶችም ያሳዩት ጨዋነት የሚያኮራ ነበር፡፡

ሚያዝያ 30/97 የመታለል ውጤት ከሆነ ላታለለውም ለታለሉትም ትልቅ ትምህርትን ትቷል፤ ቅንጅት ለሰላም የቆመ ድርጅት መሆኑን አረጋግጧል፤ ሚያዝያ 30 ቀን 1997 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ መጀመሪያውና ወደር የማይገኝለት የሰላማዊ ትግል መግለጫ ሆኖ እንደሚቆይ አያጠራጥርም፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ገና ነው፤ አያውቅም፤ እያሉ የሚንቁትን ሁሉ በተጨባጭ ያሳፈረበት ቀን ነው፤ ሕጋዊነትንም፣ ጨዋነትንም፣ መብቱንና ግዴታውን ማወቁን በተግባር አሳየ፤ የሚጠቅመውንና የማይጠቅመውን መለየት እንደሚችል በተግባር ገለጠ፤ ወያኔ/ኢሕአዴግ በኋላ ቅንጅትን ጸረ-ሰላምና የጎዳና ነውጥ ቀስቃሽ ለማስመሰል ያደረገውን ጥረት የሚያዝያ ሠላሳው እውነት ገሀድ ማስተባበያ ይሆንበታል፡፡

በኋላ ባይበላሽ  ይህ ሕዝባዊ ስብሰባ ወያኔ/ኢሕአዴግንም ሊያስመሰግንና ታሪኩን ሊያደምቅለት የሚችል ነበር፤ በሚልዮን የሚቆጠር ሕዝብ በአካል ተጣብቆ ቆሞ ምንም ዓይነት የስሜት መሻከርና ጠብ ሳይፈጠር

• በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን አንድ ለቅሶ ቤት ሁለት ሽማግሌዎች ሲጫወቱ የሰማሁትን ልንገራችሁ፤ አንደኛው የብሥራተ ወንጌል ራድዮ ጣቢያን አንስተው የወሬውን አቀራረብ፣ ትንተናውን፣ አማርኛውን እያወደሱ ተናገሩና «የኢትዮጵያ ራድዮ ለምን እንደዚያ አልሆነም?» ብለው በመደነቅ ሲጠይቁ ጓደኛቸው «አይ ያንተ ነገር! አምነውበት የሚናገሩትና በል ተብለው የሚናገሩት እንዴት እኩል ይሆናል?» አሏቸው፡፡

በመተባበርና በመደጋገፍ በአንድ በጎ መንፈስ በአንድ ላይ ተጠምዶ በራስ መተማመንን፣ ፍቅርንና ተስፋን ሰንቆ አዲስ የነጻነት ኢትዮጵያን ለመገንባት ያስብ ነበር፤ ይህ ዘላቂ ቢሆን ክብርና ምስጋናው ለወያኔ/ኢሕአዴግ ነበር፤ የወያኔ/ኢሕአዴግ የታሪክ ግንዛቤና የታሪክ ሚዛን ማጣት ወያኔ/ኢሕአዴግን ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያ ሕዝብንም አደኸየ፤ በምድረ ኢትዮጵያ ሕዝብ የወሳኝነት ሥልጣን አግኝቶ ራሱ የመረጠውን መንግሥት በመንበር ላይ ለማውጣት የሚችልበትን ሁኔታዎች ሁሉ ፈጠረና መጨረሻውን ለመቀበል ሲደርስ ወኔው ከዳው፤ የኢትዮጵያ ታሪክ ሳይለወጥ ቀረ፤ በዚህም ምክንያት ወያኔ/ኢሕአዴግ የኢትዮጵያ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ደራሲ የመሆን ዕድል አመለጠው፤ የደርግ የባሕርይ ልጅ ሆኖ ታየ።

ሚያዝያ 30 የሚያስደነግጥ እንደነበረም መካድ አይቻልም፤ በተለይ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ እምነት ለሌለውና ለፍርሃት የተጋለጠ ባሕርይ ላለው፣ ጸጥ ያለውንና የረጋውን ባሕር እንደማእበል ለሚመለከተው አስፈሪ ነበር፤ አስፈሪነቱ ግን ከሕዝቡ ሳይሆን ከፈሪው ልብ የሚመነጭ ነበር፤ ለወያኔ/ኢሕአዴግ ሚያዝያ 30 የፍርሃትና የመርበድበድ፣ የመደናበርና የመደናገጥ መነሻ ሆነባቸው፤ የአዲስ አበባ ሕዝብ ከሱም ጋር መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ወያኔ/ኢሕአዴግን በሰላማዊ መንገድ ከሥልጣን ለማውረድ ቁርጠኛ ውሳኔ ማድረጉን በማያወላውል መንገድ ለወያኔ/ኢሕአዴግ በገሀድ አሳወቀ፤ ወያኔ/ኢሕአዴግም በበኩሉ ያደረበት ድንጋጤ ድሮውንም ያልነበረውን የማሰብ ችሎታ አጠፋበት፤ ስለዚህም «እንከን የለሽ ምርጫ» በማለት የገባውን ቃል ተከትሎ የተጀመረውን ሕጋዊና ሰላማዊ መንገድ በአንድ ጊዜ ቀልብሶ ወደ ሕገ አራዊት የጉልበት እርምጃ የመሸጋገር ምልክቶች ታዩበት፤ በየገጠሩ የቅንጅት አባሎችን ማዋከብ ማሰርና ማጉላላት፣ አልፎ አልፎም መግደል ዋና የወያኔ/ኢሕአዴግ ሎሌዎች ተግባር ሆነ፤ የቅንጅትን የጣት ምልክት ማሳየት እንደከፉ ወረርሽኝ ይታይ ጀመር፤ ጣቱን የተቆረጠም ነበር ሲባል ሰምቻለሁ።

በእውነት ከሆነ ለምን የወያኔ መሪዎች ደነገጡ ብሎ የሚገረም ሰው አይኖርም፤ በምርጫው ዘመቻ ጊዜ፣ በክርክሩ ጊዜ ብዙ ሊያስደነብሩዋቸው የሚችሉ ነገሮች ተብለዋል፤ እንትን ያለበት ዝላይ አይችልም እንደሚባለው ቀላሉን ሁሉ እያከረሩ በመተርጎም ራሳቸውን በፍርሃት አናወጡትና ለመሪነት ብቃት እንደሌላቸው ለዓለም አሳዩ።

ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ብቻ ሳይሆን ለጥቁር ሕዝብ በሙሉ የነጻነት ጮራ እንደነበረች ሁሉ የዴሞክራሲን ጮራ ለማስተጋባት የነበራትን ዕድል ወያኔ መካብ ጀምሮ ወያኔ ናደው፤ ዓለም በሙሉ በዚህ እንዲያውቀው መረጠ፤ ቅንጅትም፣ ወያኔም በሚያዝያ 30 ለታሪክ በቁ።



# ፮
# ምርጫ 97

## ፩. ለምርጫ ዝግጅትና ምዝገባ

ኢትዮጵያ ሕዝብ ለምርጫው እንዲመዘገብና ለመምረጥ እንዲዘጋጅ የብዙ ግለሰቦችና ድርጅቶች ያልተቋጠባና ያላቋረጠ አስተዋጽኦ ነበረበት፤ ከድርጅቶች ኢሰመጉና በአቶ ክቡር ገና የሚመራው የመንግሥት ያልሆነ ድርጅትና ሌሎችም፣ ብዙ የግል ጋዜጦችና ግለሰቦች በጣም የተጠናከረ ጥረት አድርገዋል፤ ያለጥረጥርም ተሳክቶላቸዋል፤ በተለይ የማይረሳው የክቡር ገና ለአባማም የምርጫ ዘመቻ የደረሰ «ይቻላል» የሚል መፈክር ነው፤ ብዙ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በብዙ ቦታዎች ንግግርና ውይይት ከማዘጋጀት በተጨማሪ በግል ጋዜጣዎች ላይ የተለያዩ ማስታወቂያዎችን እያወጡ ሕዝብ እንዲመዘገብ ይወተውቱ ነበር።

እንደተለመደው ብዙ ሰዎች ስለምርጫው ከባድ ጥርጣሬ ነበራቸው፤ ወያኔ/ኢሕአዴግ ተቆጣጥሮ በሚመራው ምርጫ ቦርድ የሚካሄድ ምርጫ ትክክለኛና ፍትሐዊ ይሆናል ብሎ መገመት ከንቱ ምኞት ነው የሚሉ ሰዎች ነበሩ፤ በነዚህ ሰዎች አመለካከት አሸናፊው በቅድሚያ በታወቀበትና ሕዝቡም በተለያዩ መረቦች ተሰንጎ በፍርሃት ቆፈን ተዳክሞ በሚገኝበት አገር በምርጫ ለመሳተፍ መሞከር ለምንም የማይጠቅምና ጊዜን ለማጥፋት ብቻ የሚደረግ አጉል ተግባር ነው በማለት ጠንክረው በተደጋጋሚ በግል ጋዜጣ ላይ የሚጽፉ ነበሩ፤ እንዲያውም የወያኔን አስመሳይ ዴሞክራሲያዊነት ለማጠናከር የሚበጅ በመሆኑ ጉዳትን ያስከትላል የሚሉ አመለካከቶች ነበሩ፤ ስለዚህም በምርጫው መሳተፍን የሚያጥላሉና የሚነቅፉ የተደራጁና ድምፃቸውን አጥብቀው የሚያስሰሙ ነበሩ ለማለት ይቻላል።

በአንጻሩ ደግሞ በምርጫው መሳተፍ ጠቃሚና አስፈላጊ መሆኑን አምነው በጥብቅ የሚከራከሩ ነበሩ፤ ወያኔ/ኢሕአዴግ ለሰላማዊ የፖለቲካ ትግል በሩን ከፈት አድርጎታል፤ በዚህ በተከፈተው በር አልፎ ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ማካሄድ ለትግሉ መዘጋጀትን ይጠይቃል፤ በሕግ በተከፈተው በር እየገቡ ትግሉን ማስፋፋትና ማጠናከር የማንም ተቀናቃኝ የፖለቲካ ቡድን ግዴታ ነው፤ ሕዝቡም በመምረጥ መብቱ ሳይጠቀም ቢቀር የዜግነት ኃላፊነቱን አልተወጣም ማለት ነው፤ ከዚያም በላይ በሚያስከትለው ውጤት ቢከፋና ቢያዝን ከራሱ

በቀር ማንንም ለመውቀስ አይችልም በማለት ክርክሮች በግል ጋዜጣ ላይ ይቀርቡ ነበር፡፡[4]

እጅን አጣጥፎ በመቀመጥና ወያኔ/ኢሕአዴግ ሁሉንም ነገር አመቻችቶና አደላድሎ እስቲሰጥ ድረስ መጠበቅ ትግል አይሆንም፤ ትግሉ ያለው የተዘጋውን በር በማስከፈትና የተከፈተውንም በማስፋቱ ላይ ነው፤ ትግሉ ያለው በአለው ሕጋዊ ቀዳዳዎች ሁሉ እየተጠቀሙ የሕዝቡን አእምሮና ልብ ለመያዝ መጣር ላይ ነው፤ ትግሉ ያለው በገዥው ቡድንና በተቀናቃኝ ቡድኖች መሀከል ያለው የሀሳብ ልዩነት በገሃድ ወጥቶ እንዲጋጭና እንዲፋጭ በማድረግ ሕዝቡ ልዩነቶችን እንዲገነዘብ በማድረጉ ላይ ነው፤ ትግሉ ያለው የትኛው የፖለቲካ ቡድን በሀሳብ ማመንጨትና በአስተሳሰብ ችሎታው በሕዝቡ ላይ የአንድነትን ፍቅር የትክክለኛ አስተዳደር፣ የፍትሕና የተደላደለ ኑሮ ተስፋ፣ በራስና በወገን መተማመን ይበልጥ ያሳድራል በሚለው ውድድር ላይ ነው፤ ትግሉ ያለው በእንደዚህ ያለ ሰላማዊ መንገድ የሕዝቡን መንፈስ ማነሣሣቱ ላይ ነው፤ መሸናነፍ የፖለቲካው ትግል ውጤት በመሆኑ በቅድሚያ ማናቸውም ወገን ሊወስነው አይገባም፡፡

ስለዚህም ነው ሁኔታው ሙሉ በሙሉ የተሟላ ባይሆንም፣ እንዲያውም ወያኔ/ኢሕአዴግም ሆነ የምርጫ ቦርድ፣ ፖሊሶችም ሆኑ ካድሬዎቹ የማይታመኑና ለሕግ የማይገዙ መሆናቸው ቢነገርም ይህንንም ለማረጋገጥ ቢሆን ተቀናቃኝ ቡድኖች በምርጫው ውስጥ መግባት ነበረባቸው፤ ተቀናቃኝ ቡድኖችም የተቀበሉት ይህንን ግዴታ ነበር፤ በተለይ ቅንጅት የማያወላውልና ቁርጥ ሀሳብን ይዞ ለውድድሩ በመሰለፉ ወያኔ/ኢሕአዴግ ይህንን አዲስና ያልታወቀ የፖለቲካ ቡድን በቀላሉ በማሸነፍ አስመሳይ ዴሞክራሲያዊነቱን ለማስመስከር ምቹ አጋጣሚ እንዳገኘ ቆጠረው፤ አቶ መለስም ገና በጠዋቱ ቀኑ አልፎ አይነጋ መስሎት፣ «እንከን የሌለበት ምርጫ እናካሂዳለን» ብሎ ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ የፖለቲካ ወኔ ያለው ይመስል ወያኔአዊ ቃሉን ሰጠ፣፤ ቃልና ተግባርን ሳያጣጥመው አሥራ አምስት ዓመታት ሙሉ መዳዙ የልብ ልብ ስለሰጠው «እንከን የሌለው ምርጫ» ማለቱንም እንደተለመደው ሲነጋ የሚረሳ መስሎት ነበር፡፡ ቅንጅት ቃሉን እንደቃል እንዲወስደው ተጋፈጠው፤ ቃሉን አምርሮ ይዞ በተግባር እንዲያውለው ፈተና ውስጥ ጨመረው፤ ፈተናው ያላሰበውና አይቶት የማያውቀው ቢሆንም ከተጨባጩ ሁኔታ ተከልሎ መኖሩ ለጥርጣሬ ትንሽም ቀዳዳ እንዳያይ ጋረደው፤ አቶ መለስ በምርጫው ለማሸነፍ የነበረውን ምኞት ያህል አዲሱ ቅንጅትም በሰላማዊ የፖሊቲካ ትግል ሊያሸንፈው ቆርጦ መነሣቱን ለመገንዘብ ተሳነው፡፡

[4] በበኩሌ ለአንድ ዓመት ያህል መክመሪያ ሕዝብ ለምርጫ እንዲመዘገብ፣ በኋላም እንዲመርጥ በየሳምንቱ በጦቢያ ጋዜጣ ላይ እየጻፍሁ ሰውተውት ነበር፡፡



ሕዝቡን ለምርጫ ለማዘጋጀት የክቡር ገና ድርጅት በኃይሌ ገብረ ሥላሴ በኩል ሄዶ ለአባማ የደረሰውን (ቅደም-ተከተላቸውን ይገፔ ነው) «ይቻላል!» የሚል መፈክር አወጣ፤ ሌሎች ድርጅቶችም በየፊናቸው ለምርጫ የመመዝገቡን ግፊት አጠናከሩት፤ በጦብያ ጋዜጣ በየሳምንቱ ስለመመዝገብና ስለምርጫ መብት ጽሑፎች ይወጡ ነበር፤ በዚሁ ጉዳይ ላይ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ) ንግግሮችንና ውይይቶችን በተደጋጋሚ ሲያደርግ ነበር፤ በአንጻሩ አንዳንድ ጋዜጦች ላይ የምርጫውን ፋይዳቢስነት ከአገር ውስጥም ከአገር ውጭም የሚጽፉ ሰዎች ነበሩ፤ ክርክሩ እየዳበረና የተለያዩ ሀሳቦች እየተንፀባረቁ አብዛኛውን ሰው ተካፋይ አድርገውት ነበር፤ ይህ ነው ሰውን ሁሉ ለክፉም ለደግም መመዝገብ የማይጎዳ መሆኑን አሳምኖ የገፋፋው፡፡

ለምርጫ የሚመዘገበው ሰው ቁጥር ከዚህ በፊት በምድረ ኢትዮጵያ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ እየበረከተ ሄደ፤ ምርጫው ወዴት እንደሚያዘነብል በትክክል ባይታወቅም ዕድሜያቸው የሚፈቅድላቸው ሙሉ ቤተሰቦች እየሄዱ በመመዝገባቸው የሕዝቡ ተሳትፎ ከፍ ያለ እንደሚሆን ተረጋገጠ፤ ከዚያ በኋላ የሚቀረው ሥራ የተመዘገበው ሰው ሁሉ የሚያስፈልገውን ጊዜ ሰጥቶ እንዲመርጥ ማድረግና ማንን እንደሚመርጥ ማሳመን ነበር፡፡

## 2. የምርጫው ዘመቻ

የምርጫ ዘመቻ ምን ማለት ነው? ዴሞክራሲያዊ የሆነ ምርጫ በሚካሄድበት ጊዜ ተቀናቃኝ ወይም ተፎካካሪ የፖሊቲካ ቡድኖች በሙሉ ነጻነትና ልበ-ሙሉነት የየራሳቸውን አቅዋም ለሕዝብ ያሳውቃሉ፤ ከዚያም አልፈው አንዱ የሌላውን አቅዋም ይነቅፋል፤ ስሕተቶች የሚመስሉትን ሀሳቦችና ድርጊቶች ያጋልጣል፤ የፉክክሩ ዋና ዓላማ አንዱ ከሌላው በልጦና ተሽሎ በሕዝብ ፊት ለመቅረብና የሕዝብን የድምፅ ድጋፍ ለማግኘት ነው፤ ስለዚህም ከጨዋ ሥርዓት ሳይወጡ መነቃቀፍና አንዳንዴም አንዱ በሌላው ማላገጥ የተለመደ ነው፤ ይህ የምርጫ ዘመቻ ሥርዓት ነው፤ዋናው ፍሬ ነገር በአመራር ችሎታና በአስተሳሰብ፣ ለወደፊቱ እድገትና ልማት ባለው እቅድ፣ በሕዝቡ ላይ በሚያሳድረው የሥራ መንፈስና ተስፋ በልጦና ተሽሎ መገኘት ነው፤ በዚህ ምክንያት ነቀፈኝ፤ አጥላላኝ፤ ተሳለቀብኝ በማለት ወደማምረር መሄድ የምርጫ ዘመቻውን ዓላማ ጠንቅቆ ካለመረዳት ወይም ውጤቱን ለመቀበል ካለመፈለግ የሚመነጭ እጉል ጠባይ ነው፤ በዱሮ ጊዜ በገና ጨዋታ አይቆጡም ጌታ የሚባለው ዓይነት ነው፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ የምርጫ ዘመቻው ሁለት ገጽታዎች አሉት፤ አንዱ ገጽታ የፖሊቲካ ቡድኑ አባሎች ሁሉ በተናጠል ለየብቻቸው የየፓርቲዎቻቸው አባሎች እንዲመረጡላቸው የሚያደርጉት የማስታወቅና ፓርቲውን የማራመድ

ተግባር ነው፤ ሁለተኛው ገጽታ እያንዳንዱ ተመራጭ በየአካባቢው ለመራጩ ሕዝቡ ራሱን የሚያስተዋውቅበትና እንዲመርጡት ንግግር የሚያደርግበትና ጥያቄዎችንም የሚመልስበት ነው፤ ስለዚህ ለምርጫ ዘመቻው ፓርቲው በአጠቃላይና እያንዳንዱ ተመራጭም ኃላፊነት አለባቸው ማለት ነው፡፡

በቅንጅት ውስጥ ለምርጫው የሚደረገው ዝግጅት በጥሩ መንፈስና በሰከነ  አእምሮ በደንብ ታቅዶ ለተለያዩ ኃላፊነቶች ሰዎች ተመርጠው ተመደቡ፤ የምርጫውን ዘመቻ የሚመራው ብርሃኑ ነጋ  ሆነ፤ ከምርጫው ጋር ተያይዘው የሚመጡትን ችግሮች ደግሞ የሚከታተለውና ቀልጣፋ መፍትሔዎችን የሚፈልግላቸው ግዛቸው ሽፈራው ሆነ፤ ስለዚህም ብርሃኑና ግዛቸው የቅንጅት ምርጫ ዘመቻ ዋና ምሰሶዎች ሆነው በሚያስደንቅ ትጋትና ቅልጥፍና አገሩን በሙሉ የሚሸፍን እቅድ አውጥተው በተቀነባበረ ሁኔታ ሥራቸውን ጀመሩ፡፡

ለምርጫው ዘመቻ አንዱና  ዋናው የመጀመሪያ ተግባር በአገሩ በሞላ ለመመረጥ እጩ የሚሆኑትን የቅንጅት አባሎች መመልመል ነበር፤ እዚህ ላይ በጣም ከባድ የሆነ በቅንጅት ውስጥ ያሉት ቡድኖች ፉክክር ለቅንጅት የመጀመሪያውን አስቸጋሪ ፈተና ደቀነበት፤ በዚህ ችግር ምክንያት ቢሮ ውስጥ ልባችን እስቲወልቅ ስንከራከር ያነጋንባቸው ሌሊቶች ነበሩ፤ በመኢአድና በኢዴአፓ መሀከል የተፈጠረው ቅራኔ አንዳንዴ የማይታረቅ የመሰለበት ደረጃ ላይ ደርሶ ቅንጅትም ይፈርሳል የሚል ስጋት ላይ የወደቅንበት ጊዜ ነበር፤ አስፈላጊውን መስፈርት ሁሉ ካወጣን በኋላ የበለጠ ቁጥር ለማስመዝገብ ሲሉ የትምህርት መስፈርቱን በሐሰት የሚሞሉ እንደነበሩ ተሰምቶአል፤ በተጨማሪም እኛ ሞተናል፣ ተደብድበናል፣ ታስረናል፣ በማለት ከትምህርትና ከችሎታ መስፈርት ውጭ እጩዎችን ለማብዛት ሽንጣቸውን ገትረው የሚከራከሩ ነበሩ፤ በቀስተ ደመናና በኢዴሊ በኩል አዳዲስ ፓርቲዎች በመሆናቸውና የግል ፓርቲነትን ፈጽመው ትተው በቅንጅት ላይ ያተኮሩ ስለነበሩ ብዙ ችግር አልነበራቸውም፡፡

በመኢአድና በኢዴአፓ መሀከል የነበረው ፉክክር ግን ቅንጅት የተረሳ እንደነበረ የሚያመለክት ነበር፤ እነዚህን ቡድኖች ለማግባባት ብርሃኑ ነጋ ሌሊቱን ሙሉ ልቡ ሲወልቅ አድሮ ሲነጋ ጥሬ ይሆንበት ነበር፤ ለክልልም ሆነ ለብሔራዊ ምክር ቤቶች እጩዎችን ለማቅረብ ከሥራ ልምድ፣ ከትምህርትና ከችሎታ ውጭ መለኪያ የሚፈልጉ ሰዎች ለፖለቲካ ሥራ አፈ ጮሌነት ብቻ በቂ መሆኑን ዛሬም የሚያምኑ ናቸው፤ ለማናቸውም በአብዛኛው በብርሃኑ እልህና ጥረት የሚያስማማ የእጩዎች ዝርዝር ሊወጣ ተቻለ፡፡

የምርጫው ዘመቻ ሲጀመር ብርሃኑና ግዛቸው ላይ ከባዱ የሥራ ሸክም ተጭኖባቸው ነበር፤ በየክልሉ ሰዎችን ማሰማራትና ጽሑፎችን መላክ ችግሮች ሲከሰቱም ከምርጫ ቦርድና ከሚመለከታቸው ሹሞች ጋር መነጋገር



የሚያታክትና አድካሚ የዕለት ከዕለት ሥራቸው ነበር፤ ከድርጅቱ ያልዳበረ አቅም ጋር ሲመዘን ሥራቸው በጣም አስደናቂና ውጤታማ ነበር ለማለት ይቻላል፡፡

በምርጫ ዘመቻው ላይ ከፍተኛና ሙያዊ አስተዋጽኦ ያደረገ ደበበ እሸቱ ነበር፤ በቴሌቪዥን የተፈቀደውን አምስት ደቂቃና በራድዮ የተፈቀደውን አሥራ ሁለት ደቂቃ ግሩምና በጣም የሚስቡ ዝግጅቶችን እያቀናበረ የኢትዮጵያ ሕዝብ ራድዮኑን እንዲያዳምጥና ቴሌቪዥኑን ተግቶ እንዲመለከት አደረገው፤ የቅንጅትንም መልእክት ለሕዝቡ በሚገባውና ልቡን በሚነካው መንገድ በማስተላለፍ ደበበ ያበረከተው አስተዋጽኦ በጣም ከፍተኛ ነበር፤ የሙያ ብቃትና እምነት ሲዋደዱና ሲጋቡ እንዴት ያለ ሰማይ-ጠቀስ ውጤት እንደሚያስገኙ ደበበ እሸቱ በአጭር ጊዜ ውስጥ ማሳየቱ ትልቅ ትምህርት ነበር፤ ሰው ጠልቶት የነበረውን ቴሌቪዥንና ራድዮ ለጥቂት ደቂቃዎች ቢሆንም እንዲወደዱ አደረጋቸው፡፡

በቅንጅት ውስጥ ሌላ ድምፁን አጥፍቶና በሩን ዘግቶ በሚያስደንቅ ትጋት ሲሠራ የነበረ ሰው ዶር. አድማሱ ገበየሁ ነበር፤ አድማሱ በተፈጥሮው እዩልኝ-ስሙልኝ የሚል ሰው አይደለም፤ ስለዚህም እሱ የሠራውን ሥራ ብዙ ሰው አያውቅም፤ መረጃ የሚያስፈልገው ጽሑፍ ሲዘጋጅ፣ ደምቦችና መመሪያዎች ሲወጡ ዋናው ሥራ የሚከናወነው በቢሮው ቁጭ ብሎ በሚሠራው በአድማሱ ገበየሁ ነበር፤ ማንም እንደአድማሱ በሩን ዘግቶ ለብዙ ሰዓታት መሥራት የሚችል አልነበረም፤ በመጨረሻም በሥራ ብዛት (ምናልባትም አንዳንዴ አጉል ፉክክሩ እያስጠላው ሊሆን ይችላል) ራሱን ታመመ፤ የቅንጅት ምልክት የሆነው ሁለት ጣትም የአድማሱ አስተዋጽኦ ነው፡፡

እዚህ ላይ  ወያኔለወያኔ/ኢሕአዴግ በቅሬታ የታጠረ ምስጋና ማቅረብ ያስፈልጋል፤ ብዙ ሰዎች ወያኔ/ኢሕአዴግ ጥሩ ነገር ያደርጋል ብለው አያምኑም፤ ነገር ግን እውነቱን ልንክደው አንችልም፤ አንዳንዴ ጥሩ ነገር ሳይፈለግም ይደርሳል፤ አንደኛ ማንቁርታቸውን አንቆ ማስፈራራቱ ባይቀርም ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ቡድኖች ሕጋዊ ሆነው እንዲንቀሳቀሱ ያደረገው ወያኔ/ኢሕአዴግ ብቻ ነው፤ ሁለተኛ ራሱ ከጠመንጃ ሊላቀቅ ባይችልም የፖለቲካ ቡድኖችን ሕጋዊ በማድረጉ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የፖለቲካ ትግል በኢትዮጵያ እንዲጀመር በሩን ከፍቶአል፤ ሦስተኛ በምርጫ 97 ከላይ እንደተገለጸው ተቀናቃኝ ቡድኖች በምርጫው ዘመቻ ላይ መልእክቶቻቸውን ለሕዝብ ለአጭር ጊዜም ቢሆን በቴሌቪዥንና በራድዮ እንዲያስተላልፉ አደረገ፤ ይህ ሁሉ ምዕራባውያን አገሮችን ለማታለል ሳይሆን በቅን መንፈስ የታጀበ ቢሆን በኢትዮጵያ ታሪክ አዲስና የሚያኮራ የእመርታ ምዕራፍን ይከፍት ነበር፤ ነበር  ሆኖ ቀረ እንጂ! ቢሆንም የኢትዮጵያ ሕዝብ የፖሊቲካ ብልጭታ ማየቱን

እኔ እንደትልቅ ትምህርት እየዋለሁ፤ ከዚያም በላይ በእኔ አስተሳሰብ ወያኔ/ኢሕአዴግ ለአጭር ጊዜም ቢሆን ይገንዘበውም አይገንዘበውም የኢትዮጵያን ሕዝብ እንዲያውቀውና ራሱንም እንዲያውቅ ትልቅ ዕድልን ሰጥቶታል፤ የመንፈሳዊው ወኔና የበጎ ፈቃዱ ዕድሜ ማጠሩም በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በዓለም በሙሉ ለውርደት ዳርጎታል።

ሁላችንንም በጣም ሊያሳዝነንና ሊያስመርረን የሚገባው ነገር ወያኔ/ኢሕአዴግን በጣም ሊያስከብረውና ሊያስመሰግነው የሚችለውንና ኢትዮጵያም በአፍሪካ የነበራትን የታሪክና የሥርዓተ መንግሥት ቀዳሚነት ለማደሰና ለማረጋገጥ የሚያስችላትን ታሪካዊ ሥራ ወደማፈሪያነት መለወጡ ነው፤ በታሪክ ሚዛን በትልቅነትና በትንሽነት መሀከል ያለው ልዩነት ይህ ነው።

በአዲስ አበባ ውስጥም ሆነ ከአዲስ አበባ ውጭ የተሰማሩት የቅንጅት አባሎች ከባድ ችግር አልገጠማቸውም፤ በበኩሌ ያየሁት ችግር በደብረ ዘይት ለስብሰባ ሄደን አዳራሹን እንዳንጠቀምበት ከከተማው ሹም ትእዛዝ ተላልፎአል ተብሎ መተጓጎሉ ነው፤ በኋላ ግን ተስተካክሎ ስብሰባውን አካሂደናል፤ በናዝሬትም በተሳካ ሁኔታ በኳስ ሜዳው ላይ ትልቅ ሕዝባዊ ስብሰባ አድርገናል፤ እኔ መቀሌም፣ ደብረ ታቦርም፣ ጎንደርም በሄድሁበት ጊዜ ምንም እክል አልገጠመኝም፤ በመቀሌ አዳራሹ ውስጥ መቆሚያም ቦታ ስላልነበረ ውጭ በድምፅ ማጉያ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ያዳምጡ ነበር፤ የመቀሌ የወያኔ ካድሬዎች ለመረበሽ ተዘጋጅተው የነበረ ቢሆንም ዶር ኃይሉ አርአያ፣ ዶር ሽመልስ ተክለ ጻድቅና እኔ የምንፈልገውን መልእክት አስተላልፈን ተመልሰናል፤ በወያኔ ካድሬዎች ተጠርንፎ ድምፁን ለማሰማት ባይችልም አብዛኛው የትግራይ ሕዝብ ልቡን ለወያኔ እንዳልሰጠ ለመገንዘብ ችያለሁ፤ ከአንዳንድ ሽማግሌዎችም ወጣቶችም የሰማሁት ለወያኔ ያላቸው ጥላቻ እንጂ ፍቅር አለመሆኑን ነው፤ ከተመለስን በኋላ ግን እኔ የትግራይን ሕዝብ ታሪካዊ ጀግንነት አጉልቼ የወያኔ ጠርናፊዎች ከፋብሪካ እንደወጣ ሳሙና አንድ ዓይነት ሊያደርጉት ይፈልጋሉ ያልሁትን ጠምዝዘው ከትግራይ ሕዝብ ጋር ለማጣላት በቴሌቪዥናቸው አናፈሱት፤ ደግነቱ ንግግሩን ያዳመጡት እውነቱን ማወቃቸው ነው፤ ከዚያም በላይ እነሱ አለ የሚሉትን ዶር. ኃይሉ አርአያን አጠገቤ አስቀምጬ ልናገረው ቀርቶ ላስበው የማይቻል መሆኑንና እሱም ዝም ብሎ እንደማያሳልፈኝ ለመገንዘብ አለመቻላቸው የማሰብ ደረጃቸውን የሚያመለክት ነው።

በደብረ ታቦርና በጎንደርም ውጭ በአደባባይ የተደረገው ስብሰባ በብዙ ሺሆች የሚቆጠሩ ሰዎች የነበሩበትና ፖሊሶች በዳር ቆመው ከተመልካችነት ያላለፈ ሥራ እንዳልነበራቸው የታየበት ነበር፤ በእነዚህ ስብሰባዎች በጣም ያስደነቀኝ ነገር የኢትዮጵያ የገጠሩ ሕዝብ ምን ያህል



ለውጥን ለመቀበል ፈጣን መሆኑ ነበር፤ አንዳንዶች ስለመኢአድ ወይም ስለኢዴአፓ ሲናገሩ ብዙዎች በቁጣ ‹የምን መኢአድ/የምን ኢዴአፓ አሁን ቅንጅት ነው!› ይሉ ነበር፤ በጎጃምና በወሎ በደቡብም የተደረገውን ሕዝባዊ ስብሰባ በቪድዮ አይቼዋለሁ፤ በጣም የሚያስደንቅና የሚያኮራ ነው።

## 3. የምርጫ ዘመቻው ክርክር

በምርጫው ዘመቻ ወያኔ/ኢሕአዴግ በማናቸውም ሁኔታ የበላይነቱን በትዕቢት በማመንና ሕዝቡን በመናቅ ጀመረ፤ እሉ የተባሉ የወያኔ/ኢሕአዴግ ሹሞች በሙሉ አቶ አዲሱ ለገሰ፣ አቶ በረከት ስምዖን፣ አቶ ዓባይ ጸሐይ፣ አቶ ሥዩም መስፍን፣ ደር. ካሡ ኢላላ፣ አቶ ግርማ ብሩ፣ አቶ አባዱላ ገመዳ፣ አቶ ጁነዲን ሳዶ፣አቶ ተፈራ ዋልዋና ሌሎችንም ደቂቃን ሹሞች ለቴሌቪዥንና ራድዮ ክርክር ተሰለፉ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ የወያኔ/ኢሕአዴግን ቱባ፣ ቱባ፣ ባለሥልጣኖች ከቅንጅት ተሳታፊዎች ጋር አመዛዘናቸው፤ በጣም አንሰው አገኛቸው፤ በቴሌቪዥን ላይ በተደረገው ሙግት ሁሉ የተቀናቃኝ ቡድኖች ያሳዩት ብልጫ የሕዝቡን ቀልብ ስቦ በአደባባይ ወጥተው ለተከራከሩት የወያኔ ባለሥልጣኖች ፍርደ-ገምድል እንዳንሆንባቸው አንድ ነጥብ ለማንሣት እፈልጋለሁ፤ እነዚህ ሰዎች እንደማንኛችንም ነጻነት የሌላቸው ናቸው፤ በሹመት ወንበራቸው ላይ ባሉበት ጊዜ ባይነግሩንም ሲኮበልሉ የልባቸውን ይነግሩናል፤ ዙሪያቸውን ታጥሮባቸው እምነውበትም ይሁን ሳያምኑበት በተፈቀደላቸው ቀጭን መስመር ብቻ የሚናገሩ ናቸው፤ እንሳሳት ይሆን? ብለው በመፍራት የማያምኑበትን በልበ ሙሉነት ለመናገር ችግር ይገጥማቸዋል።

የወያኔ/ኢሕአዴግን ባለሥልጣኖች በጣም ከአጋለጠውና ቀልባቸውን ከገፈፈው የአደባባይ ሙግት ያመለጠው አቶ መለስ ብቻ ነው፤ አይፈረድበትም፤ ነገር ግን ከአደባባዩ ሙግት ራሱን ቢያወጣም በአደባባዩ ሙግት ላይ የቀረቡትን ባለሥልጣኖች የመረጠ እሱው ነው፤ ስለዚህም የመረጣቸው ባለሥልጣኖች በሕዝቡ ሚዛን ያስገኙለትን የአደባባይ ሙግት ውጤት የራሱ አድርጎ ከመቀበል ማምለጥ አይችልም።

ወያኔ/ኢሕአዴግ በምርጫው ዘመቻ ጊዜ ቀደም ሲል እንደተባለው ተቀናቃኝ ቡድኖች በቴሌቪዥን በቀን አምስት ደቂቃ፣ በራድዮ ደግሞ በቀን አሥራ ሁለት ደቂቃ አግኝተው ነበር፤ በነዚህ አጫጭር ጊዜያት በሁለቱም የዜና ማሰራጫዎች ከፍተኛ የሕዝብ አትኩሮትን ስበው ነበረ፤ የቴሌቪዥን ተመልካቾችና የራድዮ አድማጮች ቁጥር በጣም ጨምሮ ነበር፤ ተቀናቃኝ ቡድኖች የሕዝብን ቀልብ እንዲስቡ ከአደረጋቸው መንገዶች አንዱ የሠለጠኑና በፈቃዳቸው አምነው የገቡ ባለሙያዎች ኃላፊነቱን መያዛቸው ነበር።

ቅንጅት በተወሰነ ገንዘብና ጉልበት ከትግራይ እስከ ደቡብ፣ ከጋምቤላ እስከ ሐረር ተሰማራ፤ ሕዝባዊ ስብሰበባዎቹን አዳራሾች የማይችሉአቸው ሆኑ፤ በዚህም ምክንያት አብዛኛዎቹ የቅንጅት ሕዝባዊ ስብሰባዎች በኳስ ሜዳዎችና በሰፊ አደባባዮች ላይ ሆኑ፤ ሕዝቡ መንፈሱ ለለውጥ ተነሣሣ፤ የፍርሃት ቆፈኑ ለቀቀው፤ በዜግነት መብቱ ተጠቅሞ የሥልጣን ባለቤትነቱን ለማረጋገጥ በነቂስ እየወጣ እንደተመዘገበው ሁሉ በነቂስ እየወጣ መረጠ።

## 4. የግንቦት ሰባት ምርጫ

በምርጫው ዕለት (ግንቦት 7) በአዲስ አበባ ውስጥ ለመምረጥ የወጣው ሕዝብ ብዛት በቤት ውስጥ ሰው ያልቀረ ይመስል ነበረ፤ በበኩሌ የራሴን ምርጫ ገና በጠዋት ከአጠናቀቅሁ በኋላ (ፋይዳ የሌለው ቢሆንም በሕይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ መረጥሁ) በብዙ ቀበሌዎች እየተዘዋወርሁ እመለከት ነበር፤ በአንዳንድ ቀበሌዎች በሦስት ሰዓት ግድም ገና ምርጫ አልተጀመረም ነበር፤ ጠዋት ከአሥራ ሁለት ጀምሮ የተሰለፈው ሕዝብ ግን ንቅንቅ አላለም፤ ሁሉም በመምረጥ መብቱ ለመጠቀም ለመጀመሪያ ጊዜ ቆርጦ የተነሣ ነበር፤ በአንዳንድ ቀበሌዎች ሲመሽም ምርጫው አልተገባደደም ነበርና በምሽትም ቀጥሎአል፤ የሕዝቡን ቆራጥነት ረሀብና የውሀ ጥምም አላሸነፈውም፤ መብቱን አወቀ፤ መብቱን አሳየ፤ መብቱን አስከበረ፤ አሁን ወያኔ/ኢሕአዴግ ከእንቅልፉ ነቃ፤ ደነገጠ፤ ተሸበረ።

ገና በሚያዝያ 30 ሕዝባዊ ስብሰባ መርበድበድ የጀመረው ወያኔ/ኢሕአዴግ በግንቦት 7 ለምርጫ የወጣውን ሕዝብ ቆራጥነትና ጽናት ሲመለከት፣ አዲስ አበባ በሙሉ እንደተወሰደበት ሲገነዘብ፣ ቱባ ቱባ ሹሞቹ በያለበት ሲሸነፉ ሲረዳ «ያለእንከን» የተባለውንና ከማሰብ ቀድሞ የመጣውን አነጋገር ያለእፍረት በተግባር መቀልበስ ግድ ሆነበት፤ የወያኔ/ኢሕአዴግ ሊቀ መንበር በጠቅላይ ሚኒስትርነቱ ግንቦት ሰባት ማታ ለአንድ ወር የአስቸኳይ ጊዜ አወጀና ማናቸውም ስብሰባ እንዳይደረግ ከለከለ፤ ገና የምርጫው ውጤት በውል አልተሰበሰበም፤ እንዲያውም በአንዳንድ ቦታዎች ገና ምርጫው በመካሄድ ላይ ነበረ፤ ስጋት ጓዙን ጭኖ በወያኔ/ኢሕአዴግ ቤት መግባቱ ግልጽ ነው፤ የስጋቱ ምንጭ ምን እንደሆነ ለቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚደንት ካርተር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፍንጭ ሰጥቷል፤ የወያኔ/ኢሕአዴግ ካድሬዎች በመሸነፋቸው ተናድደው ችግር እንዳይፈጥሩ ለማድረግ የተወሰደ እርምጃ ነው ተብሎ መነገሩን ካርተር ገልጾአል፤ አስቸኳይ አዋጅ እንደታወጀም እንደተለመደው ማሰብን በቀደመ አነጋገር የጸጥታ ኃይሉ በቀጥታ በሱ ስር እንደሚሆን ጠቅላይ ሚኒስትሩ በአደባባይ ገለጸ።



ከዚህ በኋላ ትልቁና ዋናው ጥያቄ ማን አሸነፈ? ወይም ማን ተሸነፈ? አይደለም፤ ትልቁና ዋናው ጥያቄ የኢትዮጵያ ሕዝብ ድምፅና ፈቃድ ተከብሮአል ወይ? የሚለው ነው፤ በኢትዮጵያ የሥልጣን ባለቤትና የሥልጣን ምንጭ ሕዝብ ነው ወይስ ጠመንጃ? ከታሪካዊ ባህላችን ወጣን ወይስ እዚያው ነን? «ወደፊት ሂድ!» ተባልን ወይስ «ባለህበት ሂድ!»? ወይስ «ቀኝ-ኋላ ዙር!» የታሪክ ጥያቄዎች እነዚህ ናቸው፤ ስለዚህም ለታሪክ እንተዋቸው።

# ፯
# ቅንጅት ተሸነፈ ተባለ

## 1. ዘዴው ዓላማውን ጋረደ

ቅንጅት ከወያኔ/ኢሕአዴግ ጋር በሥልጣን ፉክክር ውስጥ የገባበት ዓላማ የአገር ጉዳይ ነው፤ ፉክክሩ ዓላማውን ለማሳካት የተደረገ ወግና ሥርዓት ነበር፤ ዋናው ቁም-ነገር ተረሳና ዘዴው ወይም ፉክክሩ ዋና ዓላማ ሆነ፤ በፉክክሩ ተጠቃሚ የሚሆነው አገር መሆኑ ተዘነጋና የተፎካካሪዎቹ ማሸነፍ ወይም መሸነፍ የግል ክስረት ወይም ክብር ሆኖ ታየ፤ በወያኔ/ኢሕአዴግ በኩል የግል ክስረት መስሎ የታየው ቱባ ቱባ ባለሥልጣኖች የፉክክር ውጤቱን ተቀብለው ከሞቀ ወንበራቸው ለመውረድ ሲሳናቸው ነው፤ ከዚያ በኋላ በተከታታይነት የተፈጸመው ሁሉ በነዚህ ፉክክሩ ባልተሳካላቸው ባለሥልጣኖች የንዴት ምክር መሆኑ አያጠራጥርም፤ በንዴት ሁኔታዎች እየተባባሱ ሄዱ፡፡

ለማናቸውም የወያኔ/ኢሕአዴግ ቆጣሪዎች እንዳስታወቁት ቅንጅት ተሸነፈ ተባለ፤ ምናልባትም ኢሳይያስ እንዳለው «አገር በአንድ ቀን ታምጣለችን? ወይስ በአንድ ጊዜ ሕዝብ ይወለዳልን?» የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ምጡ እንዲረዝም ሆነ፤ የቅንጅት አሸናፊነት መጨናገፍ መዘዙ ብዙ ነበር፤ ምክንያቶቹም ብዙ ነበሩ፤

ሕዝብ አጉረመረመ፤ በአንዳንድ ቦታም ተቆጣ፤

የቅንጅት ምክር ቤት የሕዝቡን ቁጣ ተገንዝቦ ተመራጮቹ ወደብሔራዊ ምክር ቤት እንዳይገቡ ወሰነ፤

ሌሎችም ሰላማዊ ሰልፍ ሳይሆን የመኪና ጡሩምባ እንደመንፋት ያሉ የተቃውሞ ምልክቶች በአዲስ አበባ እንዲደረጉ ቅንጅት ወሰነ፤

እነዚህ የቅንጅት ውሳኔዎችና የሕዝቡ፣ በተለይም የወጣቱ ቁጣ ባልተቀናጀ ሰላማዊ ሰልፍ መግለጥ ሲጀምር ወያኔ/ኢሕአዴግ ያዘጋጀውን አግአዚ የሚባል ልዩ አነጣጥሮ ገዳይ ጦር አሰማራ፡፡ በሰኔ 1/1997 ብዙ ሰዎች ጭንቅላት ጭንቅላታቸውን በጥይት እየተደበደቡ ሞቱ፤ የኢትዮጵያ ምክር ቤት ያቋቋመው ኮሚሽን ይህንን ጭፍጨፋ በመጠኑም ቢሆን አጥንቶ መግለጫ ሰጥቶበታል፤ የኮሚስዮኑ ሊቀ መንበር ግን ሰነዱን በሙሉ ከነቪድዮው ይዘው ከአገር ወጡ፤ ለአውሮፓ ምክር ቤትና ለአሜሪካ ምክር ቤት መግለጫ ሰጡ፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ አልተሸነፈም፤ ቅንጅት አልተሳካለትም፤ ወያኔ/ኢሕአዴግ ግን በአጠቃላይ በፉክክሩ ባይሸነፍም በፖሊቲካ ጨቅላነቱ



ያለጥርጥር ተሸንፎአል፤ በዓለም ሕዝብ ዓይን የኢትዮጵያን ሕዝብ አዋርዶአል፤ አንድ ኬንያዊ ለቢቢሲ ጋዜጠኛ ሲናገር «ኬንያ ኢትዮጵያ አይደለም፤ የሕዝብ ድምፅ ተዘርፎ አይቀርም፤» ያለው ከኢትዮጵያ ሕዝብ የበለጠ ወያኔን እስከመጨረሻው የሚከተለው ውርደት ነው፤ የኮንዶሊዛ ራይስ ሚዛን ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ሕዝብ መለኪያ ከሆነ በኬንያ የምርጫው ውዝግብ ሰሞን በኬንያ ቢያንስ ሦስት ጊዜ ስትመላለስ በኢትዮጵያ ግን ብቅም አላለች፤ የኢትዮጵያን ዕጣ ፈንታ የሚወስነው ሲ.አይ.ኤ እንጂ የአሜሪካ መንግሥት አለመሆኑ ገሀድ የወጣ ይመስላል፤ የሲ.አይ.ኤ እቅድ በሶማልያ ሌላ አፍጋኒስታንን፣ በኢትዮጵያ ደግሞ ሌላ ፓኪስታንን ያውም በጣም በርካሽ ዋጋ ለማቋቋም ይመስላል፤ ሆኖም በፓኪስታን እንዳልሠመረለት ሁሉ በኢትዮጵያም አይሠምርለትም፤ ቻይናም ቢሆን ሲ.አይ.ኤን ተክቶ ለመዝለቅ የራሱም ችግር ሆነ የዓለም ሁኔታ አይፈቅድለትም፡፡

የምርጫ 97 ውዝግብ የኢትዮጵያ ሕዝብ ወዳጅና ጠላቱን ለይቶ ለማወቅ አስችሎታል፤ በአውሮፓ ወይዘሮ አና ጎሜዝን የሚያህል እውነተኛ ወዳጅ ለኢትዮጵያ አፍርቷል፤ በአሜሪካ እንደዶናለድ ፔይን ያሉ ብዙ የአሜሪካ የምክር ቤት አባላትንና የአሜሪካ ሊቃውንትን የኢትዮጵያ ወዳጆች አድርጓል፤ ስለዚህም የኢትዮጵያ ሕዝብ አልተሸነፈም፡፡

እንዲህ ቢሆን ኖሮ ተብሎ ታሪክ አይጻፍም፤ የሆነውና የተደረገው በዝርዝር እየተጣራ የሚመዘገብበት ጊዜ እንደሚመጣ ጥርጥር የለም፤ ሌላው ቀርቶ በወያኔም በኩል እንደተሰፋዬ ገብረ አብ ያሉ ኅሊናቸው እንቅልፍ የነሳቸው ሰዎች እውነቱን ያወጡታል፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ በፖለቲካ ስልት እየሠለጠነ ታሪካዊ አሸናፊነቱን የሚያረጋግጥበት ጊዜ ይመጣል፤ ታሪክ ያመለጠው ወያኔን ነው፤ ጨብጦት የነበረውን ክብር በውርደት የለወጠው ወያኔ ነው፤ ምርጫ 97ን የኢትዮጵያ ሕዝብ በጨዋነት አልፎታል፤ ወያኔ የኢትዮጵያን ታሪክ ወደ አዲስና ዘመናዊ አቅጣጫ ለመምራት ትልቅ ዕድልን አግኝቶ በትንሽነቱ ምክንያት አመለጠው፤ ያም አልበቃው ብሎ በግፍ እጁን አጨማለቀና በዓለም ፊት ተዋረደ፡፡

## 2. የሚያዝያ 30 አፋፍና ያስከተለው ቁልቁለት

ከግንቦት አንድ ጀምሮ የምርጫው ቀን በተቃረበ መጠን የወያኔ/ኢሕአዴግ መርበትበትና ወደ ሕገ አራዊት ማዘንበሉ እየተባባሰ ሄደ፤ በዚያው መጠን የቅንጅት አባሎች፣ ሠራተኞችና ደጋፊዎች አበሳ እየጨመረ መጣ፤ በግንቦት ሰባት በምርጫው ዕለት በሕዝቡ ድምፅ አሰጣጥ ላይ፣ ቆይቶም በድምፅ ቆጠራው ላይ ጫና በማድረግ ሚዛኑን ወደ ወያኔ/ኢሕአዴግ ለማጋደል ብዙ ሙከራዎች ተጋለጡ፤ ገና የበለጡ ከባድ እርምጃዎችን ለመውሰድ

የደገሰው ጠቅላይ ሚኒስትር በምርጫው ዕለት ማታ ከሕግ ውጭ በሆነ የጊዜያዊ አዋጅ ለአንድ ወር ማናቸውም ስብሰባ እንዳይካሄድ አገደ፤ የቀድሞው የአሜካ ፕሬዚዳንት ካርተር ለምን የጊዜያዊ አዋጅ እንዳስፈለገ ቢጠይቁት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፓርቲው ስለተሸነፈ ግርግር እንዳይፈጠር ነው እንዳላቸው ለጋዜጠኞች ተናግሮአል፤ ነገር ግን በምርጫው ማግስት ገና ድምፅ ተቆጥሮ ሳይጠናቀቅ ወያኔ/ኢሕአዴግ አሸንፎአል ተባለ፤ በዚህም ለምርጫ ቦርድ መልእክት ማስተላለፍ ይመስላል፤ ምርጫ ቦርድም የወያኔ/ኢሕአዴግን ከቆጠራ በፊት የታወጀ አሸናፊነት የሚያረጋግጥበትን ሰነድ በይፋ አወጀ።

በ1997 የተካሄደው ምርጫ ዓይነቱ ፍጹም የተለየ መሆኑ ነው እንጂ በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመንና በደርግም ዘመን የተካሄዱት ምርጫዎች በወያኔ/ኢሕአዴግ ዘመናት ከተካሄዱት የተሻሉና የጸዱ ምርጫዎች ነበሩ፤ ምርጫ 97 የተለየ የሚሆነው ገዢው ቡድን ከተቀናቃኝ ቡድኖች ጋር ለሥልጣን በቀጥታና በግልጽ ለመፎካከር የተሰለፈ መስሎ መታየቱ ነበር፤ ይህ ምርጫ ለተፎካካሪዎቹ ቡድኖች ሁሉ (ለገዢውም ለተቀናቃኞቹም) አዲስ ነበር፤ በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያው ነበር፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአጠቃላይ በፍጹም የማያውቀው ዓይነት ምርጫ ነበር፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያውቀው በጠመንጃ ተፋልሞ ያሸነፈው አናቱ ላይ እየተቀመጠ ሲገዛው ነው፤ ምርጫ 97 ይህንን አሳፋሪና አጥፊ ኋላ-ቀር ባህል ለውጦ የኢትዮጵያን ሕዝብ በአገሩ ላይ የሥልጣን ባለቤት የሚያደርገውንና ራሱ የመረጠውንና የእኔ ነው የሚለውን መንግሥት በመንበር ላይ ለማስቀመጥ ያስችላል ተብሎ ነበር፤ የተባለው ይህ ነበር፤ ተስፋውም ይህ ነበር።

ነገር ግን ወያኔ/ኢሕአዴግ ሁኔታውን ተመለከተና ፈራ፤ አፈረ፤ በልጅነታችን በጨዋታ ላይ ስናፍር እንደምንለው ጨዋታ ፈረሰ፤ ዳቦ ተቆረሰ፤ ምርጫውን በሙሉ ኃይሉ ቀለበሰው ተብሎ ታማ፤ የምርጫ ሣጥን ዘረፋና የምርጫውን ውጤት በተለያዩ መንገዶች ለመለወጥ ሕገ-ወጥ ተግባሮች ተፈጸሙ ተብሎ በሰፊው ተወራ፤ በአዲስ አበባና በአንዳንድ ትልልቅ ከተማዎች የነቁ ታዛቢዎች በብዛት ስለነበሩ የምርጫ ድምፅ ዘረፋው አልተሳካም ተባለ፤ በገጠር የምርጫ ጣቢያዎች ግን ቅንጅት ታዛቢዎችን አሠልጥኖ ለማስማራት አቅሙ አልፈቀደለትም፤ በዚህም ምክንያት የገጠሩ የድምፅ ሣጥን ለዝርፊያ ተጋለጠ እየተባለ በሰላምና በጨዋነት የተጀመረው ምርጫ ደፈረሰ።

የተቀናጀ የምርጫ ዘረፋ ተካሄደ ተብሎ ስሜት በጋለበት ጊዜ ወያኔ/ኢሕአዴግን ለፍርሃትና ለስጋት ያደረሰውን ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ የሚባለውን የፖለቲካ ቡድን ቢቻል ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ለማንበርከክና ለማስገበር፣ ካልተቻለ ድራሹን ለማጥፋት አዲስ ጥረት የጀመረ መሰለ፤ ከመቀጠላችን በፊት ግን ለአንድ መሠረታዊ ጥያቄ መልስ ማግኘት



አለብን፤ በምርጫ የሚወዳደሩት እነማን ናቸው? የመንግሥት ተግባር ምንድን ነው? በየትም አገር ቢሆን የመንግሥትን ሥልጣን እንደመራጩ ሕዝብ ፍላጎት በከፊልም ይሁን በሙሉ ለመረከብ የሚወዳደሩት ሕጋዊ የፖለቲካ ቡድኖች ናቸው፤ የአንድ ፖለቲካ ቡድን አሸናፊነት እስቲታወቅ ድረስ መሠረታዊ የመንግሥት ሥራዎች ሁሉ አይቋረጡም፤ ሆኖም በሥልጣን ላይ ያለው የፖለቲካ ቡድን የመንግሥትን ሥልጣንና ኃይል ለራሱ የማሸነፍ ፍላጎት ሊጠቀምባቸው አይችልም፤ እንዲያውም ትክክለኛና እውነተኛ ምርጫን ለማካሄድ ቁልፍ ተግባርና ግዴታ ያለባቸው የመንግሥት ድርጅቶች አሉ፤ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፤

ሀ/ ለአገር ለሰላምና ለጸጥታ ኃላፊነት የተጣለበት የደኅንነት ድርጅት፤ ይህ ድርጅት ለአንድ አገር ጤንነት መሠረት ነው፤

ለ/ የአንድ አገር ሕግን ለማስከበር የቆመ የፖሊስ ሠራዊት ድርጅት የአገርን ጤንነት ጠባቂ ነው፤ የፖሊስ ሠራዊት በሕግ የተቋቋመና በሕግ እየተመራ ሕግን ለዜጎች ሁሉ በእኩልነት የሚያስከብር ኃይል ነው፤

ሐ/ የሕዝብ ዜና ማሰራጫዎች የአንድ አገር ሕዝብ እውነተኛና ትክክለኛ መረጃዎችን እንዲያገኝ፣ የተለያዩ የፖለቲካ አመለካከቶችና እምነቶች በአደባባይ በሁሉም ዘንድ እንዲታወቁና ውይይት እንዲካሄድባቸው የሚያደርጉ ለአገር እድገት መሠረት የሆኑ ድርጅቶች ናቸው።

መ/ የጦር ኃይሎች ድርጅት የአንድ አገር ህልውና መግለጫ ነው፤ የአንድ የፖለቲካ ቡድን የግል መሣሪያና አገልጋይ አይደለም፤ መለዮውና ማዕርጉ፣ ልሻኖችና ሽልማቶቹ ሁሉ ለአገር ክብር የተፈጸሙ ግዴታዎችን የሚያመለክቱና የሚያስከብሩት ናቸው።

ሠ/ ፍርድ ቤቶች በዜጎች መሀከል ሊኖር የሚገባውን መተማመንና በሕጋዊ ሥርዓት ውስጥ የመኖርን መብትና ግዴታ በትክክለኛ ፍርድ እየወሰኑ ሕጉን በመተርጎም ኃላፊነት የተጣለባቸው ናቸው።

ረ/ የምርጫ ቦርድ የሚባለው ድርጅት በመሠረቱ ተግባሩ ከፍርድ ቤቶች እጅግም የተለየ አይደለም፤ በሕጉ መሠረት የምርጫውን ሥርዓት በትክክል ለመምራት መራጮችን፣ የፖለቲካ ቡድኖችንና ተመራጮችን ወይም እጩዎችን ለመመዝገብና ያለምንም አድልዎ ሥራውን ለማካሄድ የተቋቋመ ድርጅት ነው።

ሰ/ ከፖለቲካ ሹመት ውጭ የሆኑ የመንግሥት ሠራተኞች የሕዝብ አገልጋዮች ናቸው፤ የፖለቲካ እምነታቸው ወይም ዝንባሌአቸው በሥራቸው ላይ ምንም ዓይነት ተጽእኖ ሳይፈጥርባቸው ዜጎችን ሁሉ በእኩልነትና በትክክል የሚያስተናግዱ ናቸው፡፡

እነዚህ ስድስት ድርጅቶች የአንድ መንግሥትና የአንድ ሕዝብ ድርጅቶች ናቸው፤ ለአንድ ክፍለ ሀገር፣ ወይም ለአንድ ቋንቋ ለአንድ ሃይማኖት፣ ወይም ለአንድ የፖለቲካ እምነት በወገናዊነትና በአድሏዊነት የቆሙ፣ የአንድ ቡድን መሣሪያዎች አይደሉም፤ ነገር ግን በአንድ ምክንያት ወይም አጋጣሚ የታሪክ ሁኔታ እነዚህ ድርጅቶች ሁሉ በአንድ ላይ በአንድ ቡድን ቁጥጥር ስር ከዋሉ የሥርዓተ መንግሥት መኖር አጠራጣሪ ይሆናል ለማለት የሚቻልበት ደረጃ ላይ ተደርሶአል፤ ምክንያቱም እነዚህ ስድስት የመንግሥት ምሰሶዎች የሆኑ ድርጅቶች ለሕዝብና ለአገር የሚያገለግሉ ናቸው፤ የሕዝብንና የአገርን ጥቅም የሚያስከብሩ በመሆን ፋንታ የአንድ ቡድንን ጥቅም የሚያስጠብቁ፣ የሕዝብንና የአገርን ደኅንነት፣ ጤንነትና ሰላም የሚጠብቁ በመሆን ፋንታ የአንድ ቡድንን የበላይነት የሚያረጋግጡ ሲሆኑ፤ የኃይል አገዛዝ እንጂ በሕዝብ ፈቃድ የቆመ ለሕዝብ ጥቅም የሚሠራ የሕዝብ አገልጋይ የሆነ መንግሥት አለ ለማለት ያስቸግራል፡፡

ነጻነቱን የተነናጸፈ ሕዝብ በአገዛዝ ስር ለመኖር ይቸገራል፤ ሰላማዊ ተቃውሞ እንዲያካሂድ የደኅንነቱ፣ የፖሊሲና የጦር ኃይሉ ከነመሣሪያው በሕዝብ ላይ የሚዘምትና ያልገበረውን የሚገድል፣ አካለ ጎደሎ የሚያደርግ፣ የሚያደኸይና የሚያሰቃይ ከሆነ ጭካኔው ወይ ወደ መገበርና ጸጥ ወደ ማለት፣ ወይ ወደ መጥፎና አስፈላጊ ያልሆነ የእርስበርስ እልቂት የሚያመራ ይሆናል፤ ነገር ግን ለነጻነቱ ዋጋ የሚሰጥ ሕዝብ በፍርሃት አይገብርምና የሰላማዊውን ትግል መድረክ አለመዝጋቱ ከብዙ ጥፋት የሚያድን መሆኑ አያጠራጥርም፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ የ1997 ምርጫ ውጤት የምርጫውን ዓላማ በቀጥታ የሚቃረን ነበር፤ ምርጫውና ዓላማው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደማናቸውም ሥልጡን ሕዝብ ከሕገ አራዊት እንዲወጣና በአገሩ ላይ ሕጋዊ የሥልጣን ባለቤት እንዲሆን የሥልጣን ርክክቡን ወይም ክፍያውን በሕጋዊና በሰላማዊ መንገድ እንዲፈጽም ለማድረግ ነበር፤ ይህ ሳይሆን ቀረ፤ ምክንያቱም አንደኛ ወያኔ/ኢሕአዴግ የመንግሥት ሥልጣንን ለማስረከብም ሆነ ለማካፈል ፈቃደኛ ሆኖ አልታየም፤ ሁለተኛ የምርጫ ቦርድ በትክክልና በእውነት የምርጫውን ውጤት ማውጣቱን የተጠራጠሩ ሰዎች ነበሩ፤ ሦስተኛ የደኅንነት፣ የፖሊስና የጦር ሠራዊት አባሎች በየመንገዱ በየቤቱ ሰላማዊ ሰዎችን ማደንና መግደላቸው የሰላማዊ የፖለቲካ ትግሉን አበላሸው፤ አራተኛ የመንግሥት የዜና



ማሰራጫዎች በሙሉ የወያኔ/ኢሕአዴግን መስመር ይዘው በማነብነባቸው የተለየ ሀሳብ በራድዮና በቴሌቪዥን ለሕዝብ የማይደርስ ሆነ፤ አምስተኛ ነጻ ጋዜጦች በጣም በተወሰነ መንገድ እንኳን ሕዝብን እንዳያገለግሉ ጋዜጠኞቹና አሳታሚዎቹ እየተያዙ ታሰሩ፤ ጸጥ ለጥ አድርጎ የመግዛት ሙከራ ከዚህ ሊብስ አይችልም፡፡

የሰኔ አንድ ጭፍጨፋ አልበቃ ብሎ፣ ከዚያ በኋላ በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች የቅንጅትን አባሎች ማዋከቡ፣ መደብደቡና ማሰሩ፣ መግደሉ አልበቃ ብሎ፣ በአዲስ አበባ የቅንጅት አመራር አባሎችን በየመንገዱ፣ በየሬስቶራንቱና በየቤቱ ማዋከብና ማስፈራራቱ አልበቃ ብሎ ጥቅምት 22 ቀን 1998 ሌላ ግድያና አፈሳ ተጀመረ፡፡

## 3. ተፍጻሜተ ቅንጅት

ገና ከመጀመሪያው የተበከለ መንፈስ በቅንጅት አመራር ውስጥ ገብቶ እንደነበረ ለእኔ ግልጽ ነበር፤ የተበከለው መንፈስ የሚገለጥባቸው ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ሁለት መንገዶች ነበሩ፤ አንዱ የቀረ ድርጅትን አንቆ ይዞ ከሬሣ ጋር አልላቀቅም የሚያሰኝ ሕመም ነበር፤ ሌላው የግል የሥልጣን ጥም ነበር፤ ሁለቱ የችግር መነሻዎች የተለያዩ ቢመስሉም በጣም የተቆራኙ ናቸው፤ ለዚህ ችግር መፍትሔ ለማግኘት በተደጋጋሚ በጣም ተሞከረ፤ አልተቻለም፤ በዚህም ምክንያት በአንድ በኩል የቡድን ሽኩቻ በሌላ በኩል የግለሰቦች የሥልጣን ሽኩቻ ለቅንጅት ዓላማ ከፉ ደንቃራ እንደሚሆኑ በመገንዘብ ቀደም ብዬ ለምክር ቤቱ በጽሑፍ ገልጬ፣ ሁኔታው እስቲለወጥ ድረስ አብሮ ለመሥራት የማልችል በመሆኔ ወጣሁ፤ የሚደንቀው የእኔ ከምክር ቤቱ መውጣት የቅንጅትን መሪዎች በጉዳዩ ላይ በጥሞና እንዲያስቡበትና እንዲስተካከሉ አለማድረጉ ነው፤ እንዲያውም ከንዝንዙ ተገላገልን ሳይሉ አልቀሩም ይሆናል!

በቀስተ ደመናም በኩል የተመለከትሁት የአምባገነንነት ዝንባሌ ደስ አላለኝም ነበር፤ ከዚያም በላይ በአንድ የቀስተ ደመና የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ ስለተሰበሰበ ገንዘብ ጥያቄ አቅርቤ የተሰጠኝ መልስ አሳዘነኝ፤ በዚህም ምክንያት ከዚያም ለቀቅሁ፤ ከሥልጣኑ መዋቅር ብወጣም በሀሳብና በተግባር ከሁሉም ጋር በየጊዜው እየተገናኘሁ ግዴታዬን ለመወጣት ሞክሬአለሁ፤ በአጠቃላይ ጨፍልቆ መናገር ትክክል ስለማይሆን በእኔ ግምት ከመጡበት ድርጊት ለመላቀቅ ትልቅ ችግር የሆነባቸው ዋናዎቹ በመኢአድ በኩል አቶ ዓባይነህ ብርሃንና ሻለቃ ጌታቸው መንግሥቴ ሲሆኑ ኤንጂነር ኃይሉ በሊቀ መንበርነቱም ምክንያት ብዙውን ጊዜ ራቅ የማለት ዝንባሌ ቢያሳይም ውስጥ ውስጡን የሚያበረታታቸው እንደነበረ ይታወቃል፤ ከመኢአድ ኤንጂነር

ግዛቸው አብዛኛውን ጊዜ ነጻ ነበር ለማለት ይቻላል፤ በኢዴፓ በኩል አክራሪዎቹ ልደቱና ሙሼ ሲሆኑ ዶር. አድማሱ የኢዴአፓ ፕሬዚዳንት ቢባልም ልጓሙን የያዘው ልደቱ አያሌው ነበር።

ለቅንጅት መዳከምና መፍረስ በመጀመሪያ በሩን የከፈተው ልደቱ ስለሆነ ትንሽ ሰፋ አድርጎ መነጋገሩ ተገቢ ይሆናል፤ የመጨረሻ የመገንጠያ መሣሪያ ያደረገው የኢዴአፓን ማኅተም ነው፤ ዋና ጸሐፊ በመሆኑ ማኅተሙ በቁጥጥሩ ነበርና በውኅደቱ ሰነድ ላይ እንዳያርፍ አገደ፤ የሱው ፓርቲ ፕሬዚደንትና ምክትል ፕሬዚደንት፣ እንዲሁም ሌሎች የሥራ አስፈጻሚ አባላትን አሸንፎ ተለየ፤ በስብሰባ ላይ አባላት ሁሉ በቅንጅትና በኢትዮጵያ ሕዝብ ሲለምኑት አሻፈረኝ ብሎ ሄደ፤ ከሁሉም በላይ ልደቱ የራሱን የመለየት አቅዋም ለማጠናከር ሲል ለምርጫ ቦርድና ለወያኔ/ኢሕአዴግ ቅንጅትን የመምቻ ሀሳቦችን እየደጋገመ በይፋ በጋዜጣ መግለጹ ነው፤ እነዚህን ነገሮች እዚህ መድገም አስፈላጊ አይደለም፤ የፈለገ በጊዜው የወጡትን ጋዜጦችና በተለይም በሪፖርተር መጽሔት ላይ ያደረገውን ቀለ ምልልስ መመልከት ይችላል፤ አቶ ልደቱ አቅዋሙ የተጠናከረለት እየመሰለው በንዴት ራሱን ከሚያስፈልገው በላይ አጋልጦአል፤ በጦቢያ ጥቅምት 17/1998 እንዲህ ይላል፤---

*እኔ ማንነቴን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሜ ደጋግሜ በተግባር ለማረጋገጥ ብዙ ዕድል አለኝ፤ እኔ እዚህ ፖሊቲካ ውስጥ የገባሁት የጡረታ ጊዜዬን ለማሳለፍ አይደለም፤ ወይም ደግሞ በቀብሬ ላይ የሚነበብ አንድ ታሪክ ለመጨመር አይደለም፤ ራዕይ ኖሮኝ ነው እዚህ ትግል ውስጥ የገባሁት።*

አምላክነትን ለማወጅ ምንም ያህል አልቀረውም፤ ወይም ዕድሜውን በኮንትራት የያዘው ይመስላል፤ በዕድሜ የገፉትን ተቀናቃኞቹን ለማዋረድ ሲል ራሱን አንጠለጠለ፤ ዛሬ ልደቱ በዕድሜው ላይ ሦስት ዓመት ያህል ጨምሮ ወደሽማግሌዎቹ ጠጋ ብሎአል! ልደቱ በዚህ አያቆምም፤ የሚከተለውንም ይጨምርበታል፤-

*የኢትዮጵያ ሕዝብ ማወቅ አለበት፤ ለምንድን ነው ልደቱ ላይ ይሄን ያህል ርብርብ የሚበዛው? ሰዎች እንዲህ ዓይነት ርብርብ እኔ ላይ ሲያዩ በጣም ያዝናሉ፤ የምጨነቅ፣ የምበሳጭ ይመስላቸዋል። እኔ ግን እውነቱን ልንገራችሁ በጣም እደሰታለሁ፤ አልጨነቅም፤ እኮራለሁ። ለምንድን ነው የምኮራው? የምደሰተው? ትኩረት የሳብኩ ፖሊቲከኛ ባልሆን ኖሮ ይህ ሁሉ ግምት አይሰጠኝም ነበር። ሰዎች ይህን ሁሉ ርብርብ የሚያደርጉብኝ ትርጉም ያለኝ ፖሊቲከኛ ሆኜ ስላዩኝ ነው፤ ባያዩኝ ኖሮ ይሄን አያደርጉም ነበር።*

በቅሰኛው መሀመድ አሊን ያስታውሳል! የሚያሳዝነው እንደልደቱ ያለ ትሑትና ጨዋ ሰው በሥልጣን ምኞት እንደዚህ ያለ ሕመም ላይ መውደቁ



ነው፤ ሌሎች ተቀናቃኞቹ ደፍረው ያልገለጹትን ሕመም ልደቱ መጋረጃውን ሁሉ ቀዳዶ ገልጦታል፤ በምርጫው ዘመቻ ሰሞን የሕዝቡ ጭብጨባና ውዳሴ ላልለመደው ሰው እንደከፉ መጠጥ የሚያሰክርና ጭንቅላትን የሚያሳብጥ ነበር፤ ማስተዋል ለቻለ ሁሉ ይህ በጣም ግልጽ ነበር፤ ልደቱ በመቸኮሉና በመጀመሪያ ከቅንጅት የወጣው እሱ በመሆኑ ይለያል እንጂ በቅንጅት ውስጥ በፉክክር ከተጣመዳቸው ከኤንጂኒር ኃይሉ ሻውልና ከዶር. ብርሃኑ ነጋ የመጨረሻ ጠምዛዛ ጉዞ ጋር የባሕርይ ዝምድና እንዳለው መካድ አይቻልም፤ የሰው ምክር የሚሰሙበት ደረጃ ላይ ስላልነበሩ ተናግሬ ነበር ማለቱ አይጠቅምም እንጂ ለሦስቱም በተናጠልም አንድ ላይም የጭብጨባውን ሞቅታና የፉክክሩን አደጋ ለማስረዳት ሞክሬ ነበር፤ ከምክር ቤቱ ስለይ የገለጽሁት ይህንኑ ነበር።

የምርጫ ዘመቻው እየተሳካ በሄደ መጠን የሥልጣን ጥሙም እየበረታ ሄደ፤ እንዲያውም የሚኒስቴር ወንበሮችን የሚመኙ እንደነበሩ ምልክቶች ይታዩ ነበር፤ በዚህም ምክንያት ጉዳዩ ከባድ ችግርን እንደሚፈጥር በመስጋት አንድ ሀሳብ ማናፈስ ጀመርሁ፤ ኢትዮጵያ አሁን ባለችበት ሁኔታ ከሦስቱ የመንግሥት አካሎች — ሕግ አውጪ፣ ሕግ ተርጓሚና ሥራ አስፈጻሚው — የሕግ አውጪውን አካል ማለትም የተወካዮች ምክር ቤቱን ዋናና ጠንካራ ማድረግ ያስፈልጋል፤ ቀጥታ የሕዝብ ውክልና ያለው እሱ ነው፤ የሕዝቡን ሥልጣን ማረጋገጥ የሚችለው እሱ ነው፤ ስለዚህም የሕግ ተርጓሚውንና የሥራ አስፈጻሚውን ሙሉ በሙሉ እየተቆጣጠረ መቆየት አለበት፤ በሥራ አስፈጻሚውና በሕግ ተርጓሚው በኩል የሚያስፈልጉትን ሰዎች ከኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጭ በችሎታቸውና በሥራ ልምዳቸው እየመለመለ የምክር ቤቱ ይደልድል የሚል ነበር፤ ምክር ቤቱ ከሥራ አስፈጻሚውና ከዳኝነቱ ሥራ በላይ ሆኖ በመቆጣጠር የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ ይቻላል፤ ሁሉም ይህንን ሀሳብ በቀዘቀዘ መንፈስ ስለተመለከቱት ድሉ ቢሳካም ወደሌላ ፉክክርና ንትርክ እንደሚገባ አያጠራጥርም ነበር።

ለዚህ በቂ አመልካች የሆነው ብርሃኑ ከንቲባ ለመሆን ያደረገው ጥረት ነው፤ ዶር. አድማሱም ለዚሁ ቦታ ተፎካካሪ እንዲሆን በኢዴአፓ ይገፋ ነበር፤ ፉክክሩ ወደመጥፎ አቅጣጫ እንዳይሄድ በማለት አድማሱ ከውድድሩ እንዲወጣ አስተያየት ሲደርሰው ሳያንገራግር ተቀበለው፤ አድማሱ ዱሮውንም የሥራ ሰው እንጂ የሥልጣን ጥም ስለሌለበት ያለምንም ችግር ለብርሃኑ ለቀቀለት፤ ከአድማሱ ሌላ ይህንን ማድረግ የሚችል እንደነበረ አላውቅም።

የሆነ ሆኖ ኃይሉ ሻውል፣ ብርሃኑ ነጋና ልደቱ አያሌው የ1997 የምርጫ ፖሊቲካ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ በሚያስገርም የጋለ መንፈስ፣ ትጋትና ቆራጥነት የመሩትና ያንቀሳቀሱት ሰዎች መሆናቸው ጥርጥር

የለውም፤ ስኬታማ ሥራቸውን ያገዘው ያደረባቸው የሥልጣን ጥም መሆኑን ስንገነዘብ የሥልጣን ጥምን በጎ ጎንና አስፈላጊነት እንረዳለን፤ ችግሩ የተፈጠረውና ወደፊትም የሚፈጠረው የግል የሥልጣን ጥምን ከአገርና ከሕዝብ ዓላማ ጋር ለማጣጣም ባለመቻል ነው፤ እንደተገነዘብሁት መተባበር የሚሳናቸውም የአገርንና የሕዝብን ዓላማ ከግል ዓላማቸው ጋር ለማጣጣም ባለመቻልና የግል የሥልጣን ጥም ላይ በማተኮር የተነሣ ነው፤ መጠላለፉ የሚመነጨው ከዚህ የተዛባ የፖሊቲካ አስተሳሰብ ይመስለኛል፤ ወደመጨረሻው ላይ ወደዚህ ጉዳይ እንመለስበታለን።

አሁን ግን ቅንጅትን ማን አፈረሰው? ለሚለው ጥያቄ በአጭሩ መልስ ለመስጠት እንሞክር፤ ቅንጅትን ያፈረሱት ሦስት ኃይሎች ናቸው፤ አንደኛ የቅንጅት አመራር፣ ሁለተኛ የአሜሪካው ሲ.አይ.ኤ. የስለላ ድርጅት፣ ሦስተኛ ወያኔ ናቸው፤ ቀደም ሲል እንደገለጽሁት የቅንጅት አመራር እርስበርሱ ሲጠላለፍ ድርጅቱን አፍረከረከውና ለአደጋ የተጋለጠ አደረገው፤ በሦስቱ ሰዎች መሀከል የነበረው ሽኩቻ የተቀናጀ ዓላማ የነበረውና የተቀናጀ አሠራርን የሚከተል ድርጅትን ለመትከል አላስቻለም፤ ሁሉም በየፊናው የተለያዩ ኤምባሲዎችን ይዞ በነሱ ላይ የበለጠ እምነት አሳድሮ በመኩራራት እርስበርስ ሊኖራቸው የሚገባውን ግንኙነት ለመገንባት ፍላጎት አልነበራቸውም፤ አንዳንዴ ኤምባሲዎቹ የቅንጅትን ምክር ቤት የተኩ ይመስል ነበር፤ የቅንጅት መሪዎች ለኤምባሲዎቹ ያላቸው ቅርበት እኩል ባለመሆኑ የበለጠ ጥርጣሬን እየፈጠረ መለያየቱን አባሰው፤ የሚደንቀው የፖሊቲካ መሪዎች እንሆናለን ብለው የሚዘጋጁ ሰዎች የኤምባሲዎቹን ተልእኮ በሚገባ መገንዘብ አለመቻላቸው ነው፤ ትንሽ መረጃ በመስጠት ብዙ የሚጠብቁ ናቸው፤ ለማናቸውም መሪዎቹ ውጭ ውጩን እያዩ የውስጡን በቍከከር አደከሙት።

በቡሽ አስተዳደር ሲ.አይ.ኤ. በአንዳንድ አገሮች ያልተወሰነ ሥልጣን ተሰጥቶት ነበር፤ ለምሳሌ በአፍጋኒስታን፤ በአፍሪካ ቀንድም የሶማልያ ትርምስ ለአልቃይዳ ምሽግ ይሆናል ብለው በመስጋት፣ የኤርትራም መሪ ለአሜሪካ አልገብርም በማለቱ እነዚህን በሁለት አቅጣጫ በአፍሪካ ቀንድ የተደቀኑባቸውን ችግሮች ለመቆጣጠር ወያኔ ቁልፍ ሚና ይጫወታል ብለው ሙሉ ድጋፋቸውን ሰጡ፤ በምርጫ 97 የፕሬዚደንት ካርተር ድርጅት በላካቸው ታዛቢዎች መሀከል አለመግባባት ስለነበረ የታዛቢነቱን ሥራ በሚገባ ፈጸመ ለማለት አይቻልም፤ እንዲያውም የአውሮፓውንም ቡድን ወደማምከን ደረጃ ደረሰ፤ የቅንጅት ጠንካራ የኢትዮጵያዊነት አቋም ሲ.አይ.ኤ.ን የሚመቸው መስሎ አልታየም፤ አንድ የፈረንጆች አባባል በእጅ ያለ ወፍ በጫካ ውስጥ ካሉ ሁለት ወፎች ይሻላል፤ ይላል፤ የተረጋገጠውን መያዝ ይሻላል ማለት ነው፤ ቀጥለንም ወደሶማልያ በመዝመት የአሜሪካንን ሲጋት ተጋሪዎች ሆነናል።



ለወያኔ በውስጥም ሆነ በውጭ ያለው ሁኔታ ከተመቻቸለት በኋላ በጠነከረ የኃይል እርምጃ የቅንጅትን ግብአተ መሬት ለመፈጸም አስቸጋሪ አልነበረም፤ ወያኔም ሲ.አይ.ኤ.ን ተማምኖ የወሰደው የኃይል እርምጃ የአሜሪካንን የፖሊቲካ አካሄድ በትክክል አለመረዳቱን ያመለክታል፤ የዚህ አንዱ መግለጫው የሶማልያው ዘመቻ ከምስጋና ይልቅ ወቀሳን ያተረፈ መምሰሉ ነው፤ አፄ ኃይለ ሥላሴን በአካባቢው አገሮች በጥርጣሬ እንዲታዩ ያደረጋቸውና ብዙ ችግሮችን የፈጠረባቸው ከአሜሪካ ጋር የነበራቸው የቀረበ ግንኙነት ነበር፤ ያውም የሲ.አይ.ኤ. አልነበረም፤ ዛሬ ደግሞ የሲ.አይ.ኤ. ግንኙነት ምን ዓይነት ጣጣ እንደሚያመጣብን ለማወቅ ጊዜው ገና ነው።

ከነዚህ ሦስት ኃይሎች የትኛው ቅንጅትን ይበልጥ ጎድቶታል የሚለውን አፍታትቶ ለመመለስ ሌሎች ታዛቢዎች ወይም ራሳቸው ተዋንያኑ ሲጽፉልን ለመረዳት እንችላለን፤ ለጊዜው ግን ኃላፊነቱን በሙሉ ወያኔ ላይ ብቻ እንዳንጥለው መጠንቀቅ አለብን፤ ሌላ ቢቀር በራስ በኩል የተፈጸመውን ስሕተት መቀበል ስሕተቱ እንዳይደገም ይረዳል የሚል እምነት አለኝ፤ ወይስ ነበረኝ ማለቱ ይሻላል?

፫

# እስር ቤት
# ማእከላዊና ቃሊቲ

## 1. ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ መያዝ

ሕግና ሥርዓት ባለበት አገር በወንጀል ተጠርጥሮ የሚያዝ ሰው አንዳንድ መብቶች አሉት፤ በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት የተካተተው የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫዎች፣ ሕጎችና ስምምነቶች ሁሉ አንድ በወንጀል የተጠረጠረ ሰው ማስረጃዎች ቀርበውበት መደበኛ ፍርድ ቤት እስቲፈርድበት ድረስ ከወንጀል ነጻ ሆኖ የመቆጠር መብት እንዳለው በግልጽ ይደነግጋሉ፤ በኢትዮጵያ በተግባር የሚታየው ግን ፍጹም ሕገ መንግሥቱንና ዓለም አቀፍ ሕጎችን የሚፃረር ነው፤ ማስረጃ የሚፈለገው ተጠርጣሪው ተይዞ ከታሰረ በኋላ ነው፤ አሥር ዓመትና ከዚያም በላይ በእስር ቆይተው ፍርድ ቤቶች በነጻ የሚለቅቁአቸው በዚህ ምክንያት ነው፤ ያለፍርድ በጣም ብዙ ሰዎች ለብዙ ዓመታት በእስር የቆዩ መሆናቸው የዚሁ ሕገ ወጥ አሠራር ሌላው መልኩ ነው፡፡

ሰዎች ከቤታቸው ሲያዙ ሕጋዊ ሥርዓት እንዲኖርና መብቶቻቸውም እንዲጠበቁ ያስፈልጋል፤ ሁለት በጣም የተለያዩ አሠራሮች አጋጥመውኛል፤ መጀመሪያ በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ተይዤ ነበር፤ በአንድ መጻሕፍት ቤት ቆሜ ስመለከት አንድ ሰው መጣና መታወቂያውን ከአሳየኝ በኋላ መጥሪያ ወረቀት አሳየኝ፤ እንሂድ ብሎ ይዞኝ ሄደና በወንጀለኛ ምርመራ ውስጥ አንድ ክፍል ውስጥ አስገባኝ፤ ሁለተኛው በወያኔ ዘመን በ1992ና በ1998 የተያዝኩበት ነው፤ ሁለቱንም ጊዜ ከአሥር እስከ አሥራ አምስት የሚሆኑ የታጠቁ ወታደሮች ነበሩ፤ በ1992 የተያዝሁት አንድ የመጻሕፍት መደብር ውስጥ ቆሜ ነበር፤ ከአሥር እስከአሥራ አምስት የሚሆኑ የታጠቁ ወታደሮች በአካባቢው ተበታትነው ለጦርነት የተዘጋጁ ሆነው ሲጠብቁ ሦስት ያህሉ በመጻሕፍት ቤቱ ገብተው ይዘውኝ መኪና ውስጥ አስገቡኝ፤ በጥቅምት 22/1998 ግን እቤቴ ታምሜ ተኝቼ ነበር፤ ብርቱካንና ሙሉነህ ሊጠይቁኝ መጥተው ቁጭ ብለን እናወራ ነበር፤ በድንገት የቤቱን በር ሊያፈርስ የተቃጣ ድብደባ ሰማሁና ስከፍት ጠመንጃውን ደግኖ «ኑ ውጣ!» እያሉ ማንገላታት ጀመሩ፤ ልብሴን እንድለብስም አልፈቀዱልኝም፤ ማእከላዊ ወስደው በአንዳንድ ክፍሎች ውስጥ ቆለፉብን፡፡

በጥቅምት 22/1998 የቅንጅት መሪዎችና አባሎች፣ የነጻ ጋዜጠኞችና የመንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መሪዎች ከሕግ ውጭ በሆነ መንገድ



በየተገኘንበት ተያዝን፤ አያያዙ የፍርድ ቤትን ትእዛዝ ያላገኘ ከመሆኑም በላይ ሕጋዊ ሥርዓትን ያልጠበቀና የጦርነት ስልትን የሚመስል ነበር፤ የበሩን ደወል መደወል ባያውቁበትም በጨዋ ደንብ በሩን ማንኳኳት ይችሉ ነበር፤ ሊሰብሩት ሲደርሱ ስከፍትላቸው ጠመንጃቸውን ደቅነው ዓይናቸውን እያጉረጠረጡ ገፍትረውኝ ገብተው የለበስሁት የሌሊት ልብስ ስለነበረ ልብሴን ልለውጥ ብላቸው ከለከሉኝ፤ ሰፈሩ ሁሉ በታጠቁ ወታደሮች ተጥለቅልቆ ነበር፤ ተወሰድሁ፤ ከስድብ በቀር ዱላ አልደረሰብኝም፡፡

ሊጠይቁኝ የመጡትን ብርቱካንንና ሙሉነህንም በጉልበት ይዘው ወሰዱን፡፡

ሌሎች እንደ ዶ/ር ኃይሉ አርአያና እንደእቶ በድሩ አደም ያሉ እንደእኔ የታደሉ አልነበሩም፤ ተደብድበዋል፤ ንግሥት ገብረ ሕይወትም ራስዋ ከመንገላታትዋ ሌላ ነፍሰ-ጡር ልጅዋ ተገፍትራ ወድቃ በስጋት ላይ ነበረች፤ ሌሎች ደግሞ በተለያዩ የአካል ክፍሎቻቸው ላይ ከባድ ጉዳት ደርሶባቸዋል፤ የጭንቀት ሕመም ያደረባቸው ብዙ ናቸው፤ ሕጋዊ ሥርዓትን የሚከተል የፖሊስ ኃይል እንዲህ ያለውን ግፍ አይፈጽምም ነበር፡፡

በተያዙት ላይ ግፍ ተፈጽሟል ማለት የሕይወትን ጣዕም ገና ሳይቀምሱ በሞቱትና በጥይት አካላቸው በቆሰለባቸው ላይ የተፈጸመውን እስከፊ ግፍ አይቀንሰውም፤ ወታደሮች እኛን ለማሰር ያሳዩት ጭካኔ አያስደንቅም፡፡

## 2. ማእከላዊ

ማእከላዊ የሚባለው የወንጀል መፈልፈያ ድርጅት እንኳን በኢትዮጵያ በውጭም ዋና የግፍ መሣሪያ መሆኑ የታወቀ ነው፤ ተይዘን እዚያ ውስጥ በአንዳንድ ክፍል ውስጥ ተቆልፎብን ጠዋትና ማታ ብቻ ለመጸዳዳት እየወጣን ለብዙ ቀኖች ቆየን፤ የሚያዘው ሰው እየበዛ ሲሄድ በአንድ ክፍል ሁለት አደረጉ፤ ቆይተውም ቦታ እየጠበባቸው ሲመጣ አራትም፣ አምስትም በአንድ ክፍል ውስጥ አስገቡን፡፡

እያደር ትንሽ ሰብአዊነት ይሁን ሕጋዊነት ሲሰማቸው በቀን ለ30 ደቂቃ ጸሐይ እንድንሞቅና አካላችንን እንድንታጠብ ተፈቀደልን፤ ለእኔ የተለየ እንክብካቤ ያደርጉልኝ እንደነበር ሳልናገር ብቀር እውነቱን መደበቅ ይሆናል፤ ወንበር ሰጡኝ፤ ጸሐይም ለመሞቅ በ30 ደቂቃ አልተወሰንሁም ነበር፤ በተለያዩ ክፍሎች የታሰርነው እንዳንነጋገር በጣም ተግተው ይጠብቁና ይቆጣጠሩ ነበር፡፡ በማዕከላዊ አራት ሴቶች ነበሩ፣ አንዲትዋ ሰርካ ዓለም እርጉዝ ጋዜጠኛ ነበረች፤ ከሷ ጋር ሰብለ የምትባል የቅንጅት አባል ነበረች፤ በሌላ ክፍል ደግሞ ብርቱካንና

ንግሥት ነበሩ፤ ከቅንጅት ጋር በተያያዘ ባይሆንም ብዙ ሌሎች ሴቶች፣ አንዳንዶቹም ከሕፃን ልጆቻቸው ጋር ነበሩ፡፡

በፍርድ ቤት የቀረብነው ከብዙ ቀናት በኋላ ነበር፣ በዚህም ጊዜ ውስጥ የፍርድ ቤት ትእዛዝ አግኝተናል ብለው የማዕከላዊ የምዝበራ ቡድን ቤታችንን በርብሮ ወረቀት፣ መጽሐፍ፣ ኮምፒዩተር፣ ሲዲ፣ ዲስኬት፣ ቪድዮ፣ የዘፈን ካሴት የቀረ ነገር የለም፤ የተወሰደውን ዕቃ ሁሉ በጥንቃቄ በመያዝ ፋንታ በግዴለሽነት በያለበት ለማንም መጫወቻ በማድረጋቸው ኮምፒዩተሮችና ዲስኬቶች ተበላሹ፤ የብዙ ዓመቶች ሥራዎች ጠፉ፤ እንዲህ አድርገው ያጠፉትን ሥራ ወደ ሕንድ አገር ወስጄ በስንት ጥረትና በከፍተኛ ወጪ ጥቂቱን የጠፋውን ለማግኘት ቻልሁ፤ አለማወቅና ግዴለሽነት ተደባልቆ ሕጋዊ ሥርዓት እንዳይኖር አድርጓል፡፡

ይኸው ግዴለሽነትና ከሕጋዊ ሥርዓት ውጭ መሆን ስንያዝ የተረከቡትን ዕቃ በምሕረት ስንፈታም እንኳን ለመመለስ ፈቃደኞች አላደረጋቸውም፤ እስካሁን ድረስ (መጋቢት 2002) ዕቃዎቼን በሙሉ ገና አላገኘሁም፤ ተመላልሼ ደከመኝ፤ አንድ የተሰጠኝ ምክንያት ገና አይተን አልጨረስንም የሚል ነው፤ እግዚአብሔር ያሳያችሁ፣ ዕቃዎቹ የተወሰዱት ለክሱ ማስረጃ የሚሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ነበር፤ ፍርዱ አለቀ፤ ምርመራው ግን ገና አላለቀም ማለታቸው ነው፤ ፍርዱ ከተሰጠ በኋላ ምርመራ ምን ማለት እንደሆነ ለማስረዳት ብሞክር ለመግባባት አልቻልንም፤ የሕግ አስገዳጅንት በእነሱ ላይ እንደማይሠራ ያመለክታል፤ ጉዳያችን በፍርድ ቤት ከአለቀ በኋላ፣ እኔም ከቃሊቲ ከወጣሁ በኋላ ዕቃዬን ለመመለስ ፈቃደኞች አለመሆናቸው ከጉልበት ሌላ ምንን ያሳያል?

ከላይ እንደገለጽሁት ከተመለሰው ውስጥ አንዱ ብዙ ጽሑፎችን በአማርኛም በእንግሊዝኛም የብዙ ዓመታት ልፋት ይዞ የነበረው ኮምፒዩተር፣ ሆን ተብሎ ይሁን ባለማወቅ ድራሹ ጠፍቶ አገኘሁት ለጸረ እውቀትነት በቂ ማስረጃ ነው፡፡

ጠባቂዎቻችን ከላይ እስከታች አብዛኞዎቹ ተጋዳላይ የነበሩ ወያኔዎች ናቸው፤ ወያኔ መባልን አይወድዱም፤ መለያ የወታደርም ሆነ የፖሊስ ልብስ በሥርዓት አይለብሱም፤ በመሀከላቸው የሥልጣን ተዋረድን የሚያሳይ ምልክት የለም፤ እንዲህ የሆነው ለምንድን ነው ብዬ ስጠይቅ አንዱ እንደነገረኝ ማዕርግ አላቸው፤ እነሱ እርስበርሳቸው ይተዋወቃሉ፤ ነገር ግን ማዕርጉን ማድረግ ያሳፍረናል አለኝ፤ የሚያፍሩበትን ምክንያት ለመረዳት አስቸጋሪ አይደለም፤ ከማዕርግ ጋር የሚፈለጉ እነሱ የሌሏቸው ብዙ ነገሮች አሉ፤ አብዛኞዎቹ ጠባቂዎች በበኩሌ ክፉ የምላቸው አልነበሩም፤ ሰውን እንደከብት የሚያዩ ከእጃቸው የማስፈራሪያ ዱላ የማይጠፋ፣ የሲአል ኢጋፋሪ መስለው ትከሻቸውን



የሚያሳብጡ ጥቂቶች ነበሩ፤ ከነዚህ ጥቂቶች ውስጥ የጎንደርና የወሎ ገባሮች ከወያኔዎቹ በጣም የባሱ ነበሩ፡፡

ከማዕከላዊ ወደፍርድ ቤት በምንሄድበት ቀን ማዕከላዊ ያለበት ሰፈር ብቻ ሳይሆን እስከፍርድ ቤት (ስድስት ኪሎ) ድረስ ይሸበር ነበር፤ የሚወጣው የጦር ኃይል ከነትጥቁ ለማንና ለምን ዓላማ እንደሆነ አይታወቅም፤ ምናልባትም ቅንጅት የታጠቀ ሠራዊት ያለውና እኛን ለማስፈታት የሚሰማራ በማስመሰል ያላቸውን ስጋት ለማስተጋባት ይሆናል፤ ለማናቸውም የሚወጣው ገንዘብ፣ የሚቃጠለው ቤንዚንና የሚንገላታው የሰው ኃይል በጣም ከፍተኛ ነበር፣ በመንገድ ላይም የሚታመሰው ትራፊክ የሚያሳዝን ነበር፡፡

ፍርድ ቤት ከደረስን በኋላ በፍርድ ቤቱና በማዕከላዊ መሀከል ያለውን ልዩነት ለመረዳት ያስቸግር ነበር፤ በፍርድ ቤቱ ውስጥ የፈለጋቸውን ዓይነት ትእዛዝ እየሰጡ የሚያምሱን የማዕከላዊ ወታደሮች ነበሩ፤ በፍርድ ቤት አቤቱታ ሲቀርብባቸውም ቂማቸውን ለመወጣት ይሞክሩ ነበር፤ በመጨረሻም የእኛ ነገር ሲሰለቻቸው በድንገት ተነሥተው ዕቃችሁን አዘጋጁ ብለው፣ ከባድ መኪና አቅርበው እንዲጫን አደረጉ፤ የተጫነውን ዕቃ እንደያዝን ፍርድ ቤት ቀረብንና ከማዕከላዊ እንድንወጣላቸው አመለከቱ፤ «መኖና ህክምና ወዳለበት» እንድንወሰድ ትእዛዝ ተሰጠ፡፡

## 3. ቃሊቲ

ቃሊቲ የገባነው ልክ ከማእከላዊ ስንመጣ እንደነበረው በተዘበራረቀና ሥርዓት በሌለው መንገድ ነበር፤ እንደምንም ተብሎ ማታ በተለያዩ ክፍሎች ተደለደልን፤ የገባንበት ቦታ የደርግ አባሎችና ከነሱ ጋር የነበሩ ሰዎች የታሰሩበት ነበር፤ ጥቂቶቻችን የገባንበት ቤት በደህና ጊዜ የትምርት ቤት የነበረ የግምብ ቤት ነበረ፤ ሌሎች ደግሞ ቆርቆሮ በቆርቆሮ ሆኖ በተሠራ በመደበኛ የቃሊቲ እስር ቤት ነበር፤ደርግ እስር ቤቶችን ወደትምህርት ቤት ለውጦ ነበር፤ አሁን ትምህርት ቤት ወደ እስር ቤት ተለውጦ ማየት ምን ያህል የሚያሳዝንና አገሪቱ ያለችበትን ሁኔታ በጉልህ የሚያሳይ መሆኑን ከመግለጽ በላይ ሌላ አስፈላጊ አይደለም፤ እስረኞቹ በደንብ ተቀብለውን በተቻለ መጠን እንዲመቸን ለማድረግ ሞክረዋል፡፡

የእስር ቤቱ አልጋ ከላይና ታች ሁለት ሰዎች እንዲያስተኛ ሆኖ የተሠራ ነው፤ በአብዛኛው የተጨናነቀ ነው፤ በግቢው ውስጥ ሁላችንም የምንጠቀምባቸው ሦስት የቁም መታጠቢያዎች አሉ፤ ሽንት ቤቱ ከፊትና ከኋላ ሆኖ አሥር ሰዎች ሊጠቀሙበት እንዲችሉ ተደርጎ የተዘጋጀ ነው፤ በዚህ ሽንት ቤት ለመጀመሪያ ጊዜ የሰማሁት አንድ ቃል ጡሊ ነው፤ ጡሊ በጠርሙስ ውሃ ሲሆን ልክ ዱሮ በልጅነቴ ሴቶች ሜዳ ሲወጡ የሚይዙት ውሀ ዓይነት ሲሆን፣

ሆኖም የሚታጠበው ይለያያል፤ በመታጠቢያውም ሆነ በሽንት ቤቱ ወረፋ ነበረ፤ ግን በእስረኞች መሀከል ያለው መተሳሰብና ሥነ ሥርዓት ለማንም ብዙ ችግር ሲፈጥር አላየሁም፤ የእስረኞቹ የፈጠራ ሥራ የሆነ የሽንት ቤት መቀመጫ ሌላም ቦታ ሊለመድም የሚገባው ይመስለኛል፤ በታጣፊ የብረት ዘንግ ሽራ ተሰፍቶበት መቀመጫ ይሠራል፤ ሽራው መሀሉ ላይ ይቀደድና ለሽንት ቤት መቀመጫ ያገለግላል፤ በማንጠልጠያ ይሰቀልና በሚፈለግበት ጊዜ ዘርግቶ መቀመጥ ነው፤ ለሽማግሌዎችና ለበሽተኞች በጣም አስፈላጊ ነው፤ ለእኔ እንዲህ ያለውን መቀመጫ አሠርቶ የሰጠኝ አንድ እስረኛ ኮሎኔል ነው፤ በዚህ መጀመሪያ በተሰማራንበት ግቢ ከነበሩት እስረኞች ጋር (የደርግ አባሎችም ነበሩበት) ጥሩ መግባባት ፈጥረን በተቻለን መጠን ያለፈውን ታሪክ ለመማር እንጥር ነበር።

የደርግ ሰዎችና የእኛ መግባባት አሳሪዎቻችንን ማቃዠት ጀመረ፤ በዚህም ምክንያት መጀመሪያ ሻምበል ፍቅረ ሥላሴ ወግደረስንና ኮሎኔል ካሣዬ አራጋውን ከዚያ ግቢ በድንገት አስወጥተው የእስረኛው ቁጥር ወደበዛበትና ወደተጨናነቀበት ግቢ ወሰዱአቸው፤ ቀጥለውም እኛን በአሉት ግቢዎች ሁሉ በታተኑን፤ አልፎ አልፎም ሲያስኙቸው እንደፈለጉ ይበውዙን ነበር፤ እንደሰማሁት ሻምበል ፍቅረ ሥላሴና ኮሎኔል ካሣዬ በተሰደዱበት የእስረኞች ክፍል እንደተፈለገው አልተጎዱም፤ እስረኞቹ በክብርና በመንከባከብ ይዘዋቸው እንደነበረ ሰምቻለሁ፤ ዓላማው ባለመሳካቱም ይሆናል ከጥቂት ጊዜ በኋላ ወደነበሩበት ተመለሱ።

መጨረሻ ላይ እኔ የነበርሁበት ግቢ ከሰማንያ እስከ አንድ መቶ ሰዎች ነበሩበት፤ አምስት የመኝታ ክፍሎች ነበሩት፤ በእያንዳንዱ ቤት መታጠቢያና ሽንት ቤት አለው፤ ቴሌቪዥን አለው፤ ሁሉም እስረኛ ፍራሽና ብርድ ልብስ አለው፤ አብዛኛው እስረኛ አልጋ አለው፤ ይህ ሁሉ በእስረኞች ገንዘብና ጉልበት፣ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ድጎማ የተገኘ አገልግሎት ነው፤ ጠዋት ዳቦና ሻይ፣ ለምሳና ለራት አንድ አንድ እንጀራና ዶዮ ይሰጣል፤ ሥጋ በአሥራ አምስት ቀኖች አንድ ጊዜ ነበር፤

በኋላ ግን ቀረ፤ አትክልት የሚባል ነገር በምግብ ውስጥ አለመኖሩ አስገርሞኝ ለማጣራት ብሞክር እስረኞቹ ራሳቸው የወሰኑት መሆኑን ተረዳሁ፤ ዴሞክራሲ መሆኑ ነው፤ ዓይነቱ ከሚፈለገው በታች ቢሆንም ብዛቱ ግን የሚያጠግብ ነበር፤ እንዲያውም በየቀኑ እየተረፈ የሚጣለው እንጀራ፣ ዳቦና ወጥ እስር ቤቱን የጥጋብ አገር የሚያስመስለው ነበር፤ አንድ ጎበዝ የሆነ እስረኛ ያልተነካካውን እንጀራና ዳቦ ድርቆሽ እያደረገ ለውጭ ገበያ ያቀርብ ነበር፤ ሰውዬው ለፍቶ ያገኘውን ያልሠሩት በግማሽ ይካፈሉት ነበር፤ በእስር ቤቱ ውስጥ የመሬት ኪራይ አለ፤ የቤት ኪራይ አለ፤ ታክስ አለ፤ የሙስና ሐሜትም አለ።



እኔ በነበርሁበት ከቤቶቹ የተረፈው ግቢ ከሁለት መቶ ሜትር ካሬ የሚበልጥ አይመስለኝም፣ ቤቶቹ ሁሉ ቆርቆሮ ስለሆኑ ሙቀቱ ቀን ቤት ውስጥ ገብቶ ለማረፍ አያስችልም፤ ስለዚህ ከበሽተኞች በቀር እስረኛው ሁሉ የሚውለው ውጭ ነው፤ በአሥራ አንድ ሰዓት ተኩል ግድ በየክፍላችን አስገብተው ከውጭ እስቲቆልፉን ድረስ የምንውለው በውጭ ነው፤ እሳት ቢነሳ ተጠብሶ ማለቅ ነው፤ ቁልፉ ብረት በመሆኑ እሳት ሲያግለው እሱን ይዞ ለመክፈት አስቸጋሪ ይሆናል።

በግቢው ውስጥ ብዙ ዓይነት አገልግሎቶች አሉ፤ልብስ ማጠቢያ አለ፤ የፈለገ ራሱ ያጥባል፣ ያልፈለገ ከፍሎ ያሳጥባል፤ እኔ በነበርሁበት ግቢ ውስጥ ልብስ የሚያጥቡ በጣም ጥሩ ሰዎች ነበሩ፤ ታሪካቸው ያሳዝናል፤ አንዱ ወርቁ ይባላል፤ የጎጃም ሰው ነው፤ ባለትዳር ሆኖ አንዲት በጣም የሚወዳት ሴት ነበረች፤ ወዳጁ ሌላ ወንድ ወደደች፤ ወርቁ ተናደደና አርዶ ገደላት፤ ፈረንሳዮች የፍቅር ወንጀል የሚሉት መሆኑ ነው፤ ሚስቱ ዛሬም ቀለብ ታቀብለዋለች፤ እሱም የሚያገኘውን ገንዘብ ይሰጣታል፤ ወዳጁን በመግደሉ ያደረበት ጸጸት በጣም ጥልቅ ነው፤ ሌላው ልብስ አጣቢ ኩማ ይባላል፤ የሸዋ ሰው ነው፤ አንዲት ኮረዳ ያእንጀራ ልጅ ነበረችው፤ እሱ እንደሚለው ከጎረምሳ ጋር ማምሸት ስትጀምር ለመቆጣትና ለመቆጣጠር ይጀምራል፤ የእንጀራ ልጁና ወዳጁዋ ይሰማሙና ኩማን አስገድዶ በመድፈር ይከሱታል፤ ይፈረድበታል፤ የሚያውቁት ሰዎች እንደሚናገሩት ሲገባ በጣም እያለቀሰ እግዚአብሔርን ያማርር ነበር፤ እንዴት ባላደረግሁት ነገር ሲፈረድብኝ እግዚአብሔር ዝም ይላል ብሎ ያለቅሳል፤ ከመበሳጨቱም የተነሳ ሃይማኖቱን ለውጦ እንደእስላም ቆብ ማድረግ ጀመረ፤ ልብስ የሚተኩስልን ሁሴን ነበር፤ ሁሴን የእስበ ተፈሪ ሰው ነው፤ በባቡር ሀዲድ ላይ በምብ ቀብረሃል ተብሎ የተያዘና የተፈረደበት ነው፤ ሃይማኖተኛ ነው፤ ወርቁ፣ ኩማና ሁሴን ንጹሕ ልብ ያላቸው በጣም ጥሩ ሰዎች ናቸው፤ ፀጉር ቆራጭ አለ፤ ቡናና ለስላሳ መጠጦች መግዛት ይቻላል፤ የከረምቦላ መጫወቻ አለ፤ የተለያዩ የእንጨት ሥራዎች ሚዶ፣ መስቀል፣ የመስተዋት መያዣ፣ ከዘራ በጣም በሚያስደንቅ ሁኔታ ከአምስት መቶ ዓመት በፊት በሚሠራበት መሣሪያ ዓይነት ይለፋሉ፤ ለሰውነት ማጠንከሪያ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ሁሉ ቁጥጥር አለባቸው፤ በተለይም በርከት ያሉ እስረኞች በአንድ ላይ የሰውነት እንቅስቃሴ ሲሠሩ አንዳንድ ጠባቂዎች የሚናደዱ ይመስላል፤ አንዳንዴም ይከለክላሉ።

በሁሉም የቅንጅት አባሎች ላይ ባይሆኑም በአጠቃላይ የቅንጅት እስረኞች በተባሉት ላይ የተለየ አመለካከት አለ፤ ከሌሎች እስረኞች ጋር እንዳይቀራረቡ ለማድረግ ጥረት ይደረጋል፤ ከቅንጅት እስረኞች ጋር የተሻለ ግንኙነት ያላቸውን እስረኞች ወይ ወደሌላ ግቢ ወይ ወደዝዋይ ማዘዋወር በተደጋጋሚ የታየ ነው፤ ሆኖም ሌሎች እስረኞችን ከቅንጅት ለማራቅ

አልተቻለም፤ አብረን እያደርን፣ አብረን እየዋልን መተዋወቅና መቀራረብ የማይቀር ነበር፤ ከእስረኞች መሀከል ሰላዮች እንዳሉም የታወቀ ነው፤ ከእስረኞቹ መሀከል እየተመረጡ የግቢው አለቃ፣ የቤት አለቃ፣ የህክምና ሹም፣ የሥነ ሥርዓት ሹም እየተባሉ ይሾማሉ፤ ከነዚህም መሀከል አንዳንዶቹ የፋሺስትነት ጠባይ የሚያሳዩ ናቸው::

የእስረኞቹ ወንጀል የተለያየ ነው፤ ሚስቶቻቸውን ወይም ወዳጆቻቸውን በተለያየ መንገድ የገደሉ ወይም ያቆሰሉ፣ በጠብ ሰው የገደሉ፣ የዘረፉ የወያኔ ፖሊሶችና ሌሎች፣ በአስገድዶ መድፈር የታሰሩ ሽማግሌዎች፣ ካህናትና የአካል ጉዳተኞች፣ የአነግ አባሎች የተባሉና ሌሎችም ነበሩ፤ ብዙዎቹ ፍርድ ሳያገኙ ለዓመታት ታስረው የቆዩ በመሆናቸው በሚፈረድባቸው ጊዜ ወይ ቅጣታቸውን ጨርሰዋል፣ ወይም ትንሽ የሚቀራቸው ናቸው፤ ከእስረኞቹ ለመረዳት እንደሚቻለው ለተከሰሱበት ወንጀል ማስረጃ የሚፈለገው ከተያዙ በኋላ ነው፤ በአስገድዶ መድፈር (በሕፃናት ላይ ሳይሆን) የተከሰሱትን የአካል ጉዳተኞች ያየ በጣም ግራ ይገባዋል፤ የአስገድዶ መድፈር ትርጉሙ ይጠፋል፤ አንዱ የቀድሞ ወታደር ፈንጂ ላይ ወጥቶ ከወገቡ በታች በድን ሆኖበት በሁለት ምርኩዝ እየተሰቃየ የሚንቀሳቀስ ነው፤ እሱ እንደሚለው ከእኅቱ ጋር ይኖር ነበር፤ ውጣልኝ አልወጣም በሚል ተጣልተው ሳለ ሠራተኛዋን ደፍረሃል ተብሎ ይከሰስና ይታሰራል፤ ሰውዬውን በአካል ያየ ይህንን ወሬ ለማመን አይችልም::
አጠገባችን አንድ ክሊኒክና የመድኃኒት ማደያ አለ፤ ለድንገተኛም ሆነ ሌላ ሕመም በመጀመሪያ ወደዚህ ክሊኒክ መምጣት ያስፈልጋል፤ ነገር ግን ብዙ ውጣ-ውረድ አለበት፤ በመጀመሪያ ስምን ማስመዝገብ ከዚያ መጨቅጨቅ ግዴታ ነው፤ እንደምንም ከሊኒኩ ከተደረሰ አንዳንዴ ሀኪሞች ይኖራሉ፤ አለዚያም ነርሶቹ ያስተናግዳሉ፤ እኔ እንዳየኋቸው ነርሶቹም ሆኑ ሀኪሞቹ ጥሩዎች ናቸው፤ አንዳንዴ አስፈላጊ ሲሆን ወደፖሊስ ሆስፒታል እንወሰዳለን፤ እኔ ፖሊስ ሆስፒታል የሄድሁት እንዴት እንደሆነ አላስታውስም፤ በአምቡላንስ ነው ይላሉ፤ ግን እንደሚመስለኝ አንድ አሮጌ ላንድሮቨር ሳይሆን አይቀርም፤ አሥር ቀን ያህል ተኝቼ ደንበኛ ህክምና አግኝቼ ሀኪሙ ለመውጣት ገና ነህ ሲለኝ አሻፈረኝ ብዬ ወደቃሊቲ ተመለስሁ፤ ምክንያቱም በከንዴ ግሉኮዝና መድኃኒት እየተሰጠኝ ተኝቼ ጠባቂዎቹ አልጋውን እየወረሩ ስላስቸገሩኝ ከነሱ ጋር ከመጨቃጨቁ ቃሊቲ ይሻለኛል በማለት ነበር፤ እንዳጋጣሚም ይሁን በእቅድ የጠባቂዎች አለቃ ሆኖ የመጣው ወደከፋቱ የሚያዘነብል ነበር::

የእስረኞቹ ሕመም የተለያየና የሚያሰቅቅ ነው፤ የሳንባ በሽታ፣ የኤች.አይ.ቪ ኤይድስ፣ የአስም ሕመምተኞች በብዛት አሉ፤ ሌሊት ሌሊት የሚሰማው ፃዕርና ስቃይ እንቅልፍ አያስወስድም፤ አንዳንዶቹም ሌሊቱን የሚያድሩ አይመስሉም፤ እኔ በመጨረሻ የነበርሁበት ግቢ ስንገባ የአይጥ



ሠራዊት እንዲቀበለን የታቀደ ይመስል ነበር፤ በወለሉ ላይ፣ በግድግዳው ላይ፣ በጣራው ላይ፣ በተኙ ሰዎች አፍንጫ ላይ ጭምር እንደልባቸው ይንሸራሸሩ ነበር፤ በተደጋጋሚ አቤቱታ አቅርበን አንድም ነገር አልተደረገም፤ እኛ መድኃኒት ገዝተን ለማስመጣትም ስንጠይቅ የነበረው ውጣ ውረድ ብዙ ጊዜ የፈጀ ነበር፤ በመጨረሻም በመከራ መድኃኒት ብናስገባ ለቅመን እንድናስረክብ ተገደድን፤ አስተሳሰቡን መረዳት ያስፈልጋል፤ ዓይጦቹ በሚያመጡት የተለያየ በሽታ ብንሞት ምንም አይደለም፤ ነገር ግን ድንገት በመርዙ ሰው ቢሞት መጥፎ ነው፤ የአይጦቹ አደገኛነት የተረጋገጠ ሲሆን ሰው በአይጥ መርዝ የመሞቱ ዕድል በጣም ያነሰ ነው ብሎ ማሰብ ከባድ ሆነባቸው::

በተለያየ ደረጃ የሚገኙ የአእምሮ ሕመምተኞችም አሉ፤ የእነዚህ ሕመምተኞች ሁኔታ በጣም የሚያሳዝን ነው፤ እየተባባሰ የሚሄድ ነው፤ ምንም የሚደረግላቸው ነገር የለም፤ አቶ በላቸው የማይጨው ሰው ናቸው፤ ሽማግሌ ናቸው፤ እሳቸው እንደሚሉት የቀበሌ ቤት ውስጥ ሲኖሩ ጎረቤቶቻቸው ቤታቸውን ለራሳቸው ይፈልጉትና ለቅቀው እንዲሄዱላቸው በተለያየ ተንኮል ቢሞክሩአቸውም የማይበገሩ ሆኑ፤ በጠብ እንደፈለጓቸው ሲያውቁ ከመርካቶ ቦምብ ይገዙና (ሚርካቶ ቦምብ መሸጡን አላውቅም ነበር) እንዳሰቡት ሲመጡባቸው ቦምባቸውን ወርውረው ከአንድ በላይ ሰው ይገድላሉ፤ ይህ ከመሆኑ በፊት ከቀበሌ እስከፍርድ ቤት አመልክተዋል፤ አሁንም ቢሆን እሳቸውን ለማጥቃት የሚጥሩ ሰዎች በሚያድሩበት ክፍል ውስጥ አሉ ብለው ያምናሉ፤ ዛሬም በቦምቡ ፋንታ ድንጋይ ይወረውራሉ::

ሕግ አስከባሪ ወይም ዳኛ የነበሩ ሰዎች ሲታሰሩ ቅጣታቸው እጥፍ ድርብ ነው፤ እስረኞቹ ሲመች ይመቷቸዋል፣ አለዚያ ነጋ ጠባ በስድብ ውርጅብኝ ናላቸውን ያዞሩባቸዋል፤ እኔ በነበርሁበት ግቢ አንድ ዳኛ የነበረና አንድ አቃቤ ሕግ የነበረ ሁለቱም አእምሮአቸው ትክክል አልነበረም::
እስረኞች ሁሉ ክርስቲያኖችም ሆኑ እስላሞች በጣም ጸሎተኞች ናቸው፤ አንዳንዶቹ ሌሊቱንም ቀኑንም ይጸልያሉ፤ ነገር ግን ማረሚያ ቤት እየተባለ በሚጠራው እስር ቤት አንድም ቀን በእዘቦትም ሆነ በበዓል አንድም ካህን ብቅ አለማለቱ የቤተ ክርስቲያንና የቤተ እስልምናን የመንፈስ ደረጃ የሚያመለክት ይመስለኛል፤ በዚህም ምክንያት ብዙ እስረኞች በሠሩት ወንጀል ለመጸጸትና ሕይወታቸውን ለማደስ ዕድሉም የላቸው፤ ምናልባትም ብዙዎቹ በወንጀል እየሠለጠኑ ይወጣሉ ለማለት ሳይቻል አይቀርም፤ በራሴ ላይ የደረሰውን ብቻ ለመናገር አንድ ጊዜ ግርግዳ ላይ የተንጠለጠለ የስፖርት ልብሴን ተሰረቅሁ፤ በሌላ ቀን ደግሞ ‹ሀብት ምንድን ነው?› በሚል ርእስ የጻፍሁት ሁለት ደብተሮች ሙሉ ተሰረቀ፤ ሁለቱንም ስርቆቶች አመልክቼ ነበር፤ አንድ ጣት ያንቃነቀ አልነበረም፤ የደብተሮቹ እንኳን ይገባኛል፤ ነገር ግን በመጨረሻ ስንወጣ በመዝረፍ ይሁን በውርስ ስም አላወቅሁም ብዙ ዕቃዎች እንዳስቀሩብኝ ስረዳ

በዚህ መንገድ ደመወዝ የሚከፈላቸው ይኖሩ ይሆናል ብዬ ጠረጠርሁ፤ አንድ በዘራፊነት የተያዘ ወጣት ከአሁን ወዲያ ከሀምሳ ሺህ ብር በታች አልሞክርም ሲል ሰምቼዋለሁ።

ማረሚያ ቤት የሚባለው በመንፈሳዊ ተግባር በኩል ፍጹም ባዶ መሆኑ ከሌሎች በጎ ተግባሮችም ባዶነት ወይም ደካማነት ጋር የተያያዘ ነው፤ ማናቸውንም ዓይነት ትምህርት ማበረታታት አይታይም፤ እንዲያውም ለትምህርት እንቅፋትን መፍጠር ባህል የሆነ ይመስላል፤ ኦሮምኛ ለመማር የፈለጉ እስረኞች ተሰባስበው ቢጠይቁ ቦታ የለም ተብለዋል፤ እስረኞቹ የጠየቁት ቦታ ይሰጠን ብለው አልነበረም፤ የትም ቦታ ተቀምጠው መማር ይችሉ ነበር፤ የመጻሕፍት ቤት አለመኖር ሌላው የትምህርት ማበረታታት ፍላጎት አለመኖሩን የሚያመለክት ነው፤ መጻሕፍት ከውጭ ለማስገባት እንኳን ብዙ ችግር አለ፤ በደርግ ዘመን የእስር ቤቱ ለብዙ ዓመታት በሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና በኢትዮጵያ አንደኛ ይሆን እንደነበረ የታወቀ ነው፤ ከዚያም በላይ ብዙ ሰዎች የተለያዩ ቋንቋዎችን፣ ኢኮኖሚክስና ታሪክ ተምረው የወጡ ሰዎች አሉ፤ ዛሬ ይህ የማይቻለው ለምንድን ነው? ጸረ እውቀት በመሆን ብቻ ነው።

እንቅፋት የሚያጋጥመው ለመደበኛ ትምህርት ብቻ አይደለም፤ ብዙ እስረኞች ሥራ ከመፍታት ብለው የተለያዩ የእጅ ሙያዎችን ለመማርና አንዳንድ የገቢ ምንጭ የሚሆኑ ዕቃዎችን ለመሥራት ይሞክራሉ፤ እርዳታና ማበረታታት የሚባል ነገር የለም፤ እንዲያውም አንዳንዴ የራሳቸውን የእስረኞቹን መሣሪያ ይነጥቃሉ፤ እነዚህ ሰዎች በእስር ቤት እስካሉ ድረስ በትንሹም ቢሆን ቤተሰቦቻቸውን ለመደጎም ቢችሉ፣ በተጨማሪም አንድ የእጅ ሙያ ቀስመው ቢወጡ ደህነትን መቀነስ አይሆንም እንዴ?

ቃሊቲ በሳምንት ሁለት ቀኖች እንደበዓል ይቆጠራሉ፤ ቅዳሜና እሁድ፤ አብዛኛው እስረኛ ቅዳሜና እሁድ በጠዋት ተነሥቶ ተጣጥቦና ተኳኩሎ የክቱን ለብሶ ስሙ እስኪጠራ ይጠብቃል፤ ይህ ሁሉ መቸገር ለዘመዶችና ለወዳጆች ሳይሆን ጠላቶች ደስ እንዳይላቸው ነው ይላሉ፤ ዘመድ ወዳጅ ያለው በነሱ አማካይነት ስሙ እየተጠራ ወደጉብኝቱ ቦታ ይሄድና ያገኘውን ተቀብሎ ይመጣል፤ ከዘመድ ወዳድ የሚያገኘውን ብቻውን የሚበላ እስረኛ የለም፤ ሊተላለፍ የማይችለው የዘመድ ወዳጅ ፍቅርና አሳቢነት ነው፤ ዘመድ ወዳጅ የሌላቸው የሚናፍቃቸውና ቅር የሚላቸው ፍቅር የሚሰጣቸው ማጣታቸው ነው፤ አብዛኞዎቹ እንዲህ ያሉ እስረኞች ዋናው የችግራቸው ምንጭ ከተወለዱበትና ከአደጉበት አካባቢ በጣም ርቀው በመገኘታቸውና ደሀዎች በመሆናቸው ነው፤ የተባበሩት መንግሥታት ውሳኔ ማንም ሰው ዘመዶች ባሉበት አካባቢና ከመኖሪያው ባልራቀ ቦታ እንዲታሰር ያዛል።



ቅዳሜና እሁድ ከዘመድ ወዳጅ የሚመጣ ምግብም ሆነ ሌላ ዕቃ ደንብና ሥርዓት ባለው መንገድ የተደነገገና ጠባቂዎች ሁሉ በአንድ ዓይነት መንገድ የሚሠሩበት ሁኔታ የለም፤ አንዱ ወታደር የፈቀደውን ሌላው ይከለክላል፤ ብዙ አስቂኝ ምሳሌዎችን ማምጣት ይቻላል፤ አንዳንድ ዕቃዎች በመጠየቂያው በኩል አይገቡም ይባላል፤ ለምሳሌ መጻሕፍትና ልብስ፤ አንዳንዱ ገንዘብ መቀባበል ይፈቅዳል፤ ለአንዳንዱ ደግሞ በርከት ያለ ገንዘብ ያየ እንደሆነ ዓይኑ ይቀላና ተቆጥቶ ይከለክላል፤ በጠባቂዎቹ መሀከል የማዕርግ ልዩነት መኖሩን ለማወቅ አይቻልም፤ ሁሉም እንደሹም ይወስናል፤ ሁሉም ውቃቢው እንዳዘዘው ደንብ ያወጣል፤ ለምሳሌ በሕገ መንግሥትቱም ሆነ በማረሚያ ቤቱ ደንብ በአማርኛ ወይም በትግርኛ ተነጋገሩ የሚል ሕግ የለም፤ አንዳንዶች በሌላ ቋንቋ እንዳትነጋገሩ እያሉ ያስፈራራሉ፤ እንደዚህ የሚያደርጉት አለማወቃቸው የሚጋባ እየመሰላቸው ወደሌላው ለማስተላለፍና በእነሱ የተወሰነ ሥልጣን ቁጥጥሩን በማጠንከር የበላይነት ያገኙ እየመሰላቸው ነው።

በመጠየቂያው ሰዓት የሚታይ አንድ የሚያስገርም ደንብ መሳይ ነገር አለ፤ በተለያዩ ግቢዎች የሚኖሩ እስረኞች በተርታ ቆመው ጠያቂው የሚፈቀድለት ያአንድ ግቢ ነዋሪዎችን ብቻ ነው፤ ምናልባት ወሬ እንዳይቀባበሉ ፈርተው ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን እያንዳንዱ እስረኛ ከጠያቂዎች ጋር በሚነጋገርበት ጊዜ ቢያንስ ሁለት ጠባቂዎች አጠገቡ አሉ፤ በዚህ ሁኔታ ምን መረጃ ነው ማስተላለፍ የሚቻለው? አንድ ጠያቂ በመደዳ የቆሙ እስረኞችን ለመጠየቅ በተለያዩ ቀኖች ለእያንዳንዱ እስረኛ መምጣት አለበት ማለት ነው፤ ከፋት ነው ወይስ ፍርሃት እንዲህ የሚያደርጋቸው? ጥያቄው ለሥርዓቱ ነው፤ ጠባቂዎቹማ የሥርዓቱ አገልጋዮች ናቸው፤ ሰዎች ናቸው፤ ኑሮአቸው ነው።

*«በሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች እንዳይገለፅ በሕግ ወይም በግልፅ በተሰጠ ውሳኔ የተከለከለ ካልሆነ በቀር የሕግ አውጭን፣ የአስተዳደር ወይም የፍርድ ባለሥልጣኖች የእውነተኛና የትክክለኛ ክርክሮች ወይም ውሳኔዎች ፀሐፊ፣ አሳታሚ፣ ወይም በሕግ መገናኛ ዘዴ አቅራቢ የሆነው ሰው በወንጀል ተጠያቂ አይሆንም፡፡* የማይደፈር ሙብት በሚል ርእስ ስር አንቀጽ 47 (የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ 1997 ዓ.ም.)

# ፱
# ክስና ፍርድ ቤት

*"«...ወደአራዊትነት የለወጣቸው የተቀመጡበት ሥልጣን ነው፡ የለም፤ ሰው ነን ሰብአዊ ነን ቢሉ ሥልጣኑ አንጥሮ"ይጥላቸዋል፡፡» ሪፖርተር*

## 1. መግቢያ

ከላይ የተጠቀሱት ሁለት ዓረፍተ ነገሮች በጋለ ንዴት ላይ ያለ ሰው እንደጻፋቸው ይታወቃል፤ ሆኖም ሁለቱም ዓረፍተ ነገሮች ሁለት የተለያዩ ግን ሊገናኙ የሚችሉ መሠረታዊ ቁም ነገሮችን ይዘዋል፤ አንደኛው ሥልጣን ሰውን ወደአራዊትነት በጣም ሊለውጥና ሊያበላሽ እንደሚችል የሚገልጽ ነው፤ ሁለተኛው ሰው መሆንን ከሥልጣን ጋር አጋጭቶ ያሳየዋል፤ በሁለቱም ዓረፍተ ነገሮች የተገለጹትን ሀሳቦች ለእኔ እንደገቡኝ ለማብራራት እሻለሁ፤ ሥልጣን በመሠረቱ ሕጋዊ ነው፤ ስለዚህም ሰውን ወደአውሬነት አይለውጥም፤ ሰውን ወደ አውሬነት የሚለውጠው ሥልጣን ሳይሆን ጉልበት ነው፤ ጉልበት የሕገ አራዊት መሠረት እንደሆነ ሁሉ ሕግ ለሰው የሥልጣን መሠረት ነው፤ አራዊት በሕገ አራዊት ይመራሉ፤ ሰዎች በሕጋዊ ሥልጣን ይመራሉ፤ ሰዎች በማን አለብኝነት በጉልበት ሲጠቀሙ ወደአውሬነት ይለወጣሉ፤ ሕጋዊ ሥልጣናቸውን በጉልበት ወደ ሕገ አራዊት ይለውጡታል፤ ስለዚህም ለማለት የሚቻለው ሰዎቹ ሥልጣናቸውን ወደ ሕገ አራዊት ለወጡት እንጂ ሥልጣኑ ሰዎቹን ወደአራዊትነት አልለወጣቸውም፤ አራዊትነት ከሥልጣን ቀድሞ የነበረ ባሕርይ ነው ማለት ነው፡፡



ሰብአዊነትና ሥልጣን አብረው አይሄዱም የሚለው ዓረፍተ ነገርም አጣርተን ልንገነዘበው የሚገባን ዋና ቁም ነገርን የያዘ ነው፤ ሰብአዊነትና ሕጋዊ ሥልጣን ሁልጊዜም አብረው ይሄዳሉ፤ አብረው የማይሄዱት ሰብአዊነትና ጉልበተኛነት ወይም ሕገ አራዊት ናቸው፤ ስለዚህም በዓረፍተ ነገሩ የተገለጸው ሀሳብ ለእኔ እንደመሰለኝ ሥልጣንን በሕጋዊነት ለመጠቀም የሚፈልግ ሰው የሥልጣን ቦታን ማግኘት አይችልም የሚል ነው፤ ትክክል አይመስለኝም፡፡

የሥልጣንን ትርጉም በሕጋዊነት ተቀብለን ከጥሬ ጉልበት ወይም ከሕገ አራዊት ለይተን ከአየነው በሁለቱ ዓረፍተ ነገሮች የተገለጹት ሀሳቦች የጎንደርን ሁኔታና ችግር ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ የኢትዮጵያን መሠረታዊ ችግር ለቀባሪው የሚያረዱ ናቸው፤ እነዚህ ችግሮች የኢትዮጵያዊ ኑሮ መለያ ሆነዋል፤ "በሕግ አምላክ ሲባል ውሀም ይቆማል" የሚባልበት አገር ነበር፤ መንገደኛ ሁሉ ዳኛ የሚሆንበት አገር ነበር፤ በንጉሦቹ ችሎት ሽማግሌዎች ፍርዱን የሚተቹበት አገር ነበር፤ ተከሳሾች ዋስ በራስ ብለው ቤታቸው የሚገቡበት አገር ነበር፤ አራዊትነት ሳይነግሥ፤ «እግዚአብሔር ያሳይዎ፤ ክርስቶስ ያመልክትዎ» እየተባለ የሚሟገቱበት ባህል ያለን ሕዝብ ነን፤በንጉሡ ነገሥቱም ችሎት ቢሆን ተከራካሪዎች በሙሉ ልብና በነጻነት የሚናገሩበት ባህል ያለን ነን፤ ዛሬ የአገዛዙ ጠበቃ ብቻ ነው እንደልቡ የሚናገረው፤ ፍርድ የእኔ ነው የተባለውን አምላካዊ ቃል ያልተቀበለና ያልገባው ፍርድ ቤት ባህላችንን ከማዋረዱ አልፎ ሕግን ከሚዛንነት ወደወገንተኛ መሣሪያነት ይለውጠዋል፤ ያሳፍራል ሆኖም ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 4 በሕግ ፊት ሁሉም እኩል መሆኑን ይደነግጋል፡፡

ሕግና ፍትሕ በኢትዮጵያ ባህል ያላቸው አቅዋም ከምዕራባውያን ሕጋዊ ሥርዓት (the rule of law) ከሚሉት ይጠነክራል፤ በፍርድ ከሄደች በቅሎዬ ያለፍርድ የተበላች ጭብጦዬ የሚለው ባህላዊ አባባል ግሩም አድርጎ ይገልጸዋል፤ በትክክለኛ ፍርድ የተወሰደብንን ትልቅ ሀብት ለማጣት መንፈሳችንን ያዘጋጀን ስንሆን ያለፍርድ የሚወሰደብን ትንሽ ነገር ያንገበግበናል ማለት ነው፡፡

እስቲ ደግሞ በቅንጅት አመራርና አባሎች ላይ የተመሠረተውን ክስና የተካሄደውን የፍርድ ሁኔታ በአጭሩ ለሚቀጥለው ትውልድ እናቆየው፡፡

## 2. ክስ

አንድ ክስ መነሻ ሊኖረው እንደሚገባ ለማስረዳት አንድ እኔ በአጋጣሚ ያየሁትን ልግለጽ፤ አንድ ሰው (ከ እንበለው) ሌላውን ሰውዬ (ተ እንበለው) በአንድ ሺህ ብር ዕዳ ይከስዋል፤ በሕጉ መሠረት ክስ ለመመሥረት ማስረጃ ያስፈልጋል፤ ወይ አንድ ዓይነት ውል፣ ወይ ደረሰኝ፣ ወይ ምስክሮች፣ ወይ

ሁሉም፤ ከ ከዚህ ሁሉ አንድም ለማስረጃነት የሚያቀርበው የለውም፤ ስለዚህ በግድ ማስረጃ ካስፈለገ ብሎ እሱ ራሱ ለአንድ ጓደኛው በተ ላይ ዕዳ አለበት ብሎ በደብዳቤ የጻፈውን ወሬ ከክሱ ጋር አያይዞ ያቀርባል፤ ዳኛው ተከሳሹን ሲጠይቁት የሰጠው መልስ ግሩም ነው፤ "ከ ደግ ሰው ሆኖ ዕዳውን በአንድ ሺህ ብር ወሰነልኝ እንጂ አንድ ሚልዮን ቢል ማን ይከለክለው ነበር፤ እኔ ከእሱ አንድም ሣንቲም አልተበደርሁም፤" ይላል፤ በበኩሌ እኔ የተጠባበቅሁት ክሱ በትክክል ስላልተመሠረተ ዳኛው ተቆጥተው ከ ለተ ኪሳራውን ከፍሎ ፋይሉ እንዲዘጋ ያዝዛሉ ብዬ ነበር፤ ግን ዳኛው ከ ሌላ ማስረጃ እንዲያቀርብ አዝዘው በቀጠሮ አሰናበቷቸው፤ ግልጽ የሆነ እጉል ነገርን ማጓተት ነው፤ ከ ጉልበት ያለው ቢሆንና ተን ቢያሳስረውስ ኖሮ ከ ማስረጃ እስቲያገኝ ወይም እስቲፈጥር ድረስ ተ በእስር ይንገላታ ነበር ማለት ነው፤ በልባችሁ ያዙት።

ከሳሽ የመንግሥትን ሥልጣን የያዘና ፖሊሱን፣ ዓቃቤ ሕጉንና ዳኞቹን የሚቆጣጠር ሲሆንስ የክሱንና የፍርዱን ሥርዓት ከሳሹ እንደፈለገ ሊቆጣጠር ይችላል ማለት አይደለም? የሚቀጥለውን መግለጫ ስናነብብ ከሳሽ የመንግሥት ሥልጣንን በሙሉ የጨበጠና የሕግ ሥርዓቱን በቁጥጥር ስር ያደረገ መሆኑን እናስታውስ።

እኛን ለመክሰስ የተሰለፉት ሰዎች ዓቃብያነ ሕግ አልነበሩም፤ የከሳሽ ጠበቃዎች ነበሩ፤ ዓቃቤ ሕግ ማለት ለሕግ የሚቆምና ሕግን የሚያስጠብቅ ነው፤ እኛን ለመክሰስ ለብሰው የተሰለፉት ሦስት ሰዎች ለዚሁ ሥራ በችሎታቸው ሳይሆን በጠባያቸው የተመለመሉ እንጂ በዓቃቤ ሕግነት ሥራ ላይ የተሰማሩ አይደሉም፤ እንዲያውም ታሪካቸው አያምርም፤ ሆኖም በዓቃቤ ሕግነት ባይሆን ለከሳሹ ጠቢቃ በመሆን ሽንጣቸውን ገትረው የግፍ መሣሪያ ሆነዋል፤ በአሜሪካ ያገኘሁት አንድ የቀድሞ ዓቃቤ ሕግ እንደነገረኝ በመሥሪያ ቤቱ ውስጥ የነበሩ ዓቃብያነ ሕግ በቅንጅት አባሎች ላይ ክስ ለመመሥረት በቂ ማስረጃ ባለማግኘታቸው ፈቃደኞች አልነበሩም፤ በዚህ ምክንያት አገዛዙ በትእዛዝ የሚሠሩ ልዩ ጠበቆችን ከውጭ መሰየም ግዴታ ሆነበት።

አንድ ሌላ አስገራሚ ነገር በፍርድ ቤቱ ውስጥ ይታይ ነበር፤ የከሳሹ ጠበቆች ያላቸው ጠረጴዛ ባሸበረቀ ጨርቅ የተሸፈነ ነው፤ በአንጻሩ የተከሳሽ ጠበቆች ያላቸው ጠረጴዛ ራቁቱን ነው፤ አድልዎ መኖሩን ሳያፍሩ በገሀድ ለማሳየትና ለማሳወቅ የተደረገ ይመስላል።

## 3. ተከሳሾች

ለተከሳሾች የታደለው የክስ ማስታወቂያ ሀያ አምስት ገጾች አሉት፤ አሥራ ሰባት ገጽ የተከሳሾች የስም ዝርዝር ነው፤ ከተከሳሾቹ ውስጥ ሠላሳ ዘጠኝ



የሚሆኑት ተይዘው በእስር ላይ የሚገኙ የቅንጅት አባላትና ጋዜጠኞችና አሳታሚዎች ናቸው። ለጉዳዩ ዝርዝሩን እንየው፤ ማንም ሰው ይህንን መያዣና መጨበጫ የሌለው፣ በአፍሪካ፣ በአውሮፓና በአሜሪካ የተሰራጩ የኢትዮጵያውያን ስብጥር ለአድማ የተሰለፉ ተደርገው መቅረባቸውን ሊመረምረው ይገባል፤ ማሰብ የተሳነው ሰው ብቻ ነው በዜግነት የተለያዩ፣ በተለያዩ አገሮች የሚኖሩና ብዙዎቹ የማይታዋወቁ ሰዎችን በዘፈቀደ አንድ ከረጢት ውስጥ አስገብቶ በአድማ ሊያስተሳስር የሚፈልገው፤ የአሜሪካ ራድዮን ጋዜጠኞችን አድማው ውስጥ ያስገባው ሰው የአሜሪካ ራድዮ ጣቢያ ከአሜሪካ መንግሥት ጋር ያለውን ግንኙነት አላወቀም፤ አልገባውም፤ ስለዚህም የአሜሪካ ቁጣ ከረር ብሎ ሲመጣ የአሜሪካ ራድዮ ሰዎች ስማቸው ከተከሳሾች ዝርዝር ተሰረዘ፤ አያሳፍርም! ሌሎችም ከክሱ ሳይሰረዙ አልቀሩም ይሆናል፤ በውጭ አገር ከሚኖሩት ተከሳሾች ውስጥ የቅንጅት ደጋፊዎች የማልላቸው ሰዎች አሉበት፤ ለመክሰስ የበቁት በአድማ ተሳስረው ሳይሆን የወያኔ/ኢሕአዴግን አገዛዝ አጥብቀው የሚነቅፉ በመሆናቸው ነው።

አድማ የሚመስል ነገር ነበረ ለማለት ትንሽ ማሰብ ቢጨመርበትና ማጣራት የሚመስል ነገር የሚታይበት ቢሆን እርቃኑን የወጣ ውሸት ከመሆን ይልቅ ጥርጣሬ የሚያሳድር ይሆን ነበር፤ ሌላው ቀርቶ የአንዳንዱ ተከሳሽ ስም ትክክል አይደለም፤ በፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥም ለአንዳንድ ተከሳሾች የተሰጠው ቦታም ሐሰት ወይም ስሕተት ነው፤ ለምሳሌ በተያዝንበት ጊዜ በቀስተ ደመናም ሆነ በቅንጅት ውስጥ "የአመራር አካል አባል" አልነበርሁም፤ ሌሎችም እንደዚሁ ነበሩ፤ ከዚያም በላይ ለሀያ አንድ ተከሳሾች ምንም ዓይነት የፖለቲካ ድርጅት አባልነት አልተገለጸም ፤

ስለዚህም እንዴት "የአድማው" አካል ሊሆኑ እንደቻሉ አይታወቅም፤ የእነዚህ ሰዎች ዕድሜ ከአሥራ ስድስት እስከስድሳና ከዚያም በላይ ይደርሳል።

የካሳሽ ጠበቃ አድማ ለሚለው ቃል ልዩ ትርጉም ሰጥቶታል፤ በጭራሽ ተያይተው የማያውቁ ሰዎች፣ በአውሮፓና በአሜሪካ እንዲሁም በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች የሚኖሩ ሰዎች በስልክ፣ በደብዳቤና በኢንተርኔት ዓላማቸውንና ዘዴያቸውን እየተወያዩ፣ ዓላማና ዘዴያቸውንም በጋዜጣ እያሳተሙ፣ በአደባባይ ሕዝብን እየሰበሰቡና ስለአድማቸው እየተናገሩ፣ በቪድዮና በካሴት እንዲቀረፅ እያደረጉ የሚዘጋጁበት የወንጀል ተግባር ነው፤ እንደዚህ ዓይነቱ የአደባባይ አድማ በሚደረግበት ጊዜ ሁሉ ፖሊስና ዓቃቤ ሕግ አስፈላጊውን ሕጋዊ እርምጃ ወስደው እንዲታረም ለማድረግ አልሞከሩም፤ ይህንን ልዩ የአድማ ትርጉም ፍርድ ቤት ተቀበለው፤ በዚሁ መሠረት ፍርድ ተሰጠ።

*ዓቃቤ ሕግ ያቀረበው የተከሳሾች ዝርዝር*

| ተ.ቁ. | ተከሳሾች በዓይነት | ብዛት |
|---|---|---|
| 1 | የቅንጅት አመራር የተባሉ | 39 |
| 2 | የአገር ውስጥ ጋዜጠኞችና አሳታሚዎች | 22 |
| 3 | በክሱ ላይ ምንም ያልተገለጸ | 21 |
| 4 | አሜሪካና አውሮፓ ነዋሪዎች | 25 |
| 5 | የአሜሪካ ራድዮ ጋዜጠኞች | 5 |
| 6 | የጀርመን ራድዮ ጋዜጠኞች | 1 |
| 7 | መምህራን ማኅበር | 2 |
| 8 | መያድ | 2 |
| 9 | ከያለበት | 9 |
| 10 | ድርጅቶች | |
| ድምር | | 130 |

ለዘር ማጥፋትም ልዩ ትርጉም ተሰጠው፤ ትግርኛንም ጨምሮ የተለያየ የቤተሰብ ቋንቋ የሚናገሩ ሰዎች አድማ አድርገው የትግሬን ዘር ለማጥፋት ሞከሩ! ይህ አሳፋሪ ክስ ከኢትዮጵያ ውጭ ቁጣ ቢያስከትልና ፍርድ ቤቱም በአብላጫ ድምፅ ቢጥለውም አንድ ዳኛ ተቀብሎታል።

የከሳሽ ጠበቃ ተከሳሾቹን በተከታታይ «የአድማ ወንጀል» እያለና ተከሳሾቹንም «ወንጀለኞች» እያለ ሲናገር ፍርድ ቤቱ ባለማረሙ ተከሳሾች አቤት ብለው ፍርድ ቤቱ አነጋገሩን እንዲያርም አስገድዶታል።

## 4. የክሱ ዝርዝር

ክሱ ልክ እንደተከሳሾቹ ስም ዝርዝር ድሪቶ ከመሆኑ በላይ ብርቱ የሆነ የማሰብ ችግርን ያመለክታል፤ መጀመሪያ ይህንን ክስ ደራርተው ያቀረቡት ሰዎች ስለሕግ ያላቸው ግንዛቤና እውቀት የሚያሳፍር ነው፤ ቅንጅትን የመሠረቱት ፓርቲዎች እያንዳንዳቸው ሕጋዊ እውቅናን ያገኙ መሆናቸውን ይናገራል፤ ይቀጥልና እነዚህ ፓርቲዎች

*«ከጥቅምት 29 ቀን 1997 ዓ/ም ጀምሮ ደግሞ ለብሔራዊና ክልላዊ ምርጫ የሚያገለግል ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ በአህጽሮት ቅንጅት የሚል የጋራ ጥምረት መድረክ መሥርተው ይህንኑ መድረክ ለህገወጥ አላማቸው መጠቀሚያ በማድረግ የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገመንግስትንና ህገመንግስታዊ ስርአቱን ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ለማፍረስ አሰበውና ይህን የወንጀል ድርጊት የሚያስከትለውን ውጤት ለመቀበል በሙሉ*



*ሀሳባቸው በመስማማት ከጥቅምት 29 ቀን 1997 እስከ ህዳር 5 ቀን 1998 ባለው ጊዜ ውስጥ፣ በተለይም ጎረቤት አገር ከሆነው የኤርትራ መንግሥት ጋር ጦርነት በሚያሰጋበት ጊዜ ...»(አጻጻፉ እንዳለ ከነስሕተቱ የነሱ ነው።)*

ይህ የወንጀሉ ዝርዝር በሚል ርእስ ስር የተገለጸው እኔ ስለሕግ ከሚገባኝ በጣም የራቀ ነው፤ አራቱም የቅንጅት መሥራች ድርጅቶች በሕግ የተቋቋሙና ሕጋዊ እውቅና ያላቸው የፖለቲካ ድርጅቶች መሆናቸውን በግዱ እምኖ በመቀበል ይነሣል፤ ቅንጅትም በሕግ የታወቀና በምርጫው ለመወዳደር በሕግ የተፈቀደለት ድርጅት መሆኑን እየገለጸ፣ ግን ላለመቀበል ይዳዳዋል፤ አስተሳሰብ የሚንኮታኮተው እዚህ ላይ ነው፤ ዊልሚጥ ብሎ «ቅንጅትን ለህገወጥ አላማቸው መጠቀማያ በማድረግ» ይልና «ህገመንግስቱንና ህገመንግስታዊ ስርአቱን ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ለማፍረስ አሰበውና» በማለት የማያውቀውንና ሊያውቅም የማይችለውን ነገር ያወራል፤ በንግግር ወይም በጽሑፍ ካልተገለጸ በቀር ማንም የማንንም ሀሳብ ሊያውቅ አይችልም፤ ስለዚህም አሰበዋል በማለት የወንጀል ክስ ለመመሥረት እንዴት ይቻላል? አንድ ዱሮ የሰማሁት ቀልድ ትዝ አለኝ፤ በሎንዶን ከተማ የመንግሥታት ሰላዮች ስብሰባ ነበረ፤ የመጀመሪያው የመነጋገሪያ ጉዳይ ወንጀለኛን ለመያዝ የሚፈጀው ጊዜ ነበር፤ እንግሊዞ ብዙ ወራት፣ አንዳንዴም ዓመታት እንደሚፈጅባቸውና ከባድ ችግር ሆኖባቸው ጊዜውን ለማሳጠር በመሞከር ላይ መሆናቸውን ተናገረ፤ አሜሪካኑም ተነሥቶ ተመሳሳይ ችግር እንዳለባቸው ተናገረ፤ ኢጣልያና ስፔይን ወንጀለኞችን ለመያዝ የሚያስፈልጋቸው በሳምንታት የሚቆጠር ጊዜ መሆኑን እየኮሩ ተናገሩ፤ የሶቭየት ኅብረትና ቻይና በበኩላቸው በቀኖች የሚቆጠር ጊዜ ብቻ እንደሚያስፈልጋቸው በኩራት ተናገሩ፤ በመጨረሻ የኢትዮጵያ መልእክተኛ እየተኩራራ በሌላ ሁሉ በጣም ቀድማችሁን ብትገኙም በዚህ ጉዳይ ግን እኛ ጥለናችሁ ሄደናል፤ እኛ ወንጀለኛውን የምንይዘው ገና ሲያስብ ነው! ብሎ ትልቅ ቁም ነገር አድርገው የሚወያዩበትን ጉዳይ እንዘጭ እድርጎ አወረደባቸው፤ የሌሎቹ አገሮች ወኪሎች ወንጀል ሳይፈጸም ወንጀለኛ ሊኖር አይችልም ከሚል መነሻ የተነሡ ሲሆን የኢትዮጵያው መልእክተኛ የተነሣው ደግሞ ወንጀል ሳይፈጸም ወንጀል መሥራት ይቻላል ከሚል መነሻ ነው፤ ገና ወደፊት ወንጀል ለመሥራት የሚያስበውን ሰው እናውቃለን ከሚል የተዛባ አቅዋም ተነሥቶ ነው።

አሁንም የከሳሽ ጠበቃዎች "አሰበው" ከማለት ይነሡና "ይህ የወንጀል ድርጊት" ብለው ሲቀጥሉ በከሳሽ ጠበቃዎቹ ጭንቅላት በአጠቃላይ በማሰብና **በድርጊት** መሀከል ልዩነት የለም ማለት ነው፤ ወይም በተለይ በጠበቃዎቹ አስተሳሰብ በሕጋዊ መንገድ ሲታይ በማሰብና በማድረግ መሀከል ልዩነት የለም

ማለት ነው፤ በሎንዶኑ ስብሰባ ላይ እንደተናገረው ማለት ነው፤ ጠበቃዎቹ በሕግ ትምህርት ሠልጥነዋል የተባሉ ሰዎች፣ በወያኔ/ኢሕአዴግ አመራር ለዚህ ከፍተኛ ኃላፊነት የተመረጡ ሰዎች በሀሳብና በድርጊት መሀከል ያለውን ልዩነት አያውቁም ማለት ነው፤ እርግጥ ነው ድርጊት ከሀሳብ ሊመነጭ ይችላል፤ ለእኔ እንደሚመስለኝ ትልቁና ዋናው የፖሊስና የዓቃቤ ሕግ ተግባር በሀሳብና በድርጊት መሀከል ያለውን ዝምድና በተጨባጭ ማስረጃ ማረጋገጥ ነው፤ አንዳንድ በልጅነታችን የሰማናቸው ተረቶች ስናድግ፣ ስንማርና ስንሠለጥን ሊጠቅሙን አይገባም፤ ለምሳሌ ሰውየው ከዝንጀሮ ባልንጀራው ጋር ሲጓዝ ደከምት አንድ ዛፍ ስር ያርፋል፤ ዝንብ ትመጣና በሰውዬው አፍንጫ ላይ ታርፋለች፤ ዝንጀሮ ይናደድና በዱላ ዝንቧን ይገድላል፤ ሰውዬውንም ጨምሮ! እንግዲህ አሁን ዝንጀሮው ባልንጀራውን ለመግደል «ሀሳብ» ነበረው ማለት ነው? በዱላ አፍንጫውን መትቶ ከመግደሉ ድርጊት ጋር የሚዛመድ ሀሳብ ከየት ይገኛል? ዝንጀሮ አያስብም ከሚሉ ሰዎች ጋር ክርክር አልገጥምም፤ ግን በሰውም ላይ ይደርሳል፤ በቃሊቲ ያገኘሁት አንድ ነጋዴ ነበር፤ አዲስ ሽጉጥ ገዝቶ ሲፈትሽ «የሚወዳትን» ሚስቱን ገደላት፤ እውነቱን አፍተልትሎና አረጋግጦ ሀሳብን ከመግደሉ ድርጊት ጋር ማዛመድ የሚቻለው እንዴት ነው? ይህ የፖሊስን ልዩ ችሎታና ልዩ ኃላፊነት የሚጠይቅ ተግባር ነው፤ ፍሬ ነገሩ ሀሳብና ድርጊት ሁለት እንደሰማይና እንደመሬት የተራራቁ ተግባሮች ናቸው፤ ስለዚህም ሀሳብንና ድርጊትን ለማዛመድ ቀላል የቡና ላይ ወሬ አይደለም፤ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 24/1 የሚከተለውን ይላል፤

*የአንድ ወንጀል አፈፃፀም አንድ የተወሰነ ውጤት እንደሚያመጣ የታወቀ በሆነበት ጊዜ ሁሉ፣ ውጤቱን ያስገኘው ተከሳሽ የተከሰሰበት ድርጊት መሆኑ ካልተረጋገጠ በቀር ወንጀሉ እንደተደረገ አይቆጠርም፡፡*
*በምክንያቱና በውጤቱ መካከል ግንኙነት አለ የሚባለውም በነገሮች የታወቀ ወይም የተለመደ ሂደት የተከሳሽ ድርጊት ውጤቱን ለማስገኘት የሚችል ሆኖ ሲገኝ ነው ፡፡*

ምንም እንኳን በሌሎቹ ተከሳሾችም ቢሆን ድርጊትና የወንጀል ተግባር ግንኙነት እንዳልተገኘባቸው ባምንም ለነሱ ጠበቃ ለመሆንና ስለእነሱ ለመናገር መብት የለኝም፤ ስለራሴ ግን ያለምንም ጥርጣሬ ሌሎችን ወደወንጀል የሚመራ ቅንጣት የሚያህል ድርጊት አለመፈጸሜን፣ ወይም ንግግር አለማድረጌን አውቃለሁ፤ ሌሎችም ሲያነሣሱ አልሰማሁም፤ ብሰማ ወዲያውኑ እንደማስቆመውና እኔም በቡድኑ ውስጥ አልገኘም ነበር፤ የክሱ ዋና መሠረት የኃይል ዓመፅ ለማነሣሣት መሞከር ይመስላል፤ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስለማነሣሣት የሚከተለውን ይላል፤—



*ማንም ሰው ወንጀል እንዲደረግ አነሳሳ የሚባለው አስቦ ሌላውን ሰው በመጎትጎት፣ ተስፋ በመስጠት፣ በገንዘብ፣ በስጦታ፣ በማስፈራራት ወይም በማናቸውም ሌላ ዘዴ አንድ ወንጀል እንዲያደርግ ያግባባ እንደሆነ ነው፡፡*
*2.አነሳሹ የሚቀጣው ወንጀሉ ቢያንስ ተሞክሮ እንደሆነ ነው፡፡*

በንዑስ አንቀጽ 1 የተዘረዘሩት (መጎትጎት፣ ተስፋ መስጠት፣ ገንዘብ፣ ስጦታ፣ ማስፈራራት፣ ወይም ሌላ) በተከሳሾች እንዳልተፈጸሙ በእርግጠኛነት ለመናገር ይቻላል፤ ስለዚህም በዚህ ጉዳይ ላይ አንድም ማስረጃ በማንም ላይ አልቀረበም፡፡ እንደገና የፖሊስንና የዓቃቤ ሕግን የተጓደለ ኃላፊነት ማንሣት እንገደዳለን፤ ለወንጀል ተግባር የመጎትጎቱ፣ ተስፋ የመስጠቱ፣ በገንዘብና በስጦታ መደለሉ፣ ማስፈራራቱ በሚደረግበት ጊዜ ሁሉ ገና ወንጀሉን ሲያስብ እናውቃለን የሚሉት የት ነበሩ? ለምን በዚያን ጊዜ አላቆሙትም?

የቀኑስ ጉዳይ፣ "ከጥቅምት 29 1997 እስከ ህዳር 5 ቀን 1998 ባለው ጊዜ ውስጥ" ይላል፤ ልብ በሉ፤ የምርጫውን የውድድር ጊዜ አስታውሱ፤ የሚያዝያ ሠላሳን ሰላማዊ የሕዝብ ስብሰባ አስቡ፤ የግንቦት ሰባትን የምርጫ ቀን በዓይነ ልቡናችሁ ቃኙት፤ ከቅንጅት በኩል ምን ወንጀል የሚመስል ተግባር መታየት ቀርቶ ምን ንግግር ተሰማ? ከዚያስ "ህዳር 5 ቀን 1998" የሚለው ከጥቅምት 22 ጀምሮ አብዛኛዎቻችን በማእከላዊ ታጉረን እንደነበረ የከሳሽ ጠበቃዎች አልሰሙም ማለት ነው? ይህ የማሰብ ወንጀል በምን ተአምር ነው "ህዳር 5" ያቆመው? ማእከላዊ በመግባታችን ማሰብ አላቆምንም፡፡

የማሰብ ወንጀል የተፈጸመው በከሳሽ ጠበቃዎች አስተያየት በተለይም ጎረቤት አገር ከሆነው የኤርትራ መንግሥት ጋር ጦርነት በሚያሰጋበት ጊዜ መሆኑ በጣም ከባድ ይሆናል፤ ቅንጅት እንዴት ብሎ ነው ከወያኔ/ኢሕአዴግ ይልቅ ለሻቢያ የሚቀርበው? ሻቢያ ለቅንጅት ነው ወይስ ለወያኔ/ኢሕአዴግ ውለታ ያለበት? እንዴት ቢደናበሩና ቢርበተበቱ ነው ይህንን ሁሉ የሳቱት?
የወንጀሉ ዝርዝር የተባለው የሚከተሉትን ያጠቃልላል፤

*«የኢፌዴሪ ህገ መንግስት በህዝብ ፈቃድ የጸደቀ ሳይሆን በሀይል የተጫነ ህገ መንግስት ነው፡፡»*
*«ህገ አራዊት ነው»*
*«ገዢው ፓርቲ ስልጣን የያዘው በህዝብ ፈቃድ ሳይሆን በጠመንጃ ሀይል ነው፡፡»*
*«ኢህአዴግና ሰላማዊ ትግል አይተዋወቁም»*

*«ምርጫ ቦርድ ገለልተኛ አይደለም፤ ነጻና ፍትሀዊ ምርጫ ለማድረግ አቅም የለውም»*

*«ነጻና ፍትሀዊ ምርጫ አይካሄድም»*

*«ምርጫ ቦርድ የገዢው ፓርቲ መሳሪያ ነው»*

/

በነዚህ ላይ አስተያየት መስጠት እንዲያው ጊዜ ማጥፋት ይሆናል፤ ግን አንድ መሠረታዊ ጉዳይ ማመልከት ግዴታ ነው፤ ከተዘረዘሩት ውስጥ በኋላ እንደማመለከተው ከተከሳሾች መሀል ሕገ መንግሥት ሕገ አራዊት ነው ያለ ሰው የለም፤ ፍጹም ሐሰት ነው፤ ሌሎቹ አስተያየቶች ነጻነት ባለበት አገር እንደወንጀል አይቆጠሩም፤ አስተያየቶቹ እውነት ከሆኑ እንዲስተካከሉ ይረዳል፤ ስሕተት ወይም ሐሰት ከሆኑ እውነቱን በማውጣት አስተያየት ሰጪው እንዲታረም ማድረግ ነው፤ በከሳሽ ጠበቃዎች ጭንቅላት ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች –

*«የዛቻና ህዝቡን የማነሳሳት ተግባር ተከትሎ በአዲስ አበባ ባስነሱትና በመሩት አመጽ ሰኔ 1/97 በ26 ዜጎች ላይ የሞት፣ በ15 ዜጎች ላይ የአካል ጉዳት፣ እንዲሁም ግምቱ ከአንድ መቶ ሚልዮን ብር በላይ የሆነ የመንግሥትና የግል ንብረት የወደመበትን ውጤት እንዲከሰት በማድረጋቸው ... »*

የሞቱትና የቆሰሉት ዜጎች እነማን እንደሆኑ ክሱ ላይ አልተገለጸም፤ ነገር ግን ዓለም በሙሉ ያውቀዋል፤ በአሜሪካ ምክር ቤት ተነግሮአል፤ በአውሮፖ ምክር ቤት ተነግሮአል፤ እነዚህን ዜጎች ማን እንደገደላቸውና ማን እንዳቆሰላቸው ክሱ ላይ አልተገለጸም፤ ይህንንም ዓለም በሙሉ ያውቀዋል፤ ማንም ሰው ይህንን መረጃ ከኢንተርኔት በቀላሉ ለማግኘት ይችላል።

እንዲያውም ከአንድ ገጽ በኋላ ይባስ ብለው «ከጥቅምት 22 ቀን 1998 ጀምሮ... አመጽና ረብሻ በመፍጠር» ለ34 ሰዎች ሞት፣ ለ167 ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት፣ ግምቱ ከአንድ ቢልዮን በላይ የሚሆን ንብረት እንዲወድም «ምክንያት በመሆናቸው» ይላል፤ አሁንም እነማን ሞቱ? እነማን ቆሰሉ? ገዳዩና አቁሳዩስ ማን ነው? ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ የለም፤ በእስር ላይ ያሉ ሰዎች ለመግደልም ሆነ ለማስገደል ችሎታውም የላቸውም፤ በእስር ላይ ያሉ ሰዎች ፖሊሶችና ወታደሮች ለገደሏቸውና ላቆሰሏቸው ሰዎች «ምክንያት» ለመሆን ይችላሉ ብሎ ለመገመት በትክክል ለሚያስብ ሰው አዳጋች ነው።

እግዚአብሔር ያሳያችሁ! ነገሩ ሁሉ ተምታታብኝ! በአንድ በኩል ከጥቅምት 22/98 ጀምሮ (ጥቅምት 22/98 እኛ የታሰርንበት ነው) 34 ሰዎች ተገደሉ፤ 167 ሰዎች የአካል ጉዳት ደረሰባቸው፤ አንድ ቢልዮን ብር የሚያወጣ ንብረት ወደመ፤ መጀመሪያው እንጂ መጨረሻው አይታወቅም! በሌላ በኩል



ከጥቅምት 29/97 እስከኅዳር 5/98 የጊዜ ገደብ ውስጥ (አሁንም እኛ እስር ቤት ውስጥ ነን)፤ እስር ቤት ውስጥ ሆነን ተፈጸመ ለተባለው ወንጀል ምክንያት ለመሆን የምንችለው በምን ተአምር ነው?

ከዚህ በላይ የተገለጸው 1ኛ ክስ የተባለው ነው፤ የመጀመሪያዎቹን ሠላሳ ዘጠኝ ተከሳሾች የሚመለከት ነው፤ ሌሎቹን ክሶች በአጭር በአጭሩ ቀጥዬ አቀርባቸዋለሁ፤

«2ኛ ክስ» ይህኛው ክስ ሠላሳ ዘጠኙንና «ከ96ኛ እስከ 131ኛ» ያሉትን ይመለከታል፤ (አድማውን እያፈራረሱት ይመስላል፤) ወንጀላቸው የምርጫ ቦርድን ሕጋዊ ተግባር ማደናቀፍና የሥራ ማቆም አድማ ጥሪ በማድረግ፤

‹ ‹3ኛ ክስ ሠላሳ ዘጠኙ ተከሳሾች የትጥቅ ትግል እንዲነሳ «**አሰበው**» ኃይልን በማደራጀትና በመምራት፣ «ከ96 እስከ 121ኛ» አመራር ተቀብለው በመንግስት ላይ ጦር መሳሪያ ይዘው አመጽ በማንሳታቸው» ድርጅቶቹም «ለወንጀሉ አፈጻጸም መጠቀሚያ በመሆናቸው»፣

«4ኛ ክስ» ከሌላው ይበልጥ ግራ የተጋባው ነው፤ የአገሪቱን አንድነት አደጋ ላይ የሚጥል ወንጀል መፈጸም ይልና «የአገሪቱ አንድነት እንዲፈርስ ዘረኛ እና የኢስተሳሰብ ነጻነትን የሚጋፋ ቅስቀሳና የአመጽ ጥሪ በማስተላለፍ የኢህአዴግ አባላቶችንና ደጋፊዎችን እንዲያገሉ ጥሪ በማድረግ...»፣

«5ኛ ክስ» ከሠላሳ ዘጠኙ በተጨማሪ «ከ70 እስከ 90ኛ እና ከ127ኛ እስከ 131ኛ» የሚመለከት ነው፤ «የአገር መከላከያ ኃይልን የመጉዳት ወንጀል» የሚል ሆኖ «የመከላከያ ሰራዊት ተሽከርካሪን በማቃጠል፤ ወታደሩ ወታደራዊ አመጽ እንዲያስነሳ እና እንዲከዳ በግልጽ በማነሳሳት እና በማደፋፈር፣»

«6ኛ ክስ» በመንግስት ላይ ከፍ ያለ የክዳት ወንጀል መፈጸም» ይልና «ከኢትዮጵያ ጋር ጦርነት የሚያደርገው የኤርትራ መንግስት እና በኤርትራ መንግስት የሚደገፈው አርበኞች ግንባር እንዲቀናው አሰበው»፣

«7ኛ ክስ» **«የዘር ማጥፋት ወንጀል መፈጸም»** በሚል ሽፋን ለማስተላለፍ የተፈለገው የትግሬን ዘር የማጥፋት ወንጀል መሆኑ ግልጽ ነው፤ ወንጀል ተፈጽሞባቸዋል የተባሉት «ኑር ሁሴን ኢድሪስ፣ ኮ/ል አርአያ ገብረ ዩሀንስ ሀደራ እና ወ/ት አበባ እሸቴ ተብለው የሚጠሩ» የትግራይ ተወላጆች መሆናቸውን ይገልጻል፤

በኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ውስጥ ከባድ የሚባል ወንጀል የቀረ አይመስለኝም፤ የዘር ማጥፋት ወንጀል የሚለውን ብዙ የውጭ አገር ሰዎች ከቶኛ ተቃውመውት ነበር፤ ዋናው ምክንያታቸው ከባዱንና ከፉውን ዓለም አቀፍ ወንጀል አቀለሉትና መጫወቻ አደረጉት የሚል ነበር፤ በዚህም ምክንያት ወደ ሙከራ እንዲለወጥ ትእዛዝ ተላልፎ ነበር።

የከሳሽ ጠበቃ ክሱን አነበበ፤ ተከሳሾች እምነት-ክህደት ተጠየቁ፤ ምኑ ነው የሚታመነው? ምኑ ነው የሚካደው? እንዲያው ዝም! አልን፤ ለጥያቄው መልስ አልሰጠንም፤ ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ መስሎ ታየን፡፡

## 5. የከሳሽ ማስረጃዎች

ማናቸውም ክስ የሚመሠረተው በሕጋዊ ሥርዓት ነው፤ ወይም መሆን አለበት፤ ቀደም ሲል በምሳሌነት የጠቀስሁት ከሳሽ ከሕጉ ሥርዓት ውጭ ራሱ ለጓደኛው የጻፈውን ደብዳቤ ማስረጃ አስመስሎ ክስ ለመመሥረት እንደቃጣ አይተናል፤ አሁን በምንነጋገርበት ጉዳይ ላይ ደግሞ የከሳሽ ጠበቃ በገጽ 52 በተመለከቱት ተከሳሾች ላይ የመሠረታቸውን ክሶች በአጭሩም ቢሆን አይተናል፤ እንግዲህ መመለስ ያለበት ጥያቄ የከሳሽ ጠበቃ ክሶቹን ሲመሠርት ለአንድ ነጻ ፍርድ ቤት ብቁና አሳማኝ የሆኑ ማስረጃዎችን አቅርቦ ነበር ወይ? የሚል ይሆናል፤ የአድማ ወንጀል ብሎ ለመሠረተው ክስ ማስረጃ ብሎ ያቀረባቸው የሚከተሉት ናቸው፤

የቅንጅት የተለያዩ የፓርቲው አመራር ስብሰባዎችንና የሕዝብ ስብሰባዎችን የሚያሳዩ ፊልሞች፣ አንዳንዶቹም ቪዲዮዎች በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የታዩ ክርክሮችና መግለጫዎች ናቸው፤ ወደፍሬ ነገሩ ሳንገባ ወይም ጠበቃዎቹ እንደሚሉት ወደጭብጡ ሳንሄድ በከሳሽ ጠበቃው አእምሮ የአድማው ወንጀል የተካሄደው በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ተባባሪነት ነው ማለት ነው፤ ለሕዝባዊ ስብሰባዎቹ ሁሉም የወያኔ/ኢሕአዴግ አመራርና ካድሬዎች፣ የደኅንነትና የፖሊስ ሠራዊት በሙሉ፣ በየክልሉና በየከተማው ያሉ የአስተዳደር ሹሞች በሙሉ የቅንጅት የወንጀል አድማ ተባባሪዎች ሊሆኑ ነው፤ ከነዚህ ሹሞች ተሰውሮ የተፈጸመ አንድም ነገር የለም፡፡

ሁለተኛው የማስረጃ ዓይነት ሰነድ የተባለው ነበር፤ አንዳንድ በማጭበርበር ቤት ሲበረብሩ ራሳቸው ከጨመሩት ሌላ የሰነድ ማስረጃ የተባለው ሁሉ ወይ በጋዜጣ የወጣ፣ ወይ ከቅንጅት ቢሮ ለሕዝብ የወጣ መግለጫ ነው፤ እዚህም ፍሬ ነገሩ ወይም ጭብጡ ውስጥ ሳንገባ በከሳሽ ጠበቃ አእምሮ የአድማ ወንጀል የተፈጸመው በጋዜጣ እየተጻፈና በመግለጫ እየወጣ ነው፤ ጅል ማን ነው?

ሦስተኛው የማስረጃ ዓይነት ምስክሮች ናቸው፤ ይህ ደግሞ በጣም አሳፋሪ ነበር፤ በአጠቃላይ ተገርተው የመጡ ሦስት ዓይነት ምስክሮች ነበሩ ለማለት የሚቻል ይመስለኛል፤ በአንደኛው ክፍል ፖሊሶች፣ በሁለተኛው ክፍል የትግሬን ዘር ለማጥፋት የተደረገውን ሙከራ ለመመስከር የመጡ ራሳቸው በደል ተፈጸመብን የሚሉ ትግሬዎች፣ በሦስተኛው ክፍል የቀበሌ ካድሬዎችና ደጅ ጠኚዎች የሚመስሉ ነበሩ፡፡



አንድ የመንግሥትን ሥልጣን ከነጦር ኃይሉና ከነፖሊሱ፣ ከነሰላዮቹ በቁጥጥር ስር አውሎ፣ የመገናኛ ዘዴዎችን ሁሉ የግሉ አድርጎ፣ የአገሩን ሀብት መሬቱንም ሆነ ገንዘቡን እንዳሰኘው የሚናኝ ቡድንን ከሕግ ውጭ በሆነ መንገድ በጉልበት ወይም በኃይል ከሥልጣኑ ለማውረድ የቅንጅት አባሎች ሞክረዋል ለሚል ክስ ማስረጃ ለማቅረብ በጣም አስቸጋሪ ነው፤ **የቅንጅት አባሎች በሙሉ ወያኔ/ኢሕአዴግን ከሥልጣን ማውረድ ፈልገዋል፤ ይህን ማንም አይክድም፤ ክርክር ውስጥም አይገባም፤ ቅንጅት ዓላማውን ለማሳካት የመረጠው መንገድ ፖለቲካዊና ሰላማዊ ነው፤** ቅንጅት ወያኔ/ኢሕአዴግን አቅሙ በፈቀደለት መጠን ሊያሸንፍ ተዘጋጅቶ የነበረው በዚሁ ሕጋዊ፣ ፖለቲካዊና ሰላማዊ በሆነ መንገድ ሕገ መንግሥቱ በአንቀጽ 73 በማያሻማ ቋንቋ የሚፈቅደው ነው፡፡

በቅንጅት በኩል የተደረገው ሁሉ ሕግ በሚፈቅደው መሠረት በሰላማዊ መንገድ ነው፤ ቢፈልግም ቅንጅት ሌላ አማራጭ አልነበረውም፤ በኀልዮም፣ በነቢብም፣ በገቢርም ለጠመንጃ ትግል አልተዘጋጀም፤ ከሁሉም በላይ እንደወያኔ/ኢሕአዴግ የሽፍታነት ታሪክና ልምድ የለውም፤ ቅንጅት ሲፈጠር ጀምሮ ሰላማዊ ትግልን ባሕርዩ አድርጎ ነው፤ ቅንጅት ወያኔ/ኢሕአዴግን በጠመንጃ ሊፋለም አስቦ ነበር ብሎ ክስ ለመመሥረት የማይሳነው ማሰብ ለማይችል ሰው ብቻ ነው፤ በዚህ ምክንያት ነው ማስረጃ ተብሎ የቀረበው ሁሉ ትኩር ብለው ሲያዩት ዓይን የማችል ገለባ የሚሆነው፡፡

በማስረጃነት ከታዩት ቪድዮዎች ውስጥ አንድም የምሥጢርነት ወይም የአድማ ባሕርይ ያለበት አይገኝም፤ ይህ የነበረው በከሳሽና በጠበቃዎቹ አእምሮ ውስጥ ብቻ ነው፤ እንዴት የከሳሽና የጠበቃዎቹ የሐሰት ፈትል ወደ ዳኞቹ አእምሮ እንደተላለፈ እግዚአብሔር እስቲገልጥልን መጠበቅ አለብን፤ ነገር ግን አንድ በግልጽ የታየ ነገር አለ፤ ቪድዮው በፍርድ ቤቱ ውስጥ ሲታይ ዳኞቹ በዓይናቸው የሚያዩትንና በጆሮአቸው የሚሰሙትን ሁሉ ለማደናገር የከሳሽ ጠበቃ ጭብጥ በሚል የማጭበርበሪያ ዘዴ ስለእያንዳንዱ ቪድዮ በስፋት የራሱን ልብ ወለድ ጽፎ ያቀርብላቸው ነበር፤ ማስረጃ ተብሎ የቀረበውን የቪድዮውን ምስልና ንግግር ጭብጥ በሚል የማጭበርበሪያ ዘዴ ይለውጡታል፡፡

የቪድዮ ማስረጃ ተብሎ በቀረበው ውስጥ አንድም የቅንጅት ሰው «ሕጋዊ... ሰላማዊ» ከሚል አነጋገር ውጭ ክፉ ቃል የሰነዘረ የለም፤ የሚያስደስትና የሚያኮራ ነው፤ አድማ በአደባባይ ስብሰባ፣ በሕጋዊ ምክር ቤት ጉባኤ እየተሸረበና በቪድዮ እየተቀረጸ የሚካሄድ አለመሆኑን ለማስረዳት መሞከር የአንባቢውን አእምሮ ማዋረድ ይሆናል፡፡

የሰነድ ማስረጃ የተባለውም ፍሬ አልባ ነበር፤ አብዛኛው በጋዜጦች ላይ አደባባይ የወጣ ነው፤ ከሳሾቹንና ጠበቃዎቹን ሊያሳፍራቸው የሚችል ነው፤ ለእኔ የሰነድ ማስረጃ የተባለው የቆየ የወሬ ቋንጣ ነው::

ምስክሮቹ ብዙ ዓይነት ናቸው፤ ፖሊሶቹ በእኔ አስተያየት የከሳሽ ጠበቃ ቢጎተጉታቸውም በአጠቃላይ በመንገዶች ላይ ያዩትንና የሰሙትን እንጂ ጠበቃው የፈለገውን የሐሰት ምራቂ የቸሩት አልመሰለኝም፤ በእኔ አስተያየት አብዛኛዎቹ እውነተኛ ምስክርነት የሰጡ ይመስለኛል፤ ጠበቃው ከፖሊሶቹ የፈለገውን አላገኘም::

ወደ ቀበሌዎችና ካድሬዎች ምስክርነት ስንመጣ በጥቅም ታስረው ከሚገኙ ሰዎች የሚጠበቅ ቢሆንም እነሱም ቢሆኑ ለጠበቃው ሙሉ በሙሉ አልተመቹም::

በትግሬነታቸው ለምስክርነት የቀረቡት የሚያሳዝኑ ነበሩ፤ በመጀመሪያ ነገር እነሱ ራሳቸው በተነሣው ረብሻ የተጎዱ ናቸው፤ ንዴትም፣ ቅሬታም አለባቸው፤ ሁለተኛ በጠበቃው ሠልጥነው ለጠበቃው የኩርኩራ ጥያቄ የተመቹ እንዲሆኑ ተገርተው የመጡ ነበሩ፤ በመጨረሻ ግን የእነዚህ ሰዎች ምስክርነት ከፋኛ ተበላሽና መሳቂያ ሆነ፤ እንዲህ ነው፤ አንድ ተገደለ ተብሎ የነበረ ሰው በትግራይ ተገኝቶ ለምስክርነት ቀረበ፤ እሱን ደበደቡት ከተባሉ ወጣቶች መሀል አንዱ ምስክሩን «አባባ» በማለት ጀምሮ «እኔ እርስዎን ደብድቤአለሁ?» ብሎ ሲጠይቀው መልሱ «አልደበደብከኝም» ሆነ፤ ታዲያስ ሲባል ደበደበኝ ብሎ በውሸት እንዲመሰክር የነገረው የከሳሽ ጠበቃ እንደነበረ ተናገረ፤ የማያፍረው የከሳሽ ጠበቃ ከትግራይ ድረስ ያስመጣውን ምስክር እብድ ነው ብሎ ፈረደበት፤ ሁላችንም እንደገመትነው ፍርድ ቤቱ የምስክርነት ቃሉን ሽሮ ያሰናብተዋል ብለን ስናስብ አንዱ ዳኛ ሕዳሴ ለመፍጠር ሰውዬውን መጠየቅ ጀመረና ያም ሳይሳካ የሰማው ሁሉ ጉድ! እያለ በኀዘንዚን ተደመደመ::

እንዲያውም በሙሉ ልብ መናገር የሚቻለው የከሳሽ ጠበቃ ያቀረበው የቪድዮና የሰነድ ማስረጃ የተባለው ሙግት ቢኖር ከከሳሹ ይልቅ ለተከሳሾች መከላከያ ይጠቅም ነበር፤ በመሠረቱ የከሳሽ ጠበቃ ክርክር በባህላችን የቆየና ወደ ሃያ አንደኛው ምዕተ ዓመት እንዲሸጋገር የተፈለገ ልማድ ነው፤ **የበደለ ንጉሥ ባላገር ይካስ፤** ተከሳሾቹ ግን የሚከላከሉት ምንም ነገር ስላልነበራቸው ከወህኒ ቤት እየተመላለሱ የፍርድ ቤቱን ድራማ አንዳንዴ በመደነቅ፣ አንዳንዴም በመሰልቸት፣ ሁልጊዜም በአርምሞ ሲመለከቱት ቆይተዋል::

5 ስለምስክሮቹም ሆነ ስለሌሎች ጉዳዮች የደበበ እሸቱን የእምነቱ ፈተና ማንበብ በጣም ጠቃሚ ነው።



## 6. ሙግት ያልነበረበት ፍርድ ቤት

ወደፍርድ ቤት በግድ ሲወስዱን መጠነኛ የመንፈስና የአካል ስቃይ በእኛ በተከሳሾቹ ላይ ለመፈጸም ፍላጎት ያለ ይመስላል፤ ፍርድ ቤቱ ከወህኒ ቤቱ በአሥር ደቂቃዎች የሚደረስበት ነው፤ ነገር ግን በጠዋት ያስነሱንና እያጣደፉን በአውቶቡስ ጭነው፣ ወታደሮች የጦር ልብሳቸውን ለብሰው፣ በአውቶቡስ ውስጥና በመንገዱ ዳር ዳር ከወህኒ ቤቱ እስከፍርድ ቤቱ ተሰልፈው እንደርሳለን፤ ዳኞቹ የሚገቡት ወደአራት ሰዓት ግድም፣ አንዳንዴም ቆይተው ነው፤ እኛ በሁለት ሰዓት ግድም ደርሰን ብርድም ይሁን ጸሐይ አውቶቡሱ ውስጥ ታጭቀን እንቆያለን፤ ለማሰቃየት ወይም ለማንገላታት ካልሆነ በቀር ይህ ለምን እንደሚሆን አላውቅም::

በእኔ አመለካከት ፍርድ ቤት እንደ ቤተ እግዚአብሔር ነው፤ የትኛውም ማኅበረሰብ ያለፍርድ ቤትና ትክክለኛ ዳኝነት መሠረት አይኖረውም፤ ጉልበተኞች በግልም ሆነ በቡድን ሕዝብን እያተራመሱ ሰላም እንዳይኖር እድገትና ብልጽግና እውን እንዳይሆን፣ በሰዎችም መሀከል መተማመንና መተባበር እንዳይኖር በሩን የሚከፍተው ፍርድ ቤት ሲዋረድና ዳኝነት ሲጠፋ ነው፤ የአንድ አገርን ሕዝብ የሚያስተሳስረውና የአንድነቱም መግለጫ የሆነው ፍርድ ቤትና ትክክለኛ ዳኝነት ነው፡

አንድ በጣም ትልቅ የባህላዊ ዳኝነት ቁም ነገር በአለፉት ሠላሳ ዓመታት ተረስቷል፣ በኢትዮጵያ ባህል ማንም ተራ ዜጋ ሲበደል የመጨረሻው ባለሥልጣን (ንጉሠ ነገሥቱ) ዘንድ ቀርቦ ትክክለኛ ዳኝነትን ለማግኘት መብት ነበረው፤ ዛሬ ከሳሹ የመጨረሻው ባለሥልጣን ነው፤ በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ማንአለብሽ ስለሚባሉት ልጃቸው አንዱ ተበድሎ ሳይሆን በሰሞች ትርጉም መጫወት የፈለገ ገጣሚ በውብ ቋንቋ እንደገለጸው፡

*አባትሽ ምኒልክ እናትሽ ባፈና፣*
*ባልሽ ማመድአሊ አንቺ ማንአለብሽ፣*
*ለየትኛው ዳኛ አቤት ልበልብሽ!*

ለእኛ ግን ይህ ግጥም ቅኔ ብቻ አይደለም፤ ቁም ነገሩ ያለው ለየትኛው ዳኛ አቤት ልበልብህ የሚለው ላይ ነው፤

*ለኛስ እግዜር አለን፤ ይብላኝ ለሌላቸው፤*
*ይግባኙን ልከናል መልስ እንዲሰጣቸው፤*

በከባድ ወንጀሎች ተከሰሰን ፍርድ ቤት ቀረብን፤ አንከላከልም፤ አንሟገትም፤ አልን፤ ይህንን ማለታችን  በጭራሽ አንናገርም እንደማለት የተቆጠረብን ይመስላል፤ወደሌላ ሳንሄድ በኢትዮጵያ ውስጥ እንኳን ተከሳሽ የመናገር መብቱን አይነፈግም፤ በእውነተኛ የስዒረ መንግሥት ሙከራ የተከሰሱት ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ ለፍርድ ቤቱ የልባቸውን ተናግረው ነበር፤ በኪዩባ የፊዴል ካስትሮ የፍርድ ቤት ንግግር በመጽሐፍ መልክ ታትሟል፤ እኛ ግን እድሜ ልክ ለፈረደብን ፍርድ ቤት ለአምስት ደቂቃ እንኳን እንድንናገር አልተፈቀደልንም፤ እንዲያውም በአንድ ላይም ሆነ በተናጠል ለመናገር ፈቃድ ስንጠይቅ በፍርድ ቤቱ ብስጭትና ቁጣ በግልጽ ይታይ ነበር፡፡

ከማእከላዊ እስር ቤት ተይዘን ፍርድ ቤት ስንቀርብ እስከዚያን ጊዜ አይቼ የማላውቀው ነገር አየሁ፤ ብዙ የሕግ ጠበቃዎች በራሳቸው ተነሣስተው ለቅንጅት ተከሳሾች ለመቆም ደፍረው ቀረቡ፤ የዋስትና መብት እንዲከበርልንም በጣም አጥብቀው ተከራከሩልን፤ የተፈለገው ሕጋዊ ሥርዓትን ለመከተል አለመሆኑ ከተያዝንበት ዕለት ጀምሮ የተደረገው ሁሉ የሚያመለክት ነበርና የሕግ ጠበቃዎቹ የሕግ ክርክራቸውን አዳማጭም አላገኙም፤ የፍርድ ቤቱ ተልእኮ ፍትሕ ሊሆን እንደማይችል ጥርጣሬ የገባኝ ያን ዕለት ነው፤ ያለቀ የደቀቀ ፍርድ መስሎ የታየኝም ያን ጊዜ ነው፤  ገና ከመጀመሪያው ዳኞቹ ተከሳሾቹን በጥሞና ለማናገር ፈቃደኞች አልነበሩም፤ ተከሳሾች ለመናገር በሚፈልጉበት ጊዜ ዳኞቹ ቁጣ ቁጣ እያላቸው ለማሸማቀቅ የተዘጋጁ ይመስሉ ነበር፤ በዚያ ላይ የፍርድ ቤቱን ክብር የሚያዋርዱ ግልጽ ነገሮች ነበሩ፤ አንዱ በፍርድ ቤቱ ውስጥ ጠመንጃ የያዙ ወታደሮች ዙሪያውን ቆመውና ተቀምጠው ዳኞቹን፣ የከሳሹን ጠበቆች፣ ተከሳሾችንና ለነሱ ጥብቅና ለመቆም የመጡትንና ሊመለከቱ የመጡትን ሰዎች እያተኮሩ ይመለከቱ ነበር፤ ይህ ሁኔታ ፍርድ ቤቱ ለይስሙላም ቢሆን ነጻነት ያለው እንዳይመስል አድርጎታል፤ በተለይ የውጭ አገር ሰዎች በታዛቢነት ተቀምጠው ይህ መሆኑ የኢትዮጵያዊነቴ ክብር እንደተዋረደ በጣም ይሰማኝ ነበር፡፡

አንድ ጊዜ አቶ ፍሬ ሕይወት የሚባሉ ዳኛ ከ97 ምርጫ በኋላ የተፈጠረውን ግድያ ለማጣራት በምክር ቤቱ የተቋቋመውን ኮሚሽን መርተው በቃሊቲ ፍርድ ቤት ተከሳሾቹን አግኝተው ነበር፤ በዚያን ጊዜ የወህኒ ቤቱን ጠባቂዎች በሙሉ ከፍርድ ቤቱ አስወጥተው በሩን ከውስጥ ቆልፈውባቸው ነበር፤ ይህንን ያደረጉትን ሰው በጣም አደነቅኋቸው፤ እነዚህ መርማሪዎች በሙሉ ነጻነት ሥራቸውን ለማካሄድ የፈለጉትን ያህል የታጠቁ ወታደሮች መኖር የፍርድ ቤቱን ነጻነት የሚያኮስሰው መሆኑን ለመገንዘብ ሳይቻል መቅረቱ ያሳዝናል፡፡

ከዚያም በላይ ስልክ ለጠበቆቹም ለዳኞቹም ይደወል ነበር፤ በፍርድ ቤት ለተሰየሙ ዳኞች ደፍሮ ስልክ የሚደውል ዳኞቹን በአደባባይ ለማዋረድና



ልካቸውን እንዲያውቁ ለማድረግ ካልሆነ በቀር ለተመልካቹ ሌላ ምንም መልእክት የለውም፤ ዳኞቹ በበኩላቸው በፍርድ ቤት ተሰይመው ስልክ ለመቀበልና ለማነጋገር መቻላቸው እንዴት ያለ ክፉ ወጥመድ ውስጥ እንዳሉና የነጻነታቸውም ልክ ምን ያህል እንደሆነ የሚያመለክት ነው፡፡

ከሁሉም በላይ የሚያሳዝነው ፍርድ ቤቱን የሚመሩት ዳኞቹ ሳይሆኑ የከሳሽ ጠበቃዎች መሆናቸው ነው፤ አንዳንዴ የከሳሽ ጠበቃዎች ዳኞቹ ከተሰየሙ በኋላ ይገባሉ፤ ዳኞቹም እነሱን ይጠብቃሉ፤ በከሳሽ ጠበቃዎችና በዳኞች መሀከል የተረጋገጠ የሥልጣን ተዋረድ አለመታየቱን ለማሳየት ብለን አንድ ቀን ዳኞች ከተሰየሙ በኋላ የከሳሽ ጠበቃዎች ሲገቡ ከመቀመጫችን ተነሣንላቸው፤ ግራ የተጋቡት የከሳሽ ጠበቃዎች ፈገግታ እያሳዩን ባንስማቸውም በእግዚአብሔር ብለውን ተቀመጡ! ከዚያም በላይ የከሳሽ ጠበቃዎችና የተከሳሽ ጠበቃዎች በፍርድ ቤት እኩል እንደማይታዩ የሚያመለክተው በወንበሮቻቸውና በጠረጴዛዎቻቸው ልዩነት ነው፤ የተከሳሽ ጠበቃዎች ጠረጴዛ ውብ ልባስ ነበረው፤ የተከሳሽ (የነዳንኤል) ጠበቃ ጠረጴዛ ራቁቱን ነበረ፡፡

ሁላችንም የተከሰስነው ሕገ መንግሥቱ በፈቀደው መብትና ነጻነት በመጠቀም በምርጫ ውድድሩ ጊዜ በተናገርነውና በጻፍነው ጉዳይ ነው፤ ከዚያ ውጭ ምንም የተደረገ ነገር የለም፤ በምርጫው ጊዜና ከምርጫው በኋላ የተፈጸሙትን ወንጀሎች ራሱ መንግሥት አጣሪ ኮሚሽን አቋቁሞ በከፊልም ቢሆን ተጣርቶ የወጣውን መግለጫ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ዓለም በሙሉ ያወቀው ጉዳይ ሆኖአል፤ ደረቁን እውነት ሸፍነው ባረጀና ባፈጀ የገዢዎችና የአሽከሮቻቸው የበደለው ንጉሥ፣ ባላገር ይካስ በሚል መመሪያ ተከሰስን፤ወንዙ ይወርዳል፤ ጅቡ ከወንዙ ይጠጣል፤ አህያዋም ከታች ትጠጣለች፤ ጅቡ «የምጠጣውን ውሀ ለምን ታደፈርሺብኛለሽ?» ብሎ ይቆጣል፤ አህያዋ አያ ጅቦ ሳታመኻኝ ብላኝ አለች፤ ሌላ መከላከያ አልነበራትም ሕገ አራዊት ነውና፡፡

በዚህ ከእኩይ መንፈስና ከታመመ አእምሮ በመነጨ ክስ ተይዘን ለሃያ አንድ ወራት ያህል ታሰርን፤ ከእኩይ መንፈስ የመነጨ የሚያደርገው ድፍን ውሸት መሆኑ ነው፤ ከድውይ አእምሮ የመነጨ የሚያደርገው ደግሞ ትክክለኛ አእምሮ ሊገባውና ሊቀበለው የማይችል ስንኩል አስተሳሰብ መሆኑ ነው፤ አንድ ማስረጃ ብቻ ማቅረብ ይበቃል፡፡

ይህንን ጉዳይ አንድ ምሳሌ ብቻ ሰጥቼ ልለፈው፡፡ የክሱን መሠረታዊና አጠቃላይ የአስተሳሰብ ግድፈት ለመረዳትና ማስረጃ የተባለውን ቪድዮ በጠበቃው ጭብጥ ማጣመም ብቻ ሳይሆን መለወጥ እንደተቻለ በእኔ ላይ የተለጠፈውን ክስ እንመልከተው፤ ሕገ መንግሥቱን ሕገ አራዊት ነው ብሏል የሚል ነው፤ ይህ ትርጉም የሌለው ሀሳብ ቢስና ጭንጋፍ ነገር በእኔ አእምሮ አልተፀነሰም፤ ከእኔ አንደበት አልወጣም፤ ሊወጣም አይችልም፤ ሕገ

መንግሥትና ሕገ አራዊት ሁለት ተቃራኒ ሀሳቦች ናቸው፤ ሁለት በፍጹም ተቃራኒ የሆኑ ነገሮችን ደርድሬ አንድ ናቸው ብዬ እንደከሳሾቼና እንደጠበቆቻቸው በስንኩል ማሰብ አልችልም፤ ከዚያም በላይ ሕገ መንግሥት ምን ማለት እንደሆነ አውቃለሁ፤ በአንጻሩም ሕገ አራዊት ምን ማለት እንደሆነ አውቃለሁ፤ ስለዚህም የሰማይና የመሬት ያህል እንደሚራራቁ እገነዘባለሁ፤ እንዲያውም አንዱ በሥራ ላይ በዋለበት ሌላው ሊኖር አይችልም፤ ወይም ሁለቱ በጦርነት ላይ እንደሆኑ አውቃለሁ፤ በምንም ተአምር አንዱ ሌላውን ሊሆን አይችልም፤ ይህንን ያለው ሰው በሕገ መንግሥትና በሕገ አራዊት መሀከል ያለው ልዩነት ያልገባው ሰው ነው፤ አቶ በረከት ነው፤ ለዚያውም ወዲያውኑ ተቃውሞ መልስ ሰጥቼዋለሁ::

በቅርቡ ደግሞ አንድ ተመሳሳይ ሐሰት በአቶ ሥዩም መስፍን መነገሩን በአንድ ጋዜጣ ላይ አንብቤአለሁ፤ ወያኔ ሥልጣን ለመያዝ ሲቃረብ እኔ ሥልጣኑን አስረክቡኝ ብዬ ጠየቅሁ፤ ይላል! ነገሩን ለማቅለል ወይ እኔ ቂል ነኝ፤ ወይ እሱ ቂል ነው! ይህንን ሰው በአካል አግኝቼው የማውቅ አይመስለኝም፤ በለንደን ከአቶ መለስ ጋር ስንገናኝ ከኋላ ተቀምጦ ነበር ይሆናል፤ ግን አላስታውሰውም፤ ብዙ ምስክሮች ነበሩ፤ አቶ አብዱል መሀመድ፣ ፕሮፌሰር እንድርያስ እሸቴ፣ አቶ ይስሐቅ ክፍሌና ሌሎችም ነበሩ፤ ለመዋሸት የሚያመች ሁኔታ አልነበረም::

ሕገ መንግሥት ሕገ አራዊት ነው ማለት ብርሃን ጨለማ ነው፤ ወይም ሕይወት ሞት ነው እንደማለት ያለ የአእምሮ ጉድለትን የሚያመለክት የተሰናከለ አስተሳሰብ ነው፤ ሕገ መንግሥቱ ሕገ አራዊት ነው ማለቱ ከተረጋገጠ እንዲህ ያለው ሰው ወደ እስር ቤት ሳይሆን ወደ ትምህርት ቤት ወይም ወደ አእምሮ ሀኪም ቤት መላክ ያለበት ይመስለኛል፤ ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ፍርድ ቤቱ የቀረበውን ማስረጃ አረጋግጫለሁ ያለ መሰለኝ፤ ዓይንንና ጆሮን ከዶ የከሳሽ ጠበቃን «ጭብጥ» በመቀበል ተረጋግጦአል ለማለት ይቻል ይሆናል፤ እውነት አለመሆኑን ግን በማናቸውም ጊዜ ቪድዮውን አይቶ እኔ የተናገርሁትን የሰማ ሊያረጋግጠው ይችላል፤ የከሳሽም፤ የጠበቃዎችም፣ የዳኞችም ልጆች በአባቶቻቸው ላይ እንዲፈርዱ ብቻ ሳይሆን እንዲያፍሩባቸው የሚያደርጋቸው ነው::

በምርጫው ክርክር ጊዜ በሂልተን ሆቴል እኔ ንግግሬን የጀመርሁት በሰብአዊ መብቶች በኩል ሕገ መንግሥቱን በማወደስ ነው፤ በሕገ መንግሥቱ ውስጥ ሠላሳ በመቶ የሚያህሉት አንቀጾች ስለሰብአዊ መብቶች ጉዳይ መሆናቸውንና ዓለም-አቀፍ ሕጎችም የተካተቱበትን ይህ ቀረ የማይባል ሰነድ መሆኑን በመግለጽ ነው፤ ስለሕገ አራዊት ያነሣሁት በተግባር የሚታየውን በማነፃፀር እንጂ ሕገ መንግሥቱን በሰብአዊ መብቶች ጉዳይ ለመንቀፍ አይደለም፤ ይህ በቪድዮ የተመዘገበ ነው፤ በዚህ የተነሣ የቀረበብኝ ክስ በፍጹም



ሐሰት ነው፤ በዚህ ክስ ጠበቃው ተከራክሮ፣ ፍርድ ቤቱ የዕድሜ ልክ እስራት ፈረደብኝ፤ አልተከላከልሁም፤ ይግባኝም አላልሁም፤ የከሳሽ ጠበቃ ግን የዕድሜ ልክ እስራት አይበቃም ብሎ የሞት ፍርድ እንዲፈረድለት ይግባኝ አለ፤ መጥሪያው ከደረሰን በኋላ ንቀው የተውት መሰለኝ፤ ሥርዓት ያለው መልስ አላገኘንም::

## 7. መገልበጥና መለወጥ

ሕዝብ የሥልጣን ምንጭ በሆነበት ሥልጡን አገር በሕጋዊ ምርጫ ሕዝብ ፈቃዱን በድምፁ እየገለጸ የመንግሥትን ሥልጣን ከተወዳዳሪ ቡድኖች ውስጥ ለአንዱ ይሰጣል፤ በዚህ መንገድ የመንግሥት ባለሥልጣኖች ሲለዋወጡ መንግሥት ተገለበጠ፤ መንግሥት ፈረሰ አይባልም::

ሀ/ በማናቸውም የቅንጅት ሰነድ ላይ «መገልበጥ» የሚለውን ቃል የተጠቀመበት የለም::

ለ/ በፍርድ ቤት ማስረጃ ሆነው በቀረቡት ቪዩዮች፣ ቴፖችና ሰነዶች ውስጥ «መገልበጥ» የሚለውን ቃል ማንም ሰው ሲጠቀምበት አልተሰማም::
«መገልበጥ» የሚለው ቃል የኃይል ወይም በጡንቻ የማፍረስ ባሕርይ አለበት፤ በተለይም ዓመፅ ከሚለው ቃል ጋር ሲቀናጅ ከፖለቲካ ትግል ይልቅ ወደ ጉልበት ትግል ያዘነብላል::

ዓመፅ በቁሙ ጉልበት የለበትም፤ እንዲያውም ዓመፅ ከጉልበት ለመላቀቅ መሞከርን፣ እምቢ ማለትን ስለሚያመለክት ከመገልበጥ ጋር የሕርይ ዝምድና የለውም፤ በጆርጂያና በዩክሬን የታየው ሕዝባዊ ዓመፅ በአንድ በኩል እንደጥሩ የሰላማዊ ትግል ዘዴ ሲጠቀስ በሌላ በኩል ደግሞ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ፣ እውነቱን በሐሰት ለመተካት በማቀድ ይሁን የጆርጅያና የዩክሬን ሕዝባዊ ዓመፅ በኃይል መንግሥትን መገልበጥ ተደርጎ ይወሰዳል፤ በሁለቱ አገሮች የተደረገው ሕዝባዊ ዓመፅ አንድ ጥይት ያልተተኮሰበት፣ ፖሊሱም ሆነ የጦር ሠራዊቱ ሰላምን ከማስከበር ውጭ ወገን ለይቶ ያልገባበት፣ ሕዝቡ በሰላማዊ እምቢተኛነት የሥልጣን ባቤትነቱን ያረጋገጠበት ነው፤ በጆርጂያና በዩክሬን መሪዎች ሰላማዊ ሕዝብ በጥይት እንዲደበደብ ለፖሊስና ለጦር ሠራዊቱ ትእዛዝ የሰጠ ባለሥልጣን የለም፤ ወይም ቢሰጡም የሰማቸው አላገኙም ነበር፤ በፍጹም ሰላም የተገኘውን ለውጥ በኃይል ወይም በጉልበት የመጣ ማስመሰል ዓለም በሙሉ ከደረሰበት ግንዛቤ ውጭ የሆነ ነው::

ከሳሽ በድፍን ሐሰት ላይ ቆሞ የከበደ ክስ ሲመሠርት መንግሥትን ለመገልበጥ አድመዋል፤ በኃይል ወይም በጉልበት ዓመፅ ሕገ መንግሥታዊ

ሥርዓቱን ለመገልበጥ ሞክረዋል፤ሲል በፍርሃትና በስጋት ጭንቀት ውስጥ ያለ ሰው መኪናው ሁሉ ታንክ፣ በራሪ ወረቀት ሁሉ አውሮፕላን፣ ንግግሩ ሁሉ ጥይት እየመሰለ ቢታየው አያስደንቅም ይሆናል፤ ነገር ግን እንኳን በመልክ በስም የማይተዋወቁ ሰዎችን ከአውሮፓና ከአሜሪካ መልምሎ በአድማ ማጣመድ ምን የሚሉት ዘዴ ነው? የቅንጅት አባል ያልሆኑትን ሁሉ ሰብስቦ በአድማ ተጠምደው ነበር እያለ ውሸት ከምሮአል።

ሁለት በጣም የሚደንቁ ነገሮች አሉ፤ አንደኛው፣ ከሳሽ ለአድማ ለተባለው ያቀረበው ምንም ማስረጃ የለም፤ ሊኖርም አይችልም፤ በመጀመሪያ ደረጃ የቀረቡት የአድማ ማስረጃዎች ቪድዮዎች ሲሆኑ አንዳንዶቹም በቴሌቪዥን የታዩ ናቸው፤ አንዳቸውም የምሥጢርነት ባሕርይ የላቸውም፤ በነዚህ ቪድዮዎች ውስጥ አንድም በሰያፍም እንኳን በኃይል መንግሥትን መገልበጥ የሚል ሀሳብን ያንጸባረቀ ሰው ድምፅም አልተሰማም፤ ስለዚህም ፍርድ ቤቱ በአደባባይ ከታየውና ከተሰማው የተለየ ግንዛቤ ሊኖረው ይችላል ብሎ ለመገመት አስቸጋሪ ይሆናል፤ ፍርድ ቤቱ እነዚህን ቪድዮዎች የውሸት ስም ተሰጥቶት «ጭብጥ» ከሚባለው የከሳሽ ፈጠራ ለይቶ ከተመለከተው የከሳሽ ማስረጃ ተብሎ የቀረበው የተከሳሾች መከላከያ ሆኖ ይቀርብ እንደሆነ እንጂ ክስ ለመመሥረት የማያስችልና ለሐሰት ክሱቹም ማስረጃ የማይሆን ነው፤ ነገር ግን ከብይኑ ለመገመት እንደሚቻለው ፍርድ ቤቱ ቪድዮቹን ሳይሆን የከሳሹን «ጭብጥ» የተጠቀመበት ይመስላል፤ በቀጥታ ከቪድዮዎቹ ካገኙት መረጃዎች ይልቅ የከሳሹን ጠበቃ «ጭብጥ» ለመቀበል ዝንባሌ እንደነበረ የሚያመለክት ነው።

ሁለተኛው የማስረጃ ዓይነት የተለያዩ መግለጫዎችና በራሪ ጽሑፎች፣ በጋዜጣም ላይ የወጡ አስተያየቶች ናቸው፤ በነዚህም ውስጥ ቢሆን መንግሥትን በኃይል ወይም በጉልበት መገልበጥ ለሚለው ክስ ተጨባጭ ማስረጃ ይሆናል የሚባል አንድም የለም፤ እነዚህ የሰነድ ማስረጃዎች በከሳሹ የተዛባ ግንዛቤ ካልታዩ በቀር በራሳቸው አንድም ወደ ኃይል ወይም ወደ መንግሥት መገልበጥ የሚያመለክት ነገር የለም።

ጭቆናና ስቃይ ሸሽተው በውጭ አገር በስደት ላይ የሚኖሩትን ኢትዮጵያውያንን ከቅንጅት ጋር አያይዘው የአድማ ተባባሪ ማድረጋቸው የውሸት ክሱ መውደቂያ ነው፤ በአሜሪካ ቁጣ የብዙዎች ስም ከተከሳሾቹ ዝርዝር መሰረዙ ውሸቱን ከማጋለጡ በላይ አሳፋሪ ነው።

እንዲያውም የመንግሥትን ሥልጣን በሕዝብ ድምፅ የተሸነፈው ለአሸናፊው እንደሚያስረክብና በዚህም ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ መንገድ ለውጥ እንደሚደረግ ሕገ መንግሥቱ ያዝዛል፤ በመሠረቱ የፖለቲካ ቡድኖች በምርጫ ጊዜ የሚያሳዩት ውድድር በአንድ በኩል በሥልጣን ላይ ያለው ቡድን ያለውን ዓላማ ይዞ እንዲቀጥል፣ በሌላ በኩል ደግሞ ተቀናቃኝ የፖለቲካ ቡድኖች



ለለውጥ ያላቸውን ዓላማ ይዘው ነው፤ ይህ ዴሞክራሲያዊ አሠራር የሥልጣን ባለቤት ሕዝብ ነው ከሚለው ዴሞክራሲያዊ እምነት የሚነሣ ነው፤ ሕዝብ በሥልጣን ላይ ያሉትን አውርዶ ሌሎችን በሥልጣን መንበር ላይ ማስቀመጥ ይችላል፤ ይህ የመለዋወጥ ሥርዓት ሕጋዊ ነው፤ ስለዚህም በምርጫ ጊዜ በሥልጣን ላይ ያሉትን እናወርዳለን ወይም እንለውጣለን ማለት ከመገልበጥ ጋር ምንም ዝምድና የለውም፤ በሕዝብ ምርጫ በሥልጣን ላይ ያለውን ቡድን ለማውረድና ለመለወጥ የሚደረገውን የፖለቲካ ሰላማዊ ትግል ከኃይል፣ ዓመፅና የመንግሥት መገልበጥ ጋር ማያያዝ በሁለቱም ተቃራኒ በሆነ ዘዴዎች ላይ የግንዛቤ ችግር መኖሩን ያመለክታል፤ ለውጥን በሕጋዊ ሥርዓትና በሰላማዊ መንገድ ለማያውቁ በኃይል ግልበጣ ብቻ ሊገነዘቡት ይችላሉ፤ ነገር ግን ፍርድ ቤቱ ይህንን እውነት መረዳቱ ያጠራጥራል፤ በሕጋዊ ሥርዓትና በአደባባይ ዓለም ሁሉ እያየው የተካሄደውን የለውጥ ውድድር እንደግልበጣ ሙከራ ተወስዶ የተመሠረተው ክስ ከእውነት የራቀ ግልጽ የተንኮል ዘዴ ፍርድ ቤቱ ሳተው።

መንግሥትን በኃይል ለመገልበጥ ሞክረዋል ለሚለው ፍርሃትና ስጋት መነሻው ምንድን ነው መነሻው የምርጫ 97 በመንግሥት በኩል በፍጹም ያልተጠበቀ ውጤት ነው፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ በነቂስ ወጥቶ ምርጫው ቅንጅት እንደሆነ የሚያመለክቱ አዝማሚያዎች ገና ከመጀመሪያው መታየት ጀመሩ፤ ፍርሃትና ስጋቱን የፈጠረው ይህ ወደአልተጠበቀ ውጤት የሚያመራ መስሎ መታየቱ ነው፤ ይህንን ሁኔታ በጉልበት ለመቀልበስ ወይም ለመገልበጥ የድምፅ ሣጥኖቹ መነካካትና አላግባብ ውጤቱን ወደተፈለገው ለማድረስ የተደረገው ሙከራ ነው፤ በአዲስ አበባ የሕዝቡ የንቃት ደረጃ በጣም ከፍ ያለ በመሆኑና ታዛቢዎችም በብዛት ተሰማርተው ስለነበረ የምርጫውን ውጤት ለመቀልበስ የተደረገው ሙከራ ሳይሳካ ቀረ፤ በገጠሩ ግን የተደረገውን የድምፅ ዘረፋ ለመከላከል አልተቻለም፤ ልዩ ዓይነት በጉልበት መገልበጥ የሕዝብን እውነተኛ ድምፅ በጉልበት መለወጥ ነው።

ቅንጅት ይህንን በገጠር የተደረገውን ምርጫውን በጉልበት መገልበጥ አልቀበልም አለ፤ ሕዝቡም በብዙ ቦታዎች ተቃውሞውን መግለጽ ጀመረ፤ ሰላማዊው የቅንጅትና የሕዝብ ተቃውሞ ሁለተኛውን የኃይል ወይም የጉልበት እርምጃ አስከተለ፤ ብዙ ሰዎች ታሰሩ፤ ብዙ ሰዎች አካላዊ ጉዳት ደረሰባቸው፤ ብዙ ሰዎች ተፈናቀሉ፤ ብዙ ሰዎች ተገደሉ፤ ቀጥሎም አገዛዙ ሦስተኛውን የኃይል ወይም የጉልበት እርምጃ ወሰደ፤ ከቅንጅት አመራር እየመረጠና ከአመራር ውጭ ያሉትን አባላት እየለየ፣ ጋዜጠኞችንም እንዲሁ፣ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችም ሰዎችን ሰብስቦ አሰረ፤ የሚያስደንቀው ነገር የተከሰተው በዚህ ሦስተኛው ደረጃ ላይ ነው፤ አገዛዙ በወሰደው የጉልበት እርምጃ ለጠፋው

ሕይወትና ለወደመው ንብረት ኃላፊነቱን በተከሰሱት ሰላማውያን ሰዎች ላይ ለጠፈው፡፡ የጥንቱ የበደለው ንጉሥ፣ ባላገር ይካስ ዓይነት፡፡
ከሶቹም ሆኑ ለፍርድ ቤት የቀረቡት ማስረጃዎች ሁሉ የሚያመለክቱት ከላይ እንደተዘረዘረው ሲሆን በዚህ መሠረት በፍርድ ቤቱ የተሰጠው ብይን የበደለው ንጉሥ ባላገር ይካስ የሚለውንና የተረሳውን አባባል የሚያስታውስ ነው፤ የድርጊቶቹን ቅደም ተከተልና ተከታታይነት በሚገባ የተገነዘበ ሰው የኃይል ወይም የጉልበት እርምጃ መቼና በማን እንደተጀመረ ለመለየት አያዳግተውም፤ ከዚያም በላይ በንብረትም ላይ ሆነ በሰው ላይ የደረሰውን ጉዳት ማን ምን ያህል ብሎ ለመገመት አስቸጋሪ አይደለም፤ በተጨማሪም ባልታወቀ ምክንያት ተነሣስተው ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ የተሰበሰቡት ወጣቶች በጥይት የተገደሉት በቅንጅት አቅድ እንዳልሆነ ግልጽ ነው፤ ይህ ሁሉ ሲጠራቀም የሚያመለክተው የወንጀል ፈለግ ወደ ሌላ አቅጣጫ መሆኑን ነው፡

የፍርድ ቤቱ ብይን ምክንያትና ውጤት ይዛመዳሉ ሲል ምክንያት ያደረገው፡-

ሀ/ የምርጫው ውጤት ተጭበርብሮአል መባሉንና መዘረፉን አይደለም፤
ለ/ ከሰኔ አንድ በፊት በብዙ ሰዎች ላይ የደረሰውን ድብደባ፣ እስርና ግድያ አይደለም፤

እንዲያውም የሰኔ አንዱና የጥቅምት 22/1998 ጭፍጨፋ ቢሆንም እንደምክንያት አልተወሰደም፤ ምክንያት ተብሎ የተወሰደው ተከሳሾች በምርጫ ዘመቻው ጊዜና የምርጫው ውጤት ተጭበረበረ ከተባለ በኋላ በተለያዩ ጊዜያትና በተለያዩ ቦታዎች ያደረጉትን ንግግር ነው፤ እነዚህ ንግግሮች በጊዜም ሆነ በቦታ ወንጀል ከተባለው ድርጊት ጋር በጣም የተራራቁ ናቸው፡፡

ፍርድ ቤቱ መጀመሪያውኑ ክሱን ተቀብሎ እንድንታሰር ማዘዙ ሲያስደንቀኝ፣ በዋስ እንዳንለቀቅ መበየኑ ሲያስገርመኝ ከሳሽና ጠበቃው ያቀረቡትን የቪድዮ ማስረጃ አይቶና ሰምቶ ውሳኔ በመስጠት ፋንታ የጠበቃውን የተጨማደደ ጭብጥ ለውሳኔው መሠረት ማድረጉ ሲያሳዝነኝ ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ ዓይነት ተከላከሉ ተብሎ ሲወሰን እግዚአብሔር ከዚያ ቤት እንደወጣ ገባኝ፤ በዚህም ፍርድ ቤቱ ደኸየ ወይም በልማድ እንደሚባለው ውቃቢ ራቀው፤ ስለዚህም ያንን የክስና የተከሳሶች ድሪቶ ማስረጃ ከተባለው ጋር ተቀብሎ ተከላከሉ ብሎ መወሰን የፍርድ ሚዛን እንደተረገጠ ማረጋገጥ ነው፤ በመጨረሻም የዕድሜ ልክና ከዚያም ያነሰ ፍርድ ተሰጠ፤ አብዛኛዎቹ ተከሳሾች ሳቁ፤ አላዘኑም፡፡

በመጀመሪያ ይህ ፍርድ ቤት ከአንድ ዓመት ተኩልና በሙሉ ድምፅ ባይሆንም የሰውነታችንን ክብር የሚያዋርደውን፣ የታሪካችንንና የባህላችንን ኩራት የሚገፍፈውንና የልጆቻችንንና የልጅ ልጆቻችንን ሕይወት



የሚያጨልመውን የትግሬን ዘር የማጥፋት ክስ በመሰረዙ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

ከዚህ ቀጥዬም በመጀመሪያ ስለ ክሱና ስለብይኑ በአጠቃላይ፣ ሁለተኛም በግል በእኔ ላይ ስለቀረበው ክስና ብይን በአጫጭሩ አስተያየቴን እሰጣለሁ፤ ሁነቶቹ በቅደም ተከተላቸው የሚከተሉት ናቸው፡፡

1 ምርጫው
2 የምርጫው ውጤት ልክ አይደለም የሚል ወቀሳ -- መነሻ
3 በ(2) ምክንያት የተነሣው ሰላማዊ ተቃውሞ -- በንግግር
4 ተቃውሞውን ለመቋቋም የተወሰዱ የኃይል እርምጃዎች -- ድርጊት
5 የኃይል እርምጃዎቹን የቀሰቀሱት ሰላማዊ ተቃውሞዎች -- ድርጊት
6 የመጨረሻው የብዙ ወጣቶችን ሕይወት የቀጠፈው የኃይል እርምጃ --ሰኔ 1/97 እንደገና ጥቅምት 22/98 -- ድርጊት

## 8. እስርና ክስ

እንግዲህ ክሶቹ የተመሠረቱት በተራ ቁጥር /3/ በተገለጸውና ከዚያ በኋላ በተከታታይ በተፈጸሙት ድርጊቶች ላይ ነው፤ ከላይ ከ/1/ እስከ /7/ በተዘረዘሩት ተከታታይና ተዛማጅ ሁነቶች መሀከል /2/፣/4/፣/6/፣/7/ ድርጊቶች ናቸው፤ ማለትም በገቢር የተፈጸሙ ናቸው፤ /3/ና/5/ ከንግግር ያላለፉ፤ ቢበዛም በሰላማዊ ተቃውሞ የተገለጹ ናቸው፤ በተቃውሞው ውስጥ ከቅንጅት መመሪያ ውጭ የድንጋይ ውርወራ እንደነበረ ታውቆአል፡፡

ፍርድ ቤት ምክንያትና ውጤት ለመዛመዳቸው ያገኘው ግንዛቤ በተራ ቁጥር /1/ና በተራ ቁጥር/3/ የተገለጹትን አስወጥቶ እንደሆነ ግልጽ ነው፤ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 24/2 የተደነገገውን የምክንያትና የውጤት መቋረጥ ያላገናዘበ ነው፤ በተራ ቁጥር /2/ና በተራ ቁጥር /3/ የተገለጹትን ሁነቶች ተከታታይነትና ተዛማጅነት ይዞ ያልተነሣ አስተሳሰብ በምንም የአስተሳሰብ መንገድ ትክክለኛ ሊሆን አይችልም፤ በተጨማሪም ፍርድ ቤቱ በገቢርና በነቢብ ወይም በድርጊትና በንግግር መሀከል ምንም ልዩነት ሳይታየው መቅረቱ የሚያስገርም ነው፤ የትኛው ውጤት ከየትኛው ምክንያት ጋር ተዛምዶ ነው የተመሠረተውን ክስ ሊያጸናው የሚችለው? በገቢር ለተፈጸመው ወንጀል የነቢብ አጠራጣሪ ምክንያት መፈለግ አህያውን ፈርቶ ዳውላውን ከሚለው ተረትም የባሰ ነው፡፡

በያገሩ በየጊዜው ሰላማዊ ሰልፎች ይደረጋሉ፤ አንዳንዴ በሰልፉ ላይ ሰዎች ይጎዳሉ፤ ነገር ግን ሰልፉን የጠራው ድርጅት ወይም ቡድን በወንጀል ለመከሰስ ሲበቃ አልታየም፤ በቅርቡ በዩጋንዳ መንግሥት አንድ የኖረ ጫካ ለአንድ ስኳር አምራች የሕንድ ኩባንያ ሸጠ፤ የአካባቢ ጥበቃ ድርጅት ሸያጩን

ለመቃወም ሰላማዊ ሰልፍ ጠራ፤ በሰልፉ ላይ በመንገድ አንድ የሕንድ ሰው ሲያዩ ደማቸው የፈላ ሰዎች በድንጋይ ቀጥቅጠው ገደሉት፣ ቀጥሎም የሒንዱን መቅደስ ሲያዩ አቃጠሉት፤ እነዚህ ድርጊቶች ከሰላማዊው ሰልፍ ዓላማ ጋር ግንኙነት የላቸውም፤ ሳይታሰቡና ሳይታቀዱ በድንገት በደም ፍላት የተፈጸሙ ናቸው፤ ወንጀል ተፈጽሞአል፤ አያጠራጥርም፤ ለዚህ ወንጀል ኃላፊነቱ የማን ነው? በኢትዮጵያ ቢሆን የዘር ማጥፋት ወንጀልም ይጨመርበት ነበር፤ የቅንጅት አመራር የጠራው ሰላማዊ ሰልፍ ሳይኖር ነው ፍርድ ቤቱ ምክንያትና ውጤት ተያይዞአል ያለው፤ የፍርድ ቤቱ ብይን አስተሳሰብ ከዚህም ያልፋል፤ ገቢርን በፍጹም አስወጥቶ በነቢብ ብቻ የቀረበለት ማስረጃ ሁሉ ለከሳሹ የማይመች በመሆኑ ወደ አልተባለና ወደአልታሰበ ዓላማ በመለወጥ ቀናውንና ቀጥተኛውን ንግግር የራሱን ትርጓሜ ሰጥቶታል፡፡

ፍርድ ቤቱ ችግር ውስጥ የገባው ከመጀሪያው ነው፤ አንደኛ አድማ ተብሎ የጅምላ ክስ ሲቀርብለት ወንጀል የግል መሆኑን ለማጣራት አልሞከረም፤ ሁለተኛም አድማ ተብሎ ለቀረበው ክስ አድመኞቹ በመልክና በስም የሚተዋወቁ መሆናቸውን፣ በድብቅና በምሥጢር ማቀዳቸውን ለማረጋገጥ አልሞከረም፤ ክሱን ለመመሥረት የቀረበው ማስረጃ ሁሉ አደባባይ የወጣ ነበር፤ አንዱንም ተከሳሽ በወንጀል የሚያስጠረጥር ማስረጃ አልቀረበም፡፡

በመጨረሻም በብይኑ ላይ የተንበጸባረቀው ይኸው ከላይ የተጠቀሰው ጉድለት ነው፤ አድማ የተባለውን ለመጣል ፍርድ ቤቱ ተቸገረና የከሳሹን የአድማ ትርጉም ለማጥበብ ተሞከረ፤ ቀላል መስሎ የታየው የቅንጅት የላዕላይ ምክር ቤት አባሎችን የአድማው መሪዎች ማድረግ ሆነ፤ ነገር ግን ምናልባት አንድ ሦስተኛ የሚሆኑ የላዕላይ ምክር ቤት አባሎች ተገኙለት፤ አድመኞቹ የላዕላይ ምክር ቤት አባላት ከሆኑ ይህ የታወቀው መቼ ነው? ያልተያዙ፣ ያልታሰሩና ያልተከሰሱ የምክር ቤቱ አባላት ከአድማው እንዴት አመለጡ? ይባስ ብሎም በላዕላይ ምክር ቤት ውስጥ የሌለውን አንድ ሰው (እኔን) እንደመጣያ አድርጎ ጨመረው፤ ባይሆንም ግድ የለም ብሎ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ፍርድ ቤቱ የላዕላይ ምክር ቤት አባልነትን የሚወስን ሆነ፤ ያስወጣቸው አሉ፤ የክብር አባል አድርጎም ያስገባው አለ፤ በዚህ አንካሳ ሁኔታ አድማ የሚለው አጉል አስተሳሰብ ሳይወድቅ ቀረ፤ ከዚህም ጋር ተያይዞ ወንጀል የግል መሆኑ በጠንካራ ምርመራ ሳይጠራ አመለጠ፤ የአድማው ቡድን በዘፈቀደ ከተመሠረተ በኋላ የጅምላ ወንጀል ለተሸከሙት በተናጠል ወንጀል እየተፈለገላቸው ተለጠፈባቸው፤ ምክንያትንና ውጤትን በግድ ለማገናዘብ ስለተፈለገ ለማስረጃዎቹ ልዩ ትርጉም መስጠትና ወደ ጥንቆላ መግባት አስፈላጊ ሆነ፤ ሴትዮዋ ወደጠንቋይ ቤት ሄዳ ልጅ መውለድ እንዳልቻለች ተናግራ እንዲረዳት ትማጸናለች፤ ጠንቋዩ ከመጀመሪያ ባልሽ ወንድ ልጅ ትወልጃለሽ ሲላት የመጀመሪያ ባልዋ መሞቱን ስትነግረው ቢሆንም አላት ይባላል፤ አሁንም



እኔ የቅንጅት ላዕላይ ምክር ቤት አባል ባልሆንም ፍርድ ቤቱ ቢሆንም ብሎ አስገባኝና ፈረደ! ሌሎች የላዕላይ ምክር ቤት አባላት ከክሱ ውጭ የሆኑት እንዲሁ ቢሆንም በሚል ዘዴ ነው ማለት ነው፤ የቢሆንም ዘዴ የሌለበትን ለማስገባትም ሆነ ያለበትን ለማስወጣት ይጠቅማል ማለት ነው!

## 9. አጠቃላይ አስተያየት

የተከሰስንበት መሠረታዊ ጉዳይ መንግሥትን በኃይል ለመለወጥ በመሞከርና ሕገ መንግሥቱንና የሕገ መንግሥቱን ሥርዓት ለማፍረስ በመፈለግ ነው ተብሎአል፡፡

ሕገ መንግሥት ሲባል ለከሳሽና ተከሳሽ አንድ ከሆነ ተከሳሾቹ ሕገ መንግሥቱን ለማፍረስ የሚፈልጉበት ምንም ምክንያት የለም፤ ለዚህም ዋናው ምክንያት ሕገ መንግሥቱ ብቸኛ መከታቸው መሆኑ ነው፤ እንዲያውም በቅንጅት ጉዳይ የተከሰሰው ሁሉ ሕገ መንግሥቱ የሚያጎናጽፈውን መብትና የዳኝነት ተስፋ በመጠቀሙ ነው፤ ከሳሽና የከሳሽ ጠበቃ ሕገ መንግሥቱን ያውቁታል ወይስ ችላ ብለውታል ብሎ ለመጠየቅ የሚያስደፍሩ ምክንያቶች ብዙ ናቸው፤ ከሁሉ በፊት ሕገ መንግሥቱ **የመደራጀት፣ የመሰብሰብና ሀሳብን ያለምንም ገደብ የመግለጽ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ፣ የመምረጥና የመመረጥ መብቶችን ለዜጎች ሁሉ በእኩልነት ያጎናጽፋል**፤የመንግሥት ሥልጣን ባለቤቱና ምንጩ የኢትዮጵያ ሕዝብ መሆኑን ይደነግጋል (አንቀጽ 8)፤ ከሕዝቡ በድምፅ ብልጫ ውክልናን ያገኘ ወይም ያገኙ የፖለቲካ ቡድኖች ሥልጣንን በሰላም እንደሚረከቡ ያዛል (አንቀጽ 56 60)፤ በዚህም መሠረት አዲስ መንግሥት መፍጠር ወይም ማቋቋም እንደሚቻል ይናገራል (አንቀጽ 60/2)፤ በሕገ መንግሥቱ ከተደነገገው ውጭ በኃይል ወይም በጉልበት የመንግሥት ሥልጣን እንዳይያዝ ይከለከላል (9/3)፤ ሕገ መንግሥቱ ፍጹምና ዘለዓለማዊ ባለመሆኑም ለማሻሻል የሚቻልበትን መንገድ ይደነግጋል (105)፤ በአጠቃላይ በመብቶች ጉዳይ ሕገ መንግሥቱ ይህ ቀረው የማይባል ሰነድ ነው፡፡

በሚያዝያ 29/97 ወያኔ/ኢሕአዴግ ከመንግሥት ጋር በመተባበር ሕዝባዊ ስብሰባ ጠርቶ በነበረ ጊዜ የወያኔ/ኢሕአዴግ ሊቀ መንበርና የመንግሥት ጠቅላይ ሚኒስትር የሆነው ስብሰባውን ሕዝባዊ ማዕበል ብሎት ነበር፤ ማዕበል የሚለውን ቃል የመረጠበትን ምክንያት ለማብራራት አልፈልግም፤ ሆኖም በሚያዝያ 30/97 ቅንጅት በዚያው በመስቀል አደባባይ የጠራው ሕዝባዊ ሰብሰባ አዲስ አበባን በሙሉ አጨናንቆ ሕዝባዊ ማዕበል ከተባለው እጥፍ ድርብ ነበር፤ ፍጹም ሰላማዊ በሆነ መንገድ ያለምንም እንከን ተጠናቀቀ፤ የተከሳሾቹን ሰላማዊነት ከዚህ ሕዝባዊ ስብሰባ የበለጠ በተጨባጭ ሊያመለክት የሚችል የለም፡፡

ከምርጫው በኋላ የተፈጸሙትን ዋና ዋና ኩነቶች በቅደም ተከተላቸው ማየት ፍርድ ቤቱ ምክንያትና ውጤት ያለውን ለማጣራት ይረዳል፤ በመጀመሪያ ገና ምርጫው እየተካሄደ ባለበት ጊዜ ግንቦት 7 ማታ የሕገ መንግሥቱን ሥርዓት የሚጥስ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ለአንድ ወር ታወጀ፤ ይህም ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት ታገተ፤ የኃይል ወይም የጠመንጃ አገዛዝ በይፋ ታወጀ ማለት ነው፤ ይህንን ለማረጋገጥ ግንቦት 8 ቀን ገና ቆጠራው ሳይጠናቀቅና ለምርጫ ቦርድ ሳይደርሰው በአዲስ አበባ ከተማ ቢሸነፍም በአገሪቱ በአጠቃላይ አሸናፊ መሆኑን ወያኔ/ኢሕአዴግ አወጀ፤ በዚህ አዋጁ የምርጫ ቦርድን ሕገ መንግሥታዊ ሥልጣን ገረሰሰው፤ በነዚህ በተጠቀሱት ሁለት የኃይል እርምጃዎች ተፎካካሪ የነበረው የፖለቲካ ቡድን ራሱን በጉልበት ወደ መንግሥትነት ለውጦ ሕጋዊ ሥርዓቶችን አፈረሰና ለአሰቃቂ የግፍ እርምጃዎች በርን ከፈተ፤ ስለዚህም በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ብዙ ሰዎች ተገደሉ፤ ተደበደቡ፤ ታሰሩ፤ ከቤት ንብረታቸው ተፈናቀሉ፤ ሌላ ማስረጃ ሳንፈልግ የራሱ የመንግሥት አጣሪ ኮሚስዮን ከሞላ ጎደል ባጣራው መግለጫ 193 ሰዎች ሲገደሉ ከ700 በላይ አካለ ጎደሎ ሆነዋል፤ ከተከሳሾች መሀከል ድብደባና ማስፈራራት የደረሰባቸው አሉ፤ ሕገ መንግሥቱን የሚቃረን ዛቻና ማስፈራሪያ ዛሬም አልቆመም፤ በቅርቡ በምክር ቤቱ ውስጥ «ጣታቸውን እንቆርጣለን፤ እጃቸውን እንቆርጣለን» በማለት የሕግንና የሰብአዊ ሚዛንንም የሚጥስ አነጋገር እየሰማን ነው፤ እነዚህ ጸሐይ የሞቃቸው ኩነቶች በጥቁር መጋረጃ ተሸፍነው፣ ሕገ መንግሥቱንና የምርጫ ቦርድን ሥልጣን የሻረውና በጉልበት የመንግሥትን ሥልጣን የያዘው፣ ለብዙ ሰዎች ሕይወት መጥፋትና የአካል ጉዳት ተጠያቂ ሊሆን የሚገባው ቡድን ከሳሽ ሆኖ ከአንድ ዓመት ተኩል በላይ ሕገ መንግሥታዊ መብቶቻችን ሁሉ ታግተው በግፍ እስር ላይ የቆየነው የበደለው ንጉሥ ባላገር ይካስ እየተባልን ነው፤ ግፍ በየትኛውም መልኩ አስከፊ ነው፤ ነገር ግን በሕግ ስም የሚፈጸም ግፍ ከሁሉም የከፋ ነው፤ ምክንያቱም ዜጎች ሁሉ በሕግ ላይ ያላቸውን እምኔታና አለኝታ የሚደመስስ በመሆኑ ነው፤ ይህ ለአገር የሚበጅ አይደለም፤ አንድ ቀን ሕግ እንደሚከሠን ቅንጣት ያህል አልጠራጠርም።

## 10. በእኔ ላይ የተሰጠው ብይን

ከዚህ አጠቃላይ መንደርደሪያ ተነሥቼ በተለይ በእኔ ላይ ወደተሰጠው ብይን እገባለሁ፤ ከብይኑ ሦስት ዋና ዋና ነጥቦችን እጠቅሳለሁ።

ሀ/ ቅንጅት በሰሜን ሆቴል መግለጫ በሰጠበት ዕለት ከአድማጮቹ አንዱ ነበርሁ፤ መግለጫው ከተሰጠ በኋላ መድረኩ ለጥያቄና ለአስተያየት



ሲከፈት እኔም አስተያየት ሰጥቻለሁ፤ ብይኑ ላይ «ሥልጣን ባለው መንግሥት ከፍተኛ ውንጀላዎችን ከሰነዘረ በኋላ» ይላል፤ ፍርድ ቤቱ ይህንን ሲል «ውንጀላዎች» የሚላቸው ምን ምን እንደሆኑ አልተገለጸም፤ ነገር ግን ባልታወቁና ባልተነገረ ነገር ላይ ወደ መደምደሚያ ደርሶ ለፍርድ የተዘጋጀ ይመስላል፤ «ውንጀላዎች» የተባሉትን ሳላውቅ የምከላከለው ምኑን ነው? ለመሆኑ ፍርድ ቤቱ ራሱ እነዚህ ውንጀላዎች የተባሉትን ያውቃቸዋል?

ለ/ በአፍሪካ አዳራሽ በተደረገው ክርክር ውስጥ እኔ ተሳታፊ ነበርሁ፤ ብይኑ እንደገና «ውንጀላዎች ካቀረበ በኋላ» ቢልም አሁንም ውንጀላዎች የተባሉትን አይገልጽም። አያይዞም የዓለም ሶሺያል ሳይንቲስቶች በሙሉ የደረሱበትን ውጤት እንደአከራካሪ ጉዳይ አስመስሎ ያቀርባል፤ ይኸውም ዴሞክራሲ እንደማናቸውም ሰው ሠራሽ ሥርዓቶች ግድፈቶች አሉት፤ ዴሞክራሲን ከሌሎች ሥርዓቶች የተለየ የሚያደርገው ራሱን እያረመ የሚያድግና ወደፊት የሚራመድ መሆኑ ነው፤ በአንጻሩ የአገዛዝ ሥርዓት በባሕርዩ ራሱን ማረም አይችልም የሚል ነው፤ በምንም ዓይነት መንገድ ይህንን ደረቅ እውነት ለማስተባበል አይቻልም፤ እኔም የተናገርሁት ይህንኑ ነው፤ በነጻነትና በባርነት፣ በብልጽግናና በደህነት፣ በእድገትና በኋላ-ቀርነት መሀከል ያለው መሠረታዊ ልዩነት ይኸው ነው፤ ፍርድ ቤቱ ተከላከል የሚለኝ ያልገለጹልኝንና የማላውቃቸውን ውንጀላዎች ነው? ወይስ ደረቁን እውነት?

ሐ/ በብይኑ ላይ የተገለጸው ሦስተኛው ነጥብ ይበልጥ የሚያስገርም ነው፤ እንዲህ ይላል፡- «ያለውን ሥርዓት እና ሕገ መንግሥቱን ሙሉ በሙሉ ከማስወገድ ውጭ መሻሻልና መታረም የማይታሰብ እንደሆነ ሲቀሰቅስ መቆየቱ» የማላውቀውን ነገር ያመጣል፤ እንዲህ ዓይነት ነገር እኔ አልወጣኝም፤ ፍርድ ቤቱ ከከሳሽ ጠበቃ የሰማውን ብቻ ይዞ ፍርድ የሰጠው እንዲህ እያደረገ ነው፤ የአገዛዝ ሥርዓት በባሕርይ ራሱን ማረም አይችልም የተባለውን «ሕገ መንግሥቱን ሙሉ በሙሉ» ከማስወገድ ውጭ መሻሻልና መታረም የማይታሰብ እንደሆነ ሲቀሰቅስ በማለት ለውጦ ፍርድ መስጠት ሕገ መንግሥቱን ማን እንደረገጠው የሚያሳይ ነው።

የፍርድ ቤቱ ብይን የሚያስገርምበት ምክንያት ማስረጃ ተብሎ የቀረበው ቪድዮ መሆኑ ነው፤ በቪድዮ ላይ የተቀረጸውን ድምፅና ንግግር እንደፈለጉ በስፋት መለወጥ አይቻልም፤ ስለዚህም በፍጹም ያልተባለውን ነገር የተባለ አስመስሎ በማቅረብ ብይን መስጠት ያስፈለገበትን ምክንያት መጠየቅ አስፈላጊ ይሆናል።

የከሳሽ ጠበቃ ለእውነት ክብር የማይሰጥ መሆኑን በተደጋጋሚና በተጨባጭ አሳይቶአል፤ ነገር ግን ፍርድ ቤቱን ይህንን ያህል ያሳስታል የሚል

ጥርጣሬም አልነበረኝም፤ ቪዲዮውን ሲያይና እኔ የተናገርሁትን ሲሰማ ሕገ መንግሥቱን በተለይም በሰብአዊ መብቶች ጉዳይ አወድሼ መናገሬን ሊስተው አይችልም፤ በእውነቱ ፈንታ «ሕገ መንግሥቱን ሙሉ በሙሉ» ማስወገድ የሚል ውሸት ብይኑ ውስጥ መግባቱ በጣም ያሳዝነኛል፤ ያሳፍረኛልም።

እኔ በሕገ መንግሥቱ ውስጥ ከተፈቀደው ሀሳብን የመግለጽ መብት ውጭ በኀልዮም፤ በነቢብም፤ በገቢርም ቅንጣት ወንጀል አልፈጸምሁም፤ ስለዚህም የምከላከለው የለም።

አቶ መለስ በጎዳና ነውጥና በድንጋይ ውርወራ ዴሞክራሲን መመሥረት አይቻልም ያለው ትንሽ እውነት አለበት፤ ነገር ግን ትልቁንና ዋናውን ጥፋት በትንሽ እውነት መሸፈን ያስቸግራል፤ በጥይት የልጆችን ጭንቅላትና ልብን እያፈረሱ በጭፍጨፋ ዝም ለማሰኘት መሞከር አውቶቡሶችን በድንጋይ ከመምታት ጥፋት ጋር አለማወዳደር ሚዛንን የማጣት ምልከት ነው፤ በድንጋይ ውርወራ ዲሞክራሲን መትከል አይቻልም፤ ይህ እውነት ነው፤ በጥይትም ዲሞክራሲን መትከል አይቻልም፤ ይህም እውነት ነው።



# ፲
# ሽምግልናና እርቅ

## 1. ሽምግልና

በብዙ ሚልዮን ለሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ሽምግልና አድባር ነው፤ ከቤተሰብ ጀምሮ በትንሽ ማኅበረሰብ ውስጥም ቢሆን ግጭት አይጠፋም፤ የሚፈጠረውን ማናቸውም ዓይነት ግጭት ለማለሳለስና በስምምነት ለመተካት የሚደረገው ባህላዊ ሽምግልና በመልኩም በባሕርዩም ዛሬ በሽምግልና ስም ከምናየው በጣም የተለየ ነው፤ በኢትዮጵያ ባህል ሽምግልና የሚነሣው ከመንፈሳዊ መሠረት ላይ ነው፤ ሽምግልና የአምላክ ተግባር ነው፤ ሽምግልና ለእርቅ፣ ለፍቅርና ለሰላም የቆመ መንፈሳዊ አድባር ነው፤ ይህ አድባር (ኢንስቲትዩሽን) ሕንፃ የለውም፤ ለሽምግልና የበቃው ሰው በአእምሮው፣ በልቡና በመንፈሱ ይዞት የሚዞርና ከትውልድ ወደትውልድ ሲተላለፍ የቆየ ነው፤ የሽምግልና መንፈሳዊ መሠረቱ በዋናነት የሚከተሉት ይመስሉኛል፤

*«ጽድቅን (እውነትንና ትክክለኛነትን) የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው፤ ይጠግባሉና፤»*

*«የሚምሩ (ምሕረትን የሚያደርጉ) ብፁዓን ናቸው፤ ይማራሉና) ምሕረትን ያገኛሉና)፤»*

*«የሚያስታርቁ (ሰላምን የሚያመጡ) ብፁዓን ናቸው፤ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና»*

ቃላቱ ይለወጡ ይሆናል እንጂ ቁም-ነገሩ በእስልምናም ተጠናክሮ ያለ ይመስለኛል፤ እርቅ፣ ፍቅር፣ ሰላም መንፈሳዊ ዋጋ ያላቸው ቁም-ነገሮች ናቸው፤ አሜሪካኖችና አውሮፓውያን ሽምግልናን ወደንግድ ሥራ ለውጠውት ገንዘብ የሚከፈላቸው አደራዳሪዎች ወይም አስታራቂዎች አሉዋቸው፤ ሽምግልና ዋጋ የሚከፈልበት ሲሆን ይረከሳል፤ ወደሸቀጥነት ይወርዳል፤ ሽምጋዮቹንም፣ ተሸምጋዮቹንም ያዋርዳል፡

እንግዲህ ለሽምግልና ብቁ የሚሆነው ማን ነው? ሽምግልና ወይም ከሽምግልና ጋር በተያያዘ ሽማግሌ ምን ማለት ነው? የዕድሜ ጉዳይ ብቻ አይደለም፤ ከዕድሜው ጋር ተጣምረው መገኘት ያለባቸው ብዙ ባሕርዮች አሉ፤ መንፈሳዊነት አንዱ ባሕርይ ነው፤ ለእኔ እንደሚገባኝ መንፈሳዊነት ለእውነት፣ ለእኩልነትና ለፍትሕ መገዛት ማለት ነው፤ «ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ» መሆን አለባቸው፤ ለግዑዝ ነገር፣ ለጉልበትም ይሁን ለገንዘብ የማይሸነፉ ሰዎች

ጥርጣሬም አልነበረኝም፤ ቪዲዮውን ሲያይና እኔ የተናገርሁትን ሲሰማ ሕገ መንግሥቱን በተለይም በሰብአዊ መብቶች ጉዳይ አወድሼ መናገሬን ሊስተው አይችልም፤ በእውነቱ ፈንታ «ሕገ መንግሥቱን ሙሉ በሙሉ» ማስወገድ የሚል ውሸት ብይኑ ውስጥ መግባቱ በጣም ያሳዝነኛል፤ ያሳፍረኛልም።

እኔ በሕገ መንግሥቱ ውስጥ ከተፈቀደው ሀሳብን የመግለጽ መብት ውጭ በኀልዮም፣ በነቢብም፣ በገቢርም ቅንጣት ወንጀል አልፈጸምሁም፤ ስለዚህም የምከላከለው የለም።

አቶ መለስ በጎዳና ነውጥና በድንጋይ ውርወራ ዴሞክራሲን መመሥረት አይቻልም ያለው ትንሽ እውነት አለበት፤ ነገር ግን ትልቁንና ዋናውን ጥፋት በትንሽ እውነት መሸፈን ያስቸግራል፤ በጥይት የልጆችን ጭንቅላትና ልብን እያፈረሱ በጭፍጨፋ ዝም ለማሰኘት መሞከር አውቶቡሶችን በድንጋይ ከመምታት ጥፋት ጋር ለማወዳደር ሚዛንን የማጣት ምልክት ነው፤ በድንጋይ ውርወራ ዲሞክራሲን መትከል አይቻልም፤ ይህ እውነት ነው፤ በጥይትም ዲሞክራሲን መትከል አይቻልም፤ ይህም እውነት ነው።



# ፩
# ሽምግልናና እርቅ

## 1. ሽምግልና

በብዙ ሚልዮን ለሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ሽምግልና አድባር ነው፤ ከቤተሰብ ጀምሮ በትንሽ ማኅበረሰብ ውስጥም ቢሆን ግጭት አይጠፋም፤ የሚፈጠረውን ማናቸውም ዓይነት ግጭት ለማለሳለስና በስምምነት ለመተካት የሚደረገው ባህላዊ ሽምግልና በመልኩም በባሕርዩም ዛሬ በሽምግልና ስም ከምናየው በጣም የተለየ ነው፤ በኢትዮጵያ ባህል ሽምግልና የሚነሣው ከመንፈሳዊ መሠረት ላይ ነው፤ ሽምግልና የአምላክ ተግባር ነው፤ ሽምግልና ለእርቅ፣ ለፍቅርና ለሰላም የቆመ መንፈሳዊ አድባር ነው፤ ይህ አድባር (ኢንስቲትዩሽን) ሕንፃ የለውም፤ ለሽምግልና የበቃው ሰው በአእምሮው፣ በልቡና በመንፈሱ ይዞት የሚዞርና ከትውልድ ወደትውልድ ሲተላለፍ የቆየ ነው፤ የሽምግልና መንፈሳዊ መሠረቱ በዋናነት የሚከተሉት ይመስሉኛል፤

*«ጽድቅን (እውነትንና ትክክለኛነትን) የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው፤ ይጠግባሉና፤»*

*«የሚምሩ (ምሕረትን የሚያደርጉ) ብፁዓን ናቸው፤ ይማራሉና) ምሕረትን ያገኛሉና)፤»*

*«የሚያስታርቁ (ሰላምን የሚያመጡ) ብፁዓን ናቸው፤ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና»*

ቃላቱ ይለወጡ ይሆናል እንጂ ቁም-ነገሩ በእስልምናም ተጠናክሮ ያለ ይመስለኛል፤ እርቅ፣ ፍቅር፣ ሰላም መንፈሳዊ ዋጋ ያላቸው ቁም-ነገሮች ናቸው፤ አሜሪካኖችና አውሮፓውያን ሽምግልናን ወደንግድ ሥራ ለውጠውት ገንዘብ የሚከፈላቸው አደራዳሪዎች ወይም አስታራቂዎች አሉዋቸው፤ ሽምግልና ዋጋ የሚከፈልበት ሲሆን ይረክሳል፤ ወደሽቀጥነት ይወርዳል፤ ሽምጋዮቹንም፣ ተሸምጋዮቹንም ያዋርዳል፡

እንግዲህ ለሽምግልና ብቁ የሚሆነው ማን ነው? ሽምግልና ወይም ከሽምግልና ጋር በተያያዘ ሽማግሌ ምን ማለት ነው? የዕድሜ ጉዳይ ብቻ አይደለም፤ ከዕድሜው ጋር ተጣምረው መገኘት ያለባቸው ብዙ ባሕርዮች አሉ፤ መንፈሳዊነት አንዱ ባሕርይ ነው፤ ለእኔ እንደሚገባኝ መንፈሳዊነት ለእውነት፣ ለእኩልነትና ለፍትሕ መገዛት ማለት ነው፤ «ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ» መሆን አለባቸው፤ ለግዑዝ ነገር፣ ለጉልበትም ይሁን ለገንዘብ የማይሸነፉ ሰዎች

መሆን ይገባቸዋል፤ ለሽምግልና ብቁ የሚሆኑ ሰዎች በአንድ በኩል በፈሪሃ እግዚአብሔር፣ በሌላ በኩል በሰብአዊነትና በፍቅር የሚመሩ ለሰላም የቆሙ ናቸው፤ በእውቀትም በኩል የማኅበረሰቡን ታሪክ፣ ባህልና ወግ ጠንቅቀው የሚያውቁ፣ በተረትና በምሳሌ እያዝናኑ በርቱዕ አንደበት የማስረዳትና የማሳመን፣ የማቀራረብና የማስታረቅ ችሎታና ብልሃት ያላቸው፣ የሚያሳፍረውንና የተሸሸገውን በተራቀቀ ዘዴ የመግለጥ፣ የአበጠውን የማፍረጥና የኀሊና ቁስልን የማሻር ጥበብ የተላበሱ ሰዎች ናቸው።

በነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ለሽምግልና የሚፈለጉ ሰዎች መንፈሳዊ ሥልጣን የተሰጣቸው ናቸው፤ የሚከበሩና ሲናገሩም የሚደመጡ ናቸው፤ ከሁሉም በላይ የሚታመኑ ናቸው፤ ሰሞኑን በፍልስጥኤማውያን አበሳ ላይ በቢቢሲ ውይይት ሲደረግ አንድ አስተያየት ሰጪ ጥልቅ ነገር ተናገረ፤ «ደካማ ሰዎች ሰላምን አያመጡም» አለ፤ ለሽምግልና የሚፈለጉ ሰዎች የፈረጠመ መንፈሳዊ ወኔ ያላቸው እንጂ ደካሞች ሊሆኑ አይችሉም።

መንፈሳዊ ሥልጣን ስል ክህነት ብቻ ማለቴ አይደለም፤ ክህነት ሳይኖራቸው ጨዋ ሽማግሌዎች መንፈሳዊ ሥልጣን ሊኖራቸው ይችላል፤ ማኅበረሰቡ የሚያከብራቸውና ቃላቸውን የሚያዳምጥ፣ የሚታዘዛቸውም ሲሆን መንፈሳዊ ሥልጣን አላቸው ማለት ነው፤ የክህነት መንፈሳዊ ሥልጣን ብቻውን ለሽማግሌነት አያበቃም፤ ነገር ግን በክብረ ነገሥት የተሰጠውን መመሪያ የተቀበለ ካህን ለሽምግልና ብቃት እንደሚኖረው አያጠራጥርም፤ ክብረ ነገሥት የሚከተለውን ይላል፤ «ከንጉሡ በታች ያለው ሕዝብ ንጉሡን ቢያማ ጥሩ አይደለም፤» ይልና፣

*«የክርስቶስ የእውነት ጸሐይ በልባቸው ስላለ ካህናትን ጨለማን የሚያጠፉ ብርሃን አድርጎ ሰይሟቸዋልና ልቡና ያለው ካህን ስለሚያያቸው ሥራዎች ንጉሡን ይገስፀዋል፤ ... ካህን ሆይ አንተ ደግሞ የሰውን የታወቀ ኃጢአት ስታይ መገሰፅን አትፍራ፤ ሰይፍም፣ ሰደትም አያስፈራህ፡፡»*

መንፈሳዊ የክህነት ሥልጣንን ቢይዝም የተገለጸው መንፈሳዊ ወኔ የሌለው ሰው ለሽምግልና አይበቃም፤ በክህነት ያገኘውን ሥልጣን ከሃይማኖት ውጭ በማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ ከሕዝብ አያገኘውም፤ «የእውነት ጸሐይ» ሆኖ ጨለማን፣ ጠብን፣ አለመተማመንንና አለመስማማትን የሚያስወግድ መሆን አለበት።

በሌላ በኩል ስናየው በሽምግልና የእውነተኛነትን አስፈላጊነት እንድንገነዘብ ያሻል፤ «እውነት ነጻ ያወጣል፤» የተባለው ለሽምግልና መሠረታዊ መመሪያ ነው፤ የሽምግልና ዓላማ የበደለው ሰው ከኃጢአቱ፣ የተበደለው ሰው ከቂሙ ነጻ እንዲወጣ ለማድረግ ነው፤ ነገሮችን አድበስብሶ ለማስታረቅ መሞከር



ሽምግልና አይሆንም፤ እርቁ በጣም ጊዜያዊ እንጂ ዘለቄታ የሚኖረው አይሆንም፤ በሽምግልና የበደለው ይለያል፤ የበደሉ ዓይነት ይታወቃል፤ የበደሉ መጠን ይመዘናል፤ የበደሉ ተደጋጋሚነት ይታያል፤ በመጨረሻም የበደለው ሰው ድንጋይ ተሸክሞ ይቅርታ እንዲጠይቅ ወይም ተገቢውን ካሣ እንዲከፍል ይደረጋል፤ የበደለው ሰው ካሣ እንዲከፍል ሽማግሌው የሚያደርገው ጥረት የተበደለው ሰው ይቅርታውንና ካሣውን ተቀብሎ ቂሙን ከልቡ እንዲነቅል ከሚደረገው ጥረት ያነሰ አይደለም፤ የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳ የሚባለውን ለማስቀረት ነው፤ ወንድ ልጅ ሲወለድ ደም መላሽ የሚል ስም የሚሰጠው ቂምን ለማውረስ ሲባል ነው።

እርቅ የፈለገን ንጉሥ ገበሬ ያስታርቀዋል፤ እርቅ የማይፈልግ ገበሬን ግን ንጉሥም አያስታርቀው የሚባለው ችግሩ በበዳዩ ወይም በአጥፊው ሰው ላይ ብቻ ሳይሆን ወደፊት፣ ሲመቸው በደሉን በሌላ በደል ለመመለስ አድብቶ በሚጠብቀው ላይም ስለሆነ ነው፤ የተበደለ ሰው ቂምን በልቡ ቋጥሮ ይይዛል፤ የእርቅ ዓላማ ይህንን ቂም ከስሩ ነቅሎ ለማጥፋት ነው፤ ይህ በማድበስበስ ሊሆን አይችልም፤ በተለይም ማድበስበስ የማኅበረሰቡ ባህል በሆነበት አገር ማድበስበስ መሠረታዊና ዘለቄታ ያለው እርቅ ያመጣል ብሎ ለማመን አስቸጋሪ ነው፤ አደበስብሶ ማስታረቅ ጠቡን ለወደፊት በቀጠሮ ማቆየት ነው፤ እንዲያውም ወደሚያገረሽ ጠብ ያደርሳል።

ችግርን ከመፍታት ይልቅ ችግርን የማራባት ዝንባሌ ያለው ማኅበረሰብ ትዝብታቸውና ምስክርነታቸው በእውነት ላይ የተመሠረተና ዘለቄታ ያለው እርቅንና ሰላምን የሚያመጡ አድባሮች ያስፈልጉታል፤ ዛፍ በሌለበት እምቧጮም ዛፍ ነው እንደሚለው የጎንደሬዎች አባባል እየሆነ ሽምግልና ከብፁዕነቱ፣ ከጽድቅነቱ፣ በአጠቃላይ ከአምላካዊና መንፈሳ*ዊ ተልእኮው ወጥቶ መሸጠ እየሆነ ነው፤ መሸጠ ሽምግልና ከኢትዮጵያ ባህል ጋር በጭራሽ የባሕርይም የዓላማም ዝምድና የለውም፤ ፈረንጆች ከባልና ሚስት ጠብ ጀምሮ እስከሠራተኛና አሰሪ የሚያደራድሩበት መሸጠ ሽምግልና አላቸው፤ መሸጠ ሽምግልና (ሽምግልና ካልነው) ጠበኞቹ ደንበኞች ሆነው እንዲመላለሱለት የሚፈልግ ነው፤ ንግድ ነው፤ በመሸጠ ሽምግልና እውነት በጮሌነት ይተካል፤ የማያዛልቀውም ለዚህ ነው።

እውነትን የሚፈራ ሰው ለኢትዮጵያ ባህል ሽምግልና አይበቃም፤ ራሴን ማስተዋወቅ አይሁንና አንድ ምሳሌ ላቅርብ፤ አንዲት በጣም የበሰለችና ጎበዝ ጸሐፊ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ትሠራ ነበር፤ እናትዋ ባል አግኝተውላት ሊድሩ ይደግሳሉ፤ እስዋ በበኩልዋ የምትወድደው ሰው አላት፤ ጨነቃትና ተደብቃ አስመራ ሄደች፤ በኢትዮጵያ ዓየር መንገድ የሚሠራ ወንድምዋ የቤተሰቡን መጨነቅ ነገረኝ፤ በአንድ አስመራ በነበረ ጓደኛዬ በኩል አስፈልጌ አገኟትና ወደአዲስ አበባ እንድትመጣና በእኔ ቤት እንድትቀመጥ

አደረግሁ፤ ከጥቂት ቀናት በኋላ አስፈላጊውን ሁሉ አመቻችቼ ልጅቱን ወደእናትዋ ቤት ይገዩ ሄድሁ፤ እናትና ልጅ ማዶ ለማዶ ተቀምጠዋል፤ እኔ ስለልጅቱ የማውቀውን በዝርዝር ለእናት ነግሬ፣ እሳቸው ይቺን የበሰለችና ራስዋን የቻለች ልጃቸውን እንደትንሽ ልጅ ቆጥረው ሕይወትዋን ሊያናውጡባትና የምትወዳቸውንና የሚወዱዋትን ልጃቸውን ማስቀየማቸውን በጣም በቁጭት ነገርኋቸው፤ በድንገት እናት ብድግ ብለው በቀጥታ ልጅቱ ወደተቀመጠችበት ሄደው እግርዋ ላይ «ማሪኝ!» ብለው ወደቁ፤ ልጅቱ በበኩልዋ «ማሪኝ!» እያለች ወድቃ የእናትዋን እግር ትፈልጋለች፤ ሁለቱ መሬት ላይ ወድቀው ሲንፈራፈሩ እንባ አነቀኝና ተነሥቼ ወጣሁ፤ ልጅቱ ዛሬ ትልልቅ ልጆችን ያደረሰች ወይዘሮ ነች፤ የእናቲቱን በቶሎ እውነትን የመቀበል ችሎታ በጣም አደንቃለሁ፤ እውነት ነጻ ያወጣል፡፡

ከዚህ የእናትና ልጅ አለመግባባት በጣም የላቀና የአፍሪካን አገሮች በሙሉ የሚነካ ምሳሌ አለ፤ አፄ ኃይለ ሥላሴ የአፍሪካ አንድነትን ያቋቋሙ ጊዜ (ማንም ሌላ ሰው አቋቋመው ሊባል የሚቻል አይመስለኝም) ብዙ የተጣሉ፣ አንበሶች ነን የሚሉ መሪዎች ነበሩ (እነናሳር፣ እነቤንቤላ፣ እነኒዬሬሬ፣ እነ ...)፤ የመጨረሻው ቀን የጃንሆይ የመንፈስ ሥልጣን ሁሉንም እኩል ወጥሮ ይዞ የአፍሪካ አንድነት ቻርተር ሳይፈረም ከስብሰባው አዳራሽ አንወጣም ብለው እስከሌሊቱ ስምንት ወይም ዘጠኝ ሰዓት ድረስ አቆይተው ተፈረመ፤ ያን ዕለት እንደኢትዮጵያዊ የተሰማኝ ደስታና ኩራት በሕይወቴ የማላውቀው ነው፤ እነዚያን ከእኔ በላይ ማን አለ ብለው በትዕቢት የተወጠሩ አምባገነኖች ሁሉ ማሳመንና ስነዱን እንዲፈርሙ ማድረግ በዕለቱ (በሌሊቱ) እዚያ ለነበርን ሰዎች የሚያስገርም ተአምር ነበር፤ ለተጣሉት ሁሉ የሚጠቅም የፀዳ ዓላማ ይዘው እውነት ላይ ሲቆሙ የመንፈስ ሥልጣን ይሆናል፡፡

## 2. እርቅ

እርቅ ማለት ጠብን በሰላም፣ ጥላቻን በፍቅር፣ አለመግባባትን በስምምነት፣ ጥርጣሬን በመተማመን፣ መራራቅን በመቀራረብ፣ ኩርፊያን በመነጋገርና በመወያየት መለወጥ ነው፤ እርቅ ማለት የበደለ ጥፋቱን አምኖና ካሣ ከፍሎ፣ የተበደለ ቂሙን ከልቡ ፍቆ ለአዲስ ግንኙነት በንጹሕ መንፈስ መታደስ ነው፡፡ እርቅን የሚፈልግ ማን ነው? እርቅን የሚፈልግ ሰላምን የሚፈልግ ነው፤ እርቅን የሚፈልግ ከራሱ በላይ የአምላክም ሆነ፣ የሕግም ሆነ፣ የሕዝብ ኃይል መኖሩን የሚያምንና እርቆ የሚያስብ ሰው ነው፤ ምንም ዓይነት ተጠያቂነት የሌለበት መስሎ የሚታየው፣ እያጠቃሁ ለመኖር የሚያስችለኝ ጉልበት አለኝ ብሎ የሚያምን ሰው፣ ከጉልበቱ ውጭ የሚተማመንበት ምንም ኃይል ስለሌለ እርቅን የሚፈልግበት ምክንያት አይታየውም፤ ተበዳይም ቢሆን አቅሙን አሳንሶ ገምቶ



ደሀ ተበድሎ ማሩኝ ይላል ቶሎ እንደሚባለው አለመቀየሙንም ለመግለጽ ሲል ራሱን በደለኛ አድርጎ በማቅረብ ጉዳዩን በዳዩ እንዲረሳለት ይሞክራል፤ ነገር ግን በዳዩም ሆነ ተበዳዩ ከሚያቆራኛቸው የበደል ሰንሰለት አይላቀቁም፤ በዳዩ ተበዳዩ አይተኛልኝም ብሎ በስጋትና በፍርሃት ይኖራል፤ ተበዳዩም የበዳዩን ፍርሃትና ስጋት ስለሚያውቅ ሲመቸው ያጠፋኛል ብሎ በስጋትና በፍርሃት ይኖራል፤ እርቅ የሚያስወግደው ይህንን በሁለቱም በኩል ያለውን ስጋትና ፍርሃት ነው፤ እውነት ነጻ ያወጣል የሚባለው የሚሠራው ለዚህ ነው፤ ሽምግልና በእውነት ላይ እንዲቆም የሚያስፈልገውም ለዚህ ነው፡፡

እርቅ ማለት እግዚአብሔር ነው፤ እርቅ የእግዚአብሔር ባሕርይ ነው፤ እግዚአብሔር ማለት እርቅ ነው፤ በክርስትና የመስቀል ትክክለኛ ትርጉሙ እርቅ ነው፤ ክርስቶስ ሰው ሆኖ መከራውን የተቀበለውና የተሰቀለው ለእርቅ ነው፤ አዳም በበደለ መድኃኔ ዓለም ካሠ የሚባለው ለዚህ ነው፤ በሌሎች ሃይማኖቶች ሁሉ ፍቅርና ሰላም ከፍተኛ ቦታ ያላቸው ፋይዳዎች ናቸው፤ እርቅ የእግዚአብሔር በመሆኑ ነው ትንሽና ትልቅ፣ አለቃና ምንዝር፣ ሴትና ወንድ፣ ሽማግሌና ወጣት፣ ንጉሠ ነገሥትና ሎሌ የማይለየው፤ ለዚህ ነው በጦርነት ድልን የተጎናጸፈውና የተሸነፈው በእርቅ ደማቸውን የሚያጥቡት፣ ለዚህ ነው ማራኪና ምርኮኛ ቂማቸውን በእርቅ የሚፍቁት፣ ለዚህ ነው አሳሪና ታሳሪ ከሁለቱም ለበለጠ ፋይዳ በእርቅ የሚስተካከሉት፤ እርቅ የእግዚአብሔር በመሆኑ አይናቅም፤ እርቅ የእግዚአብሔር በመሆኑ አይደበቅም፤ እርቅ የእግዚአብሔር በመሆኑ ያስከብራል እንጂ አያሳፍርም፤ እርቅ የእግዚአብሔር በመሆኑ ጽድቅ ነው፤ እውነት ነው፤ ክቡር ነው፤ ክቡር በመሆኑም ያስከብራል፡፡ ዛሬ በደቡብ አፍሪካ ብቻ የአፍሪካ ኩራት የሆኑ ትልልቅ ሰዎች የሚገኙት እርቅ የእግዚአብሔር መሆኑን በመገንዘባቸው ነው፤ አሳሪ ደ ክላርክና ታሳሪ ኔልሰን ማንዴላ ከሁለቱም በላይ የደቡብ አፍሪካ ሕዝብ፣ ደቡብ አፍሪካ የሚባል አገር፣ ሰላምና ብልጽግና፣ እግዚአብሔር ከነሱ በላይ እንዳሉ በማወቃቸው ለእርቅ ልባቸውን በመክፈታቸው ነው፤ ታሳሪውን ኔልሰን ማንዴላን በደቡብ አፍሪካ ብቻ ሳይሆን በዓለም ጭምር ለትልቅነት ያበቃው አሳሪው ደ ክላርክ ነው፤ የደ ክላርክ ትልቅነት በእምነትና በተስፋ የጉልበት አስተሳሰቡን ለውጦ ልቡን ለእርቅ በመክፈቱና በተጨባጭም የእርቁን መንፈስ ለመግለጽ ማንዴላን ከእስር አውጥቶ እኩያው ማድረጉ ነው፤ በእርቅ ትልቅ ሰው ትልቅ ሰውን ወለደ፤ ጉልህ መንፈሳዊ ወኔን አሳየ፡፡

እርቅን መናቅ እግዚአብሔርን መናቅ ነው፤ እርቅን መናቅ ከራስ በላይ ነፋስ በሚል ባዶ የተከበበ እብሪት ነው፤ ማንም ሰው የትኛውም የሥልጣን እርከን ላይ ቢንጠለጠል፣ ምንም ያህል ሀብት ቢያደልበው ከበላዩ የማይታይና

የሚታይም ኃይልና ሥልጣን መኖሩን አለማወቁ እብሪት ቢመስልም ቂልነት ነው፤ ቂልነቱ የራሱን ወርድና ርዝመት፣ የእድሜውን ውሱንነትና ከቁጥጥሩ ውጭ የሆኑ ብዙ ሁኔታዎች ሊፈጠሩ እንደሚችሉ መገመት ያቃተው መሆኑ ነው፤ ጊዜ እንኳን ሥልጣንና ሀብትን ድንጋይንም ይበላል፤ ከራስ በላይ ነፋስ ብሎ ነገር አይበጅም፤ ማስታወስ እያቃተን ነው እንጂ እንደማይበጅ በተደጋጋሚ አይተናል፤ ከራስ በላይ ነፋስ ከራስ በላይ ያለውን እውነት አይለውጠውም፤ የሚገልጸው የውስጥ ባዶነትን ብቻ ነው፤ ባዶ ሆኖ እስከቀረ ድረስ ባዶነት አይለወጥም::

ጠብ የበዳይንና የተበዳይን ግንኙነት የሚያሻክርና ለሁለቱም የማይበጅ መሆኑ በሁለቱም ዘንድ እኩል ግንዛቤን ሲያገኝ እርቅ ተፈላጊ ሊሆን ይችላል፤ ወይም ደግሞ የበዳይና የተበዳይ ግንኙነት መሻከር የማኅበረሰቡን ጤንነት ይጎዳል በሚባልበት ጊዜ ሽማግሌዎች በራሳቸው ተነሳሽነት እርቅ እንዲጀመር ለማድረግ ይችላሉ::

ስለአፄ ምኒልክ በአፍ ከሚነገሩ ታሪኮች አንዱን በመጥቀስ የፈላጭ ቆራጭነት ሥልጣን ያለውም ፈሪሃ እግዚአብሔር ያደረበት ከሆነ በጥፋቱ ተጸጽቶ እርቅን እንደሚፈልግ ላስረዳ፤ አንድ እውነተኛ ያልሆነ ወሬ ሰምተው አፄ ምኒልክ ያንዱን ራስ ወታደሮች በሙሉ ለሌላ ይሰጡና ሰውዬው ከሥራ ውጭ ሆነው በቤታቸው እንዲቀመጡ ያደርጋሉ፤ ከአንድ ዓመት ያህል በኋላ አፄ ምኒልክ እውነቱን ይረዳሉ፤ ሰውዬውን አስጠርተው ሰዎች ባሉበት ጎንበስ ብለው «ይቅር በለኝ በድዬሃለሁ፤ ጎድቼሃለሁ፤» ይላሉ አፄ ምኒልክ፤ ሰውዬውም «እረ ጃንሆይ አልበደሉኝም፤ በምንም አልተጎዳሁም፤ ራስ እገሌ በያይነቱ አህሉን፣ ራስ እገሌ ደግሞ ሙከቱንና ሰንጋውን እንዲህ አሽከሮችዎ ሁሉ እየረዱኝ ከዱሮው የበለጠ ጌታ ሆኛለሁ፤» ብለው ይመልሱላቸዋል፤ አፄ ምኒልክም እነዚያን የተጠቀሱትን ራሶች አስጠርተው «እግዚአብሔር ዋጋችሁን ይክፈላችሁ፤ እኔ ተሳስቼ እሱን ብበድለው እናንተ በእግዚአብሔር እንዳልወቀስና እንዳልኮነንባችሁ ላደረጋችሁት አመሰግናችኋለሁ፤» ብለው እስናበቷቸው ይባላል፤ የተበደሉት ራስ አፄ ምኒልክን በምንም መንገድ ሊጎዱ የማይችሉ ይሆናል፤ ስለዚህ የአፄ ምኒልክ ፍርሃት የእግዚአብሔርን ቁጣ ነበር፤ ፍላጎታቸው ጥፋታቸውን በማመን ራሳቸውን ለማዳንና እውነቱን ለመቀበል ብቻ ነበር፤ ይህ ብቻ ነው ከመንበራቸው ተነሥተው የበታቻቸውን ይቅርታ እንዲጠይቁ ያስገደዳቸው፤ የትልቅነታቸውም መሠረት ይኸው ነው፤ ተበድለው የነበሩት ራስ በበኩላቸው ከያዙት ቂም ከመፅዳታቸው በተጨማሪለአፄ ምኒልክ የበለጠ ፍቅርና ታማኝነት እንዲኖራቸው ሳያደርጋቸው አይቀርም፤ እርቅ እንዲህ ነው::



በእኔ ዕድሜ በተፈሪ መኮንን ተማሪዎች ጉዳይ አቡነ ባስልዮስ አፄ ኃይለ ሥላሴን ከጥፋት እንዳዳኑ አውቃለሁ፤ ሌላ የማስታውሰው ምናልባት በኢትዮጵያ ውስጥ የሽምግልና ተግባር የታየ የሚመስለው በ1953 ዓ.ም. በክብር ዘበኛ የስዒረ መንግሥት ሙከራ ጊዜ ነበር::
አለቃ አያሌው እንዳሉት፣

*ወንድማማቾች በማይገባ ነገር ተጣልተው፣ በሃሳብ ተለያይተው፣ የማይግባቡና የማይስማሙ ከዚያም አልፎ ነገራቸው ከዳኛ የሚያደርሳቸው አንዱ ባንዱ ላይ ክፉ ለመሥራት የሚገፋፋቸው ሆኖ ሲገኝ ከፀቡ አግባብ የሌላቸው ወዳጆች፣ ዳኞች፣ ባልንጀሮች፣ ሽማግሌዎች በመሀከል ገብተው ማልደው በፍቅር ተቆጥተው ወይም አባብለው ለእርቅ ቢያደርሱአቸው ሊፈርስ የነበረ ቤት ይታነጻል፤ የፈሰሰ ደም ይደርቃል፤ ነባር ቂም በቀል ይርቃል::*

እርቅ የሰላም መንገድ ነው፤ ስለሰላም ስናስብ በአጭሩ አይደለም፤ ለዚህ ዓመት ወይም ለሚቀጥለው አይደለም፤ እኔ ከሞትሁ ሰርዶ አይብቀል ይሆናልና፣ በአንድ የገዢ መደብ ዕድሜ መጠን አይደለም፤ ለብዙ ተከታታይ ትውልዶች፣ ለገዢው መደብ ልጆችና ለልጅ ልጆቻቸው ጭምር የማያቋርጥ ሰላም ያስፈልጋል፤ እንዘጭ! እምቦጭ! እያልንማ ያለንበት ደርሰናል፤ ኋላ-ቀር የሚባሉ አገሮች ሁሉ እርቅን የማይወዱና ሥልጣንን መግራት ያልቻሉ ናቸው፤ በአንጻሩ ሀብታሞችና ኃያላን የሚባሉት አገሮች ሁሉ በእርቀ-ሰላምና ሥልጣንን በመግራት የሠለጠኑ ናቸው፤ እነሱ ራስ ሌላው ጭራ የሆነበት ዋናው ምክንያት ይኸው ነው::

## 3. በቃሊቲ የሽምግልና/እርቅ ንግግር ነበረ ወይ?

ከምርጫ 97 በኋላ ወያኔ/ኢሕአዴግ በወሰደው የኃይል እርምጃ ብዙ ሰዎች ተገደሉ፤ ብዙ ሰዎች አካላቸው ጎደለ፤ ብዙ ሰዎች ከሥራቸው ተባረሩ፤ ብዙ ሰዎች ተሰደዱ፤ በዚህም ምክንያት የተለያዩ ሰዎች በቡድን እየሆኑ ለመሸምገልና የነበረውን የጠብ ዝንባሌ ለማብረድ ጥረት አድርገዋል፤ ሆኖም ምንም ፋይዳ አልነበራቸውም፤ ያልተሳካበትን ምክንያት እነሱ እስቲነግሩን መጠበቅ አለብን፤ ከነዚህ የሽምግልና ጥረቶች ውስጥ አንዱ ግን የታሰሩትን ለማስፈታት የተደረገው በከፊል ውጤት አሳይቶአል፤ በዚህ ላይ የማውቀውን ለማሳወቅ እሞክራለሁ::

---

[6] አለቃ አያሌው ታምሩ፣ ምልጃ፣ እርቅና ሰላም፣ አዲስ አበባ፣ 1992.

በቃሊቲ እስር ቤት አንድ የተገነዘብሁት ነገር ምሥጢር የሚባል ነገር አለመኖሩን ነው፤ እንኳን በሌላ ቦታና ጊዜ አካልን ሲታጠቡም ሆነ ሲፀዳዱ ድብቅብቆሽ የለም፤ ምንም ጊዜ ቢሆን በየቦታው ጠባቂዎች ወታደሮች አሉ፤ እስረኞች አሉ፤ ከነዚህ ተደብቆ የሚሠራ ነገር የለም፤ በቃሊቲ እስር ቤት ውስጥ የእርቅ ንግግር ከነበረ ምሥጢር አይሆንምና ብዙ ሰዎች በምስክርነት ሊጠሩ ይችላሉ ማለት ነው፤ እንዲህ ከሆነ ጥያቄው ለምን ይነሣል? የሚል ሰው ይኖራል፤ ጥያቄው መነሣት ያለበት በሁለት ምክንያቶች ነው፤ አንደኛ በመንግሥት የዜና ማሰራጫዎች ባለሥልጣኖች እርቅ የሚባል ነገር እንዳልነበረና ምንም ድርድር እንዳልተደረገ ገልጸዋል፤ ከዚያም በላይ በምክር ቤት ውስጥ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይህንኑ አረጋግጧል፤ ሁለተኛ በሽምግልና ተሰልፈው ከነበሩት ውስጥ አንዱም ይህንን ለማስተባበል የተናገረ ሰው የለም፤ ስለዚህም እኔ በበኩሌ የማውቀውን እውነት ለመመስከር ግዴታ አለብኝ፤ ይህንንም እንደማደርግ ለሽማግሌዎቹ በቃል ከመግለጼ በላይ በጽሑፍም በአደባባይ አስታውቄ ነበር፡፡

በቃሊቲ እስር ቤት ውስጥ የእርቅ ንግግር እንደነበረ ቅንጣት ያህል ጥርጣሬ ሊኖር አይገባም፤ እንዲያውም በአንድ ቡድን ብቻ ሳይሆን በሁለት ቡድኖች የእርቅ ንግግር ተደርጎ ነበር፤ የእርቅ ንግግሩ የተካሄደው ለወህኒ ቤቱ አዛዦች ትእዛዝ ተላልፎ፣ የሚመጡት ሽማግሌዎች ሰፊ ጊዜ ተሰጥአቸው፣ የተወሰኑ እስረኞችን ከየሰፈራቸው አስጠርተው፣ አንድ ሰፊ ቢሮ ውስጥ እንዲነጋገሩ ይደረጋል፤ ይህ ሲሆን የወህኒ ቤቱ አዛዦችና ፖሊሶች ብቻ ሳይሆኑ እስረኞችም ያውቃሉ፤ ከእስረኞች በኩል የሚጠሩት በመሠረቱ የቅንጅት ሹማምንት ናቸው፤ ሹም ያልሆንሁ እኔ ብቻ ነበርሁ፤ አብዛኛውን ጊዜ የምንጠራው ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል፣ ወይዘሮ ብርቱካን ሚደቅሳ፣ ዶር. ብርሃኑ ነጋ፣ ዶር. ኃይሉ አርአያ፣ ዶር. ያዕቆብ ኃይለ ማርያምና እኔ ነበርን፤ ወደመጨረሻው ላይ ነገሩ ስላላማረኝ መሄድ ባለመፈለጌ ሲጠሩኝ እቀር ነበር፡፡

የመጀመሪያው የእርቅ ሙከራ በፕሮፌሰር ዶናልድ ሌቪን የተካሄደው ነበር፤ ለጥቂት ቀናት ተመላልሶ አነጋገረን፤ በእኛ በእስረኞቹ በኩል ያለውን ሀሳብ አዳምጦ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ በኩል ያለውንም ሀሳብ ነግሮን ነበር፤ ዶናልድ ሌቪን የፈለገው ከሱ ተሰርዞ የእርቅ ንግግር እንዲደረግ ነበር፤ እንደሚመስለኝ ነገሩ አላማረውም፤ ስለዚህም አቋርጦ ወደአገሩ ተመለሰ፤ ነገር ግን በአንድ ነገር ግማሽ ውጤት አስገኝቶአል፤ የትግሬን ዘር የማጥፋት የሚለው ክስ በጣም አናዶት፣ «የዘር ማጥፋት» የፖሊቲካ መጫወቻ አይደለም፤ ብሎ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደነገረው ገልጾልናል፤ በጥቂት ቀናት ውስጥ የዘር ማጥፋት የሚለው ክስ በዘር ማጥፋት ሙከራ በሚል እንደተተካ ከፍርድ ቤቱ



ሰማን፤ ይህ የዶናልድ ሌቪን የእርቅ ንግግር ሙከራ ውጤት ነው፤ በዚሁ አበቃ፡፡

ሁለተኛው የሽምግልና ሙከራ በፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሐቅ በሚመራ ቡድን ነበር፤ በሽማግሌዎቹ በኩል ዋናው ፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሐቅ ሲሆን በመጀመሪያው ላይ አብረው የሚመጡት የታወቀው ሻለቃ ኃይሌ ገብረ ሥላሴና ካህን ዳንኤል ነበሩ፤ በኋላ አምባሳደር በቀለ እንደሻው ተጨመረ፡፡ ቆይቶም ለሁለት ቀናት ያህል ዶር. ኃይለ ሥላሴ በላይና ዶር. መሀመድ ሞሄን ከአሜሪካ ብቅ ብለው ነበር፤ በመጨረሻው ላይ የታወቀው ጠበቃና የሕግ ምሁር አቶ ታምሩ ወንድምአገኝ ከፕሮፌሰር ኤፍሬም ጋር መምጣት ጀመረ፤ ፕሮፌሰር ኤፍሬምን ዋናው ያልሁበት ምክንያት ሁልጊዜም የጠቅላይ ሚኒስትሩን ቃል ይዞ የሚመጣው እሱ ስለነበረ ነው፡፡

ፕሮፌሰር ኤፍሬም ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር መገናኘቱን እንዴት አወቃችሁ የሚል ጥያቄ ተገቢ ይሆናል፤ ምንም ዓይነት ቀጥታ ማስረጃ የለንም፤ ፕሮፌሰር ኤፍሬም የሐሰት መልእክተኛ ነበር ለማለትም ቅንጣት ያህል ማስረጃ የለንም፡፡ ነገር ግን ፕሮፌሰር ኤፍሬም በመጣ ቁጥር በወህኒ ቤቱ መግባቱና የመሰብሰቢያ ቢሮ ማግኘቱ፣ በተጨማሪም እኛን እስረኞቹን ከያለንበት አስጠርቶ ለብዙ ሰዓታት ማነጋገሩ ያለበላይ ባለሥልጣን ሊሆን እንደማይቻል የታወቀ ነው፤ በወህኒ ቤቱ ከያለንበት ስንጠራም ‹ሽማግሌዎቹ መጥተዋል» እየተባልን ነበር፤ በወህኒ ቤቱ ውስጥ የነበሩ ሁሉ ከሽማግሌዎች ጋር እንደምንነጋገር ያውቁ ነበር፤ ከዚያም በላይ በአንዳንድ የውጭ ራድዮ የተነገረና በተለያዩ ጋዜጦች ላይም የወጣ ጉዳይ ነበር፤ ይህም ሲሆን አንድም ጊዜ የማስተባበያ መግለጫ በየትኛውም የዜና ማሰራጫ አልተሰማም፤ ከፕሮፌሰር ኤፍሬም ቡድን ጋር ንግግር የተካሄደው ለብዙ ወራት ነበር፤ በዚህ ጊዜ ውስጥ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወሬው አመለጠው ማለት የሚከብድ ነው፤ እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ ፕሮፌሰር ኤፍሬም ከአሜሪካ ተጠርቶ እንደመጣ ይነግረን ነበር፤ ሥራውን ትቶ በመምጣቱና ከፍተኛ ገቢ በማጣቱም ያማርር ነበር፤ በመጨረሻም ከሽማግሌዎቹ መሀከል አንዳንዶቹ ከፕሮፌሰር ኤፍሬም ጋር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ዘንድ ቀርበው እንደነበረ ነግረውናል፤ በዚህ ሁሉ ምክንያት ሽማግሌዎቹ በተለይም ፕሮፌሰር ኤፍሬም ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር እየተገናኘ በጉዳዩ ላይ ይነጋገር እንደነበረ በበኩሌ ምንም ጥርጣሬ የለኝም፡፡

የእርቅን ትርጉምና ታሪክን አለማወቅ ሆኖ ነው እንጂ እስረኛን ከንጉሥ ጋር ማስታረቅ በኢትዮጵያ የተለመደ ነበር፤ ስለዚህም በፕሮፌሰር ሌቪንም ሆነ በፕሮፌሰር ኤፍሬም የተደረገው ሙከራ ታሪክንና ባህልን

የተከተለ፣ በበጎ መንፈስ ላይ የተመሠረተ ሙከራ ነበር፤ በሽምግልናው ውስጥ የተሳተፉት ሰዎች ሁሉ በቅን መንፈስ ተነሣስተው፣ ታሪክንና ባህልን ተመርኩዘው፣ ለአገር ሰላምና እድገት ተቆርቁረው እንደሆነ በበኩሌ አልጠራጠርም፤ እኛን ከእስር ለማስፈታት የነበራቸው ምኞት እስረኞቹ ራሳቸው ለመፈታት ከነበራቸው ምኞት የጠነከረ ነበረ፤ ቀጥዬ እንደማመለከተው ሽምግልናው አንድ ደረጃ ላይ ሲደርስ በአብዛኛዎቹ እስረኞች በኩል በሽምግልናው አካሄድ የመበሳጨትና ተስፋ የመቁረጥ ሁኔታ ቢኖርም ሽማግሌዎቹን በማክበር ተግባራቸውን እስኪጨርሱ በመታገስ ቆየን፡፡

በመሠረቱ አሳሪንና እስረኞችን መሸምገል በጣም አስቸጋሪ ነው፤ በተለይም ታሳሪዎቹ ራሱ ገዢው ቡድን በፈጠረው በኢትዮጵያ ውስጥ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ በሥልጣን ላይ ያለውን ቡድን በብርቱ ፋክክር ስለገጠሙትና ወደጠርዝ ስለገፉት በተፈጠረው ትርምስ በርግጎ ጠንካራ የኃይል እርምጃ ወሰደ፤ ለዚህ ኃላፊነቱ የማን ነው? ለእኔ እንደመሰለኝ እርቅ አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት ይህንን ጥያቄ በጨዋ ደንብ ለመመለስ ነበር፤ ምናልባት ሽምግልና የተባለው ለአሳሪው የወንድ በር ለመስጠት ዘዴ ለመፈለግ ካልሆነ በቀር ሌላ ውጤት የሚያስገኝ ነው ብሎ ያመነ አልነበረም፤ ፕሮፌሰር ኤፍሬም አቶ መለስን በሚያነጋግርበት ጊዜ አቶ መለስ በየትኛው ወንበር ላይ ተቀምጦ እንደነበረ ግልጽ አልነበረለትም፤ አንድ ቀን ስለመንግሥት ሥልጣን ይናገርና በሌላ ጊዜ ሲመጣ ደግሞ ስለወያኔ/ኢህአዴግ ፓርቲ ቢሮ ይናገራል፤ ይህ ነጥብ በቀላሉ መታየት ያለበት አይመስለኝም፤ በፓርቲ ደረጃ ከሆነ አንደኛ አሳሪው የወያኔ/ኢህአዴግ ፓርቲ ሳይሆን መንግሥት ነው፤ ይህ ነጥብ እንኳን ለእንግዳው ለፕሮፌሰር ኤፍሬምና ለአቶ መለስም ግልጽ የነበረ አይመስለኝም፤ በአሳሪና ታሳሪዎች መሀከል ለሽምግልና የሚደረገው ንግግር በወያኔ/ኢሕአዴግና በእስረኞቹ መሀከል ሳይሆን በጠቅላይ ሚኒስትር ወንበርና በእስረኞቹ መሀከል ነው፤ መንግሥትንና ወያኔ/ኢህአዴግን አንድ አድርጎ መመልከት በሁሉም በኩል የብዙ ስሕተቶች መነሻ ነው፤ ስለዚህም ይህ ሽምግልና በብዙ መልኩ አንካሳ ነበር ለማለት ይቻላል፡፡

ገና ከመጀመሪያው ፕሮፌሰር ኤፍሬም የእርቅ ሀሳብ ከሻለቃ ኃይሌና ከፓስተር ዳንኤል ጋር ይዞ ቃሊቲ ሲመጣ በአሳሪና በታሳሪዎች መሀከል የታሰበው እርቅ አንካሳ መሆኑንና ይህንን የተዛባ ሚዛን ለማቃናት በሽማግሌዎቹ በኩል የበለጠ ጥረት እንደሚያስፈልግ ገልጬለት ነበር፤ መለስ እርቅ ቢፈልግ ሁሉ በጁ ሁሉ በደጁ ነው፤ ነገር ግን ለብዙ ወራት ያህል ያሰራቸውን ሰዎች በድንገት እርቅ ብሎ ቢፈታቸው፣ ሲያሰራቸው የፈጸመውን ዓይነት ስሕተት ይፈጽማል፤ ሲፈልግ የሚያስር፣ ሲፈልግ የሚፈታ አምባገነን



ሆኖ በግልጽ ይታያል፤ ስለዚህ እርቁ ለሱ የፖለቲካ ጥቅም የሚያስገኝለት መሆን እንዳለበት ሁላችንም እኩል ገብቶን ነበር ለማለት አያስችልም፤ ስለዚህ ለመለስ የወንድ በር መስጠት በግድ አስፈላጊ መሆኑ ለእኔ ገብቶኛል፡፡የይቅርታ መጠየቅ ነገር ገና ሲነሣ በእስረኞች በኩል ጠንካራ ተቃውሞ ነበረ፤ እንዲያውም ብዙዎች እዚህ ቃሊቲ እንኖራለን እንጂ ይቅርታ የምንጠይቅበት ምክንያት የለንም ብለው ሃይማኖታዊ አቅዋም የያዙ ነበሩ፤ በአንድ በኩል አቶ መለስ ሲፈልግ የሚያስርና ሲፈልግ የሚፈታ መስሎ መታየት ስለሌበት እስረኞቹ ችግሩን ተገንዝበው ለአቶ መለስ የወንድ በር መውጫ እንዲሰጡት አስፈላጊ መስሎ ስለታየኝ ብዙዎቹን ለማግባባት ጥረት አድርጌያለሁ፤ በሌላ በኩል ደግሞ እስረኞቹም በሕዝብ ዘንድ ያላቸውን ክብራቸውንና እምነት አጥተው መንፈስ ደካሞች መስለው ለመታየት አልፈለጉምና ለእነሱም የወንድ በር መውጫ አስፈላጊ ነበር፤ በዚህ ንግግር ላይ እኔ በግልጽ የሚታየኝ በእስረኞች በኩል በአዲስ አበባና በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች የተገደሉትን በመቶዎች የሚቆጠሩና የቆሰሉ ሰዎች፣ ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉና የተሰደዱ ሰዎች፣ ከሥራቸው የተባረሩ ሰዎችና በተለያየ መንገድ ንብረታቸውን ያጡ ሰዎች ጉዳይ ዋናው ነበር፤ በእስረኞቹ በኩል ከእስር ቤት የመውጣቱ ጉዳይ ሁለተኛ ነበር፤ በሌላ አነጋገር የእኔ አስተሳሰብ በእስረኞቹ በኩል ሲታይ የእርቁ አስፈላጊነት በመሠረቱ እስረኞቹን ለማስፈታት ብቻ ሳይሆን ከእነሱ መፈታት ጋር ተያይዞ የሚመጣው የእርቅ ንግግር ለአገሩ በጠቅላላ፣ በተለይም በልዩ ልዩ ሁኔታ ለተጎዱት ሰዎች ማገገሚያ ያስገኛል የሚል ነበር፤ ይህንን ሀሳብ እስከመጨረሻው ገፍቼበታለሁ፡፡

ፕሮፌሰር ኤፍሬም በኢትዮጵያዊነት ስሜቱ፣ በቅንነቱና ቶሎ በማመን ዝንባሌው ተስፋን ይዞ የሚጓዝ በመሆኑ ልዩ ሰው ይሆናል፤ ከብዙ ዘመን ጀምሮ የሚኖረው በፈረንጅ አገር ስለሆነ የማይጠራጠር፣ የነገሩትን እንደነገሩት የሚቀበልና የተባለውን እንደተባለው የሚያስተላልፍ ንጹሕ ሰው ይመስለኛል፤ ስለዚህም ቃሊቲ መጥቶ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የተባለውን ይነግረንና ሰፊ ውይይት ከአደረግን በኋላ የኛን ይዞ ደግሞ ወደጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሄዳል፤ ተመልሶ ሲመጣ በፊት ከተነጋገርነው ጭራሽ የተለየ ነገር ይዞ ይመጣል፤ ነገሩ ሲለወጥበት በጣም ግራ ቢጋባም ጥርጣሬ ሳያቀዘቅዘው የራሱን መስመር እንደያዘ በተስፋ ይቀጥላል፤ ከላይ ሰምቶ የሚመጣው ሀሳብ በየጊዜው ሲለዋወጥበትም በጎ የመሰለውን አቅጣጫ ይዞ ወደፊት ይሄዳል እንጂ ቆም ብሎ የተለወጠውን ሀሳብና ምክንያቱን ለማሰላሰል ጊዜውን አያጠፋም፤ ወይም ያፈጠጠው እውነት ቀዝቃዛ ውሀ የሚደፋበት እየመሰለው ጠለቅ ብሎ መመርመር አያሻም ይሆናል፤ አንዳንድ ጊዜ በጣም ሲጨንቀው በጠቅላይ ሚኒስትሩ እግር ላይ እንደሚወድቅና እንደሚለምን ነግሮናል፤ በእኛም በኩል

ከረር ሲልበት እንዲሁ ወደለቅሶና ወደ እግር ላይ መውደቅ ይደርሳል፤ ጉዳዩን ለመጨረስ ከራሱ ክብር በላይ የሆነ ብርቱ ስሜት ነበረው።

አጀማመሩ ላይ የነበረውን መንፈስ ላስረዳ፤ ፕሮፌሰር ኤፍሬም ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር የተነጋገረውን በሙሉ ልብ ተቀብሎና አምኖ ለእኛ የእርቁን ሀሳብ በሚያስተላልፍበት ጊዜ በጋለ ተስፋና መንፈስ ነበር፤ እስረኞቹ በበኩላቸው የእርቁን ሀሳብ በቅን መንፈስ ተቀብለው፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩም፣ እስረኞቹም በጨዋነትና በክብር የሚገላገሉበትን መፍትሔ ለመቅረጽ አእምሮአቸውን አዘጋጅተው ነበር፤ በምርጫ 97 ምክንያት ለተከሰተው ረብሻ፣ ለጠፋው የሰው ሕይወትና ለወደመው ንብረት ወደዝርዝር ሳንገባ በደፈናው የየድርሻችንን ኃላፊነት ተቀብለን መንግሥትም፣ ቅንጅትም የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ ይጠይቁ የሚል የስምምነት ሀሳብ ላይ ተደረሰ፤ በእውነቱ በምርጫ 97 የሆነውን የሚያውቅ ሁሉ ይህ የመስማሚያ ሀሳብ ያጋደለ ከሆነ በየት በኩል እንዳጋደለ ለመገመት አያስቸግረውም፤ ከእስረኞቹ ይበልጥ የወንድ በር፣ የክብር መውጫ የሚያስፈልገው መንግሥት መሆኑን በማወቅ በእርቅ መንፈስ የተለቀቀ የሚዛን መዛባት ነበር፤ ምናልባትም ለዚህ የተዛባ የሚመስል የእርቅ መንገድ በይበልጥ ኃላፊነቱ የእኔ ሳይሆን አይቀርም፤ እርቅ መስሎ ለተሰነዘረው ሀሳብ በእውነተኛ ቅን መንፈስ መልስ ለመስጠት ሲባል የታለመ ነበር፤ ይህ ደረጃ የእርቁ ንግግር አናት ነበር ለማለት እንችላለን።

ከላይ ወደተገለጸው የመስማሚያ ሀሳብ ለመድረስ የፈጀብን የስብሰባ ቁጥር ከዚያ በኋላ ከተደረጉት ስብሰባዎች ጋር ሲወዳደር ያነሰ ይመስለኛል፤ ያንን የመስማሚያ የእርቅ ሀሳብ ለመናድ የተደረጉት ስብሰባዎች የሚበልጡ ይመስለኛል፤ ወደፊት በመራመድ ፋንታ ፕሮፌሰር ኤፍሬም አዳዲስ ሀሳቦችን እያመጣ ውሀ ቅዳ ውሀ መልስ እየሆነ አሰለቸ፤ ሽማግሌዎቹ አሳሪውንና ታሳሪዎቹን በእኩልነት ለማየት የሚችሉበት ሁኔታና እውነተኛ የእርቅ መንፈስ ቢኖር ሁለቱም ወገኖች በክብር የሚቀራረቡበትን መንገድ ለማግኘት አስቸጋሪ ቢሆንም ይቻል ነበር። ነገር ግን ኃይል ያለው ወገን የክብር መውጫውን ለራሱ የመቀበል ፍላጎት እያሳየ እስረኞቹን ደግሞ ከእስር በመውጣታቸው ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ ይገፋበት ነበር። በዚህም ምክንያት እንደተፈለገው ወደስምምነት በፍጥነት ለመድረስ አልተቻለም።

ስለዚህም ሀሳቡ በሁለቱም በኩል ተቀባይነትን ባለማግኘቱ ውሳኔው ዘገየ።
ከጠቅላይ ሚኒስትሩ በኩል የሚመጣው ግፊት እስረኞቹ ከምርጫ 97 በኋላ ለተፈጠረው ችግር ሁሉ ምናልባትም በጠቅላይ ሚኒስትሩ በሚታዘዘው ጦር



ጭንቅላታቸውን እየተመቱ ለሞቱት ሁሉ ኃላፊነቱን እስረኞቹ እንዲቀበሉና ጠቅላይ ሚኒስትሩን ነጻ እንዲያወጡ የሚሻ ይመስል ነበር፤ በዚህ ምክንያት በዚያን ጊዜ ሚዛናዊ መስሎ የታየው አማራጭ ወደ ዝርዝር ሳይገባ ኃላፊነቱን ለሁለቱም በማካፈል እስረኞቹ የራሳቸውን ድርሻ ተቀብለው ይቅርታ ሕዝብን እንዲጠይቁ፣ በጠቅላይ ሚኒስትሩም በኩል እንዲሁ ድርሻውን ኃላፊነት ተቀብሎ ሕዝብን ይቅርታ እንዲጠይቅ ነበር፤ የወንድ በር የተባለው በዚህ መንገድ ሁለቱንም አቀራርቦ በኢትዮጵያ ሕዝብ ፊት ላቅ ያለ የመንፈስ ደረጃ ያደርሳቸዋል የሚል እምነት ነበር፤ እስረኞቹ የድርሻቸውን ኃላፊነት ተቀብለው ከፈረሙ ጠቅላይ ሚኒስትሩም በበኩሉ ይቅርታ ይጠይቃል የሚል መግባባት ነበረ፤ እንዲህ ከሆነ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ዓቃቤ ሕጉ በስሩ ስለሆነ በቀጥታ ክሱ እንዲሰረዝና የፍርድ ቤቱ ጉዳይ እንዲቋረጥ የማድረግ ሥልጣን እንዳለው በሕግ ባለሙያው ተነገረን፤ (ቀደም ሲል በሌላ ክስ በ1990ዎቹ ውስጥ የዋስትና ገንዘብ አስይዤ ከተለቀቅሁ በኋላ በቀጠሮው ዕለት ፍርድ ቤት ስሄድ ዳኛው ዓቃቤ ሕጉ ክሱን ስለሰረዘ የዋስትና ገንዘብህን ተቀብለህ ሂድ አለኝ፤) ክሱን መሰረዝ ይቻል ነበር ማለት ነው።

በሁለቱም በኩል ከባድ ተቃውሞ ነበረበት፤ ሆኖም እስረኞቹ እልህ አስጨራሽ ክርክር አድርገው ስምምነት ላይ ደረሱና የሽማግሌዎቹ ወረቀት ተፈረመ፤ እስረኞቹ የፈረሙበት ወረቀት ለሽማግሌዎቹ የተጻፈ ነበረ፤ ፕሮፌሰር ኤፍሬምም የተፈረመበት ወረቀት ለሽማግሌዎቹ ሆኖ ሽማግሌዎቹ በበኩላቸው የራሳቸውን ደብዳቤ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደሚጽፉ አረጋግጦ ነገሮናል።

በመጨረሻው የፊርማ ጉዳይ ስብሰባ ላይ እኔ ለመገኘት አልፈልግሁም ነበርና አልሄድሁም፤ በኋላ ጫና ስለበዛብኝ በስብሰባው ላይ ስደርስ እንደተለመደው ብርሃኑ ነጋ መድረኩን ይዞ ለመፈረም ፈቃደኞች ያልሆኑትን ለማግባባት ይሞክር ነበር፤ ብርሃኑ በመጀመሪያው ላይ የእርቁና የይቅርታ መጠየቁን ነገር በጣም የሚቃወም ነበር፤ በኋላ ግን በውይይትና በክርክር መለስ ያለ አቅዋም ያዘ፤ ለማናቸውም እኔ በስብሰባው ላይ እንደደረስሁ ሁላችንም ለግል ክብርና ጀብደኛነት ሳይሆን ለአገራችንና ለወገናችን በማሰብ ከቃሊቲ ለመውጣትና ትግላችንን ለመቀጠል መቻል አለብን በማለት፣ ከዚያም በላይ የብዙ ታሳሪዎች ቤት እየፈረሰ የቤት ኪራይ መክፈል እያቃታቸውና ልጆቻቸውም ከትምህርት ቤት እየወጡ መሆኑን እየጠቀስሁ ተናገርሁና ሁሉም ተስማማ፤ በስብሰባው ላይ ኤንጂነር ኃይሉ ሻውል አልነበረም፤ ስለዚህም ወደሱ ዘንድ ሄደን እሱንም አሳምነነው ወደስብሰባው መጥቶ ስብሰባውን እንዲመራ አስረግን። እኔ ሁሉም እንዲፈርም በተቻለኝ መጠን ሳበረታታ ብቆይም በበኩሌ ራሴን እንደፖሊቲከኛ ሳይሆን እንደስብአዊ መብቶች

ተከራካሪ አድርጌ በመቁጠር ላለመፈረም ወስኜ ነበር፤ ነገር ግን ይህ አቅዋም ክርክር የማይችል ሆነብኝና ተገፍቶ ወደቀብኝ፤ አንተ እኛን ፈርሙ እያልህ ለራስህ አልፈርምም ካልህ እኛም የምንፈርምበት ምክንያት የለም በማለት ደበበ እሸቱ ተጋፈጠኝና ወዲያው ሀሳቤን ለወጥሁ::

የእርቁን መጨረሻ ለመስማት ስንጠባበቅና ፍርድ ቤትም በምንሄድበት ጊዜ የከሳሹ ጠበቃ ክሱን ያነሣል እያልን ስናስብ የፍርድ ቤቱ ሥራ ቀጥሎ የከሳሽ ጠበቃዎች የሞት ቅጣትን ጠየቁ፤ ፍርድ ቤቱ ደግሞ ወደ ዕድሜ ልክ እስራት በብዙዎቹ ላይ ፈረደ፤ የፍርድ ቤቱ ድራማ ተጀምሮ የነበረውን የሽምግልና ሙከራ ባይሽረውም መንፈሱን ክፉኛ ለወጠው፤ በሽማግሌዎቹ በኩል በቅን መንፈስ የተጀመረ የመሰለው ጉዳይ ፈጽሞ ከሽፈና እስረኞቹ ሁሉ የተፈረደባቸው ወንጀለኞች ሆኑ፤ የፍርድ ቤቱ ድራማ ወደፊት ብዙ የሚጻፍበት ነው::

ለጊዜው በሽምግልናው ላይ እናተኩር፤ የፍርድ ቤቱ ድራማ ሲያበቃ ሽምግልናው የሞተ መስሎ ነበር፤ ምክንያቱም ለእስረኞቹ የታሰበው የወንድ በር ድራሹ ጠፍቶ ወንጀለኞች ተባሉ፤ ነገር ግን ሽምግልናው የይቅርታ ኮሚሽኑ አጋፋሪ ሆኖ ብቅ አለ፤ በሽምግልና የተፈጸመውን ፊርማ የይቅርታ ኮሚሽኑ በደብዳቤ እንድናረጋግጥለት ፈልጎ ነበር፤ እኛ ግን አይተነው የማናውቀው ኮሚሽን ጋር በመጨረሻው ሰዓት ላይ መጥቶ ሊያስፈርመን መፈለጉ እያስደነቀን አበሳጨን፤ እንደማንፈርምም ነገርናቸው፤ ስለዚህ ለሽማግሌዎቹ በጻፍነው ደብዳቤ ላይ የሚገኘው ፊርማ የእኛ መሆኑን ብቻ በቃል አረጋገጥን፤ ከዚያን ቀን በፊት የይቅርታ ኮሚሽን ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት አልነበረንም፤ ብዙ እስረኞች የሚሞሉትንና የሚያስሞሉትን ወደአሥር ገጾች ያለው ሰነድ አንዳችንም አልሞላንም፤ በመጨረሻው ሰዓት ላይ አደናብሮ የሽምግልናውን ተግባር ወደይቅርታ ኮሚሽኑ ለማዞር ሙከራ በፃዕር ላይ የነበረውን ሽምግልና ነፍሱን አወጣው::

## 4. የሽምግልናው መጨረሻ

ዓላማው ባይሳካም የይቅርታ ኮሚሽኑ በመጨረሻው ቀን ወደቃሊቲ መምጣት በአንድ በኩል የእስረኞቹ መፈታት ጉዳይ ከመለስ ዜናዊ እጅ የወጣ ያስመስለዋል፤ ከሽማግሌዎቹም እጅ የወጣ ይመስላል፤ በዚህም ምክንያት የታሰበው የእርቅ ነገር መሠረቱ የተናደ ይመስላል፤ በሌላ በኩል የእስረኞቹ መፈታት የመለስ ዜናዊ ፈቃድ ሳይሆን የመንግሥት እንዲሆን የተፈለገ ይመስላል፤ ከመለስ ዜናዊ ውጭ ሽማግሌዎቹና መንግሥት ምን ግንኙነትና ምን



አግባብ እንደነበራቸው እስካሁን የታወቀ ነገር የለም፤ ለማናቸውም የወንድ በሩ ለመለስ ዜናዊም አልሠራም፤ ለእስረኞቹ ደግሞ የተዘጋ መሰለ፤ ይህ ሁኔታ ውርደትን በእስረኞቹ ላይ ያመጣ ቢመስልም፣ ያጋለጠውና ያዋረደው ሽምግልናውን ነው::

ይወቀውም አይወቀውም ከሁሉም ይበልጥ የተጎዳውና የመንፈስ ልዕልና እንደሌለው ራሱን ያጋለጠው አቶ መለስ ዜናዊ ነው፤ እጁን ለመታጠብና በንስሐ ለመፅዳት የቀረበለትን ዕድል በጊዜያዊ የፖለቲካ ተድላ ለወጠው፤ እስረኞቹ ከማስፈራሪያ ጋር በይቅርታ በነጻ ሲለቀቁ የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን በእስረኞቹ ላይ ዘመቻ ጀመሩ፤ እስረኞቹ ጥፋታቸውን አምነው ጠቅላይ ሚኒስትሩን ይቅርታ ጠየቁ እየተባለ ለብዙ ቀኖች ተለፈፈ፤ በማስፈራሪያ የተፈቱት እስረኞች እየሰሙ ተናደዱ ወይም ሳቁ፤ ወይም እየተናደዱ ሳቁ::

ሽማግሌዎቹ በቴሌቪዥን ሲታዩ ምናልባት አንዳንዱን በግልጽ ከእውነት የራቀ ጉዳይ ያስተካክሉታል የሚል ግምት ነበር፤ ነገር ግን ዋናው የኤፍሬም ይስሐቅ መልእክት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ስለሽምግልና ማስተማር፣ እንዲያውም ሽምግልናን እንደብሔራዊ ስሜት መግለጫ አድርጎ ለማሳየት መሞከር ብቻ ሆኖ ቀረ፤ ከኢትዮጵያም አልፎ በአሜሪካ ለእስረኞቹ ብቻ ሳይሆን ለሰብአዊ መብቶችና ለሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነት የሚደረገውን ጥረት በፀያፍ አነጋገር ማጥላላት የሽምግልና ተግባሩ አደረገው፤ ለእነዚህ በበጎ መንፈስ በተነሣሱ ሰዎች ላይ የተጠቀመበትን አስተሳሰብ፣ ስሜትና ቃላት የሽምግልናውን መንፈስ በመጨረሻ ባጨናገፉት ሰዎች ላይ ሳይጠቀምበት መቅረቱ የሚያሳዝንና ሽማግሌ ሊኖረው የሚገባውን መንፈሳዊ ወኔ ማጣቱን ያመለክታል፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከጭቆና ለማውጣት የሚደረገውን ሙከራ ኢትዮጵያዊ አይደለም በሚል ሽፋን ብቻ የቀረበው የከረረና ሚዛን የሌለው ተቃውሞ በሽምግልናው የመጨረሻ ውጤት ላይ ከተደረገው ዝምታ ጋር ሲነፃፀር የሚያሳፍር ነበር፤ የኢትዮጵያን የሽምግልና ባህል (ያውም በሌለበት) አጉልቶ ለማሳየት የአሜሪካ ምክር ቤት አባሎችና በአሜሪካ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ለኢትዮጵያ ሕዝብ በቅን መንፈስ ያቀዱትን ጉዳይ ማውገዝና ማራከስ የሰው ልጆችን መንፈሳዊ ዝምድና የሚጎድ ነው::

አሜሪካኖችና ኢትዮጵያውያን በዜግነት የተለዩ ቢሆኑም ሰዎች በመሆናቸው አንድ ናቸው፤ ስንራብ የሚያዝኑልንና ስንደኸይ እርዳታ የሚልኩልን፣ እርስበርሳችን ስንጫረስ የማይወዱት ሰላምን የሚሰብኩልን፣ እንደፕሮፌሰር ኤፍሬም ላለ ምሁር ገንዘብ እየሰጡ የሰላምና የልማት ድርጅት የሚያቋቁሙልን፣ የሰብአዊ መብቶች ሲረገጡ የሚጮሁልን እነዚህ ፕሮፌሰር ኤፍሬም እኛ በባህል እንበልጣቸዋለን፤ ለእኛ በጎ አስተሳሰብ ስለሌላቸው

ለእርቅ እንቅፋት ይሆናሉ የሚላቸው ሰዎች ናቸው፤ የሕይወት ፋይዳ፤ የነጻነትና በሕግ ፊት እኩልነት ፋይዳ፣ ያለፍርሃትና ያለስጋት የመኖር ፋይዳ፣ ሠርቶ የመኖር ፋይዳ፣ የሰላም ፋይዳ ድንበሮችን ሁሉ ጥሰው ዓለም አቀፍ ጉዳዮች መሆናቸውንና ይህ ደግሞ የሰው ልጆችን የመንፈስ እድገት የሚያመለክት መሆኑን የአእምሮና የመንፈስ ሚዛኑን ተጭኖ ያጋደለበት ኃይል ቢኖር ነው እንጂ ፕሮፌሰር ኤፍሬም ረስቶታል ለማለት አልችልም፡፡

አፄ ኃይለ ሥላሴ ሞሮኮ ሄደው ሲሸመግሉ፣ ሱዳን ሄደው ሲሸመግሉ ሰብአዊነትንና አፍሪካዊነትን የኢትዮጵያዊነት አካል በማድረጋቸው በላቀ ደረጃ ኢትዮጵያዊነትን አስከብረው ነበር፤ ኢትዮጵያዊነትን ጣራ ላይ ለማውጣት የኢትዮጵያዊነትን የሰብአዊነት ካባ መግፈፍ፣ ግፍንና ሰቃይን፣ አፈናንና ግድያን ከእይታ ማውጣት የሚጠቅመው ማንን ነው? በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ በይሁዳዎች ላይ በጀርመን አገር የደረሰው ግፍ እንዲሰማን ይሁዳዎች መሆን ያስፈልገናል? በደቡብ አፍሪካ በነጮች የበላይነት ዘመናት በጥቁሮች ላይ የደረሰው ግፍ ሁሉ እንዲሰማን ጥቁር ደቡብ አፍሪካውያን መሆን አለብን? ከጥቂት ዓመታት በፊት አሸባሪዎች በአውሮጵላን በአሜሪካ ሰላማዊ ሰዎች ላይ የፈጸሙትን አሰቃቂ ጭካኔ ለማውገዝ አሜሪካን መሆን ነበረብን? አሜሪካ በኢራቅ የሚያካሂደውን ግፍ ለማውገዝስ ኢራቃውያን መሆን አለብን? የሰው ልጆችን ከዘር፣ ከቋንቋ፣ ከቀለም፣ ከጾታ፣ ከዜግነትም ሆነ ከማናቸውም ልዩነት አውጥቶ በሰውነት ደረጃ በእኩልነት የመብቶች ባለቤቶች ያደረጓቸው ዓለም አቀፍ ሕጎች ከታወጁ ሰባ ዓመታት ሊሆን ነው፣ ፕሮፌሰር ኤፍሬም በዜግነትና በአገራዊ ባህል ላይ ያተኮረውን ነቀፌታ በሙሉ የሰው ልጅ የደረሰበትን የመንፈስ ልዕልና ባለመረዳትና የመንፈስ ልዕልናን ድንበር ዘለል ባሕርይ ሳያውቅ ቀርቶ ነው ለማለት አይቻልም፤ የሚበልጥበት ጫና አጋጥሞት ይሆናል፡፡

እንዲሁም የካህን ዳንኤል አርምሞ መንፈሳዊ ሚዛኑ በአፍአዊ ጭነት ማጋደሉን ያመለክተኛል፤ በምንሰበሰብበት ጊዜ ሁሉ እየጮኸ ያሰማንን እኔንም ልቤን ሲመስጠው የነበረውን ጸሎቱንና ለአምላክ ጽድቅ ያለውን ፍቅር እንዳያስታውስ፣ ጀርባውን ለእውነት እንዲሰጥ ያደረገው ጭነት ከባድ መሆን አለበት፡፡

ሽምግልናው ሌላም ጉድለትን አሳይቶአል፤ በአደባባይ በቴሌቪዥን የወጣውን ሐሰት ለማስተባበልና እውነቱን ለመናገር መንፈሳዊ ወኔ አልነበራቸውም፤ እኛን ለማሳመን የነገሩን ሁሉ ሳይፈጸም ሲቀር ያንን ለሕዝብ የመግለጥ ኃላፊነት እንደነበረባቸው የሚያጠራጥር አይደለም፤ ሌሎችን እናስፈታለን ብለን እኛ ለመታሰር አንፈልግም፤ ወይም ጥቅም ይጎድልብናል ቢሉ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚኖሩት ፍርሃታቸው ምናልባት ተቀባይነት ያገኝ



ይሆናል፤ በአሜሪካ የሚኖሩት ምን አስፈራቸው? ቢሆንም ለምሳሌ እኔ እስከማውቀው ድረስ እስረኞቹ ለአቶ መለስ ዜናዊ ደብዳቤ አልጻፉም፤ ሌሎችም ነገሮች እንዲሁ ተድበስብሰው እውነቱ ቁልጭ ብሎ ለሕዝብ ሳይገለጥ እንዲቀር አድርገዋል፤ ነገሮችን የማድበስበሱ ውጤት ብርቱካን ሚደቅሳ ከሕግ ውጭ በሆነ መንገድ እንድትታሰርና ከሕግ ውጭ በሆነ መንገድ ለብቻዋ እንድትሆንና ከእናትዋና ከልጅዋ በቀር ሰው እንዳይጠይቃት ተደርጋለች፤ ከጥቂት ወራት ወዲህ ግን ሁለት ሴቶች እስረኞች እስዋ ባለችበት ክፍል ስለገቡ ብቸኛነትዋ ትንሽ ተቀንሷል ለማለት ይቻል ይሆናል፤ የወዳጅና የዘመድ ጥየቃው ግን ፍርድ ቤት ቢበይንም አሁንም እንደተዘጋ ነው፤ እንዲያውም አጥብቀውት ከእናትዋና ከትንሽ ልጅዋ በቀር ማንም ሌላ ሰው አያያትም፤ እኔም ላያት ሄጄ ተከልክያለሁ፤ ይህ ጉዳይ ደግሞ በይበልጥ አሁንም ፕሮፌሰር ኤፍሬም ላይ የሚወድቅ ቢሆንም ሌሎቹም፣ በተለይም ከእስረኞቹ ጋር ሲነጋገሩ የነበሩት ሁሉ እውነቱን የመግለጥ ኃላፊነት ያለባቸው ይመስለኛል፤ መንፈሳዊ ግዴታ ማንም በማንም ላይ የሚጭነው ሳይሆን ከውስጥ የሚመጣ ነው

ሁሉንም ካልን በኋላ ግን ሽማግሌዎቹ በሙሉ ከምርጫ 97 በኋላ በቅንጅት አባሎች፣ በነጻ ጋዜጠኞችና በማኅበራዊ ድርጅት መሪዎች ላይ የተወሰደው እርምጃ ለአገሪቱ ሰላም አስጊ መሆኑን በመገንዘብ የታሰሩት ሁሉ እንዲፈቱ በቅን መንፈስ ጥረት ማድረጋቸው የሚያስመሰግናቸው መሆኑ አይካድም፤ እስረኞቹን ለማስፈታት ያደረጉት ጥረት ለአገር እርቅና ሰላም በመሆኑ በሥልጣን ላይ ላሉትም የሚጠቅም መሆኑ ምንም አያጠራጥርም፤ የታሰሩትንም ለማስፈታት የተቻላቸውን ሁሉ አድርገዋል፤ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ሕዝብ የታሰሩት ሰዎች መፈታት ብቻውን ምንም ዋጋ የለውም፤ ፋይዳ የሚኖረው በኢትዮጵያ የሚኖረው የፖለቲካና የነጻነት ጉዞ ሲቃና ነው፤ በመወነጃጀልና በመራራቅ ፋንታ ተቀራርቦ መነጋገርና መወያየት ሲቻል ነው፤ ሽምግልናው እዚህ እንዲያደርስ አልተፈቀደለትም፤ ለመግፋትም መንፈሳዊ ወኔ አጣ፤ ተሰናክሎ ቀረ፡፡

በሥልጣን ላይ ያለው ቡድን በኢትዮጵያ ሁለት አዳዲስ መሠረቶችን መጣሉ አይካድም፤ አንዱ በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የፖለቲካ ቡድኖች እንዲቋቋሙና እንዲወዳደሩ ማድረጉ አንድ ትልቅ እርምጃ ነው፤ ሁለተኛው አሁንም ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ ታሪክ ነጻ ጋዜጦች በሕግ እንዲታተሙ ማድረጉ ሌላው ትልቅ እርምጃ ነው፤ ሆኖም በሥልጣን ላይ ያለው ቡድን ይህንን ታሪካዊና አዲስ የመንግሥት መሠረት ሕገ መንግሥቱን ተመርኩዞ ተግባራዊ ለማድረግ አልቻለም፡፡ ከምርጫ 97 በኋላ የተፈጠረው ችግር ሁሉ ከዚህ የተነሣ ነው፤ እንግዲህ ጥያቄው እስረኞቹን በመፍታት ችግሩ

ሁሉ ይፈታል ወይ የሚል ነው፤ የሽማግሌዎቹ ዓላማ ከዚህ የሚያልፍ መስሎ አይታይም፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ የመብት ጥያቄ ግን ይቀጥላል፤ይህንን ሊቀዘቅዝ የማይችል የሕዝብ ጥያቄ በሕገ መንግሥቱ ውስጥ በተካተቱት መብቶች መሠረት መልስ መስጠት የሚችለው በሥልጣን ላይ ያለው ቡድን ነው፤ በጉልበት ብቻ የሕዝብን ጥያቄ አፍኖ ለማስቀረት የማይቻልበት ዘመን ላይ ነን፤ ከደህነት ለመውጣት የሚሰማው መፈክር ሁሉ የሕዝቡን ጥያቄ በማፈን አይሳካም፤ ሰላም በጠመንጃ ብቻ እንደማይመጣ እንኳን ለኢትዮጵያ ለደሀዋ አገርና ለሀብታም አሜሪካም አለመቻሉን እያየን ነው፤ ሰላምን የሚያመጣው ኢትዮጵያ የሁላችንም አገር መሆንዋን መቀበል ነው፤ ሰላምን የሚያመጣው ሁላችንም በአገራችን ሀብትና ጉዳይ ላይ እኩል መብቶች ያሉን መሆኑን መቀበል ነው፤ ሰላምን የሚያመጣው ፍቅር ነው፤ እርቅ ነው፤ ልዩነትን እንደያዙ መከባበርና መተባበር ነው፤ ሌላው አማራጭ አሸናፊ የማይኖርበት የሁላችንም ጥፋት ነው።



# ፲፩
# ፖሊቲካና የሥልጣን ጥም በኢትዮጵያ

## ፤.ባህልና ሥልጣን

በአሁኑ ጊዜ ለፖሊቲካ እድገታችን ትልቁና ዋናው መሰናክልና ችግር የሥልጣን ጉዳይ ነው፤ አገዛዙ የጨበጠውን ሥልጣን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ለማስረከብ እንደማይፈልግ በተደጋጋሚ አሳይቶአል፤ በእኔ አስተያየት ተቀናቃኝ ቡድኖችም ሥልጣንን ለራሳቸው እንጂ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንደማይፈልጉ ውስጣቸው በሚፈጠረው ከሥልጣን ምኞት በሚነሣ ቱከክርና መጠላለፍ አሳይተዋል፤ እያሳዩም ነው፤ በሁለቱም በኩል ያለው ሁኔታ የሚያመለክተው ሥልጣንን ለሕዝብ ለማስረከብ ያላቸው ፍላጎት የመነመነ መሆኑን ነው፤ ሁለቱም የሚፈልጉት በተለያየ መንገድ ሕዝቡን የሥልጣን ፈረስ ለማድረግ ነው፤ አገዛዙ ላይ ያለው ቡድን በገንዘብም ይሁን በጉልበት ሕዝቡን ለማስገበር ይጥራል፤ ተቅናቃኝ ቡድኖች በበኩላቸው በሕዝቡ ብሶትና ጭንቀት፣ ችግርና ግፍ ላይ ተመርኩዘው የሥልጣን መሰላሉን ለመንጠቅ ይጥራሉ፤ በሁለቱም በኩል በጉልህ የሚታየው የሥልጣን ጥም አገርንና ሕዝብን ዓላማ ያደረገ ሳይሆን መሣሪያ የሚያደርግ አዝማሚያ ነው።

የዚህ የሥልጣን ጥም መሠረቱ ባህላችን ይመስለኛል፤ ችግሩን መጀመሪያ ያስተዋልሁት በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ነው፤ የአንድ የትምህርት ክፍል ኃላፊ ወይም ሊቀ መንበር ለመሆን የሚስገበገቡ ሰዎች ነበሩ፤ ያውም ስም ብቻ እንጂ ተጨማሪ ክፍያም አልነበረበትም፤ የፋኩልቲ ኃላፊ ወይም ዲን የገንዘብ ድጎማ ነበረውና በዚህ ላይ የነበረው ቱከክር ጎሊናንም ለጨረታ የሚያስቀርብ ነበር፤ ከፍ ብሎ የፕሬዚደንቱ ወንበር የበለጠና ወደመሸጦነት የሚያስጠጋ ነበረ፤ በዓለማያ ዩኒቨርሲቲ የነበረው ቱከክር በኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ከነበረው በጣም በጣም የባሰ ነበረ፤ የተማሩ ሰዎችን፣ ያውም መምህራንን እንዲህ የሚያደርጋቸው ስንፍና ይመስለኝ ነበር፤ የማስተማር ሥራ ከባድ ነው፤ ፋታ አይሰጥም፤ አስተዳደር ውስጥ ሲገባ የተደላደለ ቢሮና የተዝናና አሠራር ስለሆነ የሚስባቸው ይህና ገንዘቡ ብቻ ይመስለኝ ነበር፤ ሳሰላስለው ለብዙ ዘመናት ብቆይም እውነተኛ ምክንያቱ

---

[7] አሁን አዲስ ዘዴ አየሰማን ነው፤ የውጭ ጋዜጠኞች «መቼ ነው ሥልጣን የምትለቅቀው?» እያሉ ሲያስቸግሩት እስከዛሬ «ፓርቲዬ» ነው የሚወስነው በማለት ይመልስ ነበር፤ አሁን ከቅብብሎሽ ሩጫ ጋር እያመሳሰለ መናገር ጀምሮአል፤ የትውልድ ቅብብሎሽ! ይህንን ዴሞክራሲ ነው ብለን እንድንቀበል ያስባል!

አልተገለጠልኝም ነበር፤ እንደሚመስለኝ እውነተኛ ምክንያቱን የተገነዘብሁት በቅርቡ ወደፖሊቲካው ተግባር ከገባሁ በኋላ ነው፤ ቀደም ሲል ግን በሌላ መልክ ተረድቼው በጦቢያ መጽሔት ላይ በሰኔ 1989 **ጭቆና፣ ጨቋኝና ተጨቋኝ** በሚል ርእስ አንድ ጽሑፍ አቅርቤ ነበር፤ ይህ ጽሑፍ የሚጀምረው በሚከተለው ነው፤

*ጭቆና የሰውን ልጅ የአካል፣ የአእምሮና የመንፈስ የተፈጥሮ ችሎታ ማፈንና ሰውን ከሰውነት ደረጃ ማውረድ ነው፤ ከሰውነት ደረጃ የሚወርደው ተጨቋኙ ብቻ አይደለም፤ ጨቋኙም አብሮ ይወርዳል፤ ጭቆናን እንኳን ሰውና እንስሳትም አይወዱም፤የተገሩ የቤት እንስሳት ሁሉ የጭቆና ውጤቶች ናቸው፤በየሜካው የሚገኙት የነሱ ዝርያዎች በጣም የተለዩ ናቸው፤ በጭቆና በሰው ልጅ ላይ የሚደርሰው ጉዳት በእንስሳት ላይ ከሚደርሰው እጅግ በጣም የበለጠ ነው፤ በእንስሳት ላይ ሚደርሰው ጭቆና በአካልና በባሕርይ ላይ የተወሰነ ነው፤ በሰው ላይ የሚደርስ ጭቆና አእምሮንና መንፈስንም ይጨምራል፤ ስለዚህም እድገትንና መሻሻልን ይጎዳል።*

የዚህ መረን የለቀቀ የሥልጣን ጥም መሠረቱ ባህላችን ነው፤ ተወልደን እስከንቀበር ድረስ የምንኖረው በጭቆና ነው፤ የኔ ትውልድ በሕፃንነት አብሽ የሚጋተው በሁለት ጣቶች አፍንጫውን ተይዞ በሲቃ ነበር! በልጆች ላይ የሚደርሰው ቁጣ፣ ድብደባና እስር የወላጆችን ጭቆና የሚያመለክት ነበር፤ ለጌታ ማደር ሲመጣ ደግሞ ጭቆናው የከፋ ነበር፤ ሕፃን ሆኜ ያየሁት በአእምሮዬ ተቀርጾ የቀረ ስዕል አለ፤ አንድ ትልቅ ሰውዬ በበቅሎ ላይ ተቀምጠው ወደቤታቸው በራፍ ሲደርሱ አንድ የቆመ ሰው አዩና ዱብ ብለው ወርደው አጠገባቸው ባገኙት የበሬ አጥንት ጭንቅላቱን ፈረካከሰው ደም በደም አድርገውት ጥለውት ገቡ፤ ምናቸው እንደነበረ፣ ምን እንዳደረጋቸው አላውቅም፤ በእኛ ባህል ሥልጣን የሚጠቅመው እንደዚህ እንደልብ ለመባለግ ነው።

በአለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ በፖሊቲካ እንቅስቃሴዎች አካባቢ የታዘብሁት አሳዘኝ ነገር ብዙዎች ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ የደረሱ ሰዎች፣ በፈረንጅ አገሮች ለብዙ ዓመታት ስንት ነገር እያዩ የኖሩ ሰዎች የፈለጉትን ያህል ስለዴሞክራሲ ቢያወሩ ውስጣቸው ገና ከጭቆና የሥልጣን ምኞት አለመፅዳቱን ነው፤ ሥልጣን ለቂም፣ ሥልጣን ለጥላቻ፣ ሥልጣን ለግል ክብር፣ ሥልጣን ሎሌዎች ለማሰባሰብ፣ ሥልጣን በየኤምባሲው ለመታየት፣ ሥልጣን መርጠው ወንበሩ ላይ ያስቀመጡትን ሰዎች ለመናቅ፣ ቅጥ ያጣ የሥልጣን ምኞት! በየፈረንጅ አገሩ እንደምናየው በምርጫ ወንበር ላይ የወጡ ሰዎች መራጩን ሕዝብ እያባበሉና እየተንከባከቡ ይይዙታል እንጂ አይንቁትም፤ በእኛ ዘንድ



መራጩ ለንቀት የሚበቃው ራሱን ወደሎሌነት በመለወጥ ነው፤ ያንንም የሚያደርገው በሎሌነት ሥልጣን ለማግኘት ነው፤ የበላይነቱን ወደበታችነት ለውጦ በሌሎች ላይ የበላይነትን ለማግኘት ይፈልጋል፤ እንደበላይ ዘለቀ «እናቴ በላይ ብላኛለች» ብሎ ደጀዝማችነትን የሚንቅ ብዙ ኢትዮጵያዊ የለም፤የሱም ቢሆን አነሰኝ ማለቱ ሳይሆን አይቀርም፤ እንዲህም ቢያደርግ በመወደስ ፋንታ ትዕቢተኛ እየተባለ ይወቀሳል፤የራሱ ባለቤት ለመሆን በልበ ሙሉነትና በነጻነት መወሰኑ ጌታው ለመሆን ያኮበኮበውን ያስደነግጠዋል፤ያስቆጣዋል፡

## 2. ግለሰብና ብሔረሰብ

የባህላችንን ያረጀና ያፈጀ፣ የሻገተ ሸክም ሳናራግፍ ሌላ የማናውቀውን፣ ያልገባንን፣ ያላነጠርነውን፣ ያላብሰለሰልነውን የፈረንጆች ውራጅ በላያችን ላይ እንጭናለን፤ ሀሳቡ ሳይገባን ቃላትን እንተረጉማለን፤ ለምሳሌ ብሔር፣ ብሔረሰብ፣... እነዚህ ቃላት የእንግሊዝኛው ቃላት (nation, nationality) ያዘሉት ሀሳብ በጭራሽ ባልገባቸው ሰዎች የተተረጎሙ ናቸው፤ መሠረታዊ ሀሳቡን ትቶ ቃላትን መፍጠር ነው፤ ብሔር ማለት አገር ማለት ነው፤ ብሔረሰብ ማለት የሰው አገር ማለት ነው፤ ሁለቱም ቃላት የሚያመለክቱትት አገርን በመሆኑ ትርጉማቸው አንድ ነው፤ እንዴት ብለው ነው እነዚህ ቃላት የእንግሊዝኛውን ሀሳብ የሚያስተላልፉት? እንጀራን መሶብ ብሎ እንደመተርጎም ነው፤ ሥልጣን እውቀት ሲሆን ዓላማው ማደናበር ነውና ምንም ነገር ይቻላል፤ በነዚህ ቃላት እየተጠቀሙ ሀሳቡ ያልገባቸው ሰዎች ወደሌላ ፍጹም የተሳሳተ የመብት ትርጉም ውስጥ ገብተው ይደናበራሉ፤ መብት የራሱን ሰውነት ከተገነዘበ ሰው ጋር የተያያዘ ሀሳብ ነው፤ ብሔርና ብሔረሰብ የሚባሉት ቃላት በትክክለኛ ትርጉማቸው የሚያመለክቱት ግዑዝ ነገርን (አገርን) ነው እንጂ ሰውን አይደለም፤ ነገር ግን ጎሣ፣ ወይም ነገድ የሚባሉት የአማርኛ ቃላት የሰዎችን ስብስብ ስለሚገልጹ ወደእንግሊዝኛው ሀሳብ ይጠጋሉ፤ አዲስና ትርጉም የሌላቸው ቃላትን ከመፍጠር የነበረው ይሻላል ለማለት ነው እንጂ ነገድና ጎሣም የራሳቸው ችግር አለባቸው፤ በአብዛኛው ለኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አይሠሩም፤ የቋንቋ ልዩነት ብቻ ጎሣን ወይም ነገድን አይፈጥርም፤ ብዙ አከራካሪና ውስብስብ ነገሮች ስላሉበት ብዙዎች የሚስማሙት መሠረቱ በሰዎቹ ስሜት ላይ የቆመ መሆኑን ነው።

ወደዋናው ነገር ለመመለስ -- የመብት መሠረት አካል ያለው ሰው ነው፤ ለዚህ ነው የሰብአዊ መብትም ሆነ የዜግነት መብት መሠረቱ ግለሰብ ነው የሚባለው፤ ይህንን ማለት የጎሣ ወይም የነገድ፣ የሃይማኖት ወይም የቋንቋ፣ የጾታ ወይም የሙያ ወይም ሌላ ማናቸውም ስብስብ መብት የለውም ማለት አይደለም፤ **በማናቸውም ስብስብ ውስጥ የሚገኙ ግለሰቦች ሁሉ መብታቸው**

**ከተከበረ የስብስቦቹ መብት እንደሚከበር የተረጋገጠ ነው፤ በተቃራኒው ግን ማናቸውም ስብስብ መብቱ ከተከበረለት በውስጡ ያሉት ግለሰቦች ሁሉ መብት እንደሚከበር የተረጋገጠ ነው የሚል ማሰብ የሚችል ሰው ያለ አይመስለኝም፤** የግለሰብና የብሔረሰብ መብቶች በእኩልነት በአንድ ደረጃ እንዲታዩ የሚቀርበው እምነት በተዛባ አስተሳሰብ ላይ የተመሠረተ ነው፤ ግለሰቦች የብሔረሰብን ካባ ደርበው፣ ብሔረሰብ የሚሉትን ፈረስ እየጋለቡ የራሳቸውን የግለሰብ ዓላማ ለማሳካት የሚያደርጉት ጥረት ነው፤ ለዚህ ግዙፍ ማስረጃው አንድ ብሔረሰብን እንወክላለን ብለው የተቋቋሙ **ብዙ** ድርጅቶች መኖራቸው ነው፤ አንድ ብሔረሰብ በተለያዩ ድርጅቶች የሚከፋፈለው **በግለሰቦች** የተለያየ ዓላማ ነው፤ ብሔረሰቡ ሀሳብ የለውም፤ አንደበት የለውም፤ ራሳቸውን እንደብሔረሰብ ሰይመው እኛ እናስብለታለን፤ እኛ እንናገርለታለን፤ የሚሉ ግለሰቦች ራሳቸውን ዓላማ፣ ብሔረሰብን የግል መሣሪያ የሚያደርጉ ናቸው፤ በሶማልያም ሆነ በሌሎች የአፍሪካ አገሮች የምናየው ትርምስ ከዚህ የተነሣ ነው።

ከግለሰብ የሚነሣና ለግለሰቦች ስብስብ የሚያገለግል መብት አለ፤ አስተሳሰቡን ለመረዳት አስቸጋሪ አይደለም፤ ለግለሰብ ያልተሰጠ መብት ለማንኛውም ዓይነት ስብስብ ሊሰጥ አይቻልም፤ በአካል ያለውን ነፍን በአካል ለሌለው መብት መስጠት ሊሆን የማይችል ነው፤ ነገር ግን ለግለሰብ የተሰጠ መብት ሁሉ ለስብስቡም ይሆናል፤ ሰዎች እርስበርሳቸው የሚለያዩባቸው ነገሮች ብዙ ናቸው፤ ዘር (ምን ማለት እንደሆነ የሚያውቀው ከአለ)፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ ጾታ፣ ዕድሜ፣ ሙያ ወይም ሥራ፣ ሀብት፣ … እነዚህ ልዩነቶች ሁሉ የሚገለጡት በግለሰቡ ነው፤ የፋሺስት ፍልስፍና መሠረቱ የግለሰቡን መብት በብሔረሰቡ መበት የተዋጠና ያነሰ አድርጎ ማየቱ ነው፤ ይህም ማለት በአካል የሚታየውና የሚዳሰሰው ሰው መብት ሳይረጋገጥ የማይታየውና የማይዳሰሰው ብሔረሰብ መብት ይበልጣል ነው፤ ይህ የሚሆንበት ምክንያት አለው፤ ብሔረሰብን የሁሉም አድርጎ ግለሰቡን ነጥሎ ለመምታት ስለሚያመች ነው፤ ስለዚህ የግለሰብ መብትና የብሔረሰብ መብት እኩል ናቸው ማለት መሶብና እንጀራ፣ ጠርሙስና ውሀ፣ ድስትና ወጥ፣ ጆንያና ጤፍ እኩል ናቸው እንደማለት ነው።

ጉዳዩን በሌላ በኩልም ልናየው እንችላለን፤ ቤተሰብ የሚባለው ባልና ሚስትን፣ ልጆችን ጨምሮ ነው፤ የግለሰቡና የቤተሰቡ መብት አይነጣጠልም ቢባል ምን ማለት ነው? የባል መብት የግለሰብ መብት ነው፤ የሚስት መብት የግለሰብ መብት ነው፤ የእያንዳንዱ ልጅ መብት የግለሰብ መብት ነው፤ ከነዚህ የተለየ የቤተሰቡ መብት ምን ሊሆን ነው? ቤተሰብ በመሠረቱ የአንድ ማኅበረሰብ መሠረት በመሆኑ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ መብቶች አሉት፤ ነገር ግን እነዚህ መብቶች በግለሰቡ መብቶች ላይ የቆሙ ናቸው እንጂ



ተገንጥለው በአንጻራዊ መንገድ የሚታዩ አይደሉም፤ ቤተሰብ የሌለው ሌጣ ሰው አለ፤ መብቶችም አሉት፤ ግለሰብ የሌለበት ቤተሰብ ግን አይታሰብም፤ ባዶ ቀፎ ነው፤ ለመሆኑ ባልና ሚስትን፣ ልጆችን አስወጥቶ ቤተሰብ የሚባል ነገር አለ ወይ? ባል እንደግለሰብ፣ ሚስት እንደግለሰብ፣ ልጆች እንደግለሰብ ከወጡ በኋላ የሚቀረው ቀፎ ቤተሰብ ይባላል?

ብሔረሰብ ከሚባለውም ውስጥ ግለሰቦችን ሁሉ ከነሰብአዊና የዜግነት መብታቸው ካስወጣን የብሔረሰብ ቀፎ ውስጥ የሚቀረው ምንድን ነው? ግለሰቦቹ ሁሉ ከወጡበት የብሔረሰብ ቀፎ ውስጥ ቋንቋ አለ? ሃይማኖት አለ? ሀብታምና ደሀ አለ? ጨቋኝና ተጨቋኝ አለ? ሌላው ቀርቶ ዜግነትስ አለ? ጉዳዩን እንደዚህ አድርገን በመመልከትና በማፍታታት በማሰብና በስሜት በመነዳት መሀከል ያለውን ከባድ ልዩነት ለመገንዘብ እንችላል፤ በስሜት ብቻ እየተነዱ የመብት መሠረቱ ግለሰብ ነው ሲባል የብሔረሰብን መብት እንዳለመቀበል አድርገው ለመከራከር የሚፈልጉ ሰዎች እያሰቡ አይደለም፤ ጥረታቸው የአስተሳሰብ ግድፈታቸውን በፖሊቲካ ውኸምብር ለመሸፈን ነው፤ በመሠረቱ ለግለሰብ መብቶች የቆመ ሰው የማንኛውም ዓይነት ስብስብን መብቶች አይጋፋም፤ የመብት መነሻው ግለሰብ ነው ማለት ግለሰቦች በነጻነትና በፈቃደኛነት ሲሰበሰቡ መብት የላቸውም ማለት አይደለም፤ የአርባ ቀን ዕድላችሁ ስትወለዱ ተወሰወኖላችሁአልና በየተወለዳችሁበት ከረጢት ግቡ ማለትና መብቶቻቸውን የተገነዘቡ ግለሰቦች በነጻነትና በፈቃደኛነት የሚሰበሰቡበት ድርጅት መብት የለውም ማለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው፤ የመጀመሪያው የግለሰቡን መብት ረግጦ ይነሣል፤ ሁለተኛው የግለሰቡን መብት ይዞ ይነሣል፤ ለዚህ ነው የግለሰቡ መብት መነሻ መሠረት በመሆኑ ከብሔረሰብ መብት ጋር በአንድ ደረጃ ማየት የተሳሳተ አስተሳሰብ የሚሆነው።

**ብሔረሰብና ሃይማኖት**

| ሃይማኖት | ቋንቋ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ኦርቶዶክስ | ኦሮሞ | አማራ | ኦሮአማ | አማኦሮ | 4 |
| እስልምና | ኦሮሞ | አማራ | ኦሮአማ | አማኦሮ | 4 |
| ፕሮቴስታንት | ኦሮሞ | አማራ | ኦሮአማ | አማኦሮ | 4 |
| ካቶሊክ | ኦሮሞ | አማራ | ኦሮአማ | አማኦሮ | 4 |
| ሌላ | ኦሮሞ | አማራ | ኦሮአማ | አማኦሮ | 4 |
| ድምር | 5 | 5 | 5 | 5 | 20 |

ቁልፍ--- ኦሮአማ=ድብልቅ፤ አማኦሮ=ድብልቅ፤

የአስተሳሰብ ችግሩን ራሳቸው የብሔረሰብ ድርጅቶች የተባሉት በግልጽ እያሳዩት ነው፤ አብዛኛዎቹ ብሔረሰብ የሚባሉት ክፍሎች አንድ ብቻ የፖሊቲካ ድርጅት የላቸውም፤ የድርጅቱ መሠረቱ ብሔረሰብ ከሆነና ብሔረሰቡ አንድ ነው ከተባለ ያንኑ ብሔረሰብ የሚወክሉ ሦስት ወይም አምስት የፖሊቲካ ድርጅቶች የሚያስፈልግበት ምክንያት ምንድን ነው? ይህ ቀላል መልስ እንዴት እንደተሰወረባቸው አላውቅም፤ ድርጅቶቹ የተመሠረቱት በግለሰቦች ፍላጎትና ዓላማ በመሆኑ ነው፤ የተለያዩ ግለሰቦች የተለያየ ፍላጎትና ዓላማ ስላላቸው የተለያዩ ድርጅቶችን ይመሠርታሉ፤ እንግዲህ የትኛው ድርጅት ነው ከግለሰብ የተለየ የብሔረሰብ ውክልና አለው የሚባለው?

ሃይማኖት የግል ነው ማለት የማይከብዳቸው ሰዎች ቋንቋ የግል ነው ማለት ለምን ይከብዳቸዋል፤ ከግለሰቡ ውጭ ብሔረሰብ የሚባል ቋንቋን ተናጋሪ የለም፤ ቋንቋንና ሃይማኖትን አንድ ላይ አድርገን ለአንድ ብሔረሰብ መሠረት ብናደርጋቸው ለአማርኛና ለኦሮምኛ ተናጋሪዎች ብቻ ቢያንስ አምስት ድርጅቶች ለእያንዳንዳቸው ያስፈልጋሉ፣ ኦሮምኛ ተናጋሪዎች ቢያንስ የሦስት ዓይነት ክርስትናና የእስልምና ሃይማኖቶች ተከታዮች ናቸው፤ እንዲሁም የአማርኛ ተናጋሪዎች የሦስት ዓይነት የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖቶች ተከታዮች ናቸው፤ የተደባለቁትን እነኦሮአማንና (ኦሮሞና አማራ) አማኦሮን (አማራና ኦሮሞ) ስንጨምር የበለጠ ጉራማይሌ ይሆናል፤እንዲህ በቀላሉ ግለሰቦችን በብሔረሰብ ከረጢት ውስጥ መከተት የማይቻል መሆኑን ይህ ማስረጃ ብቻ ይበቃል።

ማሰብ ከተቻለ ሌላም ተጨባጭ ማስረጃ አለ፤ የብሔረሰብ ድርጅቶች ብሔረሰብ የተባሉትን የሚከፋፍሉበት ምክንያት መሠረቱ የግለሰቦች የሥልጣን ጥም ነው፤ ከዚህ ሌላ ምንም ምክንያት ሊገኝለት አይቻልም፤ የሚጋልቡበት የፖሊቲካ እምነትና ሀሳብ ሲያጡ ብሔረሰብ ቀላልና የተላመዱት ፈረስ መስሎ ይታያቸዋል፤ በዝምድናና በወዳጅነት ላይ የተመሠረተ ድርጅት የሚያቋቋቁሙበት ምክንያቱ ይኸው ነው፤ የሚለያዩበትም ምክንያት ይኸው ነው፤ በብዙ የእስልምና ተከታይ አገሮች የሚታየው ችግር ይኸው ነው፤ አንዳንዶች የሥልጣን ጥማቸውን ስኬታማ ለማድረግ የእስልምና ሃይማኖትን የሥልጣን መወጣጫ ፈረስ ሊያደርጉት ይሞክራሉ፤ በብዙ መንገድ ፈር ቀዳጅ የነበረው ታላቁ የአረብ ሕዝብ ኋላ-ቀር ሆኖ የሚታይበት ዋናው ምክንያትም ይኸው ነው።

በኢትዮጵያም ቢሆን በአለፉት ሀያ ዓመታት ግድም ያየነው ብሔረሰብ ከሃይማኖት ጋር ሲላተም ነው፤ ቤተ እግዚአብሔርም የንትርክና የመለያየት ቦታ እየሆነ ይታያል፤ ትክክለኛ ግንዛቤ የጎደለው የብሔረሰብ ስሜት እንኳን ብሔራዊ ስሜትንና ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናቸውንም እያረከሰው ነው።



ዴሞክራሲ የሚለው ቃል መሠረቱ እኩልነትና ነጻነት ነው፤ ሰዎች በዘራቸው፣ በቋንቋቸው፣ በሃይማኖታቸው፣ በጾታቸው፣ በዕድሜያቸው ወይም በሀብታቸው ሳይሆን በፖሊቲካ ሀሳባቸውና በፖሊቲካ እምነታቸው ተስማምተው ሲሰበሰቡ በእኩልነት ነው፤ በአገር ውስጥ እንዲሰፍን የሚፈልጉት የፖሊቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የማኅበረሰባዊ እቅድና የሚዘረጉት ሕጋዊ ሥርዓት ለዜጎች በሙሉ፣ ለአገር በሙሉ ይበጃል የሚሉትን ነው፤ መሪ ይሆነናል ብለው ከመሀከላቸው አንዱን ሲመርጡ በእኩልነትና በነጻነት ላይ ሆነው በዜግነት ተቀብለውት፣ በችሎታውና በልምዱ መዝነውት ወይም መዝነዋት ነው፤ በእንደዚህ ያለ ሁኔታ የተመረጠ ሰው ቅብዓ ቅዱስ ተቀብቻለሁ እንደሚል ንጉሥ ሲሆንና የመረጡትን ሰዎች ወደሎሌነት ለመለወጥ ሲሞክር ከባህሉ የጭቆና ተጽእኖ ገና አለመላቀቁን መገንዘብ አያስቸግርም፤ የዴሞክራሲም መንፈስ ገና እንዳልሠረጸበት መረዳት ይቻላል፤ ቅንጅትን ያፈረሰው ወያኔ ብቻ ሳይሆን በውስጡ ያውም በመሪነት ደረጃ የተመረጡ ሰዎችም ጭምር መሆናቸው ለእኔ በጣም ግልጽ ነው።

መጋቢት 29/97 በኤንጂኒር ኃይሉ ሻውል በኩል ለቅንጅት ምክር ቤት አባላት ደብዳቤ ጽፌ ነበር፤ ከብዙ ጥረት በኋላ የሚሰማኝ ስላጣሁ ከምክር ቤቱ ለመልቀቅ የወሰንሁበትን ምክንያት አስረድቼበታለሁ፤ ነገር ግን እንደጥሩ አበሻ በጊዜው ለሕዝብ እንዲታወቅ ባለማድረጌ አዝናለሁ፤ ዛሬ ለእኔ ትምህርት ሆኖኛል፤ ለማናቸውም በከፊል ሚከተለውን ይላል፤--

*…ቅንጅቱ ከተቋቋመ ጀምሮ የቅንጅትን ድል የማድረግ ዓላማ የሚጻረሩ ሁለት አዝማሚያዎች ለእኔ በግልጽ ሲታዩኝ ቆይተዋል፤ አሁን ለምርጫው የቀረው አምስት ሳምንታት ያህል ነው፤ ቅንጅቱ እነዚህን አፍራሽ አዝማሚያዎች ተሸክሞ ከቀጠለ ድል የማድረጉ ዓላማ ቢያንስ የደበዘዘ እንደሚሆን ይታየኛል፤ ቅንጅቱ ድልን የማጣቱ ውጤት የኢትዮጵያን ሕዝብ ተስፋ ከማስቆረጡ ጋር ተያይዘው ብዙ ከባድ ጥያቄዎች ይነሣሉ፤ የተለያዩ መልሶችም ይሰጣሉ። በአደባባይና በይፋ መወነጃጀሉ የማይቀር ይሆናል፤ በምርጫው የሚወድቁት ሰዎች ያለጥርጥር ይከፋሉ፤ የቀናቸው ሰዎች ሠራዊት የሌለው ጀኔራሎች ይሆናሉ። የዛሬው ሁኔታ በሰኔ በፍጹም ይለወጣል።*
*ለእኔ እንደሚታየኝ የቅንጅቱ አባሎች በሰኔ የሚፈጠረውን ሁኔታ ዛሬ በዓይነ አእምሮአቸው ማየት ግዴታቸው ይመስለኛል፤ አስቸጋሪ መሆኑ ይገባኛል፤ ግን ይቻላል። ቅንጅቱ በድል አድራጊነት ቢወጣ የሚያስከትለውን በአገሪቱ ሁሉ የሚያስተጋባ እልልታ በቅንጅቱ አባሎች ላይ ከሚጥልባቸው ከባድ ኃላፊነት ጋር ቀድሞ ማየት የሚሳነን አይመስለኝም። ቅንጅቱ ቢሸነፍ ግን በአገሪቱ በሞላ ብቻ ሳይሆን በውጭም የሚያስተጋባ ሑሉታና በቅንጅት አባሎች ላይ የሚሰነዘረውን የመረረ ነቀፌታ እንዴት እንደምንጋፈጠው ከአሁኑ ማሰብ ተገቢ*

*ይመስለኛል፡፡ የአንድ አገርን ሕዝብ ተስፋ አጨናግፎ በሰላም መኖር ያስቸግር ይሆናል፤....*

*ቅንጅት ለድል እንዳይበቃ የሚፈታተኑት ሁለት አዝማሚያዎች በውስጡ እንዳሉ ይታየኛል፤ አንዱ ሁላችንም በደንብ የምናውቀውና መፍትሔ ልናገኝለት ሞክረን ያቃተን የመኢአድና የኢዴአፓ/መድኅን የማይበርድ ባላንጣነት ነው፤ በሁለቱ መሀከል ያለው ፉክክር ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ቦታ ያለው አይመስልም፤ ትልቁና ዋናው ዓላማ አንዱ ሌላውን በማናቸውም መንገድ መብለጥ ነው፤ እንዲህ ያለ መንፈስ በነገሥበት በመተባበር፣ በመረዳዳትና በአንድነት ምርጫው ለቅንጅት የተመቻ እንዲሆን ለማድረግ አይቻልም፡፡ ......*

*ሁለተኛው ችግር የድርጅቶች ሳይሆን የግለሰቦች ነው፤ ግለሰቦቹ በድርጅታቸውም ውስጥ ሆነ በቅንጅቱ ውስጥ ቁልፍ ቦታና የተግባር ተሳትፎ ያላቸው ከሆኑ ተጽእኖአቸው ድርጅታቸውን አልፎ ቅንጅትንም ይነካል፤ አንዳንድ ግለሰቦች ይህንን የ97ን ምርጫ እንደዓላማ ሳይሆን ለሌላ ዓላማ (ለ2002 ምርጫ) መረማመጃ አድርገው ይመለከቱታል፤ ስለዚህም ለአንዱ የቅንጅት አባል ዓላማ የሆነው ለሌላው የቅንጅት አባል ስልት ነው፤ የዚህ ውጤት ውዥንብርና መደናበር፣ አለመግባባትም ይሆናል፤ ፓርቲዎች የብዙኃኑን ዓላማ ማራመጃ መሣሪያዎች መሆናቸው ቀርቶ የግለሰቡን ዓላማ ማራመጃ መሣሪያ እንዲሆኑ ማድረግ የፖሊቲካን ትርጉም ይለውጠዋል፤ወይም ሌኒኒስት ያደርገዋል፡፡ ለእኔ እንደሚመስለኝ ፖሊቲካ የጋራ ዓላማ ይዘው በጋራ ስልት የሚመሩ ሰዎች ተግባር ነው፤ ... (አንዱ) ዓላማ አድርጎ የሚፍጨረጨርበትን ስልት ብቻ አድርጎ የሚመለከተው ያቀልለዋል፤ በአስተሳሰብ ከቅንጅቱ ጋር አልተቀናጁም ማለት ነው፤ ኢትዮጵያ ተመልሳ በወያኔ/ኢሕአዴግ ቀንበር ስር ከወደቀች የእኛም ውድቀት መሆኑን ያልተገነዘቡና ለ2002 ምርጫ የሚዘጋጁ ሰዎች በመሀከላችን የአሉ ይመስለኛል፤ በየዋህነት ከአየነው የዋህነት ይመስለኛል፡፡*

*ትናንት ለየብቻችን ስንፎካከር ያደረብንን ቁጪትና ቂም ዛሬም በአንድ ላይ ሆነን ተሸክመነው መቀጠሉ አውቀንም ይሁን ሳናውቅ ነገ መርዙን በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ለማራገፍ ያቀድን ያስመስላል፤ ያስከብራል ብለን የገባንበት ተግባር ለአሳፋሪ ውርደት ሊዳርገን እየተፈታተነን ነው፤ ራሳችንን አሸንፈን ፈተናውን ሳናልፍ ወያኔ/ኢሕአዴግን ለማሸነፍ የምናደርገው ትግል ይሰምርልናል ማለት ከንቱ ምኞት ነው፡፡*

ዛሬም ቢሆን ብርቱካን ከታሰረች በኋላ በአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ ውስጥ ተመሳሳይ ብቻ ሳይሆን የባሰ የንትሥ፣ የራስ-የደጃዝማችነት ባሕርይ የሚያሳዩና በግል ፍላጎታቸው ብቻ ሎሌዎች እያሰባሰቡ



ለመንዳት የሚመኙ አሉ፤ ቶሎ የሚታረምበት መንገድ ካልተገኘ አንድነት የቅንጅትን መንገድ መከተሉ የማይቀር ነው፤ እንዲያውም ዛሬ በአንድነት ውስጥ ያለው ዓይን ያወጣ የአምባገነንነት ባሕርይና አሠራር በቅንጅት ውስጥ አልታየም፤ ለመሰብሰብ ፈቃድ ጠይቁን፤ በጋዜጣ ከእኛ በቀር መጻፍ ክልክል ነው፤ በራሳችን በአንድነት ጋዜጣም ውስጥ እኛን የሚነቅፍ ጽሑፍ አይታተምም፤ የሚሉ አብዮታዊ ዴሞክራሲን የሚያራምዱ ካድሬዎች ፓርቲውን አደጋ ላይ አድርሰውታል፤ የአባሎቹን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በድርጅታዊ አሠራር እየረገጡ አብዛኛዎቹን የሥራ አስፈጻሚውንና የምክር ቤት አባሎችን በቁጥጥራቸው ስር አድርገው በማናለብኝነት ዓላማቸው ምን እንደሆነ ባይታወቅም እያራመዱ ነው፤ በርከት ያሉ ለፓርቲው ዓላማ ታማኝ የሆኑ ቆራጥ አባሎች በግልጽ እየተጋፈጧቸው ነው፤ ፓርቲው ምን አቅጣጫ እንደሚይዝ ገና አልታወቀም፤ ዛሬ ጥቂት የአንድነት አምባገነን መሪዎች ትሮትስኪ የሚባለው የሩስያ የኮሚዩኒስት ምሑር ስለሶቬየት ኮሚዩኒስት ፓርቲ ያለውን በተግባር እያሳዩን ነው፤ እንዲህ ብሎ ነበር ሕዝቡ በፓርቲው አባሎች ይተካል፤ የፓርቲው አባሎች ደግሞ በፓርቲው ማእከላዊ ኮሚቴ ይተካሉ፤ ማእከላዊ ኮሚቴው ደግሞ በሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴ ይተካል፤ በመጨረሻም የሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴ በአምባገነን ይተካል፤ ዛሬ በአንድነት ፓርቲ ውስጥ እየሆነ ያለው ይኸው ነው፤ ጠቅላላ ጉባኤው የሦስት ዓመታት ሥልጣኑን ተነጥቆ አምባገነኑ በመለመላቸው የምክር ቤት አባላት ተተካ፤ አሁን ደግሞ ምክር ቤቱ በሥራ አስፈጻሚው ተተካ፤ ሥራ አስፈጻሚውን የሚያሽከረክረው አምባገነኑ ነው፡፡

የኃይልና የተንኮል ዘዴን በዴሞክራሲና በኢትዮጵያ ሕዝብ ስም ለማራመድ የሚፈልጉ ሰዎች ከጅብ ዋሻ ወደጅብ ዋሻ ሊያስገቡን ይመኛሉ፤ በአሠራራቸው ካለው ገዢ ኃይል የማይለዩ ሆነው ከቆዩ በኋላ አሁን ደግሞ በዶር. ነጋሦና በአቶ ስዬ አማካይነት የአንድነትን ፕሮግራም ለውጠው ወደገዢው ፓርቲ ፕሮግራም አስጠጉት፤ ስለዚህም የአንድነት መሠረታዊና መለያ የሆነው የፖሊቲካ አቅዋሙ አባሎቹ ሳይወያዩበትና ሳይመከሩበት ተለወጠ፤ ፖሊቲካ ማለት ኃይልንና ጡንቻን በውይይትና በክርክር ተክቶ በሰላም ለመተራረምና ለመረታታት ነበር፤ ተቀናቃኝ የፖሊቲካ ቡድኖች በጡንቻና በኃይል፣ በተንኮልና በማወናበድ ገዢውን ፓርቲ ሊያሸንፉት አይችሉም፤ የኢትዮጵያን ሕዝብም ሊያታልሉት አይችሉም፤ የተሳካላቸው የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል እንደሚባለው ራሳቸውን ማጋለጣቸው ብቻ ነው ፡፡

## 3. ባህልና ዴሞክራሲ

አንድ ግልጽ እየሆነ የመጣ ነገር ያለ ይመስለኛል፤ ዋናውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ዓላማ ወደጎን በማድረግ በምንም ዓይነት መንገድ ወደፓርላማ ለመግባት ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የሚጥሩ ሰዎች በኅብረት የተነሣሱ ይመስላል፤ የቅንጅትን ውሳኔ ጥሰው ፓርላማ የገቡት ሰዎች በ2002 እንደገና ተመርጠው ለመቀጠል የጋለ ምኞት ያላቸው ቢሆን አያስደንቅም፤ ሌሎችም የእነሱን አርአያ ተከትለው ወደዚያው መግባቱን ዋና ዓላማቸው ያደረጉ አይጠፉም፤ ከላይ ለቅንጅት አመራር በጻፍሁት ላይ ያነሣሁትን ጥያቄ አሁንም ማንሣት ግዴታ ይሆናል፤ የአንድነት ፓርቲ ዓላማ ጥቂት ሰዎችን ለፓርላማ ወንበር ለማብቃት ነው? ወይስ ከዚያ የላቀ ዓላማ አለው? ብርቱካን ከታሰረች በኋላ አመራሩን የያዙት ሰዎች ከቅንጅት ውድቀት ምንም እንዳልተማሩ እየታየ ነው፤ እንዲያውም ባህላዊውን የአገዛዝ ሥርዓት ለመዘርጋት የሚመኙ ይመስላሉ፡፡

ለእኛ ዴሞክራሲ ማለት የሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነት ነው፤ እኩልነትን፣ ነጻነትን፣ ሕጋዊ ሥርዓትን፣ ግልጽነትን፣ ተጠያቂነትን፣ ሕዝባዊነትን በውስጡ ያዘለ ሀሳብ ነው፤ በእርግጥ ባህላችን ለዚህ አላዘጋጀንም፤ በዴሞክራሲ አመራር ውስጥ መግባት ማለት አገልጋይ መሆን እንጂ ገዢ መሆን አይደለም፤ በእርግጥ ባህላችን ለዚህ አላዘጋጀንም፤ ለእኛ ዴሞክራሲ ማለት በሙሉ ነጻነትና በሙሉ ልብ መሰብሰብ፣ በእኩልነት መወያየትና መከራከር ነው፤ በእርግጥ ባህላችን ለዚህ አላዘጋጀንም፤ ባህላችን ያዘጋጀን የበላይና የበታች በመሆን አንዱ ሲኮፈስ ሌላው አደግዳጊ እንዲሆንና እንዲቅለሰለስ ነው፤ ለዚህ ነው የፈታውራሪነት፣ የራስነት፣ ምናልባትም የንጉሥነት ምኞት ልባቸውን ያሳበጠባቸው ሰዎች በየፖሊቲካ ፓርቲው ውስጥ እየገቡ አሮጌ ምኞታቸውን በአዲስ ልብስ ሸፍነው የኢትዮጵያን ሕዝብ ግራ የሚያጋቡት፡፡

ባህላችን ያዘጋጀን ከቻልን ጨቁኖ፣ ረግጦ፣ ደበድቦ፣ ገርፎ፣ አስሮ፣ ገድሎ ለመግዛት ነው፤ ባህላችን ያዘጋጀን የቻለ ገዢ ያልቻለ ተገዢ እንዲሆን ነው፤ ባህላችን ያዘጋጀን ለማድበስበስ፣ ለመሸፋፈንና ለመደባበቅ ነው፤ ባህላችን ያዘጋጀን ሥልጣንን በገንዘብ፣ ገንዘብን በሥልጣን ለመመንዘር ነው፤ ተከበረ ብሎ ከበረ ነው፤ ባህላችን ያዘጋጀን ለባላጋራነትና ለሴራ ነው፤ ባህላችን ያዘጋጀን ለጠብና ለጦርነት ነው፡፡

ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን እየተመኘን ሥልጣን ማለት ሠርቶ ማሠራት መሆኑ ቀርቶ አዛዥና ገዢ ለመሆን፣ ሥልጣን ማለት ተጠያቂነትና ኃላፊነት መሆኑ ቀርቶ እንደልብ ያለምንም ገደብ ያሰኛቸውን ለማድረግ፣ ሥልጣን ማለት በመመካከርና በመስማማት እቅድ እያወጡ አብሮ መራመድ መሆኑ ቀርቶ ልክ እንደዱሮው ታዛዦችና ሎሌዎችን በማበራከት ኃይልን ለማጠናከር መጣር፣ የሕዝብ ጉዳይ የሆነው ነገር ሁሉ ለሕዝብ እየተገለጠና ሕዝብም እያወቀ



ተሳታፊነቱን እንዲያዳብር መጣር ቀርቶ እንደደብተራ ምሥጢር ምንም ነገር እንዳይታወቅ እያፈኑ ግራ ማጋባት ገሀድ የወጣ ሐቅ እየሆነ ነው፤ ይህ ሁሉ የሚያመለክተው የባህላችን ተጽእኖ ምን ያህል ኃይለኛ እንደሆነና እኛም ሳናውቀውና ራሳችንን ለማፅዳት ሳንሞክር የዴሞክራሲ ጋቢ በመደረብ ብቻ የዴሞክራሲ አራማጆች መስለን ለመታየት እንደከማለን፤ የድምፅ ብልጫ ብቻውን ዴሞክራሲን ያሳያል ብለው የሚያምኑ የዋሆች በጉዳዩ ጠለቅ ብለው ያስቡበት፤ ይወያዩበት፤ ይከራከሩበት፡፡

ይህንን ሁሉ በውስጣችን ተሸክመን ነው ላይ ላዩን ስለዴሞክራሲ የምናወራው፤ ወይ ዴሞክራሲ ምን ማለት እንደሆነ አልገባንም፤ ወይም ባህላችን በውስጣችን የጫነውን አናውቅም፤ የሚያነታርከንና እንዳንደማመጥ የሚያደርገን፣ የሚያጣላንና የሚያራርቀን፣ እንዳንስማማና እንዳንተማመን፣ እንዳንደጋገፍና እንዳንተባበር የሚያደርገን በአንድ በኩል የገዢና የተገዢ ባህላችን በሌላ በኩል ዘመናዊው የዴሞክራሲ ምኞታችን እየተጋጩብን ነው፤ ይህንን ሐቅ ከገዢውም ሆነ ከተቀናቃኝ ቡድን ውስጥ የሚከድ ማን ነው? ማን ነው ከገዢው ቡድን በወሬ ዴሞክራት በተግባር ንጉሥ ያልሆነ ማን ነው? ከተቀናቃኝ ቡድኖች ውስጥ በቃል የዴሞክራሲ አቀንቃኝ በተግባር ግን ራሱን «ልዑል አልጋ ወራሽ» ብሎ ያልሰየመ? የዴሞክራሲ ባህል አለን የሚሉ ወገኖች እንዳሉ ይገባኛል፤ ስለዴሞክራሲ ያለን ግንዛቤ በጣም የተራራቀ ነው ከማለት በቀር አልጨምርበትም፡፡

በውስጣችን ተዋኅዶን ያለ በመሆኑ ስለባህላችን ተጽእኖ አናስብም፤ዴሞክራሲ በበኩሉ የውስጣችንን ብልጣብልጥነትና ሴራ እያየ አልጠጋችሁም፣ አትስማሙኝም የሚለን ይመስላል፤ በይሉኝታ ተሳስረን፣ እንደበታችንን በማር ልባችንን በሬት እየቀባን፣ በተንኮልና በክፋት ተመርዘን ዴሞክራሲ ሊመጣ አይችልም፤ ግልጽነትን በግዳችን መማር አለብን፤ በልበ ሙሉነት መከራከርን በግዳችን መልመድ አለብን፤ እኩልነትን፣ ነጻነትንና ሕጋዊ ሥርዓትን በግዳችን መቀበል አለብን፤ ለዴሞክራሲ ወይም ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነት ሌላ መንገድ የለም፤ አንድ ጊዜ በጋዜጣ እንደሶማልያ ወይም እንደዚምባብዌ እንዳንሆን ያሰጋል በማለቴ አንድ ወዳጄ በጣም ተቆጥቶ በጋዜጣ መልሶልኝ ነበር፤ ሶማልያ በእርግጥ የኢትዮጵያ ሀገረ መንግሥትነት ታሪክ የላትም፤ ነገር ግን በአብዛኛው አንድ ቋንቋና አንድ ሃይማኖት ያለው ሕዝብ ነው፤ ሆኖም የያዘውን የጥፋት መንገድ እያየን ነው፤ ዚመባብዌም አስታራቂዎች ያሉት ሕዝብ ነው፤ ለዚህ ነው እኛ ከአደጋችን ሳንወጣ ዚምባብዌ አደጋውን በመጠኑም ቢሆን የተሻገረው፤ እኛ ዛሬም እዚያው ነን! እዚያው ነን ስል ምን ትዝ አለኝ መሰላችሁ! ዘመድም የሚያስፈልገው አስሮ እንዲቀጣ ነው! በማስተማርና በማግባበት አይደለም፤ ሁሌም የሚቀናን የጡንቻ መንገድ ነው፡፡

*እዚያው ነሽ ወይ? ዛሬም እዚያው ነሽ ወይ?*
*እስሮ የሚቀጣ ዘመድም የለሽ ወይ!*

ዛሬም እዚያው ነን እያልን ሦስት ሺህ ዘመናት አስቆጥረናል፤ ለምን ያለማቋረጥ የኋሊት እንሮጣለን? ለምን ሁሉም ዓይነት ሕጎች ኖረውን፣ ባህላችንም ‹ብሕግ አምላክ ሲባል ውሀም ይቆማል› የሚል ሲሆን፣ ለምን ሕግ እንደሌለን እንሆናለን? ለምን ብዙ የሕግ አዋቂዎች እያሉን ምንም እንደሌለን እንሆናለን? ለምን ብዙ የሃይማኖት መሪዎች እያሉን ምንም እንደሌለን እንሆናለን? ለምን ከሃምሳ ዓመታት በፊት ከምሥራቅና ከምዕራብ አፍሪካ እየመጡ ሲማሩበት የነበረው ዩኒቨርሲቲ ዛሬ መሳለቂያ ሆነ? ለምን በ1960ዎቹ የተጀመረው ከፍተኛ የእርሻ እድገት በድንገት ቆሞ ወደጥንቱ ተመለሰ? ለምን በኢትዮጵያ ውስጥ ንብረትን ከማፍራት ይልቅ የኢትዮጵያን ሀብት ወደውጭ ማሸሽ አስፈላጊ ሆነ (ምናልባት ከአቶ እላሙዲን በቀር)? እንዴት ነገሩ ሁሉ ቢገለባበጥ ነው ከዓረብ አገሮች የፍራፍሬ ጭማቂና ብስኩት አስመጪዎች የሆንነው? ምን ዓይነት የአእምሮ ሕመም ቢይዘን ነው ሃምሳ ዓመታት ሙሉ ከችጋር መውጣት ያቃተን? በነዚህ ዓመታት ውስጥ የኢትዮጵያን ሕዝብ ገዛሁ ብሎ የሚኮራ ጤናማ አእምሮ ያለው ሰው አለ?

በቅርቡ ፕሬዚደንት ኦባማ ከአፍሪካ አገሮች ሁሉ ትንሽዋን ጋና፣ ኢ.አ.አ. በ1956 ነጻ የወጣችውን አገር መርጠው ጎበኙ፤ ሕዝቡ የሥልጣን ባለቤት በመሆኑ ብቻ ነው፤ ቀደምቲቱ ኢትዮጵያ፣የአፍሪካ የነጻነት ጮራ ስትባል የነበረችው ኢትዮጵያ በጣም ኋላ ነች፤ ለነገሩ ጋና እንኳን በፖሊቲካው በእግር ኳስም በልጣናለች! ያሳፍራል!

ከዚህ አሳፋሪ ደረጃ ላይ ለመድረስ ከሦስት ሺህ ዓመታት በላይ ፈጀብን! በአዲሱ ሺህ ዓመት (ሚሌኒየም) መባቻ ላይ ልዩ ዘመን እናደርገዋለን ተብሎ፣ አሳላፊዎቹ ከለንደን ተመርጠው መጥተው፣ አዳራሹ ተንጣልሎ ተሠርቶ፣ ተዘፍኖ፣ ተጨፍሮ መጨረሻ እንዘጭ! ብለን ወደነበርንበት! ማንን እታለልን? ጥፋት እንጂ ምን ጥቅም አገኘን? አሁንስ? ወደፊትስ የሚችለውን ለስደት፣ የማይችለውን ለደህነት እየዳረግን በዚያው በሚያዳልጥ የብልጣብልጥ የቁልቁለት መንገድ ለመንጎድና ልጆቻችንን የምናሳፍር እንደሆንን ልናልፍ ነው? የቀድሞዎቹን መውቀስ አንችልም፤ የእውቀት አድማስ መስፋትና የዓለም ሕዝቦች መቀራረብ የጥንቶቹ ሊያልሙት እንኳን የማይችሉትን ዕድል ሰጥቶናል፤ ኃላፊነታችን የበለጠ የሚሆነው በዚህ ምክንያት ነው።

አሁን እስካለንበት ዘመን (2002 ዓ.ም.) ድረስ ተከታታይ የኢትዮጵያ ትውልዶች ሥልጣንን ለመግራት አልቻሉም፤ እኛም ይህንን የታሪክ ውድቀት ተሸክመን ለሚቀጥለው ትውልድ ለማስረከብ እየታገልን ይመስላል፤ ጭቆናንና



መከራን እንዳናወርስ ቆርጠን መነሣት የሚጠበቅብን ይመስለኛል፤ ሥልጣንን እንግራው።

## 4. ሥልጣንን መግራት

ሥልጣንን ለመግራት እንድንችል በመጀመሪያ ራሳችንን መግራት አለብን፤ ስለሥልጣን በነፍሳችን ውስጥ ሳይቀር ሳናውቀው ቋጥረን የሸሸግነው የባህል ውራጅ አለ፤ ከመከበርና ከመክበር ጋር የተያያዘ የሥልጣን ምኞት፣ ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል የሚያቃጭልበት የንቅዘት ዝንባሌ፣ ከሰው በላይ ለመሆን፣ ያለምንም ተጠያቂነት ለመገላመጥ፣ ለመሳደብ፣ ለመግረፍ፣ ለማሰር፣ ለመግደል፣ እጅ ለማስነሳት፣ ያለምንም ተጠያቂነት ለመዝረፍና ለመቀማት፣ሕግንና ደንብን እንደፈለጉና እንደተመቻ እየለዋወጡ የግል መጫሪያ ለማድረግ፣[፰] — ይህንን ሁሉ የባህል ውራጅ ከውስጣችን ማራገፍ በግድ ያስፈልገናል፤ የሕግ አምላክን (ፈረንጆቹ the rule of law የሚሉትን ለሕግ ተገዢነት) ማጠናከር አለብን፤ አንድ አጥንታችንን ዘልቆ ነፍሳችን ውስጥ እንዲገባ ማድረግ ያለብን ቁም-ነገር ደንብና ሕግ የሚሠሩት ከጥፋት እንዲጠብቁን ነው እንጂ ለጥፋት እንዲያበረታቱን አለመሆኑን ነው፤ አሁን የምናደርገው ከባህላችን ጥሩውን እየነቀስን እያወጣን መጥፎውን እያጎላንና እያራባን ነው፤ ስለሥልጣን መጻፍ ከጀመርሁ ወደሃምሳ ዓመት ሊጠጋ ነው፤ ይህ ብቻ በጉዳዩ ላይ እንዳሰብሁበት የሚያመለክት ይመስለኛል፤ ያመለጥሁትም ስላሰብሁበት ይመስለኛል።

ስለሥልጣን ያለንን አስተሳሰብ ወደዘመናዊነት መለወጥ የሚያስፈልገን ይመስለኛል፤ ሃይማኖት የእውቀትም የእምነትም ምንጭ በነበረበት ዘመን የሥልጣን ምንጭ እግዚአብሔር ነው ይባል ነበር፤ ስለዚህም በጉልበተኛነት ሥልጣን ላይ የወጣውን ሁሉ በእግዚአብሔር ፈቃድ ነው እየተባለ ሕዝብን ለግፍ እያሳለፉ መስጠት ልማድ ነበር፤ በኦሪት ብቻ አይደለም፤ በሐዲስም ይህንን አስተሳሰብ የሚያራምዱ መመሪያዎች ሞልተዋል፤ እግዚአብሔር የግፈኞች አምላክ፣ የግፈኞች ደጋፊ አይደለም፤ እግዚአብሔር የፍትሕ፣ የነጻነትና የእኩልነት አምላክ ነው፤ ስለዚህም የሥልጣን ምንጭ ሕዝብ መሆን አለበት፤ እግዚአብሔር ለአዳምና ለሔዋን በገነት የሰጣቸውን በራሳቸው ፈቃድ የመወሰን ነጻነት ዛሬ እኛን ነፍጎናል ብለን አናምንም።

በወንበሩ ላይ ያለውን ሰው፣ ወይም ያሉትን ሰዎች መለወጥ ብቻ የሥልጣን ለውጥን አያመጣልንም፤ የሥልጣን ወንበሩ ባሕርይ አብሮ መለወጥ አለበት፤ የሥልጣን ወንበር በሰይፍ ብቻ ሳይሆን በሕጋዊ ሥርዓት የተወጠረ

---

፰ የእኔንና የሥልጣንን እየተያዩ ተኳርፎ መተላለፍ በሰፊው ከዚህ ምእራፍ መጨረሻ ላይ ገልጫለሁ።

እንዲሆን ያስፈልጋል፤ ለማንም እይታና ትችት ክፍት ሆኖ ከወንበሩ ውጭና ከወንበሩ በላይ የበለጠ ኃይል መኖሩን ማመንና መቀበል ያስፈልጋል፤ ሥልጣን በአንድ ሰው እጅ በተቋጠረ መጠን ሥልጣን ለሕዝብ የሚሰጠው ጥቅም ይቀንሳል፤ ሕዝብን በድንቁርና ማፈን በተቻለ መጠን የሥልጣን ብልግና ስር እየሰደደ ይሄዳል፤ በአጭር በአጭሩ ፍሬ ነገሮቹን ልደርድራቸው፤--

ሥልጣን የአገልግሎት እንጂ የጥቃት መሣሪያ አይደለም፤

ሥልጣን ርስት ወይም ርስተ-ጉልት አይደለም፤ የሚነቀልና የሚተከል፣ የሚለዋወጥ ነው፤

የሥልጣን ምንጭ ሕዝብ ነው፤ ሌላ ማደናገሪያ ሊገባበት አይችልም፤

የሥልጣን ዓላማ አገርንና ሕዝብን ማገልገል ነው፤

ሥልጣን የሚገኘው ሕዝብ በሙሉ ነጻነት፣ ያለምንም ፍርሃትና ጫና ከቀረቡለት አማራጮች ውስጥ የሚፈልገውን ሲመርጥና በድምፅ ብልጫ ሲያሸንፍ ብቻ ነው፤

የሥልጣን ባሕርይ ምንጊዜም ሕጋዊ መሆን ያስፈልገዋል፤ ሥልጣን ከሕግ ሲያልፍና ከሕግ በላይ ለመሆን ሲሞክር ያባልጋል፤ ለግፍና ለንቅዘት በርን ይከፍታል፤

ሥልጣን ወደፊት እያየ የሕዝብን ኑሮ ለማሻሻል የሚጥር እንጂ ወደኋላ እየተመለከተ በበቀልና በጥላቻ ጊዜንና ጉልበትን የሚጨርስ መሆን የለበትም፡፡

አንድ ነገር መረዳት ያለብን ኢትዮጵያውያን ለሥልጣን ያደረብን ምኞት ስር የሰደደ በመሆኑ ለእኩልነት የመጣውን ቁም ነገርም ወደሥልጣን መለኪያ እንለውጠዋለን፤ ለምሳሌ በደርግ ዘመን ጓድ የሚለው ቃል ከሶቭየት ኅብረት ተተርጉሞ የመጣልን ሁላችንንም ለማስተካከል ነበር፤ ነገር ግን አንዳንድ የቀበሌ ሎሌዎች ደብዳቤ ሲጽፉ ከፊርማቸው ስር «ጓድ» ይሉ ጀመር፤ ትንሽ ቆይቶም «ጓድነትዎ» ማለት ተጀምሮ ነበር፤ በዚህም ምክንያት ጓድ የሚለው ቃል ዓላማ ፈጽሞ ተበላሸ፡፡ አንድ ጊዜ ሬስቶራንት ውስጥ አሳላፊውን ለመጥራት ድምፄን ከፍ አድርጌ «ጓድ!» ብዬ ስጠራ የነበሩት ሎሌዎች በሙሉ ወደኔ ዞር አሉ፤ በኋላ አንዱ የማውቀው መጥቶ «አውቀህ እኛን ለማዋረድ ብለህ አይደለም አሳላፊውን «ጓድ» ያልከው?» በማለት ጥርጣሬዬን አረጋገጠልኝ፤ በሱ ቤት አሳላፊውን ጓድ በማለቴ ከፍ ሳደርገው ‹የክብር ወይም የሥልጣን ስማቸውን› ለሌላ በእሱ ግምት ለማይገባው ሰው በመስጠቴ ሎሌዎቹን ደግሞ አዋርጃለሁ ማለት ነው! ይህ የበሽታ መግለጫ አይደለም? ደማችን ውስጥ ያለ እንደሚመስል አፄ ምኒልክ ለራስ ቢትወደድ መንገሻ በጻፉት ደብዳቤ ይታያል፤ በከፊል የሚከተለውን ይላሉ፤--

*ይፍራታና ግድም እንደጮኸ እንደለፈለፈ ተለያየ፤ ቤግምድርም እንደጮኸ እንደለፈለፈ ተለያየ፤ ሳይንትም እንደዚሁ ተፈታ፤ ደግሞ አሁን ሜጫን፣ ይልማና (ዴንሳን) እንዲህ አድርገህ ታስጨንቀዋለህን፤ .... እንዲህ አድርገህ ደህውን ብታስጨንቀው ምን ትጠቀማለህ፤ ይህ ሁሉ የጨዋ ልጅ ሸማግሌ እንግዲህ ተመልሰን አገራችን እንገባም፤ የራስ መንገሻን ፊት አናይም፤ እንደወጣን እንቀራለን ብሎ እዚህ መጥቶ ያለቅሳል፤ ይህንን እግዚአብሔር ይወደዋልን፤ የመረረው ደሀ ይገባል ከውሀ የሚሉ ተረት ባንተ ደረሰ፤ ... ነገር ግን ደብዳቤ ብልክብህ፣ በመከርሁም አትሰማኝ፤ ተመከረህም አትድን፤ እንግዲህስ ሁለተኛ እንዲህ ያለ ነገር የሰማሁ እንደሆነ መንገሻ ሙት፤ ማርያምን፤ ደህው ከወደደበት እንዲኖር አዋጅ አነግርለታለሁ፤ ...*

ከዚህም በኋላ አፄ ምኒልክ ለጨቋኙና ለበዝባዡ ራስ በሌላ ጥፋት ሌላ ማስጠንቀቂያ ጽፈውላቸዋል፤ ነገር ግን የሥልጣኑ ባሕርይ ሳይለወጥ ራስ መንገሻንም ሆነ ሌላውን ለመለወጥ ያዳግታል፡፡

አሁን ሥልጣንን ወደመግራቱ ሀሳቤ ልመለስ-- አንደኛው ዋና ነገር ራሳችንን መግራት ነው ብያለሁ፤ ሁለተኛ ሥልጣንን የመግራቱ ዘዴ ወይም ስልት ሲቀየስ ያለፈውን የሥልጣን ብልግና የምንፍቅበትና ከአለፈው ወደአዲሱ የሚተላለፍ ምንም የቂምና የከፋት ነገር እንዳይኖር የኢትዮጵያ ሕዝብ በክብሩ ዋስትና የሚሰጥበት ፍጹም አዲስ ምዕራፍ እንዲሆን ያስፈልጋል፤ ጥላቻን አቅፈን ወደፍቅር ልንደርስ አንችልም፤ ጥፋትን እያሰብን ልማትን ማካሄድ አንችልም፤ ያለፉት ሠላሳ ዓመታት ይህንን ካላስተማሩን ከባድ ችግር አለብን ማለት ነው፡፡

እንደሚመስለኝ ሥልጣንን የመግራቱን አስፈላጊነት የሚቃወም የለም፤ ችግሩ ያለው እንዴት ሥልጣንን እንግራ በሚለው ዘዴ ላይ ነው፤ እንደሚመስለኝ በዚህም ላይ ቢሆን ችግሩ ያለው በዘዴው ላይ ሳይሆን ባለመተማመን ላይ ነው፤ ወይ እንደደቡብ አፍሪካ ታላላቅ ሰዎች የሌሉበት ማኅበረሰብ፣ወይም (በአፍሪካ ሌላ አገር መጥራት ስለሚያስቸግር) እንደደቡብ አፍሪካ ታላላቅ መንፈሳዊ መሪዎች የሌሉበት ማኅበረሰብ፥ ወይም እንደምዕራባውያን አገሮች ጋዜጠኞችና ምሁራን ነቅተው እየተጠባበቁ ሕዝቡን የሚያነቁበት ማኅበረሰባዊ መዋቅር በሌለበት የሥልጣን ተቀናቃኞችን ጥርጣሬና ስጋት ለማስወገድ ያስቸግራል፤ በአሁኑ ጊዜ ትልቅ ሰውነትን በተመለከተ ኢትዮጵያ ምድረ-በዳ ሆናለች ለማለት ይቻላል፤ ለዚህ ነው እኛም ሆንን ሌሎች የእኛ ቢጤ ሕዝቦች ትልቅ ሰው የሚባለውን ከአሜሪካ ወይም ከአውሮፓ መዋስ የሚያስፈልጋቸው፤ ይህንን የሚያደርጉ መሪዎች ውርደቱ በጭራሽ አይሰማቸውም፤ እንዲያውም የተከበሩና በአገራቸው ውስጥ ከነሱ በቀር ሌላ ሰው አለመኖሩን የሚያስመሰክርላቸው አድርገው ይመለከቱታል፡፡[10]

[10] አንድ ሰው ለመጥቀስ ያህል፣ የይድነቃቸው ተሰማን ትልቅነት ኢትዮጵያ ሳታውቅለት ዓረፈ፤ ይህ ሰው በብዙ ነገሮች ማንም በየዩኒቨርሲቲው ዲግሪ ከለቃቀሙ ሰዎች የበለጠ እውቀት ነበረው፤ በብዙ የአፍሪካ አገሮች ለአገር መሪዎች የሚሰጥ አቀባበል ያገኝ ነበር፤

## 5. የትልልቅ ሰዎች ያለህ!

ፍላጎቱ ካለን ግን ትልልቅ ሰዎችን ማፍራት እንችላለን፤ ከአሉን አንዳንድ ሰዎች ውስጥ የተደበቀ ትልቅነትን ማውጣት እንችላለን፤ እምነታችንን ልንጥልባቸው የምንችልባቸው ሰዎች ጥቂት አይደሉም፤ እኔ የማውቃቸው በማንኛውም የፖሊቲካ አመለካከት ውስጥ ያሉ ሊታመኑና ሊከበሩ የሚችሉ ሰዎች በኢትዮጵያም ውስጥ በውጭ አገሮችም አሉ፤ ልባችንን ለርኅራኄና አእምሮአችንን ለቀና አስተሳሰብ ከአዘጋጀን ትልልቅ ሰዎችን በማፍራት ኢትዮጵያን የትልልቅ ሰዎች አገር እናደርጋታለን፤ ትልልቅ ሰዎች የማይበቅሉበት አገር ትልቅ አገር ሊሆን አይችልም፤ ትልቅነት በመወለድ መሆኑ ቀርቷል፤ አሁን ደግሞ ትልቅነት በሥልጣን መሆኑን እናስቀረው፤ እነዚህ ትልልቅ ሰዎች ሌሎቻችንን እንድንደማመጥ፣ እንድንከባበርና እንድንተማመን በጣም ይረዱናል፤ ነገር ግን ትልቁና ዋናው ነገር እነዚህ ትልልቅ ሰዎች በአገሩ ውስጥ የተዘረጋውን የፖሊቲካ ጥላሸት መግፈፍ እንዲችሉ ከፖሊቲከኞቹ በተለይም ከገዢው ቡድን ለእነዚህ ትልልቅ ሰዎች የሚሰጠው ልባዊ ከብር ነው፤ ስለዚህም ትልቁ ጥያቄ ፖሊቲከኞቻችንና ገዢዎቻችን ከራሳቸው ከፍ አድርገው የሚመለከቷቸውን ሰዎች ለማየት ይፈልጋሉ ወይ? የሚል ይሆናል፤ ጥርጣሬ ስላለኝ ነው እንጂ ቢያንስ የአሥር ሰዎችን ስም መጥራት እችል ነበር፤ አንዳንዶቹም በአገዛዙ ውስጥ ያሉ ናቸው፡፡

የቅርቡ ታሪካችን ገዢዎቹንም ሆነ ተቃዋሚዎቹን ፖሊቲከኞች ሊያስተምራቸው ይገባል፤ አፄ ኃይለ ሥላሴ ሞተው እንደነገሩ ተቀብረዋል፤ ዛሬ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ሙጋቤን የሙጢኝ ብሎ ለሙጋቤ ዕድሜ እየለመነ ይኖራል፤ ነፍሱ አለ፤ ጀኔራል ተስፋዬ ገብረ ኪዳን በማያምር ሁኔታ ሞቷል፤ ጀኔራል ሐዲስ ኢጣልያን የሙጢኝ ብሎ ይኖራል፤ ነፍሱ አለ፤ ኮሎኔል ብርሃኑ ባየህም ኢጣልያን የሙጢኝ ብሎ ይኖራል፤ ነፍሱ አለ፤ በቃሊቲ ታጉረው አሥራ ሰምንተኛ ዓመታቸውን የቆጠሩት የደርግ አባሎች ይኖራሉ፤ ነፍሳቸው አለ፤ እነዚህ ሁሉ ሰዎች በሥልጣን ላይ በነበሩ ጊዜ በመጨረሻ የወደቁበትን ደረጃ በዓይነ አእምሮአቸው ማየት ያልቻሉበት ምክንያት ምንድን ነው? ልዩዎች ነን፤ ማንም አይችለንም፤ ቀዳዳዎቹን ሁሉ ደፍነን ራሳችንን እንጠብቃለን፤ ብለው እንዳመኑ ግልጽ ነው፤ ነገር ግን ይህ እምነታቸው ለብዙ ሰዎች ገሀድ ሆኖ የሚታየውን እውነት እንዳያዩ ዓይናቸውን ብቻ ሳይሆን አእምሮአቸውን ያወረባቸው ምንድን ነው? የሥልጣን ጥም የሚያመጣው

---

ኢትዮጵያ ሲመጣ ግን ተራ ሰው፤ በዲፕሎማሲ ችሎታው፣ በቋንቋዎች ችሎታው በአርቆ አስተዋይነቱ የሚደነቅ ሰው ነበር፤ አሁን ደግሞ ፍቅሩ ኪዳኔ አዳዲስ መረጃዎችን ስለይድነቃቸው ሰጥቶናል፤ የፒያሳ ልጅ በሚለው መጽሐፉ፤ 2002፡፡



ሕመም እንዳለ የታወቀ ነው፤ በተራ ደረጃ እንኳን ማሰብ የሚችል ሰው ከዚህ ሕመም የሚገላገልበትን መንገድ ፈልጎ ለማግኘት ይችላል፤ የሕመሙ አንዱና ዋናው መገለጫው ደህና ሰው፣ ሕመሙን ለመገንዘብ የሚችል ሰው አለማስጠጋቱ ነው፤ እንዲያውም ይህ ሕመም የያዘው ሰው በምንም ዓይነት መንገድ ትንሽም የሚበልጠውን ሰው አያስጠጋም፤ የሚያጅቡት ሁሉ በአእምሮአቸውም ሆነ በመንፈሳቸው ዝቅተኛ ግምት የሚሰጣቸው አድር-ባዮች፣ ትእዛዝ ተቀባዮችና አስተላላፊዎች፣ የመንፈስ ድንከዬዎች ናቸው፤ በዚህም ምክንያት ራሱን ለመመርመርና በሚያዛልቀው እውነት ለመመራት ዕድሉን አያገኝም፤ በዚህም የተነሣ በእውነት የሚያስከብሩትንና የሚያስወድዱትን ሰዎች እያራቀ፣ ጥላቻን በጥላቻ እያስወለደ ያራባል፡፡

በአለፉት አሥራ ሰምንት ዓመታትም ቢሆን ብዙ አይተናል፤ አንድ ሰሞን መድረኩ ሁሉ ለዳዊት ዮሐንስ ጠብቦት ሳያስብና ሳይጨነቅ እንደልቡ ይናገር ነበር፤ ዛሬ ድምፅ የለውም፤ ታምራት ላይኔ የፀዳ አዲስ ልብስ ለብሶ ከአንደበቱ የሚወጣው አድማጩን ያቆሽሽ ነበር፤ ዛሬ የክርስቶስን መንገድ ይዞ እያለቀሰ ነው፤ ብዙ መስዋእትነት የተከፈለበትን ታሪክ ለመለወጥ፣ ሌሎች የደከሙበት እንዳይታወቁ እያፈኑና እያጠፉ ቀለም በመቀባት ዘለቄታ ያለው ስም ማትረፍ እንደማይቻል የማያውቁ ሰዎች ሲናብዙ እያየን ነው፤ የተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት፣ የእቴጌ መነን ትምህርት ቤት፤ የእቴጌ ጣይቱ ሆቴል፣ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ትምህርት ቤትና ዩኒቨርሲቲ፣ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቲአትር ቤት፣ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሆስፒታል፣ የልዕልት ጸሐይ ሆስፒታል፣ የልዑል መኮንን ሆስፒታል (በደመወዛችን የተሠራ)... እንደኢትዮጵያ ዓየር መንገድ አርማ ያሉም ... ስምን ወይም ምልክትን በመለወጥ ታሪክን ለመለወጥና ባለቤት ለመሆን አይቻልም፤ ሬሳ መደብደብ ታሪክ አይሆንም፤ ቁም ነገሩ ጊዜውና ዘመኑ የሚጠይቀውን ታሪክ መሥራት ነው፤ ይህንን አለማድረግ ያለፉት ባለሥልጣኖች ሳይሆን የዛሬዎቹ ድክመት ነው፡፡

ከሥልጣን ጋር ተያይዞ የሚመጣ እንደኤሌክትሪክ ማሞቂያ አካልን የሚያግልና የሚያሳብጥ፣ ልብን የሚያደነድን ስሜት ይፈጠራል፤ አድር-ባዮች፣ አደግዳጊዎች፣ አሜቶሪዎችና አጨብጫቢዎች ራሳቸውን ለማስተዋወቅ የሚያደርጉት የሥልጣን አድናቂነት የሥልጣን ጥም ላደረበት ሰው ሕመሙን የሚያባብሰውና አእምሮውን ለተለየ አመለካከት የሚዘጋበት ይሆናል፤ በእንደዚህ ያሉ አድናቂዎች በየዕለቱ መከበብ ሥልጣንን ጣፋጭ ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ ነው፤ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚመጣው ስሜት በሰዎች ላይ የበላይነትን ማግኘትና በኑሮአቸው ላይ ብቻ ሳይሆን በሕይወታቸው ላይም ከሕግ ውጭ የመወሰን ችሎታ ነው፤ አንድ የሥልጣን ጥም ያደረበት ሰው እዚህ ደረጃ ላይ ሲደርስ ወደአምላክነት መንጠራራትና በስሩ ያሉትን ሰዎች ሁሉ

መናቅ ባሕርዩ ይሆናል፤ ንቀቱ በአየለ መጠን ሰዎች ለሱ ያላቸው ከፍርሃት ጋር የተቀላቀለ ጥላቻ ይጠነክራል።

አንድ ሌላ ከሕገ-ወጥ ሥልጣን ጋር የሚዛመድ ነገር በዘረፋና በንቅዘት ሀብት ማካበት ነው፤ ፍቅረ-ንዋይና ፍቅረ ሥልጣን ይመሳሰላሉ፤ ሁለቱም ልካቸውን አያውቁም፤ ሁለቱም በጨመሩ መጠን የበለጠ ምኞት ያድርባቸዋል፤ ሁለቱም የመጨረሻ ዓላማ የላቸውም፤ ሁለቱም ዕድሜያቸውን መገመት አይችሉም፤ ሁለቱም ነገ የዛሬ ቅጂ ይሆናል ብለው ይታለላሉ፤ ሁለቱም ደባል ፍቅርን አይፈልጉም፤ ለየብቻቸው አእምሮንና ልብን ሞልተው መንሰራፋትን የሚሹ ናቸው።

እነዚህን የጠቃቀስኳቸውንና ሌሎችንም የሥልጣን ሕመም መገለጫዎች ተገንዝበን ከውስጣችን ጠርገን ለማስወጣት ከቻልን ትልልቅ የምንላቸውን ሰዎች ለመቀበልና ለማከበር፣ እነሱ ባሉበት በወግና በሥርዓት ለመወያየትም ሆነ ለመከራከር የመንፈስ ወኔ ይኖረናል፤ ሥልጣንን ከጠመንጃ ጋር የሚያቆራኙት ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ መንፈሳዊ ወኔ የላቸውም፤ መንፈሳዊ ወኔያቸውን ጠመንጃው ይበላዋል፤ ስለዚህም መንፈሳዊ ወኔያቸውን ለማዳበር የበለጠ ጥረት ማድረግ ግድ ይሆንባቸዋል፤ ቀላል አይደለም፤ ግን ይቻላል።

ታዲያ ምን እናድርግ? በመጀመሪያ ሁለት የተያያዙ ሀሳቦችን እንገንዘብ፤ አንደኛ በረጅሙ ታሪካችን ሥልጣንን መግራት አቅቶናል፤ እንዲያውም ሥልጣንን የመግራት ችግር ልንፈታው ያልሞከርነውና የችግሮቻችን ሁሉ ምንጭ ሆኖ ታሪካችንን ሲያደፈርስ መቆየቱን መቀበል አለብን፤ ይህንን ጉልህ እውነት ከተቀበልን በአፍሪካ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በዓለም ውስጥ አዲስ ታሪክ ለመሥራትና አርአያ ለመሆን እንችላለን፤ የተገራ ሥልጣን ቦይ እንደተቆፈረለት ውሀ ነው፤ በዘፈቀደ አያጥለቀልቅም፤ በተቀደደለት ቦይ ውስጥ ብቻ ይፈስሳል።



# ፲፪
# መደምደሚያ

ኢትዮጵያ በጣም ረዢም ታሪክ ያላት አገር መሆንዋን ማንም ያውቃል፤ ዛሬ ኢትዮጵያ መናጢ ደሀ ከሚባሉት አገሮችም ውስጥ መጨረሻ ግድም እንደምትገኝ ማንም ያውቃል፤ የቀይ ባሕርን ባሻገር ጭምር ስትቆጣጠር የነበረች አገር ዛሬ ታፍና ትገኛለች፤ በምንም በምንም ከእኛ የማይለዩ ወንድሞቻችንና እኅቶቻችን ተለይተውን አዲስ መንገድ ይዘዋል፤ ይህንኑ መንገድ የሚመኙ ሌሎች መኖራቸውንም እናውቃለን፤ በአለፉት ሀያ ዓመታት ውስጥ የኢትዮጵያ ግዛት ተቀንሶአል፤ ሕዝቡም ተቀንሶአል፤ ፍቅሩም ተቀንሶአል፤ ተስፋውም ተቀንሶአል፤ ሌላውን ሁሉ ትተን በአፍሪካ ውስጥ ኢትዮጵያ ከዓርባ ዓመታት በፊት በእግር ኳስ የነበራት ደረጃ የት ነበረ? ዛሬስ የት ነው? ቁልቁል መሄድ እንደባህል የሆነብን ይመስላል፤ እንወጣለን ስንል ያንሸራትተናል፤ እንነሣለን ስንል እንወድቃለን፤ እንበለጽጋለን ስንል እንደኸያለን፤ አእምሮአችን ውስጥ አንድ የላላ ነገር አለ? ወይስ የዕለት እንጀራችንን ስጠነ ዛሬ ከተሳካልን የምንጨነቅበትና የሚቆረቁረን ነገር የለም? ከዓለም ዝቃጭ፣ ከአፍሪካም ዝቃጭ መሆን እንዴት አይቆረቁርም!

ደሀዎች መሆናችንን፣ ምፅዋት ካልደረሰልን በችጋር የምናልቅ ለማኞች መሆናችንን ዓለም ሁሉ ይነግረናል፤ ይጽፍልናል፤ እኛም በይፋ ያለምንም እፍረት እናውጃለን፤ ከወገኖቻቸው ባለሙያዎች ጋር ችግራችንን ለመወያየት የሚጠየፉ ሰዎች ለማንም ፈረንጅ አካላቸው ሁሉ ጆሮ ሆኖ ያዳምጣሉ፤ ፈረንጆቹ ራሳቸው እስቲደንቃቸው ድረስ! ፈረንጅ ደግሞ ይሉኝታ አያውቅ፣ ምሥጢር አያውቅ፣ እያፌዘ ይዘከዝከዋል! ባህላዊውን ኢትዮጵያዊ ክብርና ኵራት በሠላሳ ዓመታት ውስጥ ምን ከውስጣችን ሙልጭ አድርጎ አጠበብን?

ከአንድ ወጣት ጋር ስንጨዋወት አፄ ኃይለ ሥላሴ በመንገድ ሲያልፉ አንድ ሞተር ቢስክሌት ከፊታቸው ይሄዳል፤ መኪናችንን አቁመን እንወጣና እጅ እንነሳለን፤ አንዳንዴም ሳንወጣ ያልፉናል፤ ከዘውዲቱ ሆስፒታል ዳገቱን ወደኢዮቤልዩ ቤተ መንግሥት በእግራቸው ያለምንም ጠባቂ ሲሄዱ አይቻቸዋለሁ፤ አንድ ጊዜ ደግሞ በአቧሬ ኮረኮንች መንገድ ላይ በማልጠብቅበት ሁኔታ መኪናቸው ብቅ ብሎብኝ ወደኋላ ተመልሼ አሳልፌአቸዋለሁ፤ ይህንን ሁሉ ስነግረው ወጣቱ «የናንተ ትውልድ የታደለ ነው፤» አለኝ።

የዛሬው ወጣት መታደል ያለው የተገኘው በአፄው ዘመን በራስ መተማመንም፣ በሌሎች ላይም እምነት ማሳደርም በመቻሉ ነው፤ በአንጻሩ ዛሬ አለመታደላችንን ያመጣው በራስ መተማመን ሙጥጥ ብሎ መጥፋቱና እርስበርሳችንም አለመተማመናችን ነው፤ ፈረንጆቹን ከኢትዮጵያውያን ይበልጥ

ማመኑ የሚመነጨው በራስ መተማመን ከመጥፋቱና እርስበርስ ካለመተማመን የተነሣ ነው፤ ለምሳሌ ሪፖርተር እንደገለጸው በቅርቡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በአልጀዚራ ቴሌቪዥን በራስ* ዴቪድ ፍሮስት ፕሮግራም ላይ የሚከተለውን መናገሩን ጽፎአል --

*«መላእክቶች ብቻ ናቸው ስሕተት አንሠራም የሚሉት፤ ባለፉት ዓመታት ብዙ የተሠሩ ስሕተቶች ስለመኖራቸው እርግጠኛ ነኝ፤ የሠራኋቸው ስሕተቶች ቢኖሩም እነዚህ ስሕተቶች የተፈጸሙት በመልካም ፈቃድ እጦት ምክንያት ሳይሆን በችሎታ ማጣት ሊሆን ይችላል፡፡»*

ይህንን አነጋገር በትክክል የተቀበለና እውነተኛነቱን ያመነ ሰው ለጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰጠው የአእምሮ ብስለትና የመንፈስ ደረጃ ግምት ከፍተኛ ይሆናል፤ ራስ ዴቪድ ፍሮስት እንግሊዝ ስለሆነና እንደዚህ ያሉ ሰዎችን ማነጋገር ሥራው ስለሆነ በማናቸውም መለኪያ ከፍ ዝቅ አድርጎ ለመገመት ሳይሆን ለማጋለጥ ብቻ ነው፤ ስለዚህም እሱ የጮሌ መልስ ብቻ አድርጎ ይወስደዋል፤ አንድ ኢትዮጵያዊ ጋዜጠኛ (ቢኖር) ግን ጥያቄውን አቅርቦ ይህንን መልስ ቢያገኝ የራሱ፣ የአገሩና የወገኑ ጉዳይ በመሆኑ የዚህን መልስ እውነተኛነትም ማረጋገጥ ግዴታ ይሆንበታል፤ ስለዚህም በመልሱ ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎችን በማቅረብ የወደፊቱን አቅጣጫ ለመገመት ይችላል፤ የአቶ መለስ አነጋገር ጆርጅ ቡሽ መጨረሻው ላይ ከተናገረው የተለየ አይደለም፤ ልዩነቱ ጆርጅ ቡሽ አንድ አግሩ ከመድረኩ ከወረደ በኋላ የተናገረው መሆኑ ነው፤ አቶ ታምራት ላይኔም እንባው እየወረደ ስሕተቱን ተናግሮአል፤ አቶ ስዬ አብርሃምም ቢሆን በተደጋጋሚ ያለእንባ መንፈሳዊ ወኔውን ገልጾአል፤ ሁለቱም ሰዎች የአእምሮና የመንፈስ እመርታ አሳይተዋል፤ በዚህም የተነሣ በራሳቸው ለመተማመን ችለዋል፤ አቶ መለስ ግን ገና ነው፡፡

በዛሬ ጊዜ ችግሩ እውቀት አይደለም፤ ለመማር፣ ለማወቅ ለፈለገ ሰው እውቀት በሽበሽ ነው፤ በጠቅላይ ሚኒስቴር ወንበር ላይ የተቀመጠ ሰው የፈለገውን ዓይነት ኢትዮጵያዊ ባለሙያ ለማግኘት በፍጹም አያስቸግረውም፤ ሥልጣን ወደእውቀት አይለወጥም፤ ነገር ግን ሥልጣን እውቀትን አገልጋዩ ለማድረግ ይችላል፤ ብዙ ሰዎች የሚያውቁት አንድ ምሳሌ ላቅርብ፤ በደርግ ዘመን ኮሎኔል መንግሥቱ በደብረ ዘይት የሚገኘውን የእርሻ ምርምር ጣቢያ ይጎበኛል፤ በቴሌቪዥን ይታያል፤ በጣም ተናዶ ምንድን ነው ይሄ የሥራ ድግምግሞሽ! በዓለማያ፣ በሆለታ በጂማ ... ስንት የእርሻ ምርምር ጣቢያ ነው ያለው! ይሄ ጣቢያ አሁኑኑ ወደፎገራ እንዲዛወር! ሲል እኔ ብቻዬን ሳቅሁ፤

---

* ራስ ያልሁት የእንግሊዞን Sir የሚለውን ሹመት ነው፡፡



በኋላ ሳስበው ግን አሳዘነኝ፤ በሁለት ቀናት ውስጥ በደብረ ዘይት የእርሻ ምርምር ውስጥ የሚሠሩ ስለጣቢያው ብዙ ነገሮችን አስተማሩኝ፤ እኔ በበኩሌ ደግሞ ለጄኔራል እምቢበል (የኮሎኔል መንግሥቱ ጸሐፊ፣ ጀኔራሉ የኮሎኔሉ ጸሐፊ መሆኑ ግራ ቢሆንም) ስልክ ደወልሁለትና ትልቅ ስሕተት ሊሠራ ነው፤ የኢትዮጵያን የእርሻ ምርምር ሠላሳ ዓመት ወደኋላ ልትመልሱት ነው፤ የደብረ ዘይትን የዓየር ጠባይና አፈሩን ወደፎገራ ማዛወር አይቻልም፤ ነገር ግን በፎገራ አዲስ የእርሻ ጣቢያ ማቋቋም ይቻላል በማለት በዝርዝር አስረዳሁት፤ ከጥቂት ቀናት በኋላ ዱሪ መሀመድ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚደንት ደወለልኝና ጓድ ለገሠ አስፋው ቢሮ ትፈለጋለህ አለኝ፤ በዚያን ሰሞን ትልልቅ ካድሬዎችን ያበሳጨ ጽሑፍ በትኜ (ያኔ ማሳተም አይቻልም) ስለነበረ ስለሱ ጉዳይ መስሎኝ ተዘጋጅቼ ኮስተር ብዬ ጓድ ለገሠ ቢሮ ገባሁ፤ ለጄኔራል እምቢበል ስለነገርሁት ጉዳይ አነሣና ጠየቀኝ፤ እኔ ነገሩ ከንክኖኝ ነው እንጂ ባለሙያ አይደለሁም፤ ለምን ባለሙያዎቹን አትጠይቅም? ስለው «ጓድ ሊቀ መንበር ባለሙያዎችን ሳያማክሩ አንድም ውሳኔ አይወስኑም፤ እኛ ምን እናውቃለንና ነው፤ ጠቅላላ እውቀታችንም የተወሰነ ነው፤ ይሄ አጎብዳጅ ሁሉ ነው የሚያሳስተን፤...» ባለሙያዎቹን እንዳላማከራችሁ አውቃለሁ፤ አንተ ባለሙያ የምትላቸው በሥልጣን ላይ ያስቀመጣችኋቸውን ከሆነ አሁን አጎብዳጅ የምትላቸው፣ ቀድሞውኑ ስትመርጡ አጎብዳጁን ስለሆነ ነው፤ እውነተኛ ባለሙያ አጎብዳጅ አይሆንም፤ ብዬው ብዙ ተነጋገርን፤ በሦስተኛው ቀን ይመስለኛል ዱሪ ደውሎ በተዘዋዋሪ መንገድ ውሳኔው እንደተቀለበሰ ነገረኝ፤ ዛሬ እንደዚህም ማድረግ አይቻልም፤አንደኛ ማንንም ማነጋገር አይቻልም፤ ሁለተኛ ሁሉንም እንደባላንጣ አድርገው ስለሚመለከቱ ማናቸውንም ነገር በከፋት ይተረጉሙታል፡፡ ለምሳሌ የኢሰመጉ ዋናው ዓላማ ስሕተቶች በቶሎ እንዲታረሙና ሕጋዊ ሥርዓት እንዲረጋገጥ ለማድረግ ነበር፤ ግን ወደሌላ ትርጉም በመሄዱ ስሕተቶችን ለማረም አልረዳም፡፡

የሃይማኖት ባህላችን ስለንስሐ ያለው አቅዋም በጣም የከረረና ጠንካራ ነው፤ ኃጢአት የሠራ ሰው ንስሐ ገብቶ፣ የንስሐ አባቱ የሚሰጠውን ግዴታ ከአሟላ በኋላ ኃጢአቱ ይሰረይለታል፤ ሥጋ ወደሙንም ለመቀበል የበቃ ይሆናል፤ ነገር ግን ተመልሶ ወደኃጢአቱ የሚገባ ከሆነ ሥጋ ወደሙን የመቀበል ዕድሉ ያከትማል፤ በሌሎች ቤተ ክርስቲያኖች ግን አይቋረጥም፤ የተሳሳተው ሰው ንስሐ እየገባ፣ እየቆረበ፣ እየተሳሳተ፣ ንስሐ እየገባ፣ እየቆረበ ይኖራል፤ አብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን የሚቆርቡት ወይ በሕፃንነታቸው፣ ወይም በስተርጅና የሚሆነው በዚህ ምክንያት ነው፤ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መሳሳት የሚፈቀደው አንድ ጊዜ ብቻ ነው፤ ወጣ ገባ ማለት አይቻልም፡፡

እንደሚመስለኝ (ባለሙያዎቹ ካልተቆጡኝ) ይህ የሃይማኖት ባህል ስለጥፋትና ስለይቅርታ ሰብአዊና አምላካዊ መሠረት የተዛባ ግንዛቤ

አሳድሮብናል፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ስንት ጊዜ ይቅርታ ላድርግ ተብሎ ሲጠየቅ የሰጠው መልስ ወሰን የሌለው ነው፤ አንድ የግል አጋጣሚ ልናገር፤ አንድ ጊዜ አፄ ኃይለ ሥላሴ አስጠርተውኝ ሰውን ሁሉ አስወጡና ብቻችንን ቀረን፤

—ለምንድን ነው ሃይማኖትህን የለወጥከው;

ነገሩ ግራ ስለሆነብኝ ፈገግ ብዬ «የነገረዎት ሰው ተሳስቶአል፤ ሃይማኖቴን ለውጬ አላውቅም፤

--የለም ዱሮ ቤተ ክርስቲያን ታዘወትር ነበር፤ አይደለም?

«ዱሮ ቤተ ክርስቲያን አዘወትር ነበር፤ እጾም ነበር፤ እቆርብ ነበር፤ አሁን ይህንን ሁሉ አለማድረጌ ሃይማኖት መለወጥ አይደለም፤»

--ታዲያ ምንድን ነው?

«የክርስቶስ ትእዛዞች በጣም ከባዶች ናቸው፤ ለነገ አታስብ ይላል፤ እኔ ልጆች አሉኝ፤ ግራህን በጥፊ ሲመታህ ቀኝህን ስጥ ይላል፤ እኔ መልሼ መማታት ይቃጣኛል፤ እነዚህን ችግሮቼን ሳላስተካክል ክርስቲያን ነኝ ለማለት ኅሊናዬን ስለሚጨንቀው ነው እንጂ የክርስቶስን ትምህርት በጣም እወደዋለሁ፤ የእኔ ድካም ነው፤»

ፈገግ አሉና -- ከአራቱ ባሕርያት የተፈጠረ ሰው ይህንን ሁሉ ይፈጽማል ማለት አይደለም፤ የክርስቶስ ትእዛዞች (በፈረንሳይኛ) ከፍተኛ ግቦች ናቸው፤ ወደነሱ ለመድረስ እንድንጥር ነው፤

«የክርስቶስን ትእዛዝ የፈጸሙ ሰዎች አሉ፤ ለምሳሌ ሌዎ ቶልስቶይ፣ ክርስቲያንም ባይሆን ማሃትማ ጋንዲ፣ ስለዚህ አንድ ሰው ከፈለገና ከቆረጠ የክርስቶስን ትእዛዞች ለመፈጸም ይችላል ማለት ነው፤»

መጨረሻ ላይ የሚደንቅ ነገር ተናገሩ፤ «በል አሁን አንተም አላሸነፍህም፤ እኔም አላሸነፍሁም፤ በሌላ ቀን አንድ ዳኛ ይዘን ክርክራችንን መቀጠል አለብን፤» ስንነጋገር እኔ እያሉ ነበር እንጂ እንደተለመደው እኛ እያሉ አልነበረም። ዓላማው እስከዛሬ አልገባኝም፤ ነገር ግን በወሩ የጊሚራ አውራጃ ገዢ ተብዬ ተመደብሁ፤ ሌላ ምክንያት ባጣ ምናልባት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትዝብት የሌለበት ቦታ ተፈልጎልኝ ይሆናል ብዬ አሰብሁ!

ከልዑል ራስ ዕምሩ ጋር በሕንድ ስለእግዚአብሔር ቃል (መጽሐፍ ቅዱስ ነው? ቁራን ነው? ባህግባድ ጊታ ነው? ታልሙድ ነው? በሚል) ያደረግሁት ክርክር የተቋጠረው ልዑል ራስ «መስፍን በሎጂክ (በአስተሳሰብ) አንተ አሸንፈሃል፤ እኔ ግን እንዳለሁ ብቆይ ይሻለኛል፤» ብለው ነው።

እነዚህን ምሳሌዎች የጠቀስሁት ራሴን በእነዚህ ትልልቅ ሰዎች በማንጠልጠል ከፍ ለማለት አይደለም፤ በዕድሜም ሆነ በብዙ ሌሎች ነገሮች የማልደርስባቸው ናቸው፤ ከልዑል ራስ ጋር ስነጋገር ሃያ አራት ዓመት ግድም ቢሆነኝ ነው፤ ከአፄ ኃይለ ሥላሴም ጋር ስነጋገር ወደ ሠላሳ አምስት ዓመት



ቢሆነኝ ነው፤ ሆኖም ስከራከር ሀሳቤን በሙሉ ልብና በነጻነት እየገለጽሁ እኩያ መስዬ ነበር፤ ከልዑል ጋር ለብዙ ሰዓታት እንከራከርና የምሳ ሰዓት ሲደርስ አብሬ እንድሄድ ያዙኛል፤ እኔ ደግሞ ከሳቸው ጋር ቀርቤ መብላት ስለሚያቅተኝ ብማፀንም አይለቁኝም፤ የምፈራው ልኬን የሚያሳውቁኝን ልዕልት ጽጌ ማርያምን፣ የልዑልን ባለቤት ነበር፤ ለዓይናቸው ስለማልበቃ አያዩኝም፤ ግን በዓይናቸው ጨረፍታ ትቢያ ሲያደርጉኝ ይሰማኝ ነበር! ቢናገሩ «ምን ቁ--ር-ጥ አድርጎህ ከእኛ ጋር ገበታ ቀረብህ!» ይሉኝ ነበር!

እነዚህ ታላላቅ ሰዎች ከእኔ ጋር እንደእኩያ በመከራከራቸው ምን ጎደለባቸው? እኔን በአእምሮና በመንፈስ አበለጸጉኝ እንጂ እነሱ አልተዋረዱ፤ ልበ ሙሉና በራሳቸው የሚተማመኑ መሆናቸውን አሳወቁኝ፤ በሀሳብ ተግባብተን ነገር ግን ሳንስማማ መለያየታችን ለጥቃት አልዳረገኝም፤ እንዲያውም ልዑል ራስን እንዲያቀርቡኝ አደረጋቸው፤ አፄም ቢሆኑ «ደረቅ ነው» ከማለት አላለፉም።

ዛሬ በራስ መተማመን ለምን ጠፋ? እንደሚመስለኝ በራስ መተማመን የጠፋው መናናቅ ሲመጣ ነው፤ መጠላላት ሲመጣ ነው፤ መናናቅና መጠላላቱስ ከየት መጣ? አሁንም ለእኔ እንደሚመስለኝ ሕጋዊ ሥርዓት ባለመኖሩ ነው፤ ሕጋዊ ሥርዓት ቢኖር መጠላላቱንና መናናቁን በግልጽና ሥርዓት ባለው መልክ እየተወያየንበት ልናርመውና ልናጠፋው እንችል ነበር፤ እዚህ ላይ ሌላው ጋሬጣ ያጋጥመናል፤ መተማመን ያስፈልገናል፤ ባንስማማም እንተማመን ብለን መወሰን አለብን፤ ግን እንደመናገሩ ቀላል አይደለም።

በአገዛዙ ውስጥ ያሉት ሁሉ እንደማይተማመኑ በተደጋጋሚ አይተናል፤ በየጊዜው ከተለያዩ የመንግሥት ዘርፎች የሚኮበልሉት ሰዎች ቁጥር ትንሽ አይደለም፤ ሁኔታዎች በጣም ካልተለወጡ ኩብለላው እንደማያባራ እርግጠኛ መሆን ይቻላል፤ ሕጋዊ ሥርዓትና አስተማማኝ ሁኔታ ከሌለ ለራስ ሕይወት፣ ለቤተሰብ መስጋት የማይቀር ይሆናል፤ በዚያ ላይ የኅሊና ስቃይ አለ፤ በአገዛዙ ውስጥ ለሥልጣንና ለሀብት ያለው ፉክክር ንቅዘትን እያስፋፋ ሲሄድ ስጋትና አለመረጋጋት በዚያው መጠን ይጨምራል፤ ይህ በአገዛዙ ውስጥ ያለውና የሚፈጠረው አለመተማመን ነው።

በአገዛዙና በተቀናቃኝ ቡድኖች መሀከል ያለውና የሚፈጠረው አለመተማመን ደግሞ ሌላ ነው፤ እዚህም ያለመተማመኑ ዋና ምክንያት ግልጽነትና የተደላደለ ሕጋዊ ሥርዓት አለመኖር ነው፤ በጉልበትና በጦርነት መንግሥት ሊገለብጡ ነው የሚባለው የተደጋገመ ውንጀላ ቅዠት የወለደው ነው፤ በአለንበት ዘመን በደም መፋሰስ ሥልጣን ይገኛል ብሎ ማሰብ ቂልነት ነው፤ ይህንን ለመረዳት ከአሥር ደቂቃ የበለጠ ማሰብም አያስፈልግም፤ አገዛዝና ተቀናቃኝ ቡድኖች የኢትዮጲያን ሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነት በሙሉ ልባቸው ከተቀበሉ መተማመን ይመጣል።

በእውነት የተለያዩ ቋንቋዎችና የተለያዩ ሃይማኖቶች በኢትዮጵያ ውስጥ መኖራቸው የማይፈቱ ችግሮችን ፈጥረውብናል? እውነትንና በቅንነትን ተመርኩዞን ከተወያየን ለዚች ጉራማይሌ ውበት ላላት አገራችን ዘላቂ መፍትሔ መግኘት አያቅተንም፤ ዘላቂ መፍትሔ ማለት ዘለዓለማዊ መፍትሔ ሳይሆን በአንድ ዘመን ያሉትን ትውልዶች ወደተሻለ የመግባባት ደረጃና ወደተሻለ ሕጋዊ ሥርዓት የሚያረማምድ ነው፤ አንድ ጊዜ የሚያግባባንንና የሚያስተማምነንን ትክክለኛ ፈር ከቀደድን ኢትዮጵያን የምንኮራባት አገር ልናደርግ እንችላለን።

(እዚህ ላይ አንድ ሰሞኑን ከአንድ የአሜሪካ ቴሌቪዥን ጣቢያ የሰማሁትን ቴክኖሎጂቲ (የእውቀት ጥበብ) የፈጠረውን አዲስ እውቀት ልናገር፤ እስከዛሬ ማሰብ ማንም ሊደርስበት የማይችል የግል ተግባር ነበር፤ ዛሬ ተደፍሮአል፤ ሳይንቲስቶቹ የሰውን አንጎል በማጥናት ሰው የሚያስበውን ለማወቅ የሚችሉበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል፤ ለጊዜው በሰፊት ሥራ ላይ ባይውልም በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ውስጥ የሀሳብ የግልነት የገሰሳል፤ ስለዚህም መኪናውን ካገኘን ማን ምን እንደሚያስብ እያወቅን መነጋገር እንችላለን፤ አለዚያም እንጠናለን።)

ፖሊቲከኞቹ ሁሉ አንደኛ ራሳቸውን ገርተው ሥልጣንን የመግራት አስፈላጊነት፣ ሁለተኛ ውስጣቸውን ከባህላዊ የሥልጣን ውራጅ የማፅዳት አስፈላጊነት፣ ሦስተኛ ትልልቅ ሰዎችን የማብቀል አስፈላጊነት እንዲቀበሉ ግልጽና ነጻ ውይይት ለማድረግ የምንችለው እንዴት ነው? ሁለት ከባድ እንቅፋቶች ከገዢው ቡድን በኩል ይታዩኛል፤ በጎ ፈቃድ ማጣትና የመጋለጥ ፍርሃት፤ የመጋለጡን ፍርሃት በውይይቱ አዘገጃጀት ለማስቀረት እንደሚቻል እርግጠኛ ነኝ፤ በጎ ፈቃዱን ለማግኘት ግን መንገዱም ያለ አይመስለኝም፤ የበጎ ፈቃዱንና የመተማመኑን መንፈስ ለመፍጠርና ለማጠናከር አስተዋጽኦ ለማድረግ የሚችሉ በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ትልልቅ ሰዎች የሉንም፤ ፖሊቲከኞቹ አእምሮአቸውንና ኅሊናቸውን በማዳባሪያ ኮትኩተው ትልልቅ ሰዎችን ለማፍራት የሚችሉ ቢሆኑልን ችግሩ ይቃለላል።

ተቀራርቦ መወያየቱ የማይቻል ከሆነ የሥልጣኑን መሠረት መለወጥ ግድ ይሆናል፤ ችግራችንን ፍርጥርጥ አድርገን ካወጣነው ጎሣ ወይም ቋንቋ ከሥልጣን ጋር እየተቆራኘ ስለመጣ ለዚህ ዘለቄታ ያለው መፍትሔ መፈለግ ግዴታችን ይሆናል፤ ሁለት አማራጮች ይታዩኛል፤ አንዱ አማራጭ ወደሶማልያ አስከፊ ሁኔታ ውስጥ ከመግባታችን በፊት ለአውሮፓ ወይም ለአሜሪካ ወይም ለተባበሩት መንግሥታት አገሪቱን በኮንትራት ሰጥተን እነሱ እንደፈለጉ ያስተዳድሩን! ይህንን አማራጭ የሚፈልግ ኢትዮጵያዊ ያለ አይመስለኝም።

ሁለተኛው አማራጭ ከዚህ በፊት በ1986 አቅርቤው የነበረ ሀሳብ ነው፤ ሥልጣንን ከአንድ ሰው እጅ ማውጣት ያስፈልጋል፤ አንድ ሰው ሁልጊዜ



አማራ፣ ኦሮሞ፣ ትግሬ፣ ጉራጌ፣ ሱማሌ ... ነው፤ ቢደበላለቅም የሚታወቀው በአንዱ ነው፤ በዚህም ምክንያት የጎሠኛነት ሐሜትን ያስነሣል፤ ሁለተኛም ለአምባ ገነንነት በርን ይከፍታል፤ ስለዚህ የአገሩን አመራር በአንድ ሰው ቁጥጥር ብቻ መሆኑ እንዲያበቃ ያስፈልጋል፤ በምትኩ ከተለያዩ ጎሣዎች ወይም ቋንቋ ተናጋሪዎች የሚወከሉ ሰዎች አንድ ኮሚቴ አቋቁመው በአንድነት የአገር መሪዎች ይሆናሉ፤ በ1986 **ኢትዮጵያ ከየት ወዴት**? በሚል ርእስ በጻፍሁት ውስጥ የሚከተለውን ብዬ ነበር፦

*በኢትዮጵያ ... የመጨረሻውን ሥልጣን ለአንድ ሰው ከመስጠት ይልቅ ለአምስት ወይም ለሰባት ከተለያዩ (ቋንቋ ተናጋሪዎች) ለተወከሉ ሰዎች አስረክቦ እነዚህ በልዩ ምርጫና በተራ መሪ እንዲሆኑ ቢደረግ የሕዝብን የሥልጣን ባለቤትነት ይበልጥ ያረጋግጥልናል፤ ከሁሉም ይበልጥ ደግሞ የትኛው ጎሣ ገዢ ነው የትኛው ተገዢ የሚባለውንም ንትርክ ፈጽሞ ያጠፋልናል።*

አሁን ግን በተሻለና ጠንካራ መሠረት ላይ ለማቆም በመፈለግ ትንሽ አሻሽዬዋለሁ፤ ጉራጌን እንደጥንቱ አንድ አድርገን ከወሰድነው በኢትዮጵያ ውስጥ በሙሉ ከአንድ ሚልዮን በላይ ቁጥር ያላቸው የተለያዩ ቋንቋዎች ተናጋሪዎች አሥር ግድም ናቸው፤ በስታቲስቲክስ ጽሕፈት ቤት ውሳኔ «ዋና» የሚባሉት ጎሣዎች ከነሕዝብ ቁጥራቸው በሚቀጥለው ሠንጠረጅ ተዘርዝረዋል። እነዚህ አሥር ጎሣዎች ከጠቅላላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር ከሰማንያ ሰባት በመቶ በላይ የሚሆነውን ያካትታሉ፤ የሚቀሩት ከአሥራ ሦስት ከመቶ በታች ናቸው፤ እነዚህን ከሥልጣን ውጭ አድርጎ መተው ተገቢ አይመስለኝም፤ ስለዚህ ባይሆን ከ500000 በላይ የሕዝብ ቁጥር ያላቸው እንዲገቡ ቢደረግ ጠቅላላ የጎሣዎች ቁጥር ወደአሥራ አምስት ከፍ ይላል፤ የሚጨመሩት አገው፣ ከፊቾ፣ ከምባታ፣ ስልጤ ናቸው፤ ከቀሩት ትናንሽ ጎሣዎች ደግሞ ለአንድ የምርጫ ዘመን ከመሀከላቸው አንድ በተራ ቢገባ የኢትዮጵያን ሕዝብ በሙሉ የሚወክል መንግሥት ማቋቋም ይቻላል።

እንግዲህ በአገር አመራር ደረጃ እነዚህ የአሥራ አምስት ቋንቋዎች ተናጋሪዎች በእኩልነት ደረጃ የአገር መሪዎች ይሆናሉ፤ ሁሉም የሚመረጡት በቀጥታ በየጎሣቸው ሕዝብ ነው፤ በየዓመቱ በተራ ሥርዓት ባለው መንገድ እየተለዋወጡ የአንዱ ቋንቋ ተናጋሪ ፕሬዚደንት ይሆናል፤ ከአንድ ዓመት በላይ ፕሬዚደንት ወይም የጠቅላይ አመራሩ ሊቀ መንበር መሆን እንዳይቻል ማገጃ ሕግ ካልወጣ አንዱ ተደላድሎ ለመልቀቅ አልፈልግም እያለ ችግር እንዳይፈጥር መጠንቀቅ ያሻል፤ የአሥራ አምስቱ መሪዎች የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ሆኖ ከሁለት የምርጫ ዘመኖች በላይ እንዳይራዘም መደረግም ሳያስፈልግ አይቀርም።

**አሥር «ዋና» የተባሉ የኢትዮጵያ ጎሣዎች**

| ተራ ቁ | ጎሣ (ቋንቋ) | የ 2007 እእእ የሕዝብ ቁ | ከመቶ (ሀ%) | % av (ሀ/8.74) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ኦሮሞ | 25,488,344 | 34.5 | 3.95 |
| 2 | አማራ | 19,867,817 | 26.9 | 3.08 |
| 3 | ሶማሌ | 4,581,793 | 6.2 | 0.71 |
| 4 | ትግሬ | 4,483,776 | 6.1 | 0.70 |
| 5 | ሲዳማ | 2,966,377 | 4.0 | 0.46 |
| 6 | ጉራጌ | 1,867,350 | 2.5 | 0.29 |
| 7 | ወላይታ | 1,707,074 | 2.3 | 0.26 |
| 8 | ሀድያ | 1,284,366 | 1.7 | 0.19 |
| 9 | አፋር | 1,276,372 | 1.7 | 0.19 |
| 10 | ጋሞ | 1,107,163 | 1.5 | 0.17 |
| ድምር አማካይ | | 63,630,432 | 8.74 | 9.81 |

ከስታቲስቲክስ ጽ/ቤት የተገኘ መረጃ

ይህ የአሥራ አምስት ሰዎች ጉባኤ ርእሰ ብሔርም ርእሰ መንግሥትም ይሆናል፤ ትልቁ ችግር (ለእኛ ሁሉም ችግር ነውና) እነዚህ አሥራ አምስት ሰዎች በየዓመቱ አዲስ ፕሬዚደንት ለመምረጥ ሁሉም እኩል ድምፅ ይኖራቸዋል? ወይስ ድምፃቸው በሚወክሉት ሕዝብ መጠን ይሆናል? የሚለው ነው፤ ነገሩ ሳይንሳዊ የሆነ ቀላል መፍትሔ ሊገኝለት ይችላል፤ ለምሳሌ በሰንጠረዥ በመጨረሻው ረድፍ ላይ የሚታየውን ስሌት ከተከተልን ኦሮሚኛ ተናጋሪው አራት ድምፅ፣ አማርኛ ተናጋሪው ሦስት ድምፅ፣ ሶማልኛና ትግርኛ እያንዳንዳቸው አንዳንድ ድምፅ ይኖራቸዋል፤ ምናልባትም ሲዳምኛ ተናጋሪውም አንድ ድምፅ ሊኖረው ይችል ይሆናል፤ የቀሩት ግን በመጨረሻው ረድፍ ላይ ከ0.5 በታች ያገኙት ሁሉ አምስቱ አንድ ላይ አንድ ድምፅ ብቻ ይኖራቸዋል፤ በድምር አሥራ አንድ ድምፅ ይሆናል፤ አራቱ ትንንሽ ጎሣዎች ምን ያህል ድምፅ ማግኘት እንደሚገባቸው መወሰን ያስፈልጋል፤ ሌላው ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ነገር በምንም ዓይነት መንገድ ምርጫው ቢካሄድ ሁልጊዜም ሚዛኑን የሚደፉት ትልልቆቹ ጎሣዎች ከሆኑ ትንንሾቹ ሥልጣናቸው ይደፈጠጣል፤ ስለዚህም ከትንንሾቹ ሰባት ያህሉ የተቃወሙት ጉዳይ እንደማይጸድቅ የሚደረግበት መንገድ ማበጀት ያሻ ይሆናል፤ አለዚያ የሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነት ፍትሕና እኩልነት



የጎደለው የድምፅ ብዛት ብቻ ይሆናል; በበኩሌ ይህ ስሌት በጣም ግርድፍ እንደሆነ ይሰማኛል፤ እንደፕሮፌሰር አየነው እጅጉ ያለ የስታቲስቲክስ ሊቅ በጣም የተለየና የማያወላዳ ዘዴ ለማምጣት እንደሚችል አውቃለሁ።

እንግዲህ ጉባኤው የአገርና የሥራ አስፈጻሚው ቁንጮ ሲሆን የሕግ አውጪውና የሕግ ተርጓሚው ሁለተኛውና ሦስተኛው የመንግሥት አካሎች ይሆናሉ ማለት ነው።

ይህ ዘዴ በትክክል ከተሠራበት ለጎሣዎች በሙሉ በመጨረሻውና በከፍተኛው የሥልጣን ደረጃ እኩል ሥልጣንን ይሰጣል፤ ማናቸውንም ዓይነት የመንግሥት ተግባር አብረው በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ይመራሉ፤ ከመሀከላቸው አንድ ሰው ብቻውን ምንም ማድረግ ስለማይችል የሥልጣን ብልግናም ሆነ በሥልጣን መመዝበር ሊጠፉ ባይችልም በጣም ይቀንሳል፤ እንደምንገነዘበው የሥልጣን ጥም ያለው ፖሊቲከኛ ሁሉ የሚታየው አንድ እሱ የሚይዘው ወንበር ብቻ ነው፤ መጋራት ቀርቶ መተባበርም ዳገት ነው፤ ስለዚህም ይህንን ሀሳብ ብዙ ዓይነት እቃቂር እያወጡለት እንደሚያጣጥሉት መገመት ይቻላል፤ አሠራሩ በስዊትዘርላንድ ለብዙ ጊዜ ያለምንም እንከን ሲሠራበት የቆየ ነው።

ከዚህ በፊት አንድ የሰማሁት እቃቂር የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዚህ ዓይነት ውስብስብ አመራር አልተዘጋጀም፤ ገና አልደረሰም የሚል ነው፤ እውነቱ ግን ያልተዘጋጁት ፖሊቲከኞቹ ናቸው እንጂ የኢትዮጵያ ሕዝብስ በቀላሉ ይገባዋል፤ ይለምደዋልም፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነጻነት፣ እኩልነት፣ ሕጋዊ ሥርዓትና የሥልጣን ባለቤትነት ይገባዋል፤ ይገነዘበዋል፤ ፈትኑት!

ገዢው ፓርቲ መንፈሳዊ ወኔ ቢኖረው ይህንን ሀሳብ በሙሉ ነጻነት የፖሊቲካ ቡድኖችና ሌሎችም እንዲወያዩበት በማድረግ ሌላ የታሪክን ምዕራፍ በመክፈት ከዚህ በፊት ያመለጠውን ክብር ለማግኘት ዕድሉን ይፈጥር ነበር። እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሲል ልቡና ከቅን መንፈስና ከወኔ ጋር ይስጣቸው።

# ክፍል ሁለት



## መግቢያ

በዚህ በሁለተኛው ክፍል የተካተቱት ጽሑፎች በአለፉት ሃያ ዓመታት ውስጥ በተለያዩ መጽሔቶች የታተሙ ናቸው፤ ጽሑፎቹ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እንዲካተቱ የተፈለገው በሦስት ማከንያቶች ነው፤ አንዱ ምክንያት በወያኔ አገዛዝ በተደጋጋሚ የተከሰስሁበትና በኋላም ከብዙ ጓደኞቼ ጋር ዕድሜ ልክ እስራት የተፈረደብንና ወዲያው በምሕረት የተለቀቅነው ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ እንደነበረና በማናቸውም መልኩ ትናንትም ዛሬም የጡንቻን ዓመፅ መደገፍ ቀርቶ ሕጋዊ በሚባለው ግድያም እንደማላምን ለማስመስከር ነው፤ ሁለተኛው ምክንያት ከሳሾቼ፣ የከሳሾቼ ጠበቃዎችና ዳኞቹ ሁላችንም በአንድ ከተማ ውስጥ እየኖርን ከጠቅላላ እውቀት የማያልፍ መረጃ እንኳን ለማግኘት የማይችሉበት ሁኔታ ውስጥ በመሆናቸው ምን ያህል በብዙ በኩል የተጎዱ መሆናቸውን ለማስመስከር፣ሦስተኛው ምክንያት የከሳሾቼ፣ የጠበቃዎቻቸውና የዳኞቹ ልጆች የሁላችንም አገር በሆነችው በኢትዮጵያ ውስጥ ከእኛ ልጆችና የልጅ ልጆች ጋር የሚኖሩ ናቸውና እውነቱን እንዲያውቁት ማስረጃ ለመስጠት ነው።

ምንም ጊዜ በምንም ዓይነት ምክንያት ቢሆን አስቦና ተዘጋጅቶ ሰው ሰውን እንዲጎዳ በሚያምን ድርጅት ውስጥ ገብቼ አላውቅም፤ ሰዎች በንዴትና በደም ፍላት ይጎዳዳሉ፤ ይህ የእንስሳ ባሕርያችን ነው፤ አንዳንድ ሰዎችም ከእንስሳ ደረጃ እጅግም ያልወጡ መሆናቸውን እናያለን፤ እንሰማለንም፤ በአንጻሩ ብዙ ሰዎች ደግሞ አእምሮአቸውንና ኅሊናቸውን በማኅበራዊ ኑሮ የኃላፊነት ስሜት የእንስሳ ባሕርያቸውን ሞርደው የሰውነት ባሕርያቸውን የሚያዳብሩ ሞልተዋል፤ እኔ ከልጅነቴ ከወጣሁ ጀምሬ ከነዚህ ውስጥ ነኝ ብዬ አምናለሁ፤ የአንድ ሰውን ሕይወት ለማጥፋት ምንም ምክንያት የለም፤ እንኳን በግፍና በሕጋዊ የሞት ቅጣት አላምንም፤ አንድ ሰው በሌላ ሰው ሕይወት ላይ የሚጨክነው ወይ በፍርሃት፣ ወይ በአእምሮ ሕመም (ተደብቆ የኖረ ወይ ግልፍተኝነት) ነው፣ በተለያዩ ታሪካዊና ልብ-ወለድ ፊልሞች ውስጥ እንደምናየው በአጃቢዎች ተከልሎ አንበሳ ለመምሰል የሚጥረው ሰው አጥሩ ሲፈራርስና አጃቢዎች ሲበተኑ መንቀጥቀጥና መርበትበቱ የተደበቀውን ፍርሃት ያወጣና ያጋልጠዋል፤ አቅመ-ቢስንና ደካማውን በግፍ የሚያሰቃዩና የሚገድሉ በመሠረቱ ፈሪዎች ናቸው።

በወያኔ/ኢሕአዴግ ዘመን ሦስት ጊዜ በኃይል ዓመፅ መንግሥትን ለመገልበጥ በሚል ተከሰሻለሁ፤ አንዱ ክስ ተሰረዘ፤ አንዴ አንድ ወር ታስሬ በዋስ ወጣሁና ስድስት ዓመታት ያህል ተሟገትሁና ነጻ ወጣሁ፤ ሁለቱ የመጀመሪያ ክሶች ከዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ጋር የተያያዙ ነበሩ፤ ሁለተኛው ክስ ላይ ለዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ስለሰብአዊ መብቶች ስናገር በሕገ መንግሥቱ የተፈቀደላችሁን መብት ለማስከበር «አትፍሩ» ማለቴ አንዱና ዋናው ክስ ነበር፤

አትፍሩ ማለት ወንጀል የሚባልበት ዘመን! በሁለተኛው ክስ ዕድሜ-ልክ ተፈረደብኝ! ቅንጅት ቅንጣት ያህል የጉልበት አዝማሚያ የሚያሳይ ፓርቲ ቢሆን አጠገቡም አልደርስ ነበር፤ እዚህ ላይ ከአለቃ አያሌው የሰማሁትን አንድ ታሪክ አስታወሰኝ፤ ሰውዬው ዓይነ-ስውር ነው፤ ሌሊት ከሚስቱ ጋር ተኝቶ ኡኡታ ይሰማል፤ ብድግ ይልን ሚስቱን «ነይ ተነሽ! ውሰጂኝ!» ይላታል፤ ሚስቱም «እርስዎ አሁን ቢሄዱስ ምን ሊያደርጉ ነው?» እያለች ለማስቀረት ብትሞክርም አልሆነም፤ ተነሥታ እየመራቻው ወደበሩ ሲቃረቡ ዓይነ-ሰውሩ ከኡኡታው ጋር «የጎበዝ ያለህ!» ሲባል ይሰማና «በይ አሁን ወደመኝታዬ መልሽኝ!» አላት! በቅንጅት ውስጥ ማንም «የጎበዝ ያለህ!» ሲል ብሰማ እኔም አልኖር ነበር፣ ማንም ስለኃይል እርምጃ ሲናገር ሰምቼ አላውቅም፤ የከሳሽ ጠበቃ ለፍርድ ቤት ያቀረባቸው የቪድዮ ማስረጃዎች ሁሉ ይህንኑ ይመሰክራሉ፤ የወጣቶችን ሕይወት ለአደጋ ማጋለጥን በጣም እጠላለሁ፤ ራሳቸው በፈቃዳቸው ሲያደርጉትም ተቃውሜአለሁ፤ አሁንም እቃወማለሁ፤ ሆኖም ዛሬ በወያኔ/ኢሕአዴግ ጠበቃ ተከስሼ፣ በወያኔ/ኢሕአዴግ ዳኞች የተፈረደብኝና በሽማግሌዎች አማካይነት ይቅርታ የተሰጠኝ ወንጀለኛ ነኝ፤ ይህንን እውነት ለከሳሽ፣ ለከሳሽ ጠበቆችና ለዳኞቹ ለራሳቸው ሳይሆን ለልጆቻቸውና ለልጅ ልጆቻቸው ከማቆየት ሌላ ዓላማ የለኝም።

የሚቀጥለው የመጀመሪያ መጽሐፍ በአደባባይ የቀረበው በኅዳር 1996 ነው፤ ኢኮኖሚስቶች ቁጥር ካላዩ ሀሳብን በተለይም ራእይን መጨበጥ ይቸገራሉ፤ ስለዚህም ጽሑፉን ካቀረብሁ በኋላ አስተያየት የሰጡት ኢኮኖሚስቶች ግራ እንደመጋባት ብለው ነበር፤ እነሱ እንደለመዱት አሐዝ እያስደገፍሁ ባለመናገሬ ከምን ተነሥተው አስተያየት እንደሚሰጡ ቸገራቸው፤ አንዳንዶቹም በግልጽ ተናግራዋል፤ የኢትዮጵያን ሁኔታ በየእለቱ ለሚከታተልና የኢትዮጵያውያንን የልብ ትርታ ሥራዬ ብሎ ለሚያዳምጥ የሚመጣውን ሁኔታ ለመተንበይ ጠንቋይ መሆን፣ ወይም ነቢይ መሆን፣ ወይም አሐዝ መሰብሰብ በግዴታ አስፈላጊ አይደለም፤ በግዴታ የሚያስፈልገው ፍቅርና እምነት ነው፤ እንደነፍስ ለሚወድዋት አገርና ለሚወዱት ወገን ጥልቅ ፍቅር ካለ ልማቱም ሆነ ጥፋቱ፣ ነፍስን ዘልቆ በሚገባ ፍንደቃ ወይም ጭንቀት ይሰማል፤ እንደሕጻን ፍንድቅድቅ ያለ ሳቅ፣ ወይም እንደሕጻን ምርር ያለ ለቅሶ፤ አዘቅቱ የከፋና የኢትዮጵያ ሕዝብ በታሪኩ አይቶት የማያውቀው ደህነትና ችጋር ጭካኔን እየወለደ፣ በጎሠኛነት ሞተር እየተነዳ በጥላቻና በቂም እየታወረ ከፋት በገሃድ የሚወጣበት መተላለቅ ነው።

በዚህ መተላለቅ ከአካባቢያችን የሚረዱን አይጠፉም፤ በአለፉት ዓመታት ከሶማልያና ከኤርትራ ጋር የተደረገው መዳማት፤ ከጅቡቲ ጋር የተደረገው አለመግባባት፤ በአንድ በኩል ከአሜሪካ ጋር፣ በሌላ በኩል ከሱዳን ጋር የተደረገው ሽር ጉድ የሚከተሉትን ዓመታት ለኢትዮጵያ የሚመቹ



አያደርጓቸውም፤ እኔ እንደምገምተው ሁሉም የተነበየው አዘቅት ወይም አፋፍ ላይ በ1997 መጨረሻ እንደርሳለን፤ አዲስ ኢትዮጵያ የምትወለደው ከኤርትራ እስከቦረና ከጋምቤላ እስከጂጂጋ ሁሉም በአንድ ጊዜና በአንድ ላይ በሚሰማው የጭንቀት ምጥ ይሆናል፤ ሕገ አራዊት የሚያደርሰን እዚህ ነው፤ የሰው ልጅ አእምሮ ውስብስቡን የኑሮ ገመድ ሲገምድና ሲፈታ እኛ ገና ከቀላሉ የማስፈራራትና የጡንቻ ዘዴ አልወጣንም፤ በማስፈራራትና በጭቆና የጨቆኝም የተጨቆኝም አእምሮ ደንዝዞ፤ መንፈስም ታምሞ በደነዘዘ አእምሮና በታመመ መንፈስ ትርጉም ያለው ሥራ ለራሳችንም ሆነ ለማኅበረሰባችን ለማበርከት አንችልም።

አንብቡትና አብረን እንጨነቅ፤ አብረን ስንጨነቅ መፍትሔውን አምጠን እንወልደዋለን።

ትውልድ በአንድ ጊዜ አያልፍም፤ የሚያልፈው እያስተላለፈ ነው፤ የሚቀጥለው ትውልድ ታሪካቸውንና ታሪኬን አውቆ ይፍረድብኝ።

# አንድ
# ራእይ
# ኢትዮጵያ በ2020 -- ከየት ወዴት

መስፍን ወልደ ማርያም
ለኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ማኅበር
ሒልተን ሆቴል ኅዳር 1996

## 1. መግቢያ

ያለንበትን ዓለም አጠቃላይ ሁኔታ መገንዘብ የሚያስፈልግ ይመስለኛል፤ መስከረም አንድ ቀን 1993 በአሜሪካ ላይ የደረሰው አስከፊና አረመኔያዊ ጥቃት፤ አሜሪካ ለዚያ መልስ በአፍጋኒስታን፣ ቀጥሎም በኢራቅ ላይ የወሰደቻቸው ተመሳሳይ ወታደራዊ እርምጃ፣ በሰሜን ኮርያ፤ በሶርያና በፋርስ ላይ የምታሰማው ዛቻ፣ የእስልምና አክራሪዎች በሚባሉት በኩልም በኬንያ በኢንዶኔዥያ፤ በኢራቅና በአፍጋኒስታን የሚደረገው ሁሉ በቋፍ ያለውን የዓለም ሰላም እያደፈረሰው ነው፤ ምናአልባትም ለዚህ ሁሉ ጦሱ የፍልስጤማውያንና የእስራኤላዊያን መጨረሻው የማይታይ ክፋትና ጭካኔ የተሞላበት ግብግብ ሳይሆን አይቀርም፤ በአንድ በኩል በማይመጣጠን ሃይል የሚጠቀም ጭቆና ፍልስጤማዊነትን ወደ አረብነት ከዚያም ወደ እስላምነት ሲለውጥ በሌላ መልኩ ደግሞ እስራኤላዊነትን ወደ ምዕራባዊነት ወይም ወደ አሜሪካንነት እየለወጠ ነው፤ ስለዚህም የግብግቡ ኢላማ የሰፋና የተለየ ሲሆን የግብግቡም መሣርያ በጣም የተለያየ ሆኖአል፤ በፍልስጥኤማውያኑና በደጋፊዎቻቸው በኩል ኢላማው የአሜሪካን ወገን የሆነ ሁሉ፤ የአሜሪካ ንብረት የሆነ ሁሉ፤ ለአሜሪካ ጥቅም የዋለ ነገር ሁሉ ነው፤ በአሜሪካና በእስራኤል በኩል ኢላማው ሽብርተኛ የሚሉት ነው፤ ለቀሪው የዓለም ሕዝብ በሁለቱም ወገን የሚሰጠው ምርጫ የኔ ወገን ካልሆንህ የጠላት ወገን ነህ የሚል ነው፤የውጊያውም ዓይነት ከዚህ በፊት በዓለም ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ ነው፤ የጦር ሜዳውም ያልተወሰነና ዓለምን በሙሉ የሚያጠቃልል ነው፤ የጦር መሣርያውም ዘመኑ ያስገኘው ደፍጥጦ የሚያነድ ነው፤ የተቃዋሚዎቹ የጥቃት መሣርያ የሰው ልጅ ሕይወት ነው፤ ከሁለቱም ወገን በየሳምንቱ ብዙ የሰው ሕይወት እየጠፋና ብዙ ንብረትም እየወደመ ነው፤ በሁለቱም ወገን በግልጽ አይሎና አመዝኖ የሚታየው ርኩስ መንፈስ እንጂ ቅን ወይም ቅዱስ መንፈስ አይደለም።

በአለፈው የፈረንጆች ምዕተ-ዓመት ተከብረው የቆዩ ቁም ነገሮች እየተሻሩ ናቸው፤ የአንድ አገር ሉዓላዊነት በኃያላኑ ፈቃድ ብቻ የሚገኝ



ሆኖአል፤ዩጎዝላቪያ፤ አፍጋኒስታን፤ ኢራቅ የደረሰባቸውን እናውቃለን፤ በሰሜን ኮሪያና በኢራን፤ እንዲሁም በሶርያ ላይ የሚሰነዘረው ዛቻና ያንዣበበውም ስጋት ይህንኑ የሚያመለክት ነው። የመረጣችሁትን መሪ ለውጡ የሚል ትእዛዝ ለአንድ ሕዝብ ማስተላለፍ በአሜሪካ ተጀምሮ አሁን አልቃይዳ የራሱን ትእዛዝ እያስተላለፈ ነው፤ በአጠቃላይ ሲታይ በብዛት ሰዎችን መግደልና ንብረትንና የልማት መዋቅሮችን ማውደም የጉልበተኞች ብቻ ሳይሆን የደካሞችም ዘዴና ሙብት እየሆነ ነው፤ የመስፈስ ልዕልና እንኳን በዓለማዊው ክፍልና መንፈሳዊ በሚባለውም ክፍል ክፉኛ ዘቅጦአል። አካላችንን ብቻ ሳይሆን ነፍሳችንንም ለገንዘብ የምንሸጥበት ጊዜ ነው፤ የሰው ልጅ ኩራትና ክብር ዋጋ አጥተዋል።ዓለማችን ለእኔ ይህንን ይመስላል፤ መናጢ ደሀዎችና ደካሞች ሆነን ያለነው እዚህ ዓለም ውስጥ ነው።

ያለንበት የዓለም ሁኔታ በአጠቃላይ ለጭቆና አገዛዝ የማይመች የሚመስል ዝንባሌ ቢኖረውም ኃያላኑ የጭቆና አገዛዞችን በአሽከርነት ለማሳደርም ዝንባሌ እንዳላቸው ይታያል፤ የምእራባውያን ዋናው የሽብርተኞች ችግር ከጭቆና አገዛዝ ጋር ያላቸው መቆራኘት መሆኑን ገና የተገነዘቡት አይመስልም፤ የጭቆና አገዛዝ እስካለና ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል እስኪታፈን ድረስ አመፅና ሽብርተኝነት ይኖራል፤ ዓመፅና የሽብርተኝነት ኢላማም ከጭቆና አገዛዙ በስተጀርባ ያለውን ድጋፍም እንደጠላት እየቆጠረ ማጥቃቱም የማይቀር ይሆናል፤ አሜሪካ የሽብርተኞች ኢላማ የሚሆንበት ሌላ ምክንያት አለ ብዬ አላምንም፤ የአሜሪካ ታሪካዊ ተልእኮዎች ነጻነት፤የሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነት ወይም ዴሞክራሲ ትክክለኛ ፍትሕና የንብረት ማፍራት መብቶች ለሰው ልጆች ሁሉ የሚበጁ ቢሆንም የአሜሪካ መንግሥት የማያወላውል አቋም የሆነው የውጭ ግንኙነት መመርያ አላደረጋቸውም፤ እንዲያውም የአሜሪካ መንግሥት በተለያዩ ምክንያቶች የጨቋኞች ወዳጅና ደጋፊ እየሆነ ይገኛል፤ ችግሩ ይህ ይመስለኛል።

በምዕራባውያን ሕዝቦችና በሌሎቻችን መሀከል ያለው ልዩነት እየገዘፈና እየጠለቀ በመሄድ ላይ ነው፤ ሌሎቻችን በአራት ሺህ ዓመት ያልደረስንበትን እነሱ በአራት መቶ አልፈውት መሬት እየጠበባቸው ወደ ሕዋው እየመጠቁ ነው፤ እኛ አህያ እየነዳን በቀን ሰባት ኪሎ ሜትር ስንገሰግስ እነሱ በሰዓት ብዙ ሺህ ኪሎ ሜትሮች በመንፈላሰስ እየተጉዋዙ ነው፤ እኛ ጉልሁንና ግዙፉን ነገር ማይት ሲሳነን እነሱ በዓይን የማይታየውን ሁሉ እያዩና እየመረመሩ ነው፤ እኛ እነሱ የሠሩትን መሣርያ እየገዛን ስንከሰክስና ሞትንም ስናነግሥ እነሱ የሕይወትን ሙሉ ጣዕም እየተደሰቱበት ነው፤ እኛ በጠባቡ በአገራችን ውስጥ አብሮ መኖር ሲያቅተን እነሱ ሰፊውን ዓለም በግድም በውድም አገራቸው እያደረጉ ነው፤ እኛም ያጠፋነውን አገራችንን እየጣልን ወደነሱ አገሮች መሰደዱን ባህላችን አድርገን ይዘነዋል፤ ገና ላልተሰደድነውም

ቢሆን ከአገዛዝ ሥርዓት ጀምሮ እስከ ግብረ ሠናይ ድርጅቶችና ማኅበሮች የምንንቀሳቀሰው በነሱ ችሮታ ነው፤ ከነሱ ችሮታ ውጪ ያለን ህልውና ዋስትና የለውም፡፡

እንግዲህ ጥያቄው ምን አለን? ብቻ አይደለም ምንድን ነንም ነው፡፡

## 2. የዓለምና የአካባቢው ሁኔታ በኛ ላይ ያለው ተጽእኖ

የኢትዮጵያዊነትን ህልውና የሚፈታተነው የውስጥ አመራር ብቻ ሳይሆን የውጪም ነው፤ ታሪክ ጠባሳን ይተዋል፤ የተለያዩ የአውሮፓ የቅኝ ግዛት ኃይሎችን በተለያየ ጊዜ የኢትዮጵያ አልበገርነት አሳፍሮዋቸዋል፤ አሜሪካም ቢሆን ይህንኑ አልበገርነት አይቶታል፤ እንዲሁም ቱርክ ግብፅና አረቦች በተለያየ መንገድ የኢትዮጵያዊነትን አለመበገር የተረዱበት ሁኔታዎች አጋጥሞዋቸዋል፤ ጎረቤቶቻችን ከሆኑት ጋር ግን የሚያያይዘን የደምም የባህልም ማንተም በሁለታችንም ላይ እንደቀረ አይጠረጠርም፤ አንዱና ዋናው ማንተም እስልምና ነው፤ እስልምና እንደሃይማኖት አረብ የሆነውን ያህል ኢትዮጵያዊም ነው፤ ከክርስትናና ከእስልምና በፊት ኢትዮጵያዊነት ከአይሁድነት ወይም ቤተእሥራኤልነት ጋር ግንኙነት ነበረው፤ በእኔ አስተያየት አይሁድነትም፤ ክርስትናም፤ እስልምናም በተለያየ ጊዜ ኢትዮጵያዊነትን ለመተካት ሞክረዋል፤ አንዳቸውም አልሆነላቸውም፤ ኢትዮጵያዊነትን በመተካት ፋንታ ሁሉም ኢትዮጵያዊነትን ተጎናጽፈው ኢትዮጵያዊ ሆኑ፤ ኢየሩሳሌም ለሦስቱም ሃይማኖቶች ቅድስት መካን የመሆንዋን ያህል ኢትዮጵያዊነትም ከዚያች ታሪክ ተካፋይ ነው፡፡

ሦስቱም ሃይማኖቶች ከኢትዮጵያ ውጪ ምእመናን አልዋቸው፡ ስለዚህም ሃይማኖቶቹ በኢትዮጵያና በሌሎች ሀገሮች መሀከል እንደድልድይ ሆነው በማገልገላቸው ሰዎች ሀሳቦችና ባህሎች ተዛምደዋል፤ ዛሬ ግን አይሁድነት ኢትዮጵያዊነትን አውልቆ እሥራኤላዊነትን ለብሶዋል፤ ይህ ሁኔታ ከሌላው የስደት ጎርፍ ጋር ተዳምሮ ኢትዮጵያዊነትን የማራቆቱ ጉዞ መጀመርያ እንደሆነ አድርገን ልናየው የምንችል ይመስለኛል፤ ከዚያም በላይ የቤተ እሥራኤል እሥራኤላዊነት በእስልምና ኢትዮጵያዊነት ላይ ምንም ተጽእኖ ሊያስከትል እንደሚችል አናውቅም፤ ክርስትናም በጎሠኝነት እየተተራመሰ የኢትዮጵያዊነት የክብር ልብሱ እየተቀደደበት ነው፤ እስካሁን ድረስ ጎሠኝነትን ተጋፍጦ በቆራጥነት የተቋቋመው እስልምና ብቻ ነው፤ በአሁኑ ጊዜ ከእስልምና ወይም እንደሚባለው የእስልምና አክራሪዎች ጋር ምዕራባውያን በያዙት ግብግብ ውስጥ የኢትዮጵያን እስልምና ለማስገባት የሚፈልጉ አይጠፉም፤ ስለዚህም በውጭ ተጽእኖ ተገፋፍቶ የኢትዮጵያ እስልምና ኢትዮጵያዊነትን ያዳክማል፤ አገሪቱንም ለአደጋ ያጋልጣል የሚል ስጋት ይሰማል፤ አገዛዙ



ከሱማልያው አል ኢትሀድ ጋር የሚያደርገው ግብግብ በዚህ በማሳበብ ነው፤ እንዲህ ያለው የግጭት ምክንያት የኢትዮጵያን እስልምና ኢትዮጵያዊነት እንዳይመርዘው መጠንቀቅ የሚያስፈልግ ይመስለኛል፤ የክርስትና ኢትዮጵያዊነት በውስጥ አመራር ምክንያት እየተዳከመ ባለበት ጊዜ የእስልምና ኢትዮጵያዊነት ደግሞ በውጭ አመራር ምክንያት ቢዳከም በኢትዮጵያዊነት ላይ የሚደርሰው ጉዳት እንደሚባባስ በበኩሌ አልጠራጠርም፤ በገንዘብ እየተደለሉ ለምዕራባውያን ሎሌነት ማደር ለአገዛዙ የአጭር ጊዜ ጥቅም የሚያገለግል ቢሆንም ለኢትዮጵያ የረጂም ጊዜ ጉዳትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

## 3. ከየት ተነሥተን ያለንበት ደረስን?

የአፄ ኃይለ ሥላሴ አገዛዝ ለእኛ በጊዜው ወጣቶች ለነበርነው በአጉል ባህል የተተበተበ ኢ-ፍትሐዊ የመሬት ስሪት የሰፈነበት ኋላ-ቀርና አዝጋሚ ነበር፤ ከሞተ ሠላሳ ዓመታት የሆነውን ሥርዓት ከዚህ በላይ አልወቅሰውም፤ ሆኖም ከጊዜው ጋር መሄድ ስላቃተውና የ1953 የክብር ዘበኛ ዓመፅ ምንም ሊያነቃውና ሊያስተምረው ባለመቻሉ መጥፎ አወዳደቅ አጋጠመው፤ ደርግ ከነትንሽነቱና ከነጭካኔው የዘውዱ አገዛዝ እልህ ውጤት ነው፡፡

በእኛ ዘመን የዘውድ አገዛዝ ለኢትዮጵያ አጠቃላይ እድገት ያበረከተው አስተዋጽኦ በጣም ትልቅና ከዚያ ወዲህ ከመጡት ጋር አገዛዞች ጋር ሊወዳደር የማይችል ነው፤ በተለይ በሦስት ዓላማዎች ላይ በአጭሩ የዘውዱ አገዛዝ ያበረከተውን አስተዋጽኦ ላመልከት፤

- በመጀመርያ በአንድነት ላይ በተለይ ኤርትራን ወደ እናት አገርዋ ለመመለስ የተደረገውን ተጋድሎ አምባሳደር ዘውዴ ረታ ምስጋና ይድረሰውና በቅርብ ለማወቅ ችለናል፤ የዛሬውም የኤርትራ ችግር በዚያን ጊዜ የተፈጠረ መሆኑን ተገንዝበናል፤

- ሁለተኛ የመሬት ስሪቱን ትተን በእርሻ በኩል የተጀመረው እድገት ቢቀጥል ዛሬ ኢትዮጵያ ራሰዋን ከመቻል አልፋ የተለያየ የእርሻ ምርቶችን ለዓለም ገበያ ማቅረብ የምትችልበት ደረጃ ላይ ትደርስ ነበር የሚል እምነት አለኝ፤

- ሦስተኛ የዘውድ አገዛዙ በትምህርት በኩል ኢትዮጵያ ራሰዋን ወደምትችልበት ደረጃ አድርሶአት እንደነበረ ሁላችንም የምናውቀው ነው፡፡ የትምህርቱን ጉዳይ ትንሽ ዘርዘር አድርጌ ልገልጸው እፈልጋለሁ፤አፄ ኃይለ ሥላሴ ራሳቸው ከየሄዱበት ልጆች በመኪና እያስጫኑ በየትምህርት ቤቱ

በአዳሪነት ያስገቡ ነበር፤ ይህ ዕድል ባይኖር ብዙዎቻችን የዘመናዊ ትምህርት በርም አንደርስም ነበር፤ እንደማስታውሰው በተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት በአዳሪነት ከገቡት ውስጥ ለምሳሌ ከኦጋዴን ሶማሌዎች፤ ከሐረር አደሬዎች፤ ከጎጃም፤ ከጎንደር፤ ከሲዳሞ፤ ከአርሲ፤ ከኤርትራ፤ ከወለጋና ከአዲስ አበባም ዙርያ የመጡ ነበሩ፤ ፍትሐ ነገሥት «በፍትሕሰ ኢይትኳነን ወልድ በጌጋየ አቡሁ ወአብ በአበሳ ወልዱ» ልጅ በአባቱ ወንጀል ወይም አባት በልጁ ወንጀል አይከሰስም ያለውን በመከተል የታወቀው ከሀዲ የኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ልጅና የአርበኛው ዓመፀኛ የበላይ ዘለቀ ልጆች በአዳሪነት ይማሩ ነበር፤ የተፈሪ መኮንን ተማሪዎች ባመፅንበት ጊዜ «ከየትም ለቃቅመን አምጥተን» በማለት ንዴታቸውን የገለጹት ለዚህ ነበር፤ የተናገሩት እውነት ቢሆንም እኛን ማስከፋቱ አልቀረም፤ ለዚህም ነው ማቴዎስ ጥግነህ የሚባል ተማሪ «ጃንሆይ! አባቶቻችን ታከስ ይከፍላሉኮ!» ያላቸው::

ይህ ባህላዊ አገዛዝ ከውስጥም ከውጭም ተቆጣጣሪ ኃይሎች ነበሩበት፤ ከውስጥ ኅሊና ከውጭ እግዚአብሔርና ይሉኝታ ነበሩበት፤ ሽማግሌዎችም ነበሩ፤ በተጨማሪም አፄ ኃይለ ሥላሴ ብቻ ሳይሆኑ አሽከሮቻቸውም ጭምር ለየራሳቸው ክብር የሚሳሱ ነበሩ፤ ስለዚህም ከውስጣቸውም ከውጭም የሚሰሙት ድምፅ ነበረ፤ ሆኖም አገዛዝ መማር አይችልምና የ1953 የስዒረ መንግሥት ሙከራ አገዛዙን ሳይለውጠው ቀረ::

በእኔ ግምት የአፄ ኃይለ ሥላሴ አገዛዝ በኢትዮጵያ ዘመናዊ ትምህርትን በማስገባትና በማስፋፋት በኩል ወደር የሌለው እርምጃን አሳይቶአል፤ ትምህርት በአጠቃላይና የከፍተኛ ትምህርትም በር ለማናቸውም ችሎታቸውን ላሳየ ድሀ ክፍት ነበር:: የልዑላን፤ የመሳፍንትና የመኳንንት ልጆች ከደሀው ልጅ ጋር አብረው እየተማሩ አደጉ፤ እ.ኤ.አ. በ1951 «ላይፍ» የሚባለው መጽሔት ኢትዮጵያ አንድ መሃንዲስ እንኳን የሌላት ደሀ አገር ነች ብሎ መጻፉ እንዴት እንዳናደደኝ አስታውሳለሁ፤ ጥሩው ነገር በዚያው ዓመት የከፍተኛ ትምህርት ተጀመረ፤ ያለምንም ጥርጣሬ የአፄው መንግሥት በትምህርት በኩል ኢትዮጵያን ገፍቶ ወደ ሃያኛው ምዕተ-ዓመት አስገብቶአት ነበር ለማለት ይቻላል:: ይህ በጦር ትምህርትም ቢሆን እውነት ነበር፤ በሐረር አካዳሚ፤ በደብረ ዘይት ዓየር ኃይልና በምፅዋ የባሕር ኃይል የነበረው የመኮንኖች ሥልጠና ሁለገብና በጣም ከፍተኛ ነበር፤ ኢትዮጵያ ከራስዋ ልጆች አልፋ የብዙ አፍሪካ አገሮች ወጣቶችንም በየመስኩ ታሠለጥን ነበር፤ ከነዚህ መሃል በየአገሮቻቸው ሚኒስትሮችና አምባሳደሮች የሆኑ ነበሩ::

በትምህርት የተደረገውን ከፍተኛ እርምጃ በገሃድ የሚያሳዩ ጥቂት መሥሪያ ቤቶች ነበሩ፤ የኢትዮጵያ ዓየር መንገድ፣ የኢትዮጵያ ቴሌኮሙዩኒኬሽን፣ የመብራት ኃይል፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክና ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በኋላ የቀዳማዊ ኃይለሥላለሴ ዩኒቨርሲቲ፣ በዘመኑ እነዚህ ድርጅቶች



ከየትም አገር ተመሳሳይ ድርጅቶች ጋር ተወዳድረው የማያሳፍሩ ነበሩ፤ ዛሬ እነዚህ ድርጅቶች ያሉበትን ሁኔታ እንድነግራችሁ የምትፈልጉ አይመስለኝም::

የአፄ አገዛዝ ለትምህርት ይህንን ያህል ትኩረት ቢሰጥም የትምህርትን ባሕርይ ለመገንዘብ አልቻለም ነበር፤ በመሠረቱ መማር መለወጥ ነው፤ የተማሩ ሰዎች በተማሩት መጠን ይለወጣሉ፤ የጥራዝ ነጠቅ መለወጥ ሳይሆን፣ ጥልቀት ያለው ለውጥ ማለቴ ነው፤ በተለወጡት መጠን አካባቢያቸውን ለመለወጥ ይፈልጋሉ፤ አካባቢውን ወደተሻለ ሁኔታ ለመምራትና ለመለወጥ የሚደረገውን ማናቸውንም እርምጃ የአገዛዝ ሥርዓት አይፈቅድም፤ ስለዚህም በአስተዳደርና በልማት በኩል የተማረው ኃይል የተመኘውን ያህል መራመድ አልቻለም፤ በአገዛዝና በተማረው ኃይል በኩል ቅራኔው ሰፊና ጥልቅ እየሆነ ሄደ፤ በዚያን ጊዜ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ውስጥ የተሻለ ደረጃ የነበራት አገር በመሆንዋ ያንን ደረጃ መጠበቅ ብቻ ሳይሆን እንድትገሰግስና ለሌሎች አርአያ እንድትሆን የዘመኑ ወጣት ምኞት ነበር፤ ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ብቻ ሳይሆን ለጥቁሩ ዓለም የነጻነት ጮራና የተስፋ አርአያ ሆና እንደኖረች ሁሉ በኢኮኖሚውም በኩል የከበረችና የበለጸገች አገር እንድትሆን ከፍተኛ ጉጉት ነበር፤ ነገር ግን የኢትዮጵያ እድገት የኤሊ ጉዞ ሆነበት፤ የአገዛዙ ትልቁ ድክመት ትምህርትን ለማስፋፋት ያደረገውን ጥረት ያህል የትምህርትን ውጤት ለመቀበል አለመቻሉ ነበር::

በመጨረሻም ይህ ባህላዊው አገዛዝ ሲወድቅ ኢትዮጵያ ያልፍላታል፤ የእድገት ግስጋሴዋ ይጣደፋል ተብሎ ነበር፤ ነገር ግን አገዛዙ ሥልጣንን ለብቻው ጨብጦ በአንድ ሰው እጅ ለመቋጠር ሲል ሰዎች እንዲሰባሰቡና እንዲደራጁ፣ሀሳባቸውንም በይፋ እንዲገልጹ የማይፈቅድ በመሆኑ አገዛዙም ሕዝቡም በጮሌ የበታች መኮንኖች ተጠለፉና የሳንድኸርስትና የሳን ሲር ምሩቅ ጄኔራሎች በነበሩበት አገር ሻለቃዎችና የበታች ሹማምንት ነገሡባት፤ ስለዚህም የባሰና ለሰው ሕይወት ምንም ዋጋ የማይሰጥ የጭካኔ አገዛዝ ተተካ፤ ስደት የኢትዮጵያውያን ባህል ሆነ፤ የትምህርት እድገት በጥራዝ ነጠቅ ማርክሲስት ሌኒንስት እምነት ቆረቆዘ፤ ተጀምሮ የነበረው ከፍተኛ የእርሻ እድገት እንቅስቃሴ ተገታ፤ ጥሩምባ እየነፉ መግደልና መንጠቅ የጊዜው ባህል ሆነ፡

በደርግም ዘመን ልክ እንደዘውዱ አገዛዝ ሥልጣን በአንድ ሰው እጅ ተቋጥሮና ሕዝቡ በጭካኔ ታፍኖ በማንአለብኝነት ግፉን እየተቀበለ እስቲያንገሸግሸው ድረስ ቆይቶአል፤ በመጨረሻም የነቃ፤ የተደራጀና የታጠቀ ኃይል ያሸንፋል፤ በሚለው የራሱ የደርግ መፈክር መሠረት ተገፍቶ ገደል ገባ፤ ደርግን የተካው ወያኔ ከጫካ የወጣ ጆሌ ነው፤ የአፄ ኃይለ ሥላሴ ጄኔራሎች በበታቾቻቸው እንደተበለጡ ሁሉ ደርግም ከጫካ በወጡ ጆሌዎች ተበለጠ፤ ከአፄ መውደቅ ጋር የተጀመረው የቁልቁለቱ መንገድ ገና አላቆመም፤ ያለንበትን ሁኔታ ስናስበው ይህንን ለመገንዘብ አዳጋች አይደለም::

## 4 ያለንበት ሁኔታ

በአጭሩ በነደፍሁላችሁ ርኩስ መንፈስ በሰፈነበት ዓለም ውስጥ እንገኛለን፤ ይህ ርኩስ መንፈስ ሩቅ አይደለም፤ ደሀነታችን፣ የምኞት ባሮች መሆናችን፣ የውስጣችን መንቃት ወይም መሰነጣጠቅ ርኩስ መንፈስን ከያለበት የሚጋብዙ ናቸው፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላማዊና መከራን የሚችል ነው፤ እንደኛ ጀግናና ትእግስተኛ ሕዝብ የለም፤ ተዘረፍን ብለን ሳንቆጣ፤ ተጠቃን ብለን ሳንጮህ፤ ሕጋዊ ሥርዓት ተፋለሰ ብለን ሳንበሳጭ የደሀውና የሥራ አጡ ለቅሶና ብሶት ሳይሰማ፤ ሁላችንም በዕለት ተዕለት የኑሮ ግዴታ ተጠምደን፣ ተጨንቀን ሳናስብ እንኖራለን፤ የተማረው ያልተማረውን፣ ያልተማረው የተማረውን እየናቀው፤ ወጣቱ በሽማግሌው፣ ሽማግሌው በወጣቱ፣ ሀብታሙ በደሀው፣ ደሀው በሀብታሙ፣ ገጠሬው በከተሜው፣ ከተሜው በገጠሩ እያመካኘ፣ ጠመንጃ ያነገተው ሌጣውን ቀንበር እያሸከመው፣ ትናንት ስንሰግድለት የነበረውን ዛሬ እያዋረድን፣ ነገ የምናዋርደውን ዛሬ እያከበርን የኑሮ ግዴታችንን (ማለት በልቶ ማደርን) ብቻ ዓላማ አድርገን እንኖራለን፤ ስለነገው አንጨነቅም፤ ስለ ነገ የማንጨነቅበት ዋናው ምክንያት ነገን የሚያንፁትና የሚያቅዱት ጌቶች ስለሆኑ እኛን አይገባንም፤ ስለነገ አለመጨነቅ የባርያ ባሕርይ ነው፤ ስለዚህም ነገ የራሱን ጣጣ ይዞ ሲመጣ ራሳችንን ለአዲስ ጣጣ ከማዘጋጀትና ጊዜያዊ የግል ጥቅማችንን ከማረጋገጥ ሌላ ለማሰብ ዝንባሌውም ፍላጎቱም የለንም፤ «ያለው ላይቀር ምን አታገለኝ» የሚል ፍልስፍና ነው መመሪያችን።

የአንድ አገር ሕዝብ የአገርና የሥልጣን ባለቤትነቱን ለማሳወቅና ለመታገል ካልተነሣ እንዴት ያልፍለታል? ችግሩን ሁሉ በአገዛዝ እያመካኘ አምላክን፣ መላእክትንና ሰማዕታትን በመማፀን ብቻ መፍትሔ በመጠበቅ ሁለት ሺህ ዓመታት ሲሞላን ነው፤ ጸሎቱንም የሚያሰምርልን ልብ የለንም፤ ልባችን በከፋትና በጥላቻ፤ በቂምና በምቀኝነት የተሞላ ስለሆነ የልባችንን የሚያውቅ አምላክ የአፋችንን ጸሎት የሚሰማበት ጆሮ ያለው አይመስለኝም፤ በቀን ብዙ ጊዜ እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል እያለ የሚጸልየው ሁሉ የምሕረትና የይቅርታ አቋም በሚያስፈልግበት ጊዜ አካሉ እየተንቀጠቀጠ አንበቱ የበቀልን እሳት ይተፋል፤ እንኳን የቅርቡን የምእተ-ዓመታት ታሪክን እያስታወሰ ለበቀል ጦር ይሰብቃል። ስለዚህ ለጸሎትም ቢሆን ልባችን ንጽሕና ይጎድለዋል፤ አገራችን በመንፈሳዊነትም የከሰረች ነች፤ መንፈሳዊነትን በሃይማኖታዊ ትርጉም ብቻ እንደምወሰደው፣ እኔ የምጠቀምበት ለእውነት፣ ለነጻነትና ለፍትሕ፣ ለእኩልነትና በአጠቃላይ ከፉውንና በጎውን ለምንለይባቸው የጎሊና ተግባሮች ሁሉ ጭምር ነው።

በዚያ ላይ ጎመን በጤና በሚል ሰንካላ ፍልስፍና ተመርዘናል፤ ፍርሃት ወኔያችንን ገድሎታል፤ ኢትዮጵያውያን የምንላቸው የእውቀትና የሀብት ባለቤት የሆኑትን ብቻ ቢሆን እኔ በበኩሌ አገዛዙ የሚገባቸው ነው ለማለት



አያዳግተኝም ነበር፤ ነገር ግን ከዘጠና በመቶ በላይ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በችግርና በችጋር እየተጠበሰ የሚኖር ነው፤ ለእነሱ፣ በጭቆናና በብዝበዛ ስር በችግር ተወልዶ በችጋር ለሚሞተው አገዛዝ ጸሩ ነው፤ የሀብትና የእውቀት ባለቤቶች ምርጫቸው ብዙ ነው፤ ከተገነዘቡት ባላቸው መጠን ግዴታቸው ወይም ኃላፊነታቸው ከባድ እየሆነ ይሄዳል፤ ይህንን ግዴታ አለመቀበላቸው ካላቸው የምርጫ ብዛት ጋር በጭቆና ስር መውደቃቸው የሚታዘንላቸው አያደርጋቸውም፤ ማኅበረሰቡ ከነዚህ ከፍሎች የሚጠበቀውን የአለኝታነት፤ የመከታነት የአመራር በረከት ገና አላገኘም፤ ለማኅበረሰባችን መንፈሳዊ ውድቀት አንዱና ዋናው መገለጫ የሀብትና የእውቀት ባለቤት የሆነው ክፍል ግዴታ-ቢስነት ነው፤ ከተመቸውና በኢትዮጵያ መጠቀም ከቻለ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለግዴታ መኖርን፣ ካልተመቸው በሌላ አገር ሄዶ መኖርን እንደአማራጭ ይዞ ያለ ነው፤ በሌላ አነጋገር አንድ እግሩን በፈረንጅ አገር አንድ አግሩን በኢትዮጵያ አንፈራጥጦ የሚኖር ነው፤ እንደአንድ አገር ሕዝብ የብዙኃኑ ስቃይና ብሶት እንዲጋባብንና እንዲሰማን ኅሊናችን አስገድዶን ኢትዮጵያ ለእኛ የወፍራም እንጀራ ምንጭ ብቻ ሳትሆን እኛም የርስዋ እንጀራ ምንጭ መሆናችንን መቀበል ገና አልቻልንም፤ በራሳችን ዓይን ያለውን ጉድፍ ሳናወጣ አገዛዙ ላይ ጣታችንን መጠቆሙ ብቻ የትም አያደርሰንም።

የመንፈስ ደካሞች በመሆናችንም አሁንም የምንኖረው እንደተለመደው ከእኛ ቁጥጥር ውጪ በሆነ የአገዛዝ ሥርዓት ስር ነው፤ የአገዛዝ ሥርዓቱ መሠረታዊ ባሕርይ ሁሉንም ነገር ለብቻ በሞኖፖል መያዝና ሁሉንም ነገር መቆጣጠር ነው፤ የአገር ሥልጣንን ለብቻው፣ የሀብት መሠረት የሆነውንም መሬትን ለብቻው፣ የሕዝብ የዜና ማሰራጫዎችን ለብቻው፣ የአገዛዝ ሥርዓቱ ራሱ የፖለቲካና የኤኮኖሚ ጥገኛ ሆኖ ሳለ የአገሩን ባለሀብቶች በጥገኝነት እየፈረጀ ለማሳፈርና እድገታቸውን ለመግታት የሚሻው ጥገኝነትንም በሞኖፖል ለመያዝ ይመስላል፤ በዚያ ላይ ሥርዓቱ የዜና ማሰራጫ፤ የዜና ወኪል፤ የንግድና የኢንዱስትሪ፣ የቲአትር የማስታዊያና የማተሚያ ድርጅቶች ቢያንስ የእጅ አዙር ባለቤት ሆኖ ሌሎች ባለሀብቶች የሚያገኙትን ዕድልና ድጋፍ በማግኘት ከውድድር ውጪ ያደርጋቸዋል፤ በማርክሲስቶች አነጋገር ይህ የቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝም ነው።

ኢትዮጵያውያን በሙሉ ባይስማሙበትም አፄ ኃይለ ሥላሴ ለምንወደው ሕዝባችን እንዳሉት ባይሆንም፣ ለምንገዛቸው ነሣዎቻችን በሚል መንገድ የተሰጠና መነሻ ሆኖ ሊያሠራ የሚችል ሕገ መንግሥት ለወጉ አለ፤ ዛሬ ጥያቄው ሕገ መንግሥቱ ጥሩ ነው? ወይስ መጥፎ? የሚል አይደለም፤ ጥያቄው ሕገ መንግሥቱ ነፍሱ አለ ወይ? ነው፤ አገዛዙ ራሱ በገሀድ ያለምንም ሃፍረት የሕገ መንግሥቱን ጥርስ ሲያፈርሰው እያየን ነው፤ እንዳሁኑ የአገዛዝ ሥርዓት

ፍትሕን ሙሉ በሙሉ በቁጥጥር ስር ያደረገ ከዚህ በፊት አልታየም፡፡ በአሁኑ አገዛዝ ደሀዎች፤ ሴቶችና ወንዶች ልጆች ከየመንገዱ ላይ እየተለቀሙ ከከተማ ውጪ ስንት ጊዜ ለጅብ ተጣሉ? በቅርብ አንዱን ጋዜጠኛ እንደአባብ ራስ ራሱን ቀጥቅጠው ከድልድይ ወደወንዝ ወረወሩት፤ ዛሬ በሕግ አምላክ ማለት ዋጋ የለውም፡፡ ስንት ሺህ ሰዎች ናቸው ፍርድ ቤት እንኳን ሳይቀርቡ አሥር ዓመት ያለፉቸው? ስንት መቶ ሰዎች ናቸው ተገድለው ደማቸው ደመ ከልብ ሆኖ የቀረው? ስንት ሰዎች ናቸው በጥርጣሬ ብቻ በእስር ቤት የሚማቅቁት? ስንት ሺህ ሰዎች ናቸው ከኤርትራ ተፈናቅለው ከአሥር ዓመት በላይ ከአንድ መጠለያ ወደሌላ መጠለያ እየተባረሩ የሚኖሩት? ስንት ልጆች በየመጠለያው እየተወለዱ በየባቡር መንገዱ ያድጋሉ? ስንት ሺህ ሰዎች በኤርትራ ጦርነት ምክንያት ከየቤታቸው ተፈናቀሉ? ስንት ሺህ ሰዎች በጎሣ ምክንያት ተፈናቅለው በችግር ይኖራሉ? አሁን ደግሞ ስንት ሰዎች ከጅቡቲ ተፈናቅለው መጥተዋል? የመንም ኢትዮጵያውያንን እያባረረች ነው ይባላል፤ እነዚህ ሰዎች ሁሉ አገርና መንግሥት አላቸው? ወገን አላቸው?

አሁን ያለንበት የአገዛዝ ሥርዓት የደርግ የባሕርይ ታናሽ ወንድም ነው፤ በደርግና በወያኔ አገዛዞች መሀከል ያለው ልዩነት የጌቶቻቸው የባሕርይ ልዩነት ብቻ ነው፤ የደርግ አገዛዝ አፍአዊ ገጽታውን የሶሺያሊስት ቀለም እንዲቀባ የተገደደውን ያህል የወያኔ አገዛዝም አፍአዊ ገጽታውን የዴሞክራሲ ቀለም እንዲቀባ ተገደደ፤ ጉልቻውና ቀለሙ ተለዋወጠ እንጂ ማገዶውና የሚጠበሰው ያው ነው፤ የበላውና የጠገበው ሲሄድ የራበውና ሁሉ ብርቁ ይተካል፤ በሁለቱም ላይ ቢሆን ራስን መጠራጠር፣ በጎ ፈቃድና መንፈሳዊ ወኔ የለም፤ በሁለቱም ላይ ጎልቶ የሚታየው በተለያየ መንገድ ከእነሱ የሚበልጡ ሰዎች በአገር እንዳይኖሩ ነው፤ ወደ አውሮፓም ሆነ ወደ አሜሪካ፤ ወደ አውስትሬሊያም ሆነ ወደ አረብ አገሮች ስደትን የኢትዮጵያውያን ባህል ያደረጉ አገዛዞች ናቸው፡፡

## 5. የያዝነው አቅጣጫ የት ያደርሰናል?

ከተለያየ የትምህርትና የሥራ መስክ የመጡ ቢሆንም ከዚህ በፊት የተናገሩት ሁሉ በአንድ ነገር ላይ ይስማማሉ፡- አሁን በተያዘው መንገድ መቀጠል አንችልም፤ የያዝነው መንገድ ወደ «ክፉ ዕድል» ወደ«መዓት» ወደ«ውድቀት» የሚያመራ መሆኑ ተገልጾአል፤ ለእኔ የአዘቅቱ መንገድ የሚታየኝ እንደሚከተለው ነው፤ በሸምበቆ አጥር የተለያዩና የሚተራመሱ ጎሣዎችን ጭኖ የሚከንፍ ባቡር ይታየኛል፤ ነጂው መትረየሱን ይዞ ፊቱን አዞሮ የተቀመጠው ወደሚነዳበት አቅጣጫ ሳይሆን ወደተሳፋሪዎቹ ነው፤ ተሳፋራዎቹ የሚያዩት ወደፊት ነው፤ ነጂው የሚያየው ወደኋላ ነው፤ ስለዚህም ነጂው ገደሉን



ስለማያይ ይበልጥ የሚያስፈራው የተሳፋሪዎቹ ትርምስ ነው፤ ተሳፋሪዎቹን የሚያስፈራቸው የሚታያቸው መትረየስና ገደል ነው፤ በባቡሩ ላይ ያሉ ተሳፋሪዎች ሁሉ በባቡሩ ፍጥነት ላይም ሆነ አቅጣጫው ላይ ምንም ዓይነት ቁጥጥር የላቸውም፤ የባቡሩ ነጂ ተሳፋሪዎቹ የሚያዩትን አያይም፤ እንዲነግሩትም አይፈልግም፤ የነጂውና የተሳፋሪዎቹ አስተሳሰብ ለየቅል ነው፤ አይነጋገሩም፤ ተሳፋሪዎች በዝምታ ነጂውም ባለማወቅ ወደማያየው ገደል ውስጥ ለመግባት ቆርጠዋል፤ ባቡሩን አቁም ብለው ቢጮሁ መልሱ መትረየስ መሆኑን ያውቃሉ፤ በዝምታ አብሮ ገደል መግባት ነው፤ በዚህ አጣብቂኝና የፍርሃት ቆፈን ተይዘናል፤ ከተረዳንለት ነጂውም አጣብቂኝና የፍርሃት ቆፈን ውስጥ ነው፤ ነጂውና ተሳፋሪዎች ካልተነጋገሩ ባቡሩም፤ ተሳፋሪዎችም፤ ነጂውም ከገደሉ ማምለጥ አይችሉም፡፡

እንግዲህ መሣሪያ የያዘውም ይፈራል፤ መሣሪያ ያልያዘውም ይፈራል ማለት ነው፤ የሁለቱም ጠላት አለመተማመንና መሣሪያው ነው፤ አለመተማመንን ሳናጠፋ መሣሪያውን ማጥፋት አንችልም፤ ሳንነጋገር አለመተማመንን ማጥፋት አንችልም፤ ልባችን ከቂምና ከበቀል ካልፀዳ ተነጋግረን መግባባት አንችልም፤ ባቡሩ እውር ድንብሩን እየሄደ ገደል የሚገባው ለዚህ ነው፡፡

የባቡሩ ገደል መግባት የአደጋው መጀመሪያ እንጂ መጨረሻ ይሆናል የሚል ግምት የለኝም፤ አደጋው የጎሣ ትርምስና የቂም መወጫ ሁኔታን ይፈጥራል፤ ለብዙ ምዕተ- ዓመታት ወደኋላ ሄደን ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች ጋር እንሰለፋለን፤ የያዝነው መንገድ ወደዚህ እንደሚያመራ ለእኔ ግልጽ ነው፤ ይህንን የሚጠራጠር ትንሽ ያስብበት፤ ለሌሎች የተዘራው የጎሣ መርዝ ባልታሰበበት መንገድ ሄዶ በኤርትራና በትግራይ ተወላጆች መሃከል የከፋ መልኩን ማሳየቱ የሚያሳዝንና የመርዙንም ጠምዛዛነት የሚያመለክት ነው፤ የዚህ ጦስም የትግራይ ተወላጆችንም በመከፋፈል ላይ ነው፤ አነግ ጎልቶ የሚታይ ቢሆንም በሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች በማቆጥቆጥ ላይ ያለው ጎሠኛነት ጉዳዩን ለሚከታተሉ ሁሉ ግልጽ ነው፤ በጎሠኛነት ተኮትኩተው ያደጉ ልጆች እየደረሱ ነው፤ አንድ ትውልድ ሊሆን ምንም አልቀረውም፤ብዙዎቻችንን የሚያሳስበን ደህነቱና የችጋሩ ጉዳይ ነው፤ የኢትዮጵያን ህልውና ጉዳይ ባንረሳውም አደጋውን ላለመቀበል አእምሮአችንን የምንጋርደው ይመስለኛል፤ ጭንቅላታችንን አሸዋ ውስጥ ቀብረን የምንፈልገውን መመኘቱ ብቻ አቅጣጫችንን አይለውጠውም፤ እኔ የማውቃትና አገሬ የምላት ኢትዮጵያ አሁንም በከፊል የለችም፤ በያዝነው መንገድ ከቀጠልን ደግሞ ያሁንዋም ኢትዮጵያ 2020 የምትደርስ አይመስለኝም፤ በያዝነው መንገድ ከቀጠልን የብዙ አፍሪካ አገሮች ሁኔታ ውስጥ መግባት የማይቀር ነው፤ ኢትዮጵያ የምትባል አገር ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን በጥያቄ ምልክት ውስጥ መግባትዋ የሚቀር አይመስለኝም፤ ከዘመነ መሳፍንት የባሰና

እስከፊ ሁኔታ እንደሚያጋጥመንና በሆነ ባልሆነው መከሳከሳችን ይቀራል ብዬ አልገምትም፡፡

የወደፊቱ ግጭት ከእሁን በፊት ከለመድነው በጣም የተለየ ይሆናል፤ እስከዛሬ የምናውቀው ግጭት በአፈንጋጭ የማኅበረሰቡ ከፍልና በአገዛዙ መሀከል ነበር፤ ቀደም ሲል እንደተናገርሁት ደርግ ራሱ ባወጣው «የነቃ የተደራጀና የታጠቀ ያሸንፋል፤» በሚለው ሕግ ወደቀ፤ ወያኔም ራሱ የጠነሰሰውና ሕጋዊ ያደረገው ጎሠኛነት የሚፈጥረው ግጭት እንደበፊቱ በአገዛዝና በአፈንጋጭ መሀከል ሳይሆን በተለያዩ ጎሣዎችም መሀከል ይሆናል፤ በጎሠኛነት ተኮትኩቶ ያደገ ትውልድ በማኮብኮብ ላይ ነው ብያለሁ፤ ዛሬ በትግራይና በኤርትራ ተወላጆች መሀከል ያለው ስሜት ነገ በሌሎች መሀከል ይከሰታል፤ በተነጠቁት መሬት የተነሳ ወሎና ጎንደር ውስጥ ያለው ንዴት ቀላል አይደለም፤አፋር ተከፍሎና ታፍኖ አይኖርም፤ አነግ እየተዋጋ ነው፤ ኦጋዴን ለመገንጠል ይችላል የሚል ማደፋፈርያ ተሰጥቶታል፤ ሌላው በየጎራው እያብላላው ነው፤ የጎሣው ግጭት የሚፈጥረው ትርምስና መተላለቅ ከጀመረ በራሱ ኃይል እየተቀጣጠለ ስለሚስፋፋ ላማቆም አስቸጋሪ ይሆናል፤ ስለዚህም ሰላም ይኖራል ብዬ አልገምትም፤ አዘቅቱ የከፋና የኢትዮጵያ ሕዝብ በታሪኩ አይቶት የማያውቀው ደህነትና ችጋር ጭካኔን እየወለደ፣ በጎሠኛነት ሞተር እየተነዳ በጥላቻና በቂም እየታወረ ከፋት በገሃድ የሚወጣበት መተላለቅ ነው፡፡

በዚህ መተላለቅ ከአካባቢያችን የሚረዱን አይጠፉም፤ በአለፉት ዓመታት ከሶማልያና ከኤርትራ ጋር የተደረገው መዳማት፤ ከጅቡቲ ጋር የተደረገው አለመግባባት፤ በአንድ በኩል ከአሜሪካ ጋር፣ በሌላ በኩል ከሱዳን ጋር የተደረገው ሽር ጉድ የሚከተሉትን ዓመታት ለኢትዮጵያ የሚመቹ አያደርጓቸውም፤ እኔ እንደምገምተው ሁሉም የተነበየው አዘቅት ወይም አፋፍ ላይ በ1997 መጨረሻ እንደርሳለን፤ አዲስ ኢትዮጵያ የምትወለደው ከኤርትራ እስከቦረና ከጋምቤላ እስከጂጂጋ ሁሉም በአንድ ጊዜና በአንድ ላይ በሚሰማው የጭንቀት ምጥ ይሆናል፤ ሕገ አራዊት የሚያደርሰን እዚህ ነው፤ የሰው ልጅ አእምሮ ውስብስቡን የኑሮ ገመድ ሲገምድና ሲፈታ አኛ ገና ከቀላሉ የማስፈራራትና የጡንቻ ዘዴ አልወጣንም፤ በማስፈራራትና በጭቆና የጨቋኝም የተጨቋኝም አእምሮ ደንዝዞ፤ መንፈስም ታምሞ በደነዘዘ አእምሮና በታመመ መንፈስ ትርጉም ያለው ሥራ ለራሳችንም ሆነ ለማኅበረሰባችን ለማበርከት አንችልም፡፡

እንደምትገምቱት ይህንን መናገር ቀላል ነገር አይደለም፤ እስካሁን ድረስ ሦስት አገዛዞች በውርደት ሲወድቁ አይቻለሁ፤ የሁለቱ አገዛዞች መውደቅ በቅድሚያ ታውቆኝ በአደባባይ ተናግሬ ነበር፤ የአሁኑ አገዛዝ በዓይነቱ የተለየ ነው፤ ራሱንም ለማረም በጊዜ ካልጣረ አወዳደቁም የተለየና አገሪቱንም



የሚያጠፋ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ባሕሩ[11] እንዳለው ኢትዮጵያ የተአምር አገር ነች፤ አለቀላት ሲባል ነፍስ ዘርታ ትነሣለች፤ እንደዚያ ከሆነ ደስታው የሁላችንም ነው፤ በተአምር ባምንም እጆቻችንን አጣምረን በመቀመጥ ከአንዣበበው አደጋ እናመልጣለን ብዬ ግን አላስብም፡፡

## 6. አደጋውን ለማስቀረት ምን ማድረግ አለብን?

ይህንን ጽሑፍ በማዘጋጅበት ጊዜ ከፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ በቅርቡ የሚታተም መጽሐፍ ረቂቅ ደርሶኝ እያነበብሁ ነበር፤ ስለደቀ እስጢፋኖስ በአሥራ አምስተኛው ምዕተ-ዓመት መጀመሪያ ላይ የሆነውን ከግዕዝ የተረጎመው ነው፤ ከተጻፈ ስድስት መቶ ዓመታት የሆነው ነገር ሁሉ ዛሬም የሚሆን ነው፤ የሚያሳዝንም የሚያስደንቅም ነው፤ በሥልጣን ላይ ያሉት ሰዎች የሀሳብ ልዩነትን መቀበል የማይችሉ መሆናቸውንና እንዲህ ያሉትን ሰዎች በተለያየ መንገድ ማሰቃየታቸው፤ የማሰቃያው መንገድም ብዛቱ እንዳለ ምንም ሳይለወጥ መቆየታችንን በግልጽ ያመለክታል፡፡
ለእኔ እንደሚታየኝ አቃለልከው ካላላችሁኝ ታሪካዊ ችግሮቻችን ሁለት ብቻ ናቸው፤ አንደኛ በረጂሙ ታሪካችን ውስጥ የምናየው በሕገ አራዊት መመራትን ነው፤ ከኃይል የተሻለ የመተዳደርያ ዘዴ አልፈጠርንም፤ የበላይና የበታች በመሆን፣ ባለመብትና ባለግዴታ እየተለየ፣ ጌታና ሎሌ በመሆን እኩል መቻቻል እንጂ በእኩልነት ላይ የተመሠረተ ግንኙነት የሚሆን ዘዴ አላገኘንም፤ ሥልጣንን መግራት ሳንማር 1996 ደርሰናል፤ ሥልጣንን መግራት የሥልጡን ሕዝብ መታወቂያ ምልክት ነው፤ በሕገ አራዊትና በጉልበት እየተገለባበጥን እንቀጥላለን፤ የእድገትና የልማት አንዱ ምሥጢሩ ሥልጣንን መግራት ነው፤ ሥልጣንን በእኩልነት ሕጋዊ ማድረግ ነው፡፡
ሕገ አራዊትን መመሪያችን በማድረጋችን ነው በአጠቃላይ ባህላችን የነፍጠኛነትና የጀብደኛነት የሆነው፤ ጠመንጃ ተይዞ በፉከራና በሽለላ ታጅቦ፣ ጀግና፣ ገዳይ፣ በመሆን ነው፤ «እኔ ያንተ አሽከር ያንተ ቡችላ» የሚባልለት፤ አሁን ደግሞ ማጅራጀት መቺ፣ አከርካሪት ሰባሪ ሆኖ በሕገ አራዊት ለሚያደናብረው ነው አሽከርነት የሚያድረው፤ አሽከር ዛሬ ስሙ ተለውጦ ካድሬ ሆኖአል እንጂ እዚያው ነን፤ በባህላችን ብዙ መሳፍንትና መኳንንት ስለነበሩ አሽከር ምርጫ ነበረው፤ ዛሬ ጌታው አንድ ብቻ በመሆኑ ምርጫም የለም፤ ዘመናዊነቱና ለውጡ እስከዚህ ድረስ ነው፤ የምናየውና የምንሰማው ያንኑ የለመድነውን ጭፍን እልህ ነው፤ የጂቡቲው ፕሬዚዳንት ጉሌድ ዲፕሎማሲያዊ ቋንቋውን ጥለው «የኢትዮጵያና የኤርትራ ሰዎች ከሚገባው

---

[11] ፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴ በሌላ ጊዜ በዚያው መድረክ ላይ ተናግሮት የነበረው ነው፡

በላይ ቁጡና ጠበኛ»12 ናቸው ብለው መናገራቸው በሕገ አራዊት ላይ የተመሠረተው አገዛዝ ድንበር አልፎ መታወቁን የሚያመለክት ነው።

ሁለተኛው ችግራችን ሥልጣንና ሕገ ኀልዮት አለመተዋወቃቸው ነው፤ ሕገ አራዊት አይሎ ነው እንጂ ሕገ ኀልዮት ለኢትዮጵያ ባዕድ ሆኖ አይደለም፤ የፈላሰፋዎችን የዘርዓ ያዕቆብንና የወልደ ሰንበትን ጽሑፎች ያነበበ ሁሉ እንደሚረዳው፣ አሁን ደግሞ ፕሮፌሰር ጌታቸው ለመጀመርያ ጊዜ ከግዕዝ ወደ አማርኛ እየተረጎመ የሚያሳትማቸው መጻሕፍትም እንደሚያሳዩን ማሰብ በጡንቻ እየተጨፈለቀ ደብዛው እንዲጠፋ ተደረገ እንጂ በአዲስ መንገድ ማሰብ የሚችሉ ሰዎች በየጊዜው ብቅ ብቅ ብለው እንደነበረ እናያለን፤ የሀሳብ ልዩነት የማይፈቀድና ለከባድ አደጋ የሚዳርግ መሆኑ ቢያንስ ከአሥራ አምስተኛው ምዕተ ዓመት መነሻ ላይ እንደጀመረና ለስድስት መቶ ዓመታት ቆመን እንደቀረን ያሳየናል፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጦርነት ሲሉት ፈንቅሎ የሚወጣውን ያህል ለሰላማዊ ትግል አንድነቱን ቢያሳይ ኢትዮጵያን ከታሪካዊ ችግሮችዋ መገላገል ይቻል ነበር።

ከኤርትራ ጋር ለተደረገው የወንድማማች ጦርነት የሀብትና የእውቀት ባለቤቶች ያደረጉት ከባድ አስተዋጽኦ የሚያስደንቅ ነው፤ በእነሱ አመራርም በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የኢትዮጵያ ወጣቶች ለባድመ ተማገዱ፤ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ስትገነጠል ግን ከዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በቀር የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጣውን ለማሳየት እንኳን አልሞከረም፤ ለሞት በቀላሉ እንነዳለን፤ ለሕይወት ግን በሰላም ለመታገል እንፈራለን፤

ዛሬም የባድመ ነገር የሚያንገበግባቸው ብዙ ናቸው፤ በአንጻሩ ደግሞ የአሰብ ጉዳይ የሚያቃጥላቸው ብዙ ናቸው፤ የባድመ ተቆርቋሪ የአሰብ ተቆርቋሪው ንዴት የሚገባው አይመስልም፤ እንዲሁም ለዚያኛው፤ ለቁጣችንም ሆነ ለትእግስታችን ሚዛን የለንም፤ ይህ ሁሉ የሚያሳየው ሕገ አራዊት በሕገ ኀልዮት ላይ ያለውን የበላይነት ነው፤ ይህ መለወጥ አለበት፤ እኛ መለወጥ አለብን፤ እኛ ራሳችንን ሳንለውጥ ምንም ነገር መለወጥ አንችልም።

ለጦርነት የምናሳየውን የጋለ ስሜት ለሰላማዊ ትግል አናሳይም፤ ሰላማዊ ትግል ወይም ፖለቲካ አልገባንም፤ ደርግ ሰላማዊ ትግሉን ወደ ሶሻሊስት የመደብ ትግል ለወጠው፤ መደብ በሌለበት አገር፤ ወያኔ ደግሞ በልጅነት ጥበቡ የሰላምን ትግል መሠረታዊ የሰው ልጅን አንድነት በሚቃረንና ወደድርድር በማይቀርብ የጎሣ ትግል ለወጠው፤ የደርግ ሶሺያሊስት ትግል ሁሉንም ድሃ በማድረግ መፍትሔ ለማግኘት ይችል ነበር፤ ሁሉንም ሀብታም ለማድረግ እስኪቻል ድረስ፤ የወያኔ እልህ ግን ከመበታተን ሌላ መፍትሔነት ያለው አይመስልም፤ የሚደንቀው የጎሣ ትግሉ በእያንዳንዱ በአመራር ደረጃ ላይ

---

[12] አዲስ አድማስ ጋዜጣ ጥቅምት 21/1996



ባለ ሰው ላይ የፈጠረውን የውስጥ ቅራኔ እንኳን መገንዘብ አለመቻሉ ነው፤ እንኳን ራቅ ካሉ ጎሣዎችና በጣም በተቀራረቡትም በትግራይና በኤርትራ መሀከል መደባለቅ ችግር እየፈጠረ እናያለን፤ መበታተኑ ወግና ሥርዓት ባለው መንገድ እንደማይሆን ባድመ እያስተማረን ነው (ገና ጥንት አብርሃም ሊንከን አንድ ቤት ውስጥ ሆነው ለመፈጸም ያልተቻለውን ውል ከተለያዩ በኋላ ያስቸግራል ብሎ ነበር) በደቡብም በየጊዜው የሚከሰቱት ግጭቶች የወደፊቱን ችግር እያመላከቱን ነው፤ መበታተኑንም ቢሆን ሰላማዊ ላይሆን ይችላል የሚል ስጋት አለኝ፡

በሕገ ኀልዮት የምንመራ ቢሆን ለማናቸውም ዓይነት እድገትና ልማት የሕዝቡ የሥልጣን ባለቤትነት ወይም ዴሞክራሲ የሚባለው ወሳኝ መሆኑን መረዳት አያዳግተንም ነበር፤ የተዳፈነውና የታመቀው የሕዝብ የአካል፣ የአእምሮና የመንፈስ ኃይል ለኑሮውና ለሕይወቱ ባለቤት የሚሆንበት ሁኔታ ሲፈጠር ብቻ ነው፤ በኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር፤ በኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር፤ በኢትዮጵያ ነጻ ጋዜጠኞች ማኅበርና በከተማና በገጠር ቀበሌ ማኅበራት ላይ የሚደረገው አፈናና ጫና ዴሞክራሲን በኢትዮጵያ ለመገንባት አይረዳም፤ ዴሞክራሲ የሚገነባው በልበ-ሙሉ ዜጎች ነው፤ ማስፈራራትና ማሸበር ቀርቶ የሥልጣን ትግል ሁሉ ሰላማዊና ሕጋዊ ሲሆን ነው፤ በተጨማሪም የዴሞክራሲ ጥቅም እያንዳንዱ ዜጋ፣ ሕዝብም በአጠቃላይ ለራሱ ኑሮና ለአገሩ እድገት ኃላፊነትን እንዲሸከም ማድረጉ ነው፤ በአገዛዝ ስር ያለ ሕዝብ ነጻነትም ኃላፊነትም የለውም።

የኢትዮጵያን ህልውና ጠብቀን የሚቀጥለውን ትውልድ ከደሀነት፣ ከችጋር፣ ከጦርነትና ከእርስበርስ እልቂት የሚያድነው የሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነትና የሕግ የበላይነት በሚቀጥለው ምርጫ መደምደሚያ ያገኛል ብለው የሚያምኑ ሰዎች ያሉ ይመስለኛል፤ በምኞትም ሆነ በተስፋ ደረጃ ከእነሱ ጋር እቆማለሁ፤ ግን ከፍተኛ ጥርጣሬ አለኝ፤ የዛሬ አሥራ ሁለት ዓመት ግድም በየዋህነት አንድ ነገር ተናግሬ ነበር፤ ወያኔ ትክክለኛ ምርጫ አካሂዶ ካሸነፈ ጥሩ፤ ካላሸነፈም ለኢትዮጵያ አዲስ የዴሞክራሲ ምዕራፍ ከፍቶ በክብር የሚቀጥለውን ምርጫ ይጠብቃል ብዬ ነበር፤ ይህ ምኞት ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ ነበር፤ በኋላ እንደተማርኩት እንኳን በዚያን ጊዜና ለምንጊዜም ሥልጣንን እንደማይለቅቁ ነው፤ ሌላውን ሁሉ ትተን ለአገርና ለወገን የሚያስብ ሰው ከኤርትራ ጦርነት በኋላ ስሕተትንና ብዙ ጉዳዮችን ማስተካከል ይቻል ነበር፤ በድንበሩ ምክንያት የተነሣውንም ውዝግብ በአዲስ መንገድ መፍታት ሳይቻል አይቀርም ነበር።

በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ያንዣበበውን አስከፊ ችግርና የአገሪቱንም ህልውና የሚፈታተነውን ሁኔታ እያቃለሉ መገሙቱ በሁሉም በኩል ቁርጠኛነት

እንዳይኖር ያደርጋል፤ እውነቱ አስደንጋጭ ቢመስልም ኮስተር ብለን እንድንዘጋጅ ይረዳናል፤ የአእምሮና የመንፈስ ዝግጅትም ግዴታችን ይሆናል፤ አእምሮአችንንና ልባችንንም ማፅዳትና መተማመን ያሻናል፤ ጠባችን የሀሳብ ልዩነት አይደለም፤ አለመተማመንና መፈራራት ነው፤ መንገድ ፈልገን እንተማመን፤ እኛ በሰላም ተከባብረን ሀሳቦቻችን ይጋጩ፤ይፋጩ፤ በሚወጣውም ብርሃን አገራችንን እንገንባ፤ የአገራችን እንገንባ፤ የአገራችን ጥሩ ባህል ስለነበረው እርቅ አለቃ አያሌው የሚከተለውን ጽፈዋል፤[13]--

*ወንድማማቾች በማይገባ ነገር ተጣልተው፣ በሃሳብ ተለያይተው፣ የማይግባቡና የማይስማሙ ከዚያም አልፎ ነገራቸው ከዳኛ የሚያደርሳቸው አንዱ ባንዱ ላይ ክፉ ለመሥራት የሚገፋፋቸው ሆኖ ሲገኝ ከፀቡ አግባብ የሌላቸው ወዳጆች፣ ጓደኞች፣ ባልንጀሮች፣ ሽማግሌዎች በመሀከል ገብተው ማልደው በፍቅር ተቆጥተው ወይም አባብለው ለእርቅ ቢያደርሱአቸው ሊፈርስ የነበረ ቤት ይታነጻል፤ የፈሰሰ ደም ይደርቃል፤ ነባር ቂም በቀል ይርቃል።*

መንፈሳዊ ወኔውን አግኝተን ይህንን ለማድረግ ከቻልን ኢትዮጵያን ከአደጋ ማውጣት ብቻ ሳይሆን የምንኮራበትና የምንመካበት አገር ልናደርጋት ችሎታው አለን፤ ከዱሮ ጀምሮ የነበረኝ እምነት ኢትዮጵያ ትክክለኛ መንግሥት ስታገኝ በአንድ ትውልድ የአፍሪካ ጃፓን ለመሆን ትችላለች፤ ሆኖም ጊዜ የለንም፤ ዛሬ መጀመር አለብን።

13 አለቃ አያሌው ታምሩ፣ ምክኛ፣ እርቅና ሰላም አዲስ አበባ፣ 1992.



# ሁለት
# የሞት ቅጣት
# አገዛዝና የባለሥልጣኖች ወንጀል

*መስፍን ወልደ ማርያም*
*መስከረም 1998*

ሰሞኑን ፍርድ ቤቶች የሞት ቅጣት እየፈረዱ ነው፤ አንደኔ ጉዳይ የሚያስጨንቃችሁ ካላችሁ አብረን እንጨነቅበት።

«የሞት ቅጣት» መሠረታዊ የአስተሳሰብ ችግር ያለበት አባባል ነው። የተሳሳተ አስተሳሰብ የማኅበረሰቦች ማንተምን ያገኝና ዕድሜው ይረዝማል። መግደል በግለሰብ ደረጃ ሲፈጸም ትክክል አይደለም፤ የተወገዘ ተግባር ነው። እያንዳንዱ ሰው በተናደደና ግልፍ ባለው ቁጥር መግደል ከቻለ ማኅበረሰብ ሊመሠረት አይቻልም፤ ይተላለቃል። እያንዳንዱ ሰው ሌላውን ሲገድልም ቢሆን ሕጉ የሚፈቅድበት ሁኔታ አለ፤ ለምሳሌ አልሞት ባይ ተጋዳይ ማለት የራሱን ሕይወት ለመጠበቅ ሲል ሌላውን የሚገድል ነው።

እንግዲህ በአጠቃላይ ሰው መግደል የተከለከለ ነው፤ ነገር ግን አልሞት ባይ ተጋዳይ ሲሆን ይፈቀዳል፤ በፍርድ ቤት ትእዛዝም መግደል ይፈቀዳል። የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 14 የሚከተለውን ይላል፤ ማንኛውም ሰው በሕግ በተደነገገ ከባድ ወንጀል ቅጣት ካልሆነ በስተቀር ሕይወቱን አያጣም። በሕይወት መኖር «የማይደፈርና የማይገሰስ» መብት ነው ከተባለ በኋላ በቅጣት እንደሚደፈርና እንደሚገሰስ ይደነግጋል። አንድ ሰው ከባድ ወንጀል ሲፈጽም የሞት ቅጣት ሊበየንበትና ሕይወቱን ሊያጣ ይችላል ማለት ነው። በኦሪት ዘጸአት እንደተደነገገው «ሕይወት በሕይወት፣ ዓይን በዓይን፣ ጥርስ በጥርስ፣ እጅ በእጅ፣ እግር በእግር፣ መቃጠል በመቃጠል፣ ቁስል በቁስል፣ ግርፋት በግርፋት ይከፈል፤» ማለት ንጹሕ የበቀል መንገድ ይመስለኛል፤ «ይከፈል» የሚለው ቃልም የሚያመለክተው በቀልን ነው። እግዚአብሔር ያሳያችሁና አንድ ሰው የሌላውን ሕይወት ቢያጠፋና ጉዳዩ በሕይወቱ ይከፈል ቢባል ትርጉም ያለው ነገር ነው? ዓይን ያጠፋ ዓይኑን በማጥፋት ይከፈል፣ ጥርስ ያወለቀ ጥርሱን በማውለቅ ይከፈል ማለት፣ እግር የቆረጠ እግሩ ይቆረጥ፣ እጅ የቆረጠ እጁ ይቆረጥ… ማለት ትርጉም ያለው ነገር ነው? የሚከፈል ነገር ከፋይና ተቀባይ አለው፤ የገደለ ሲሞት ጉዳይ ምንም የሚቀበለው ነገር የለም፤ ዓይን ያጠፋ ዓይኑ ሲጠፋ መጀመሪያ ዓይኑ የጠፋበት ምንም አይቀበልም፤ የጥርሱም የእግሩም የእጁም ያው ነው።

ከአራቱ ሕግ የምንገነዘባቸው ሁለት ነጥቦች አሉ፤ አንደኛው አንድ ጥፋት ተመሳሳይ ጥፋት ማስከተሉን እንመለከታለን፤ ሁለተኛው ነጥብ ደግሞ አንዱ ጥፋት በአንድ ግለሰብ የተፈጸመ ሲሆን ሁለተኛው ተመሳሳይ ጥፋት የሚፈጸመው በማኅበረሰቡ መሆኑን እንረዳለን። ግለሰቡ ሲገድልም ሆነ ሲቆርጥ በንዴት ወይም በቁጣ ስሜቱ ገንፍሎበት በእንስሳ ባሕርዩ ተመርቶ የሚያደርገው ጥፋት ነው። ማኅበረሰቡ የግለሰቡን ተመሳሳይ ጥፋት ሲፈጽም ግን በመናደድ ወይም በእንስሳ ባሕርይ ተመርቶ ሳይሆን የሰውነት ባሕርዩን የማሰብ ችሎታ እየተጠቀመ ነው፤ ስለዚህም የማኅበረሰቡ ጥፋት ከግለሰቡ ጥፋት ጋር የሚመሳሰለው በውጤቱ ብቻ ነው እንጂ በሌላ ነገር በምንም አይመሳሰሉም። ያለምንም ጥርጥር የማኅበረሰቡ ጥፋት ከግለሰቡ ጥፋት ጋር በሙሉ ሁኔታው ተመሳሳይ አይደለም። የማኅበረሰቡ ተግባር ቀጥታ በቀል ነው። አንድ ሰው ስላበደ ማኅበረሰቡ በአጠቃላይ ጨርቁን ጥሎ ይበድ ማለት ነው።

የግለሰቡ ጥፋት ማኅበረሰቡን ያጎድላል፤ ይጎዳል። የማኅበረሰቡም የበቀል እርምጃ ማኅበረሰቡን ያጎድላል፤ ይጎዳል። እንዲ ከመጎዳት ሁለቴ መጎዳትን የሚመርጥ ማኅበረሰብ የአእምሮና የመንፈስ የእድገት ደረጃው ከአራት ዘመን አልወጣም ማለት ነው። በበቀል እርምጃው ማኅበረሰቡ ምንም የሚጠቀመው ነገር የለም። የሞተ ሰው ገዳዩ ቢሞትለት የሚያገኘው ጥቅም የለም፤ እጁ የተቆረጠበት ሰው የቆራጩ እጅ ቢቆረጥለት የሚያገኘው ጥቅም የለም። አንዱን ጥፋት መልሶ መላልሶ በመፈጸም የመጀመሪያውን ጥፋት ማረም አይቻልም። ማንኛውም ማኅበረሰብ በግለሰቦች የሚፈጸሙ ጥፋቶችን ለመቆጣጠርና ለማረም ይፈልጋል፤ ተገቢም ነው። የአንድ ማኅበረሰብ መሠረት አስተማማኝ ሰላም ነው። ስለዚህም አጥፊዎች መቀጣት አለባቸው፤ ይህ አያከራክርም።

እንግዲህ ቅጣት ምን ማለት ነው? በመሠረቱ ቅጣት የበቀል ልጅ ነው። የበቀል ቅጣት ምን ዓይነት እንደሆነ በአራት ሕግ አይተነዋል። ከበቀል ፈጽሞ ነጻ የሆነ ቅጣት አይኖርም ይሆናል፤ ነገር ግን በቀሉን ቀንሶ መቅጣት የሚቻል ይመስለኛል። ለእኔ ቅጣት አጥፊው በማኅበረሰቡ ላይ የፈጸመውን በደል እንዲከሥና እንዲታረምም ማድረግ ነው። በአራታዊው በቀል ካሣም የለ፤ መታረምም የለ፤ በኪሳራ ላይ ኪሳራ ብቻ ነው። የሞተ ሰው ካሣ አይከፍልም፤ ከመታረምም ውጭ ነው። እጁንም ሆነ እግሩን የተቆረጠ ሰው፤ ወይንም ዓይኑ የጠፋበት ሰው ካሣ አይከፍልም፤ እንዲያውም የማኅበረሰቡ ሸክም ይሆናል፤ የሚታረመውስ እንዴት ነው?

ቅጣት አጥፊውን እያረመ ለማኅበረሰቡ ካሣ ማስከፈል ካልቻለ በቀል ብቻ ይሆናል። በምንም ዓይነት ጥፋት ይሁን ሰውን መግደል ቅጣት የማረሚያ ዘዴ ሊሆኝ አይችልም። ቅጣት ማረሚያ ከሆነ ሞት እንዴት ማረሚያ ይሆናል?



ለማንስ ቅጣት ይሆናል? በቅጣት ማረም የሚቻለው በሕይወት ያለን ሰው እንጂ የሚሞትን ሰው አይደለም። የሞተ ሰው ከቅጣት ተገላገለ ማለቱ ሳይሻል አይቀርም። ስለዚህም ለማኅበረሰቡ ካሣ የሚከፍልበት መንገድ የለም፡

ደግሞስ መግደል፤ የሰውን ሕይወት ማጥፋት ትክክል አይደለም ከተባለ በሕግ ስም መግደል እንዴት ትክክል ይሆናል? በማኅበረሰባችን ውስጥ የሚደረገውን ነገር በጥሞና ስትመረምሩት ይገርማል። ቄሱ «እግዚአብሔር ኃጢአትሽ እግዚአብሔር ይፍታ» ይላል፤ ዳኛው በበኩሉ «ዕድሜህ ይፍታህ» ብሎ ይፈርዳል። ምን ማለታቸው ነው? ቄሱ ከኃጢአት እስራት ፈትቼሃለሁ፤ ንጹሕ ነህ ማለታቸው ነው። ዳኛው ደግሞ ዕድሜህ አልቆ ስትሞት ነጻ ትሆናለህ ማለታቸው ነው። ሌላው ዳኛ ደግሞ ሌላውን ተከሳሽ «ይሙት፤በቃ፤» ብለው ይፈርዱበታል። ሞት የተፈረደበት ሰው ሲገደል ከወንጀሉ ነጻ ይሆናል? ወይስ ከነወንጀሉ ነው የሚሞተው? ሃይማኖት ያላችሁ ሰዎች ከሆናችሁ ደግሞ ሌላም ጥያቄ ማንሣት ትችላላችሁ፤ ተፈርዶበት የሞተው ሰው መንግሥተ ሰማያት ይገባል ወይስ ገሀነም? መንግሥተ ሰማያት ከገባ ኃጢአቱ ተሰርዮለታል (ከወንጀሉ ፀድቶአል) ማለት ነው፤ ገሀነም ከገባ ከነኃጢአቱ ወይም ከነወንጀሉ ነው ማለት ነው። ከነወንጀሉ ገሀነም ከገባ የሞት ቅጣቱ በእግዚአብሔር ዘንድ አልተቆጠረለትም ማለት ነው። ሞት የፈረደበት ዳኛስ መንግሥተ ሰማያት ይገባል? ወይስ ገሀነም? በእግዚአብሔር ሥራ ገብቼ የምዘባርቅ እንዳይመስላችሁ፤ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ፣ ከአሠርቱ ቃላት አንዱ የሆነውን፣ «አትግደል» የሚለውን መሠረት አድርጌ ነው የተነሣሁት። በግለሰብ ደረጃ አትግደል፤ በማኅበረሰብ ደረጃ ግን ግደል አላለም። እግዚአብሔር የሰጠውን ሕይወት መንሣት ለማንም አልተፈቀደም።

አንድ ማኅበረሰብ በአንድ ነፍስ ገዳይ አንድ ሰው ሲሞትበት ይደኸያል፤ ማኅበረሰቡ ተንከባክቦ ያሳደገው፣ ያበላውና ያጠጣው ነው፤ እውቀት ካለው እውቀቱ፣ እውቀትም ባይኖረው ጉልበቱ ለማኅበረሰቡ ይጠቅም ነበር፤ ተገደለ፤ ገዳዩ ደግሞ ሲገደል ማኅበረሰቡ ይበልጥ ይደኸያል። መግደል ጥቅሙ ምንድን ነው? ይልቅስ ገዳዩን በሕይወት አቆይቶ እንዲጸጸትና ጠባዩን እንዲያቃና አድርጎ እንደችሎታው በተለያዩ ሥራዎች ለማኅበረሰቡ ካሣ እንዲከፍል ቢደረግ የተሻለ አይሆንም ነበር? እንዲህ ለማሰብ ከበቀል ነጻ መሆን ያስፈልጋል።

ዕድሜ ልክ እስራት ቀላል ነገር አይደለም፤ ሁኔታዎች ከተመቻቹ እስረኛው ለኑሮው የሚያስፈልገውን ሁሉ በጉልበቱም ሆነ በእውቀቱ ለማምረት ይችላል። ከሥነ ጽሑፍና ፍልስፍና እስከ ጠበቃነት፣ በተለያዩ የእጅ ሙያዎችም በጣም የተራቀቁ እስረኞች በአውሮፓም በአሜሪካም አሉ። በአገራችንም ቢሆን ብዙ እስረኞች ብዙ ጠቃሚ ሙያዎችንና ቋንቋዎችን በቀድሞው አገዛዝ ዘመን ተምረዋል። በዚህም ምክንያት የማኅበረሰቡ ጠቃሚ አገልጋዮች በመሆን ለጥፋታቸው ካሣ ሊከፍሉ ይችላሉ፤ በቂ ቅጣት ነው።

የተለያዩ ወንጀሎች በተለያዩ መንገዶች በተለያዩ ግለሰቦችና ቡድኖች ይፈጸማሉ፡፡ ከሁሉም ይበልጥ የሚያስቅቀው ወንጀል ግን የመንግሥትን ሥልጣን በያዙ ድርጅቶችና ሰዎች የሚፈጸም ወንጀል መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ አንድ ሕዝብን በመሣሪያ ኃይል አስገብሮ የሚገዛ የመንግሥትን ሥልጣን ቢይዝም የሕዝብ ፈቃድ እስከሌለው ድረስ መንግሥት አይደለም፤ አገዛዝ ነው፡
በቅርቡ የጦር ሠራዊትና የፖሊስ መኮንኖች በግላቸው ሳይሆን በደርግ አገዛዝ ስር በተደለደሉበት መደበኛ ሥራቸው ለፈጸሙት ወንጀል ተፈርዶባቸዋል፤ በፍርድ ቤቱ ከተጠቀሱት ወንጀሎች የሚከተሉት ይገኙባቸዋል፤
ያለፍርድ የግድያ ውሳኔ ማስወሰን፣
በወቅቱ የነበረውን የፖለቲካ ሥርዓት በሚቃወሙት ሰዎች ላይ አሰቃቂ ምርመራዎች፣ ግድያዎች ማካሄድ፣
እጅግ ጭካኔ የተሞላበት አረመኔአዊ ምርመራ፣
ይህ ፍርድ በግድ አንዳንድ ጥያቄዎችን እንድናነሳ ያደርገናል፤
የጦር ኃይል መኮንን እንዴት ብሎ ነው ከሥራው ጋር በተያያዘ ሁኔታ በሕዝብ ላይ ወንጀል ሊፈጽም የሚችለው? የጦር ኃይሉ ዋና ዓላማ አገሩንና ሕዝቡን ከውጭ ጠላት ለመከላከል ነው፤ የውል የውጭ ጠላትን እንዲከላከልበት በአደራ የተሰጠውን መሣሪያና ሥልጣን እንዴት ብሎ ወደ ሰላማዊው ወገኑ አዙሮ ወንጀል ይፈጽምበታል? ይህ የሚሆነው የሕዝቡ ድምፅ በታፈነበትና የመንግሥት ሥርዓት ተገርስሶ የአምባገነን አገዛዝ በሰፈነበት ሥርዓት ብቻ ነው፤ በአምባገነን የአገዛዝ ሥርዓት የጦር ኃይሉ ለአገርና ለወገን የቆመ ሳይሆን ለአምባገነኑ መሣሪያ ሆኖ የሚያገለግል ነው፡፡ በአምባገነኑ የአገዛዝ ዘመን የአምባገነኑ ፈቃድ ከሕግ በላይ ስለሆነ የጦር ኃይሉ በአገሩና በሕዝቡ ላይ የሚፈጽመው ግፍ እንደወንጀል አይቆጠርም፤ እንዲያውም ለሹመትና ለሽልማት ያበቃ ይሆናል፡፡ ስለዚህም የአገዛዝ ሥርዓት ለአገርና ለወገን መከታ የቆሙትንም ቢሆን ወንጀል እንዲፈጽሙ ያደርጋቸዋል ማለት ነው፡፡
የፖሊስ መኮንኖችስ እንዴት ብለው በግላቸው ሳይሆን በሥራቸው በሕዝብ ላይ ወንጀል ሊፈጽሙ ይችላሉ? በመሠረቱ ፖሊስ ሕዝቡን ከወንጀለኞች የሚከላከል ሠራዊት ነው፤ ፖሊስ ራሱ ወንጀል የሚፈጽም ሲሆን ግን አንድ የተበላሸ ነገር አለ ማለት ነው፡፡ የተበላሸው ነገር የአገዛዝ ሥርዓት ነው፤ የአገዛዝ ሥርዓት የፖሊስን መሠረታዊ ተግባር ለውጦ የአምባገነን መሣሪያ ያደርገዋል፤ ይህ ሲሆን ወገን የነበረው ጠላት፣ ወንጀል ተከላካይ የነበረው ወንጀለኛ፣ ሕግ አስከባሪ የነበረው ሕግ አፍራሽ ይሆናል፡፡ የአምባገነኑን ተቃዋሚዎች ማሰር፣ ለምርመራ እየተባለ ማሰቃየትና መግደል የተለመደ ተግባር ይሆናል፡፡
ሌላም ጥያቄ አለ፤ እነዚህ የጦርና የፖሊስ መኮንኖች ዛሬ ወንጀል የተባለባቸውን ድርጊት በጊዜው ላለመፈጸም ምርጫ ነበራቸው ወይ? ምርጫቸው ሰዎችን መግደል ወይም እነሱ ራሳቸው ጸረ አብዮተኞች ተብለው መገደል ቢሆንስ? ይህ



ጥያቄ እነሱ የነበሩበትን ትክክለኛ ሁኔታ ለመረዳት ይረዳናል እንጂ ፈጸሙት ለተባለው ወንጀል ሰው በመሆናቸው፣ ዜጋ ወይም ወገን በመሆናቸውና የተማሩ መኮንኖች በመሆናቸው ያለባቸውን ኃላፊነት አይለውጠውም ይሆናል፡፡ ነገር ግን ስንት ሰው ነው ለሌሎች ሰዎች ሕይወት የራሱን ሕይወት ለመሰዋት ፈቃደኛ የሚሆነው ብለንም ራሳችንን ለመጠየቅ እንገደዳለን፡፡ አንድን ሰው ዝናብ ውስጥ እንዲቆም አስገድዶ ለምን ረጠብህ ማለት ይቻላል ወይ? ይህንን ሀሳብ ይበልጥ ለማፍታታት ከዚህ በፊት በብዙ ቦታዎች ያነሳሁትን አንድ ጥያቄ ላቅርብ፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ማንትስ «ይውደም!» ያላለና በቃላት ወንጀል ያልፈጸመ ስንት ሰው አለ? «ይውደም» ማለት ፍርድ መስጠት ከሆነ ፍርዱን የፈጸመው ከፈራጁ የሚለየው እንዴት ነው?
ከላይ የጠቀስሁት በጦርና በፖሊስ መኮንኖች ላይ የተሰጠው ፍርድ የሚያመለክተው የአገዛዝ ሥርዓት ምን ያህል የተበላሸና የሚያበላሽ መሆኑን ወለል አድርጎ የሚያሳይ ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች ወንጀል ፈጸሙ ተብለው ለአሥራ አራት ዓመታት በእስራት ሲሰቃዩ ቆይተው ሲፈረድባቸው፣ በወያኔ/ ኢሕአዴግ አገዛዝ ያሉት የጦርና የፖሊስ መኮንኖች ከዚህ ምንም ትምህርት ሳያገኙ በመሣሪያነት እያገለገሉ ወገናቸውን የሚጎዱና ወንጀል የሚፈጽሙ መኖራቸው የሚያሳዝን ነው፡፡

# ሦስት
# መግደልና ማስገደል
# ተንጋሎ የተፋ፣ ለራሱ ከፋ

መስፍን ወልደ ማርያም
ጥቅምት 1990

## 1. መግቢያ

የወንድምህ የደሙ ድምፅ ከምድር ወደ እኔ ይጮሃል። አሁንም የወንድምህን ደም ከእጅህ ለመቀበል አፍዋን በከፈተች በምድር ላይ አንተ የተረገምህ ነህ። ምድርንም ባረስህ ጊዜ እንግዲህ ኃይልዋን አትሰጥህም፤ በምድርም ላይ ኮብላይና ተቅበዝባዥ ትሆናለህ። (ኦሪት ዘፍጥረት 3/10 እስከ 13)

ባህላችን መግደልን ከወንድነትና ከጀግንነት ጋር ያገናኝ እንደነበረ የታወቀ ነው። ምንም እንኳን ‹ተራ ነፍሰ ገዳይ› ክብር ባይሰጠውም፣ ደም መላሽ የሚባለው ሌላው ገዳይ ሚስቱንና ወገኖቹን ያኮራና ያስከብር ነበር፤ አዝማሪዎችም ሰሙን ያወድሱ ነበር። ገዳይ የሚከበርበት ዘመን ቢያልፍም ከደርግ አገዛዝ ጀምሮ ግድያ ዋና ተግባር ሆኖ ቀጥሎአል። የሰው ሕይወት ምንም ዋጋ የሌለው እየሆን ነው።

መግደል የማይጠገነውንና የማይተካውን የሰው ሕይወት ማጥፋት ነው፤ ሰው በሰው ላይ ያለውን እምነት መናድ ነው፤ ሰው በማኅበረሰቡ፣ በአገሩና በወገኑ ላይ ያለውን አለኝታ ማጥፋት ነው፤ ሙዋቹና ቤተሰቡ ያላቸውን ተስፋ መቅጨት ነው፤ ማኅበራዊ ኑሮን በዱር አራዊት የደመ ነፍስ ጥርጣሬ፣ ስጋትና ፍርሃት መለወጥ ነው። ኅብረተሰቡ የተገነባበትን ካብ ማፍረስ ነው።

የተገደለውን ሰው ስናስብ ሰው መሆኑን ብንረሳም እያንዳንዱ ሰው የተከማቸ የኅብረተሰብ ሀብት መሆኑን መዘንጋት የለብንም፤ በማሕፀን ውስጥ ካለበት ጊዜ ጀምሮ ሙሉ ሰው እስኪሆን ድረስ በብዙ መንገድ የኅብረተሰቡ ጉልበት፣ እውቀትና ገንዘብ የተከማቸበት ሀብት ነው፤ ሰው ከመሆኑ ሌላ።

መግደል የገዳዩን አእምሮና ኅሊናም ያፈርሳል፤ ገዳይ ምን ጊዜም ቢሆን እየፈራና እየባነነ፣ እየሰጋና እየፈራ ይኸው ሁኔታው ደግሞ ጭካኔውን እያጠናከረለት መግደል እንደሱስ የሚሆንበት ደረጃ ላይ ይደርሳል። ስለዚህም ገዳይ በኅብረተሰቡ ላይ ጉዳትን የሚያደርሰው በሁለት መንገድ ነው፤ አንደኛው የተገደለውን ሰው ኅብረተሰቡ በማጣቱ፣ ሁለተኛው ገዳዩ ራሱ ኅብረተሰቡን በሚያፈርስ ተልእኮ በመሰማራቱ ኅብረተሰቡ እሱንም እንዳጣው በመቆጠሩ ነው።



አንዳንድ ተመራማሪዎች እንደሚሉት መግደል በሰው ውስጥ ከአውሬነት የቀረ ርዝራዥ ነው። አውሬዎች ሲገድሉ ተፈጥሮ የጣለባቸውን ግዴታ ለመወጣት ነው። የሚገድሉት የሚበሉትን ነው። ሰውን የሚገድል ሰው ቢመቸው የሰው ሥጋ አይበላም ለማለት አይቻልም። ምናልባት የሚያግዱት ሁለት ምክንያቶች ይሆናሉ፤ አንደኛ፣ አጠገቡ ያለውን ሌላ ገዳይ በመፍራት ሊሆን ይችላል፤ ሁለተኛ፣ የሰው ሥጋ ቀምሶ ባለማየቱ ሊሆን ይችላል። በህንድ አገር ኩማኦን በሚባል ቦታ በረሀብ ምክንያት ሰዎች በብዛት ስለሞቱና አስከሬናቸውን የሚያቃጥልም በመጥፋቱ በገደል ወረወሩአቸው። በአካባቢው የነበሩ የነብር ዓይነት አውሬዎች በድንገት የሰዎቹን ሬሳ ቀመሱና ጣፈጣቸው። ከዚያ በኋላ ሰው እያደኑ መብላት ጀመሩ፤ ስለዚህም ሰውን የሚገድሉ ሰዎች ቢመቻቸው የሰው ሥጋ ይበሉ ነበር ማለት ፈር የለቀቀ አስተሳሰብ አይደለም። ለመሆኑ ሰው ከመግደልና የሰውን ሥጋ ከመብላት የቱ ይከብዳል? ከመግደሉ ሞቶ ከተገኘ መብላቱ የቀለለ ሳይሆን የሚቀር አይመስለኝም። በችጋር ጊዜ በእኛው አገር እናት ልጅዋን፣ ባል ሚስቱን እንደበሉ ይነገራል። ያልገደሉትን የሰው ሥጋ ለመብላት የራበውና የተቸገረ ሰው መሆን ብቻ የሚበቃ ይመስለኛል። ሰውን ለመግደል ግን አውሬ፣ ያውም በድን አውሬ መሆንን ይጠይቃል።

## 2. የመግደል ምክንያቶች

መግደል ብዙ ምክንያቶች ሊኖሩት ይችላል። አገዳደሉ የሚያሳየውን የጭካኔ ዓይነት ትተን መግደልን ብቻ ስንመለከት ምናልባት በሰባት ደረጃ ለመከፈል እንችል ይሆናል። አንደኛ፣ በጦርነት ላይ መግደል አለ። በጦርነት ላይ መግደልን ልዩ የሚያደርገው ሁለት ወገኖች ለመጋደል ተዘጋጅተው፣ መሣሪያቸውን በየዓይነቱ ደርድረው መጋጠማቸው ነው። በሁለቱም በኩል የተሰለፉት ወታደሮች ለመግደል ያላቸውን ያህል ዕድል ለመገደልም አላቸው። በሁለቱም በኩል የተሰለፉት ወታደሮች ለመግደልም፣ ለመሞትም ይችላሉ። ጀግንነቱ የሚመነጨው ከዚህ እኩል ዕድል ነው፡

ሁለተኛው በፍርድ የሚፈጸም መግደል ነው፤ ዳኛው ይሙት ብሎ ይፈርዳል፤ ሌላው ደግሞ ይገድላል። ምንም አቅም የሌለውን ሰው በሥራው ጥፋት ወይም ስሕተት ምክንያት የሚፈጸም የኅብረተሰብ በቀል ነው። በኅብረተሰቡ ላይ አንድ ጥፋት በመደረጉ በበኩሉ ኅብረተሰቡ ያንኑ ጥፋት በቅጣት ስም ይፈጽማል። ይህ ሕጋዊ መግደል ይባላል። በሕግ የተደገፈ በቀል ነው። ሕጋዊ ጥፋት ነው።

ሦስተኛው በድንገትና በንዴት የሚፈጸም ግድያ ነው። አንድ ሰው በተለያዩ ምክንያቶች አእምሮውን ይስትና ሳያስበው የሰውን ሕይወት ያጠፋል። ኅብረተሰቡ፣ ሕጉ ይፋረደውና በሁለተኛው የተባለው ይደርስበት ይሆናል።

በኢትዮጵያ ባህል እንደዚህ ያለው የንዴት ግድያ አብዛኛውን ጊዜ በሦስት ምክንያቶች የሚፈጸም ነበር:: በመሬት፣ በሚስት፣ ወይም አጥንትን ይነካል በሚባል ስድብ ነበር ጨዋ የሚባለው በንዴት ሰውን የሚገድለው::

አራተኛው አስቦ፣ አቅዶና አድብቶ መግደል ነው:: መነሻው ምንም ይሁን ምንም ይህ ከከፋትና ከቂም የሚመነጭ ነው:: በግል ሲሆን ከፈሪነት ጋርም የተያያዘ ነው፤ በብዙ አገሮች ባህል ሰውን አድብቶ መግደል የሚጠላና እንደፈሪነት የሚቆጠር ነው፤ በተለይም ከኋላ መግደል::

አምስተኛው የመግደል ምክንያት የጭፍን እምነት ባሪያ መሆን ነው:: አሁን በብዙ አገሮች፣ በተለይም በአልጂርያ የሚደረገው ሴቶችና ሕፃናት ሳይቀሩ እንደከብት እያረዱ መጣል በዚህ ደረጃ የሚገባ ነው:: በእኛም አገር ቢሆን በአርባጉጉ የተፈጸመው ከዚህ የተለየ አይደለም:: የበደሉም አስከፊና የሚዘገንን ጭካኔ ያው ነው:: እንደዚህ ዓይነቱ እብደት የአንድ ሰው ሳይሆን የመላ ኅብረተሰቡ ነው::

ስድስተኛው በዘር ወይም በጎሣ ጥላቻ የተነሣ አንድ ኅብረተሰብን በሙሉ በሴትና በወንድ፣ በሕፃንና በሽማግሌና አሮጊት መሀከል ምንም ልዩነት ሳያደርጉ ጨርሶ ለማጥፋት የሚደረግ የመግደል ዘመቻ ነው፤ ጀርመኖች ይሁዲዎችን ለማጥፋት እንደሞከሩት፣ በሩዋንዳና በቡሩንዲ ቱትሲዎችና ሁቱዎች ለመጠፋፋት እንደሚሞከሩት፣በሶማልያ እርስበርስ እንደሚተላለቁ፣ በሌሎችም አገሮች እንደምንሰማውና እኛም በዝግጅት ላይ ያለንበት ከእንስሳት ደረጃ እንኳን የወረደ የጥፋት ተልእኮ ነው:: ይህም አጠቃላይ እብደት ነው::

ሰባተኛውና ከሁሉም የከፋው መግደል የመንግሥትን ሥልጣን የያዘ የፖለቲካ ቡድን በሕዝብ ሀብትና በውጭ እርዳታ ገዳዮችን እየመለመለና እያሠለጠነ፣ በሰፊው አስታጥቆ ሰላማዊውን ሰው ከየቤቱና ከየመንገዱ እያደኑ መጣል ነው:: ይህ ከከፋትም ከጭካኔም፣ ከእምነትም፣ ከጥላቻም ያልፋል:: ማናቸውንም ሰብአዊ፣ መንፈሳዊ፣ አምሮአዊና ማኅበራዊ ሚዛን ሁሉ አንኮታኩቶ የሚሰብር ነው:: እግዚአብሔር ያሳያችሁ፤ ሰላማዊው ሕዝብ ከወንጀለኞች ይጠብቁኛል ብሎ የሚተማመንባቸው መለዮ ለባሾች እነሱ ራሳቸው የተፈቀደላቸው ነፍሰ ገዳዮችና ወንጀለኞች ሆነው ሕይወቱን ሲያጠፉበት ምን ይባላል? የኅብረተሰቡ ሕጋዊ መሠረት ፈረሰ ማለት ነው:: እነዚህ ነፍሰ ገዳዮች ከሚገድሉት ሰው ጋር የግል ጠብ ያላቸውም፤ የእምነት ልዩነት ያላቸውም፤ ገዳዮቹ ራሳቸው ከተለያዩ ጎሣዎች የተውጣጡ ሊሆኑ ስለሚችሉ የጎሣ ጥላቻም አላቸው ለማለት አይቻልም:: ከሥልጣን ስስትና ከፍርሃት የመነጨ ጭካኔ ነው:: በኢትዮጵያ ባህል እስከደርግ ዘመን እንዲህ ዓይነቱ ግድያ የታወቀ አይመስለኝም::



## 3. ነፍሰ ገዳዮች

በሰባተኛው ምክንያት ሰውን የሚገድሉት ሰዎች በራሳቸው ፍላጎት ሳይሆን የሌሎች በድን መሣሪያ ሆነው ነው:: የማያስቡና የማይሰማቸው በድን መሣሪያዎች ለመሆናቸው ብዙ ማስረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል:: በመጀመሪያ መለዮ ሲለብሱ ትንሽም ቢሆን ስለሕግና ስለኃላፊነታቸው ይማራሉ፤ ሌላ ቢቀር በራዮና በጋዜጣ፣ እንዲሁ በወሬም ቢሆን የመማር ዕድል አላቸው፤ የሕዝብንና የአገርን ደኅንነት የሚጠብቁ የሕዝብ አገልጋዮች እንጂ የገዢዎቹ የግል አሽከሮች አለመሆናቸውን ያውቃሉ፤ በደርግ ዘመን እንደነሱ ሰዎችን ሲገድሉ ነበር የተባሉ ሁሉ ተለቅመው በየእስር ቤቱ ታጉረው ሲሰቃዩና ቤተሰቦቻቸውም ሲጨነቁ ያያሉ፤ በድን መሣሪያ ላልሆነ ሰው ይህ ሁሉ ያስተምራል፤ ያሳስባል::

እንኳን እነሱና እኛም የምናውቀው ሌላም አደጋ አለባቸው፤ የነፍሰ ገዳይ ዕድሜ አጭር ነው፤ ነፍሰ ገዳይ ጠላትን የሚያፈራው በሁለት በኩል ነው፤ አንደኛው በተገደለው ሰው ወገኖች በኩል ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ በአስገዳዩ በኩል ነው:: በተገደለው ሰው ወገኖች በኩል ያለው ቂም ግልጽ ነው፤ የአስገዳዩ ጥላቻ ግን ማብራሪያ ያስፈልገው ይሆናል:: አስገዳዩ ገዳዩን በጣም ይፈራዋል፤ ትእዛዙ ወይም ዋጋው ከፍ ከአለ ለገዳዩ እሱንም እንደማይምረው ያውቃል፤ በተጨማሪም የአስገዳዩን ትእዛዝ ሊያጋልጥና ሊመሰክርበት የሚችል ገዳዩ ነው፤ ስለዚህም ይህ ምስክር እንዳይኖር ማድረግ የአስገዳዮች የተለመደ ዘዴ ነው:: በደርግ ጊዜም ቢሆን ተደጋግሞ የታየ ነው፤ ዛሬ ገዳይ የነበረው ነገ ይገደላል፤ ነገ ገዳይ የሚሆነው ከነገ ወዲያ ይገደላል:: ወንጀለኞች ሁሉ የተጠቀሙበትን መሣሪያና ማስረጃ ማጥፋት ልማዳቸው ነው::

በአሜሪካ ውስጥ ሰውን መግደል ሥራቸውና ሙያቸው አድርገው የሚኖሩ ሰዎች አሉ፤ ነፍሰ ገዳዮች (ሂት ሜን) ይባላሉ:: የሚፈልጉትን ገንዘብ ካገኙ ማንንም ለመግደል ዝግጁ ናቸው:: እነዚህ ለአሜሪካ ፖሊሶች ራስ ምታቶች ናቸው:: በዚህ ዓይነቱ ሙያ የተሰማሩት የእኛ መለዮ ለባሾች ከነዚህ ነፍሰ ገዳዮች በምን ይለያሉ? የአሜሪካ ነፍሰ ገዳዮች ጨለማን ተገን አድርገው፣ ከሕጉ ጋር በይፋ ተጣልተውና ከሕግ ውጭ ሆነው፣ በሕጉ ላይ ሸፍተው ራሳቸውን የሚያስተዳድሩ ናቸው:: የኛዎቹ ለሕግ በሕግ የቆሙ፣ ሕዝብ በሚከፍላቸው ደመወዝ የሚተዳደሩና ይጠብቁናል ብሎ ኅብረተሰቡ ተስፋ የጣለባቸው ናቸው:: ትልቅ ግፍ የሚሆነውም በዚህ ምክንያት ነው::

ሰውን የማጥፋት ሱስ እንዲይዛቸው አድርጎ ነፍሰ ገዳዮችን ማሠልጠንና በኅብረተሰቡ ላይ ማሰማራት የመንፈሳዊውን ነገር እንኳን ችላ ብንለው በፖለቲካውም በኩል ቢሆን የማያዋጣ ዘዴ ነው:: የራስን ወገን ለአውሬ እንደመዳረግ የሚቆጠር ነው፤ አለዚያም ወገን መሆናቸውን መካድ ነው:: ከዚህም በላይ ኅብረተሰቡ በሕግ እንደማይተዳደር ግዙፍ ማስረጃ

መስጠት ነው፡፡ ሰውን እያደኑ መግደል የለመዱ ሰዎች የኅብረተሰብ ጠንቅ እንደሚሆኑ አያጠራጥርም፡፡

የአውሬ አደን የለመዱ ሰዎችን ተመልከቱ፤ ስፖርት ነው ይባላል፤ ግን ከክፋትና በራስ ከአለመተማመን በሽታ የሚመነጭ ሱስ ነው፡፡ ተኩሶ አውሬውን መምታትና ሲንፈራፈር ማየት ትልቅ ደስታን ያሳድርባቸዋል፡፡ ጤናማ ሰው በዚህ እንዴት ይደሰታል? ከአውሬ አደን ወደ ሰው አደን፣ ከአውሬ ገዳይነት ወደ ሰው ገዳይነት መሸጋገር በጣም ቀላል ይመስለኛል፤ ልዩነቱ ለሁለቱ አዳኞች የሚሰጣቸው የፈቃዱ ዓይነት ነው፡፡ ዋናው ነገር ሁለቱም የመግደል ሱስ አላቸው፤ አንዱ አውሬን፣ ሌላው ሰውን፡፡

ነፍሰ ገዳዮች በመሠረቱ በአእምሮ ህክምና ላይ መሆን ያለባቸው በሽተኞች ናቸው፡፡ የአራት ኪሎውን ነፍሰ ገዳይ (ግርማ የሚባለውን) እናስታውስ፤ የበደኖውን ጉድጓድ እናስታውስ፤ የአርባ ጉጉን ከአልጄሪያ ሁኔታ ጋር ተመሳሳይ የሆነ የማረድ ግድያ እናስታውስ፡፡ ይህ ሁሉ የበሽተኞች ሥራ ነው፡፡ ነፍሰ ገዳይ እሱ የሚወድደው ሰው የሌለው፣ እሱን የሚወድደው ሰው የሌለው፣ የኑሮ ተስፋው የተሟጠጠ፣ በራሱም ሆነ በሌሎች ሰዎች ምንም እምነት የሌለው፣ ልቡ ፍጹም ባዶ የሆነ በድን አካል ነው፡፡ ስለዚህ ቢገድልም፣ ቢሞትም ምንም ስሜት የለውም፡፡

እንግዲህ ትልቁ ጥያቄ፣- እንዴት አንድ ኅብረተሰብ ሆነ ብሎ በሽተኞችን እየመለመለና እያሠለጠነ የሚያጠፋውንና ለፍርሃትና ለስጋት የሚዳርገውን የገዳይ ቡድን ያደራጃል? ይህ የሚሆነው ከላይ እስከታች በሽታው ሲሰራጭና በተለይም ሥልጣንና ጥቅም ከበሽታው ጋር ሲቆራኝ ነው፡፡ የአንድ ኅብረተሰብ የመንፈስ ብክለት ልንለው እንችላለን፡፡

ገዳይና ተገዳይ ለአንድ ጊዜም ቢሆን ይገናኛሉ፤ ይገናኛሉ ማለት ይተያያሉ ማለት ላይሆን ይችላል፡፡ አንዳንድ ነፍሰ ገዳዮች የሚሠለጥኑት ከጀርባ ለመምታት ነው፡፡ በየአካባቢያችሁ የደረሱ አንዳንድ ግድያዎችን ብታስታውሱ አብዛኛዎቹ ከጀርባ በኩል የተመቱ ሆነው ታገኙአቸዋላችሁ፡፡ ይህ የሚሆንበት ዋናው ምክንያት የገዳዩን ተግባር በተቻለ መጠን ለማቃለልና በአእምሮው ተቀርጾ በሚቀረው የግድያ ስዕል ውስጥ የሙዋቹ ዓይኖች አይኖሩም፤ ሙዋቹም መጨረሻ ያየው ገዳዩን አይሆንም፡፡ ስለዚህም ገዳይ ሙዋች አላወቀኝም፤ አላየኝም፤ እያለ ራሱን ማታለል ይችላል፡፡

## 4. አስገዳዮች

አስገዳይና ተገዳይ ምናልባት በፍጹም ተያይተው አያውቁም ይሆናል፡፡ አስገዳይ ኢላማ የሚሆነውን ሰው የሚያውቀው በተለየ ሀሳቡ ወይም በተለየ እምነቱ ነው፤ ኢላማ የሚሆነው ሰው ከአስገዳዩ የተለየ ሀሳብ ወይም



የተለየ እምነት አለው፡፡ ተገዳዩ የያዘው ሀሳብ ወይም ቃል በአስገዳዩ የሚጠላ መሆኑን ያውቃል፡፡ ይህ የሚጠላ ቃል ኢድኅ፣ ኦነግ፣ መኢሕድ ሊሆን ይችላል፡፡ አስገዳዩ ችግር ያለበት ሰው መሆኑን ለመረዳት የሚያዳግት አይደለም፤ በመሠረቱ አስገዳዩ ለመግደል ወይም ለማጥፋት የሚፈልገው ቃሉን ወይም ሀሳቡን ነው፤ ያ ቃል ወይም ሀሳብ ደግሞ በእሱም በራሱ ማለት በአስገዳዩ ውስጥ አለ፡፡ ክርስቶስ ለምን ተሰቀለ? ጲላጦስ ‹የአይሁድ ንጉሥ ነህን?› ብሎ ሲጠይቀው፣ ‹አንተ ትላለህ፤› ብሎ መለሰለት፡፡ የክርስቶስ ወንጀል የተባለው ቃል ወይም ሀሳብ እንዲሰቀል አሳልፎ በሰጠው ሰው ውስጥ ነበረ ማለት ነው፡፡ ክርስቶስ ተሰቀለ፤ ቃሉ ለመለመ፤ አበበ፡፡ ሰዎች ተገደሉና ቃል ወይም ሀሳብ አይጠፋም፤ ይህ እውነት ባይሆን ኖሮ ክርስትናም ሆነ እስልምና በየተወለዱበት መንደራቸው ተቀብረው ይቀሩ ነበር፡፡ ቃልን መግደል አይቻልም፤ ቃልን መቅበር አይቻልም፡፡

አስገዳይ ሰውን ሲያስገድል ቃልን ያስገደለ እየመሰለው ነው፤ ሊገድለው ወይም ሊያጠፋው የሚሻው ቃል በራሱም አእምሮ ውስጥ መሽጎ እንደተቀመጠ አያውቅም፡፡ እንዲያውም የፍርሃቱ መነሻና ወደ ጥቃት የሚገፋፋው ብአእምሮው ውስጥ የመሸገውና ከሱ ጋር የማይዋደደው ቃል ነው፡፡ የሚፈራው ጠላት ሲያገኝ ጠላቱን ማኅደር አድርጎ እያቃጠለ መኖር የቃል ወይም የሀሳብ ልዩ ባሕርይ ነው፡፡ ቃልን በቃል ለመግጠምና ለማሸነፍ የአእምሮው ብቃት የሌለው ሰው የቃሉ ፈቃደኛ ማኅደር የመሰለውን ሰው በማስገደል ቃሉን የሚያጠፋው ይመስለዋል፡፡

በገዳዩ ውስጥ ሆኖ ቀንና ሌሊቱን በሙሉ እንደቆላ ቁስል የሚጠዘጥዘው ሀሳብ ሰዎችን በመግደል ይጠነክራል እንጂ አይሞትም፤ አንድ ሰው በሞተ ቁጥር ቢያንስ አንድ ቤተሰብ ለዚያ ሀሳብ ለመቆም በቂ ምክንያትን ያገኛል፤ ለተገደለው ሰው ያላቸው ፍቅርና ታማኝነት ያስገድዳቸዋል፡፡ አስገዳዩ ሊገድላቸው ከሚችላቸው ሰዎች ቁጥር በላይ በሕልሙና በእውኑ ተደርድረው ይታዩታል፡፡ የቆላ ቁስሉ ይበልጥ ይጠዘጥዘዋል፡፡ በሽታውና ፍርሃቱ ሌላ ዘዴ ስለማያሳውቁት መንገዶች ሁሉ በሰው ሬሳ እስኪሸፈኑና በሰው ደም እስኪጨቀዩ ያስገድላል፡፡ ይበልጥ በአስገደለ መጠን ይበልጥ አረመኔነቱንና ወንጀለኛነቱን እያረጋገጠ ለሚቃወመው ሀሳብ ወይም ቃል የበለጠ ጥንካሬን ይሰጣል፡፡ የአብዛኛው ሰው ልብ እየሸፈተበት ሲሄድ የቆላ ቁስሉ ይብስበታል፡፡ በደርግ ዘመን አንድ ለቅሶ ቤት ሰዎች በየአቅጣጫው ያዩትን የወጣቶች ሬሳ ያወራሉ፤ አንዲት አሮጊት ደረታቸውን እየመቱ «እግዚኦ! እግዚኦ!» አሉና ‹ጉድ ነውኮ የግዜር ሥራ! እነሱም ይገድላሉ ሥራ ሆኖባቸው፤ እግዜርም ሥራው ነውና መፍጠሩን ይቀጥላል፤ በየመንደሩ የሚወለደው ልጅኮ ብዛቱ!› አሉና በአሳቸው ፍልስፍና ደመደሙት፡፡ የተፈጥሮ ሕግ ነው፤ የጥቃት ኢላማ የሆነ ሁሉ የመራባት ኃይሉ በጣም ይጨምራል፡፡ አንዳንድ የዓሣ ዝርያዎች በዓመት

እስከ አምስት መቶ ሚልዮን እንቁላል ይጥላሉ:: በአንጻሩ ጎሪላ የሚባሉት ትላልቅ ዝንጀሮዎች በሁለት ዓመት አንድ ልጅ ብቻ ይኖራቸዋል:: የማጥፋት ተልእኮ ተፈጥሮን ራሱን የሚቃረን ነው::

አስገዳይ ከነፍስ ገዳይ የሚብስበት አንድ ነገር ያለ ይመስለኛል፤ አስገዳይ ፈሪ ነው:: እሱ ራሱ ሊያደርገው የማይፈልገውን ወይም የማይችለውን መጥፎና ርካሽ ተግባር ለማከናወን ከሱ ያነሰና ለሱ በድን መሣሪያ የሚሆነው ፍጹም ታዛዥ ፈልጎ ይጠቀምበታል:: እሱም በሁለት በኩል በፍርሃት ተሰንጎ ይኖራል፤ መኖር ከተባለ:: በአንድ በኩል የቆላ ቁስል ሆኖበት የሚያሰቃየው ሀሳብ ሰላምና እረፍት እንዳያገኝ ያደርገዋል፤ በሌላ በኩል ሌላ አስገዳይ ነፍስ ገዳዩን ወደሱ መቼ እንደሚልክበት እያሰበ ይባንናል:: ይወቀውም አይወቀውም፣ ይግባውም አይግባው የሕግ አለመከበር የሱንም የራሱን ኑሮ በስጋት ላይ ይጥላል::

## 5 መደምደሚያ

ከሰውነት ደረጃ ለወጣ ሰው ሰውን መግደልም ሆነ ማስገደል በጣም ቀላል ነው:: እንኳን ሰላማዊውን፣ ምንም የማይጠረጥረውን ሰውና በቂ የታጠቁ ጠባቂዎች ያሉአቸውም ሰዎችም ተገድለዋል:: ነፍስ ገዳይነትም ሆነ አስገዳይነት የወንጀለኛነትና የጸረ ኅብረተሰብነት ባሕርይ እንጂ ከጀግንነት ጋር የሚዛመድ አይደለም:: ከሁሉም በላይ ጀግንነት ሰው ሆኖ ለሰው መቆምን ይጠይቃል፤ ለሕይወት፣ ለጥንካሬ፣ ለእድገትና ለብልጽግና መቆምን ይጠይቃል:: ጀግንነት የክብርና የኩራት ጉዳይ ነው፤ በተለይም የወገን ክብርና የወገን ኩራት:: ነፍስ ገዳይነትና አስገዳይነት ክብርም ኩራትም የሌለበት የዕለት ሆድን የመሙላትና የተራ ወንጀለኛነት ተግባር ነው:: ለቤተሰቡ፣ በተለይ ለልጆቹ ውርደታቸውና ማፈሪያቸው ነው::

በማናቸውም መስፈሪያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጨዋና የሠለጠነ ነው:: እንዲህ ያለ ሕዝብ ሁሉ ለሚያውቃቸው፣ አስገዳዮችና ነፍስ ገዳዮች ግን የማያውቋቸው አራት ሚዛኖች አሉ:: የመጀመሪያውን ሚዛን የያዘው እግዚአብሔር ነው፤ በዚህ ሚዛን በጎና ክፉው፣ ጻድቅና ኃጥእ ገሀድ ይለያል:: በመጀመሪያው የዮሐንስ መልእክት (1/14-15) እንዲህ ይላል፤ ‹እኛ ወንድሞችን የምንወድ ስለሆንን ከሞት ወደ ሕይወት እንደተሻገርን እናውቃለን፤ ወንድሙን የማይወድ በሞት ይኖራል፤ ወንድሙን የሚጠላ ሁሉ ነፍስ ገዳይ ነው፤ ነፍስ ገዳይም የሆነ ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት በእርሱ እንዳይኖር ታውቃላችሁ::› ልብ በሉ፤ ዮሐንስ የሚያስተላልፈው ትክክለኛው የክርስቶስ መልእክት ነፍስ ገዳይ የሚለው ወንድሙን የሚጠላውን ነው፤ ወንድሙን የሚገድለውን ከዚያ በባሰ ደረጃ ይመድበዋል ማለት ነው::



ሁለተኛውን ሚዛን የያዘው ሕዝብ ነው፤ በዚህ ሚዛን እውነተኛውና ውሸታሙ፣ ትክክለኛውና አጭበርባሪው፣ ቁምነገረኛውና አበላ ባዩ ይለያሉ:: ይህ ሚዛን ይሉኝታም ይባላል:: ማንም ነፍስ ገዳይና ማንም አስገዳይ ከሕዝቡ ጋር በጠላትነት የቆመ ነው:: ይዋል ይደር እንጂ ሕዝቡ እነዚህን እሾሆች እየፈነቀለ ያወጣቸዋል::

ሦስተኛውን ሚዛን የያዘው ኅሊና ነው፤ በዚህ ሚዛን እያንዳንዱ ሰው ሌላውን ሰው ብቻ ሳይሆን ራሱንም የሚያውቅበት ችሎታ አለው:: ማንም ሰው ሲዋሽ ወይም ሲያታልል መጀመሪያ የኅሊናውን ሚዛን ሰብሮ ነው:: ለራሱ ሳይዋሽ ለሌላ መዋሸት አይችልም፤ ራሱን ሳያታልል ሌላውን ማታለል አይችልም:: በራሱ ሕይወት ላይ ሳይፈርድ በሌላ ሰው ሕይወት ላይ መፍረድ አይችልም::

አራተኛውን ሚዛን የያዘው ሕግ ነው:: ሕግ ጥፋት የተባሉትን ድርጊቶች ይለያል፤ ያጠፋውንም እንደየጥፋቱ እየለየ ይቀጣል::

ለማስረጃ ያህል፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጨዋና የሠለጠነ መሆኑን እንዳረጋገጠ ሁለት ምሳሌዎችን ልስጥ:: አንደኛ፣ ከ1966 የካቲት ጀምሮ እስከ 1968 መጀመሪያው ግድም ድረስ በኢትዮጵያ ውስጥ መንግሥት ነበረ ለማለት አይቻልም ነበር፤ የትርምስ ጊዜ ነበር:: እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ በእንዳዚህ ያለ ጊዜ ሰላም የሚሰፍንበት ሌላ አገር የለም ብዬ በድፍረት ለመናገር እችላለሁ:: በ1953ም ቢሆን ለጥቂት ቀናትም ቢሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ ጨዋነቱን አስመስክሮአል:: ይህንን ለመረዳት የፈለጉ በአውሮፓም ሆነ በአሜሪካ ትንሽ ጸጥታ ሲደፈርስ በሰውና በንብረት ላይ የሚደርሰውን ጥፋት ቆም ብለው ያስቡት፤ በአፍሪካማ በዙሪያችን ያየነውና የምናየው ነው::

ሁለተኛው ማስረጃዬ ኮሎኔል መንግሥቱ ተስፋ ወደ መቁረጡ ሲጠጉ ቢያንስ ሁለት ጊዜ ሕዝቡ ትግርኛ ተናጋሪዎችን እያደነ እንዲገድል የተሸፋፈነ ጥሪ አድርገው የከሸፈባቸው ነው:: እኔ ለሳቸውም መከራከሪያ በር ለመክፈት የተሸፋፈነ ልበለው እንጂ ለብዙ ሰው ግልጽ ሆኖ ተሰምቶታል፤ ከአልተሳሳትሁ ከተናገሩት አንዱ ዓረፍተ ነገር ‹ይህ ጦርነት በእያንዳንዱ ሰው ቤት ውስጥ መግባት አለበት፤› የሚል ነበር:: ምን እንደተፈለገ ለማሳየትም በደብረ ዘይትና በአዋሳ ሰዎች እየተገደሉ ተቀጥለው ነበር:: የኢትዮጵያ ሕዝብ የሰጠው ምላሽ ግን ዓይናችሁ ላፈር የሚልና እኩይ ጥሪውን ማጥላላት ነበር::

ይህ የኢትዮጵያ ሕዝብ መንፈሳዊ ሀብትና ቅርስ የሚያኮራውና የሚያስከብረው ሆኖ ቆይቶ ነበር:: በአለፉት ሃያ አራት ዓመታት ውስጥ የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ሀብት እየተሸረሸረ ነው:: ቶሎ ከነቃንና ከተባበርን መሸርሸሩን ልናቆመው እንችላለን:: አንድ የደረሰብኝን ነገር ልንገራችሁ፤ ወደዝርዝር ነገሩ ሳልገባ ከጥቂት ወራት በፊት መሸት ብሎአል፤ ጠመንጃ የያዙ ሰዎች አስቆሙኝ፤ ጠመንጃውን ወደኔ ደቅነው ዓይኖቹ ተጎልጉለው ወጥተዋል፤

ያጉረጠርጣቸዋል፤ ይጠይቀኛል፤ እመልስለታለሁ፤ ደግሞ ይጠይቀኛል፤ ደግሜ እመልስለታለሁ፤ ለብዙ ጊዜ እንደተሰበረ ሸክላ ያንኑ ተባባልን፡፡ በመጨረሻ ስማ አንተና እኔ ልንግባባ አልቻልንም፤ ሌላ ሰው ከአለ ውሰደኝ፤ ለማናቸውም አንተ ባለጌና ሥነ ሥርዓት የማታውቅ ነህ፤ የእኔ ትንሹ ልጄ ከአንተ ይበልጣል፤ ጠመንጃ ስለያዝህ ከሥርዓት ውጭ ሰውን ማንጉዋጠጥ ተገቢ አይደለም፤ ትራፊክ ፖሊስ እንዳንተ ጠመንጃ ሳይሸከም በፊሽካ ብቻ ያስቆመናል፤ ያንተን ጠመንጃ አልፈራም፤ አልኩት፡፡ ልጁ - (ልጅ ነው፤ ምናልባት ሃያ ወይም ሃያ ሁለት ቢሆነው ነው፤) ከዚያ በኋላ እርስዎ ይለኝ ጀመር፡፡ ዋናው ነጥቤ ይኸ ነው፡፡ ይህ ነፍጠኛ (ገዳይ እንዳልሆነ ተስፋ አለኝ) በኢትዮጵያዊነቱ የወረሰው ጨዋነት ተሙዋጥጦ አልጠፋበትም፤ በእንደዚያ ያለ ሁኔታ ውስጥ በአንድ አፍታ ታረመ፡፡ በጣም አስደነቀኝ፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ የደርግን የጭካኔ ዘመን ተሻግሮና የጭካኔውን ትምህርት አሻፈረኝ ብሎ አሳለፈና ዛሬ ለሌላ የጭካኔ ዘመንና ለሌላ የጭካኔ ትምህርት ተዳርጓል፡፡ በደርግ ዘመን የተጀመረው ግድያና ሬሣን በየመንገዱ ማጋደም አሁንም እየቀጠለ ነው፡፡ በአፍአዊ ወግና ሥርዓት እየተኩራሩና እየተመጻደቁ የሚወዳደሩት ቤተ ሃይማኖቶች ጆሮ ዳባ ልበስ ያሉ ይመስላሉ፤ የአንዳቸውም ድምፅ አይሰማም፡፡ ፍርሃት፣ ትዕቢትና ክህደት የተደባለቀበት የሐፍረት መለዮአቸውን ለብሰው ‹እኔ ወንድሜን ጠባቂ ነኝ እንዴ!› እያሉ የቃየንን ድምፅ የሚያስተጋቡ ይመስላል፡፡ በደርግ ዘመን ወሎዬዎች እግዚአብሔር አገሪቱን እንደራቃት ተረድተው ቢቸግራቸው አንጎራጉረው ነበር፡

*ቀና ብዬ ባየው ሰማዩ ራቀብኝ፤*
*አላህን ሰፈራ ወሰዱት መሰለኝ፡፡*

ሰውን እንደ አውሬ እያደኑ መጣል አገርን አያቀናም፡፡ በየመንገዱ የሰው ደምን በማፍሰስ ፍቅርን፣ መተማመንንና ተስፋን ለልጆቻችን ለማውረስ አንችልም፡፡ የሰው ደም ይጮሃል፤ እግዚአብሔርም፣ ሕዝብም፣ የነፍሰ ገዳዮችና የአስገዳዮች ልጆችም፣ ትውልድም ይሰማል፤ በትዕቢት ያዳፈንነውን የጨዋነትና የመንፈስ ሀብት እናውጣና እንታደስ፤ የነፍሰ ገዳዮችና የአስገዳዮች መንገድ ቁልቁለትና ክፉ ኮረኮንች ሆኖ የሚያመራውም ወደ እልም ያለ ገደል ነው፤ በዚያ በኮረኮንች ቁልቁለት በደም ጎርፍ ተግበስብሰን ወደ ገደሉ እንገባለን፤ ምን ዓይነት በሽታ የያዘው፣ ምን ዓይነት ዛር የሰፈረበት ሰው ነው ይህንን የደም መንገድ ለልጆቹ የሚመኝ፡፡



# አራት
# መላ ወይስ ዱላ

*መስፍን ወልደ ማርያም*
*መስከረም 1989*

## 1 መግቢያ

ዓላማዬ ሁለት ነው፤ አንዱ በገዢነትም ይሁን በተቃዋሚነት በሥልጣን ጉዳይ ተሰልፈው በአገር ውስጥም ሆነ በስደት ለሚታገሉት ኢትዮጵያውያን ወደኋላ እንዲመለከቱና የወደፊቱንም በዓይነ አእምሮአቸው እንዲቃኙ ለማበረታታት ነው፡፡ ሁለተኛው ኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በስደት ያሉትን ወጣቶች ራሳቸውን ከእሳት፣ ወላጆቻቸውን ከጸጸት እንዲያድኑ ለማስጠንቀቅ ነው፡፡ ያንኑ ስሕተት መደጋገም ከሞኝነት የባሰ ነው፡፡ መሠረታዊ የሆነ የማሰብ ችግር መኖሩን ያመለክታል፡፡
አሸንፈው ወንበሩ ላይ የተቀመጡት ሰዎች የተሸነፉት ትክክለኛ ቅጂ እንደሆኑ እያየን ነው፣ ሌሎች ደግሞ በዚያው መንገድ እነዚህን አሸንፈው የእነዚህ ትክክለኛ ቅጂ ለመሆን በዝግጅት ላይ ያሉ ይመስላል፡፡ ከአንድ ስሕተት ወደ ሌላ ስሕተት፤ ከአንድ ጉዳት ወደሌላ ጉዳት በፉከራና በሽለላ ለመረማመድ የሚሹ እየበረከቱ ነው፡፡ ለወጣቶቹ ልናስተላልፍላቸው የምንችለው ውርስ የጦርነት ማገዶነትን ሳይሆን የመንፈስ ጥንካሬንና መስዋዕትነትን ነው፡፡ ከፍርሃት ነጻ እንዲሆኑ ከፍርሃት ነጻ ሆነን እናስተምራቸው፡፡ ራሳችን የማናደርገውን ለወጣቶች ማስተላለፍ ኃላፊነት የጎደለው የመንፈስ ውርደትና ራስንም ሌሎችንም የማታለል አባዜ ነው፡፡
ታሪክን ማወቅ አንድ ነገር ነው፤ የታሪክን ጥቅም መረዳት ደግሞ ሌላ ነገር ነው፡፡ ታሪክን መሥራች ከሆኑት ሕዝቦች መሀከል የምንገኝ ብንሆንም የታሪክን ጥቅም ባለመረዳትና ታሪካችንን ባለማወቅ ተወዳዳሪ የሌለን ሳንሆን አንቀርም፡፡ አሁን ደግሞ ከዚያም አልፈን ታሪክን በመካድ ተወዳዳሪ የሌለን ሆነናል፡፡ በአንድ በኩል ድንቁርናን በሥልጣን እያጌጥን በልበ ሙሉነት ውሸትን በማራባት፣ በሌላ በኩል የእውነትን ኃይል በመፍራት፤በአንድ በኩል አስተሳሰብን ማጥራት የሚጠይቀውን ጭንቀት በመሸሽ በቀላሉና በሰፊው የመሀይም ጎዳና እየተንፈላሰሱ አፍ እንዳመጣ በመናገር አዋቂ በመምሰል፣ በሌላ በኩል ራስን በማታለል ለራሳችንና ለይተን ወገን ላደረግናቸው ስንል ድብብቆሽ በመጫወት ራሳችን በፈጠርነው ድፍን ጨለማ ውስጥ የምንተራመስ ሕዝብ

ሆነናል፡፡ ይህ ትርምስ ታሪክንና የታሪክን ጥቅም ካለማወቅ ብቻ ሳይሆን ኃላፊነትንም ለመሸሽ ከሚደረግ ጥረት የሚመነጭ ይመስለኛል፡፡

የታሪክ ዋና ጥቅሙ ያለፈው ትውልድ ባደረገው ጥሩ ነገር የሚከተለው ትውልድ እንዲኮራና ያለፈው ትውልድ ያደረገውንም ስሕተት አውቆና ተረድቶ ራሱን እንዲጠብቅ ለማድረግ ነው፡፡ እኛ ከአንድ ስሕተት ወደ ሌላ ስሕተት የምንረማመደውና ወደ ስሕተት አዘቅት የምናመራው ሁሉም ራሱን እያፀዳ በማሳየቱ ነው፡፡ የእኔ ትውልድ በአሸከርነትና በፍቅረ ንዋይ ምክንያት ፋይዳ ሳይሠራ እንደተዋረደ ሁሉ ከዚያ የሚቀጥለውም ትውልድ የራሱ ስሕተቶች ነበሩት፡፡ እነዚህ ስሕተቶች እየተድበሰበሱ ከታለፉ ለሚቀጥለውም ትውልድ ጠንቅ ስለሚሆኑ በግልጽ እንድንነጋገርባቸው ያስፈልጋል፡፡

ማሰብ የግል ሰብአዊ ባሕርይ ነው፡፡ የሰው ልጅ የተፈጥሮ ባሕርይ ቢሆንም በትምህርትና በልምድ የሚገራና የሚሳል ኃይል ነው፡፡ በትምህርት ላይ ባሉበት ጊዜ ከአስተማሪዎቻቸውና ከመጻሕፍት በሚቀስሙአቸው ሀሳቦች አእምሮአቸው እየዳበረ ተማሪዎች ማሰብ ይጀምራሉ፡፡ ለዚያውም ጥቂቶች ናቸው፡፡ አብዛኛው ማዕድ ላይ እንደቀረበ ሰው ያመጡለትን ተመግቦ የማሰብን ጭንቀት ሳያውቅ ተመርቆ የሚወጣ ነው፡፡ አንድ ተማሪ ማሰብ የሚጀምረው ከትምህርቱ የሚያገኛቸው ሀሳቦች ከአገሩ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር ያላቸውን የከፋ ቅራኔ መገንዘብ ሲጀምርና ለመፍትሔው አስተዋጽዖ ለማድረግ ለምን እንዲህ ይሆናል ለምን እንዲህ አይሆንም እያለ ጥያቄ ሲጠይቅና መፍጨርጨር ሲያሳይ ነው፡፡ ለዚህ የሚበቁ ብዙ አይደሉም፡፡ ሆኖም ቀደም ሲል በዩኒቨርሲቲ ኮሌጅና በኋላም በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ብዙ ተማሪዎች ነበሩ፡፡ እነዚህን ተማሪዎች አወዳቸዋለሁ፤ አከብራቸዋለሁ፤ እስከተወሰነ ደረጃም አብሬአቸው ተሰልፌአለሁ፡፡ ‹ፋኖ ተሰማራ› ማለት ሲጀምሩ ግን ማሰቡን እንዳቆሙ ተረድቼ ተለየኋቸው፡፡ በዚሁ ልጀምር፡፡

## 2 ፋኖ ተሰማራ

ወጣቶች ትምህርታቸውን አጠናቅቀው ሲወጡ ወዲያውኑ በኑሮ ጣጣ ይጠመዱና ሚስት ማግባት፣ ልጅ መውለድ፣ መሬት መግዛት፣ ቤት መሥራት ወዘተ በሚል የማኅበረሰቡ ግዴታና ውድድር ውስጥ ይገቡና አእምሮንና ኅሊናን ወደ ማስተኛቱ ይደርሳሉ፡፡ አእምሮንና ኅሊናን ያላስተኙ የሚመስሉት ደግሞ በአንድ በኩል በወጣትነት ትዕቢት በሌላ በኩል በቀላል የማርክሳዊ ሌኒናዊ የቃል ድግምት እንኳን የኢትዮጵያን የዓለምን ችግር ሁሉ ለመፍታት እንደሚችሉ ወደ እርግጠኛነት ደረጃ ላይ ደርሰው ነበር፡፡ እነዚህኞቹ ለአገራቸውና ለወገናቸው የነበራቸውን መቆርቆር መካድ አይቻልም፡፡ ነገር ግን ስሜታቸውን በይበልጥ የሚገፋፋው ለአገርና ለወገን ያላቸው መቆርቆር ይሁን



ወይስ የራሳቸው የሥልጣን ጥማት ሊነግሩን የሚችሉት እነሱ ናቸው፡፡ በበኩሌ ሁለቱ የተደባለቀባቸው ይመስለኛል፡፡

በተለይ ለዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ፋኖ ተሰማራ የሚለው መዝሙር ከሀሳብ የመነጨ ነው ለማለት አልችልም፡፡ ምንም ሀሳብ ካልተቀላቀለበት ስሜት የመነጨ ይመስለኛል፡፡ በመሠረቱ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የሚኖሩበት የአእምሮ ሥራንና የማሰብን ጭንቀት የሚማሩበት እንጂ የጉልበትና የጥፋት ተልእኮ የሚሰበከበት ዓለም አይደለም፡፡ እንዲያውም ሁለቱ ተልእኮዎች በቅራኔ የተጣመዱ ናቸው፡፡ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች መንገዱን የሳቱት ፋኖ ተሰማራ ማለት ሲጀምሩ ነበር፡፡ በአእምሮ ችሎታ፣ በሀሳብ ልዕልና፣ በመንፈስ ኃይል በልጠው በማሸነፍ ፋንታ ዝቅ ብለው የጡንቻውን መንገድ ተያያዙት፡፡ አእምሮም፣ መንፈስም እንዘጭ ብለው የወደቁት ያን ጊዜ ነው፡፡

በተጨማሪ የማርክሳዊና ሌኒናዊ ፍልስፍና ቅንጫቢ ለሁሉም ችግር የተዘጋጀ መፍትሔ ያለው መስሎ ስለታያቸው የማሰቡ ጭንቀት ጭራሹኑ ጠፋ፡፡ ይህ ትውልድ በአንድ ዓይነት ስሜት እየተገፋ እንደነበረ የሚያመለክተው በተለያዩ ስሞች የተመሠረቱትና በባላንጣነት ሲፋለሙ የነበሩት ሁሉ ማርክሳዊ ሌኒናዊ መሆናቸው ነው፡፡ ስለዚህም መከፋፈሉና ጠቡ ከፖለቲካ እምነት የመነጨ ሳይሆን ከሥልጣን ጥምም ነበር ለማለት ይቻላል፡፡

ሌላም ጥያቄ ለማንሣት እንገደዳለን፤ የአገርና የወገን ፍቅር በምን ደረጃ ላይ ነበር የማርክሳዊ ሌኒናዊ የፖለቲካ እምነትና የሥልጣን ጥም በአንድ በኩል፣ የአገርና የወገን ፍቅር በሌላ በኩል ምን ዓይነት ግንኙነት ነበራቸው? ወይም በሌላ መንገድ ያንኑ ጥያቄ ለማንሣት፣ ዓላማው የቱ ነበር? መሣሪያው የቱ ነበር? እነዚህ ጥያቄዎች ሊያስነሡ የሚችሉት ንዴትና ብስጭት ይሰማኛል፡፡ ነገር ግን ሊጠየቁና መልስ ሊያገኙ የሚገባቸው ጥያቄዎች ናቸው ብዬ አምናለሁ፡፡

የአገርና የወገን ፍቅር የሚገፋፋቸው ሰዎች ለአገርና ለወገን ብለው በሚያስቡትና በሚናገሩት፣ በሚጽፉትና በሚሠሩት ሁሉ ዋና ዓላማቸው አድርገው የሚመለከቱት አገርንና ወገንን ነው፡፡ ዓላማቸው አንድ ቢሆንም ለዚህ አንድ ዓላማ የተለያዩ ቡድኖች የተለያዩ ዘዴዎችና የተለያዩ መንገዶች ይቀይሱ ይሆናል፡፡ እንግዲህ በዘዴ ቢለያዩም ሁሉም በአንድ ዓላማ ስር ያሉና ለዚያው ዓላማ የሚገዙ ናቸው ማለት ነው፡፡ ይህ እውነት ከሆነ አንዱ የሌላው ጠላት ሆኖ ወደ መጋደል ደረጃ የሚደርሱት ለምንድን ነው? አገርና ወገን ማለት እነዚያን የሚገዳደሉትንም ሰዎች ይጨምራል፡፡ በሚሞቱትም ሰዎች መጠን አገርና ወገን ይጎዳል፡፡ በሚቃጠለውም ንብረት መጠን አገርና ወገን ይቸገራል፡፡ በእኔ አስተያየት ወደ መገዳደል ደረጃ የሚደርሱት ዓላማቸውን ሲስቱ ነው፡፡

የሥልጣን ትግሉ አንድ ደረጃ ላይ ሲደርስ ከመነሻው የአገርና የወገን ዓላማ የሥልጣን አምሮት በልጦና ጎልቶ ይታያል፡፡ በዚህ ሁኔታ የሥልጣን አምሮታቸው የበረታባቸው ሰዎች አገርንና ወገንን ከዋና ዓላማነት ሽረውና አውርደው የራሳቸውን የሥልጣን አምሮት ወደ ዓላማነት ከፍ ያደርጉታል፡፡ ነገሩ ሁሉ ተለዋወጠ ማለት ነው፤ አገርና ወገን ዓላማ መሆኑ ቀርቶ መሣሪያ ይሆናል፤ የሥልጣን አምሮት ዋና ዓላማ ይሆንና አገርንና ወገንን መሣሪያ አድርጎ የወገንን ደም እየጠጣና የወገንን ሕይወት እየበላ ይፋፋል፤ ይደረጃል፡፡ በትንንሽ ልጆች ሕይወት የሥልጣን ጥማቸውን ያረካሉ፡፡ ይህ አንዱና መሠረታዊው ዓላማን የመሳት መግለጫ ነው፡፡ የአገር ዓላማ በግል ዓላማ መተካቱ ብቻ ሳይሆን፣ የአገር ዓላማ ለግል ዓላማ ማረማመጃ መሣሪያ ይሆናል፤ ይህ ያየነውና የምናየው ነው፡

በአንድ ትውልድ ውስጥ ያሉ ሰዎች የሥልጣን አምሮታቸውን ለማርካት እርስበርሳቸው ተጫረሱ፤ በመሣሪያነት የተጠቀሙበትን ከነሱ በታች ያለውንም ትውልድ አጫረሱት፡፡ ይህ ከአገር ዓላማ የሚመነጭ አይደለም፡፡ የአገር ዓላማ በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ የጋራ ነው፤ የሥልጣን አምሮት ግን የግል ወይም የትንሽ ቡድን ነው፡፡ ትሮትስኪ የሚባለው የሌኒን ጉዋደኛ እንዳለው አጠቃላዩ የፖለቲካ ቡድኑ በድርጅቱ ይተካል፤ ድርጅቱ ደግሞ በማዕከላዊ ኮሚቴው ይተካል፤ ማዕከላዊው ኮሚቴ በፖሊትቢሮው ይተካል፤ በመጨረሻ ፖሊትቢሮው በፈላጭ ቆራጩ አምባገነን ይተካል (በቃሌ ነው የምጠቅሰው)፡፡

የእኛም ወጣቶች በሥልጣን አምሮት የተነሣ ከባላንጣ ቡድኖች ጋር በትጥቅ ትግል ከመፋለማቸው በፊት በእያንዳንዱ ቡድን ውስጥ በሥልጣን ትግልና ፉክክር ተጋድለዋል፤ አጋድለዋል፡፡ ከዚያም ባላንጣ ከሚሉአቸው ጋር ተጋድለዋል፡፡ ቁጥራቸው በውል ያልታወቀ በሺህ የሚቆጠሩ ወጣቶች አልቀዋል፤ ተላልቀዋል፡፡ ለማን ሲሉ ሞቱ? ለምን ዓላማ ሞቱ? ለአገርና ለወገን? ወይስ ለጥቂቶች መሪዎቻቸው የሥልጣን አምሮት? በማናቸውም በኩል የሞቱት አላሸነፉም፤ በማናቸውም በኩል የቆሰሉትና አካለ ጎደሎ የሆኑት አላሸነፉም፤ አልተጠቀሙም፤ በማናቸውም በኩል የተሰደዱት አላሸነፉም፤ አልተጠቀሙም፤ በጠመንጃ አፈሙዝ በሥልጣን ኮርቻ ላይ የወጡትና የሕዝብን የሥልጣን ባለቤትነት ረግጠው የሚገዙትና ይህንኑ ዓይነት የሥልጣን አምሮት ለማርካት የሚያኮበኩቡት ሁሉ በሌጋ የወገን ሕይወት የተጫወቱና የሚጫወቱ ናቸው፡፡ ለአገርና ለወገን መቆማቸውን የሚያጠራጥር ሌላም ማስረጃ አለ፤ የማርክሳዊ ሌኒናዊ የፖሊቲካ እምነታቸው ከአገርና ከወገን ይበልጥባቸው እንደነበረ የታወቀ ይመስለኛል፡፡ ነገሩን ለመጀመር ያህል በ1967 ይመስለኛል የኢትዮጵያ ኅብረተሰባዊነት (ሶሺያሊዝም) ሲታወጅ፣ የእኛ ወጣቶች ተበሳጭተው ነበር፤ የኢትዮጵያ ኅብረተሰባዊነት የሚሉት ነገር ከየት የመጣ ነው! እንዲህ ያለ ነገር



ተሰምቶም አይታወቅ! እየተባለ መሳለቂያ ሆኖ ነበር፤ የማርክሳዊ ሌሊናዊ እምነት አለን የሚሉ ሁሉ የኢትዮጵያ ጥቅም ወይም የአገር ጥቅም የሚባል ነገር መስማት አይፈልጉም ነበር፤ ለእነሱ ዋናው ጉዳይ የአገር ጥቅም ሳይሆን ወዛደራዊ ዓለም አቀፍነት ነበር፤ ለዚህ ነበር በደርግ ዘመን አገር ወዳድ የሚሉትን ኢትዮጵያዊ እንደየዋህ መሀይም ይመለከቱት የነበረው፤ አሁንም አቶ መለስ ሰንደቅ ዓላማውን ጨርቅ ሲሉ፣ ወይም አቶ ዳዊት ኢትዮጵያ የምትባል አገር የለችም አሉ ሲባል (ሲሉም ሆነ ሲያስተባብሉ እኔ አልሰማሁም)፣ ያንኑ የማርክሳዊ ሌኒናዊ ጥራዝ ነጠቅነት ቅኝት የሚያመለክት ነው፤ እምነታቸው፣ አገር ማለት ዓለም በሙሉ ነው፤ ወገን የዓለም ወዛደር በሙሉ ነው፤ የሚል ነበር፡

በሥልጣን አምሮት ማየል የተነሣ አገርና ወገን ዋና ግብ መሆናቸው ቀርቶ የሥልጣን መቆናጠጫ መሣሪያ እንደሆኑ ሁሉ በማርክሳዊ ሌኒናዊ የጥራዝ ነጠቆች እምነትም የተነሣ የፖሊቲካ እምነቱ ወደ ዋና ግብነት ተለውጠ አገርና ወገን የዚህ እምነት ማጠናከሪያ መሣሪያ ብቻ ተደረጉ፤ የማርክሳዊ ሌኒናዊ የፖሊቲካ እምነት ራሱ ለሥልጣን አምሮት አገልጋይነቱ የተፈተነ ነው፤ በተለይ ሌኒናዊው ክፍል ሌላ ጥቅም የለውም ለማለት ይቻላል፤ ተፈላጊነቱ ጸጥ፣ ለጥ አድርጎ ያለጥያቄና ያለማጉረምረም አፍኖ ለመግዛት ነው፤ የሥልጣን አምሮት ከሌኒናዊ እምነት ጋር ሲጋባ ጨካኝና ለሰው ሕይወት ደንታ የሌለው ይሆናል፤ ለሥልጣን አምሮት ወይም ለፖሊቲካ እምነት መግደል አብዮታዊ ጀግንነት ነው፤ የሥልጣን አምሮታቸው መሞትን የማይፈቅድላቸው መሪዎች ጀሌውን ታጋይ ይሞታል እንጂ ትግል አይሞትም እያሉ ያደፋፍሩታል፤ ሞትን የሚያናንቁና ሌሎችን ለሞት የሚጋብዙ ሁሉ ለራሳቸው ሞትን አጥብቀው ይፈሩታል፡፡

በተግባር በሚገልጸውና በሚያሳየው ሁሉ እኛን ለመጠበቅ እናንተ ሙቱ፣ እኛን ለማስከበር እናንተ ተዋረዱ፣ እኛን ለማበልጸግ እናንተ ደህዩ የሚል ቡድን የመንፈስ ጉድለት አለበት፤ እዚህ መደምደሚያ ላይ ለመድረስ የምንችለው የሁሉም ሰው ሕይወት እኩል ነው፤ በማናቸውም ዓይነት ሚዛን ቢለካ የማንም ሕይወት ከማንም ሕይወት አይበልጥም፤ የሚል እምነት መነሻ ስናደርግ ነው፤ ይህ የእምነት መነሻ ከሌለን፣ የሁሉም ሰው ሕይወት ለራሱና ለዘመዶቹ ውድና ክቡር መሆኑን ካልተቀበልን መንፈሳዊ ጉድለት አለብን ማለት ነው፤ የሰውን ልጅ፣ ያውም ገና ወጣቱንና ጨቅላውን የራሱ የሆነ ዓላማ እንደሌለው ግዑዝ ነገር ተመልክተነው ለእኛ ዓላማ በድን መሣሪያ ማድረግ መንፈሳዊ ችግርን ያመለክታል፤ ፖሊቲካም ሆነ ሕግ የተበላሸ መሆኑን ከአውሮፓና ከእኛም የቅርብ ታሪክ መገንዘብ የሚያዳግት አይደለም፡

እኛ እንድንኖር እናንተ ሙቱ ማለት ከአፍንጫ በማይርቅ አስተሳሰብ ላይ የተመሠረተ ነው፤ የማንም ሰው ሕይወት የተወሰነ ነው፤ ለዘለዓለም

የሚኖር የለም፤ አሞኝቶ ያስገደለውም ተሞኝቶ እንደሞተው አፈር ይሆናል፤ ከሞት በኋላ ሁለት ነገሮች ይቀራሉ - ልጆች ያፍራሉ፤ እኔ ከሞትሁ ሰርዶ አይብቀል ያለችው አህያ እንደሆነችም እናውቃለን፤ ለራሱ ልጆችና ዘመዶች የማያስብ ሰው ፖሊቲካ ውስጥ ምን አስገባው ፖሊቲካ ለሰዎችና ለታሪክ ሲባል የሚገቡበት ተግባር ነው፤ ራስን ለማድለብማ ብዙ ሌላ ሥራ ሞልቶአል፤ ታሪክ የነዚያን ስም አያነሣም፡፡

አንዱ ቡድን ከሱ በኩል የሞቱትን የኢትዮጵያ ሰማዕታት ሲያደርጋቸው፣ ገዳዩን ቡድን የኢትዮጵያ ጠላቶች ያደርጋቸዋል፤ ሌላው በበኩሉ ከራሱ ቡድን የሞቱትን ሰማዕታት አድርጎ ገዳዮቹን የኢትዮጵያ ጠላት ያደርጋቸዋል፡፡ እያንዳንዱ ቡድን የየራሱን ሙዋቾች ‹ሕይወታቸውን መስዋዕት ያደረጉ ጀግኖች› ሲያደርግ በእያንዳንዱ የተገደሉት ደግሞ ማንንም የማያጎዱ ትርፍና ግዑዝ ነገሮች እንደሆኑ አድርገው የሚያቀርቡአቸው ይመስላል፤ የተጋደሉት ቡድኖች ሁለት ብቻ አይደሉም፤ ሁሉም ራሳቸውን የማይጠይቁት አንድ ጥያቄ አለ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብስ ምን ያስባል? ምን ይላል? በሁሉም በኩል ልጆቻቸው የሞቱባቸው እናቶች ምን ይላሉ? የተጋደሉት ቡድኖች ሁሉ ይህንን ጥያቄ የማያነሡበት ምክንያት አላቸው፡፡ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚበጀውን ሁሉ የሚያውቁና በጎውንና ክፉውን የሚወስኑለት እነሱ ብቻ መሆናቸውን እያንዳንዱ ቡድን ያለማወላወል ስለሚያምን ነው፡፡

ፉኖ ተሰማራ መዝሙር ሆኖ አልቀረም፤ በእርግጥም ፉኖ ተሰማራ፡፡ በከተማው ውስጥ መጋደል የተዳከሙት ቡድኖች በግድ ወደጫካ እንዲገቡ ተገደዱ፡፡ ጫካም ከገቡ በኋላ ጫካ ከገቡት ውስጥ የተለያዩ ቡድኖች ተፈጥረው በነዚህ ቡድኖች መሀከል መጋደል አልቀረም፡፡ ከነዚህም ውስጥ ያሸነፉት ገዢዎች፣ የተሸነፉት ደግሞ የአሸናፊው ሎሌዎች ወይም ስደተኞች ሆነዋል፡፡ የፉኖ ተሰማራ የመጨረሻው ውጤት አሁን ያለው የአገዛዝ ሥርዓትና አሁንም ያልቆመው የስደት ባህል ነው፡፡ ምናልባትም የኢትዮጵያ ደኖች ተመንጥረው ስላለቁ የፉኖዎች መሰማሪያ አሜሪካና አውሮፓ ሆነዋል ለማለትም ይቻል ይሆናል፡፡

የፉኖ ተሰማራ ውጤት ከዚህም አልፎ የኢትዮጵያን ህልውና ከፉኛ እየተፈታተነ መሆኑን በተግባር እያየነው ነው፡፡ መጨረሻውን ገና አላየንም፡፡

ከፉኖ ተሰማራ የፈለቀ ሌላ ችግርም አለ፤ በጦር ሜዳ የበለጡትና ያሸነፉት ድሉን የሕዝብ ሳይሆን የግላቸው አድርገውት እንደወርቅ የጠራ አምባገነንነትና ዘረኛነት፣ በገሀድ ከሚታይ የሀብት ስግብግብነት ጋር ስልታቸው ሆኖአል፡፡ በዱላ ያገኙትን የሕዝብ ሥልጣን በመላ ለሕዝቡ የሚመልሱበት ሁኔታ ለማመቻቸት ፍላጎቱም ሆነ ችሎታው ያላቸው አይመስልም፡፡ ስለዚህም የተበለጡትና የተሸነፉት የሕዝቡን ሥልጣን ለማግኘት የሚሹት በመላ ሳይሆን በዱላ ነው፡፡ መላው የፖሊቲካ ትግል ነው፤ ዱላው የጦርነት ትግል ነው፡፡



እንግዲህ የፉኖ ተሰማራ ጥሪ ገና አላበቃም ማለት ነው፡፡ ለገዢዎችም ሆነ ለተቀናቃኞቻቸው ሁልጊዜም ምርጫው ከመላ ይልቅ ዱላ እስከሆነ ድረስ ፉኖ ተሰማራ ዘለዓለማዊና የማያቋርጥ ጥሪ ይሆናል፡፡ ፉኖ ተሰማራ ባህል ሆኖ ይተከላል ማለት ነው፡፡

ፉኖ ተሰማራ ወደጠብና ወደጫካ፣ ወደመገዳደልና ወደጥፋት የሚያመራ መንገድ ነው፡፡ የመላ ሳይሆን የዱላ መፍትሔን የመረጠ ነው፡፡ እድገትና ብልጽግና፣ የተረጋጋና አስተማማኝ ኑሮ ለማካሄድ የማያስችል ምርጫ ነው፡፡

## 3 መላ መላ ሌላው አማራጭ

ሌላው አማራጭ በአብዛኛው የአገዛዝ ሥርዓቱን በሚመሩት ሰዎች እጅ ነው፡፡ እነሱ ለጊዜው በአላቸው ዱላና በዱላ አቀባዮቻቸው ተማምነው የሰላማዊውን ትግል በር ሁሉ ከቆለፉት፣ ተቀናቃኞቻቸው ለመከላከል ዱላ እንዲያነሱ ምክንያት ይሆናሉ፡፡ የሰው ልጅ በአጠቃላይ፣ እኛ ደግሞ በተለይ የደረስንበት የመንፈሳዊ ደረጃ እያሰብንና መላ እየፈጠርን ችግሮችን በውይይት ከመፍታት ይልቅ በስሜትና በጉልበት የምንተማመንበት ላይ ነን፡፡

በብዙ መንገድ የእኛ የሥልጣን ጥመኞች ከአረቦችና ከእሥራኤላውያን ጋር በጣም ይመሳሰላሉ፡፡ ሁለቱም ወገኖች የሚንቀሳቀሱት በእልህ ነው፤ አንዱ ከሌላው ጋር ለመግባባትና ለመቀራረብ ሳይሆን ደፍጥጦ ለማሸነፍ፡፡ መላ መፈለጉ አቅቶአቸው በዱላ ሲጋደሉ ይኸው ስድሳ ዓመታት ሊያስቆጥሩ ነው፡፡ በሁለቱም በኩል የወደመው ንብረት፣ የጠፋው የሰው ሕይወትና የፈሰሰው እንባ፣ የተጓደለው እድገት በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ እሥራኤላውያን የፍልስጥኤማውያንን መብት መቀበልና ማክበር እንዳይችሉ አድርጎአቸዋል፡፡ ሁለቱም ወገኖች በቀላሉ የተውሶ ጡንቻ የማግኘት ዕድል ባይኖራቸው በእርግጥ ጉዳታቸው ያነሰ ይሆን ነበር፤ ምናልባትም መላ ለመፈለግ ይገደዱ ነበር፡፡ እንዲሁም በአየርላንድ በካቶሊኮችና በፕሮቴስታንቶች መሀከል ያለው የማይበርድ እሳት ትውልዶችን አስቆጥሮአል፡፡

የፍልስጥኤማውያንንና የእሥራኤላውያንን፣ እንዲሁም የአየርላንድን ቅጥና መላ ያጣ መፋጀት ያነሣሁት ለሁለት ምክንያቶች ነው፡፡ አንደኛ፣ ጥላቻ ስር ከሰደደና ከሁለት ትውልዶች በላይ በዚያ ጥላቻ ውስጥ ከአደጉ ተነጋግሮ መላ ለመፈለግ በጣም የሚያዳግት መሆኑን ለመጠቆም ነው፡፡ ሁለተኛ፣ የተውሶ ጡንቻ አጉልና የማያዛልቅ ትዕቢት ስለሚያስከትል ይህ በገባበት መጠን ለችግሩ መላ እንዳይፈለግለት አስተዋጽዖ ማድረጉን ለማመልከት ነው፡፡ እልቂቱና ጉዳቱ ሙሉ በሙሉ የተፋላሚዎቹ ነው፡፡

መላ የሚገኘው ከመነጋገር ነው:: ስለመነጋገር ብዙ ሰዎች የማይገነዘቡት አንድ ነገር አለ፤ መነጋገር ትርፋማ የሚሆነው በሀሳብ ከሚለይ ሰው ጋር ሲሆን ነው:: በሀሳብ ከሚስማማ ሰው ጋር መነጋገሩ ዋጋ የለውም፤ ራስን በሌላ ድምፅ ለመስማት ካልሆነ በቀር:: አንድ ሰው ማሰብ የሚጀምረውም ተቃዋሚ ሀሳብ ሲገጥመው ነው:: አብረው የሚኖሩ ሰዎች በመሀከላቸው ምንም ያህል የከረረ ቅራኔ ቢኖራቸውም ቢያንስ ለመነጋገር ፈቃደኛ መሆን አለባቸው:: የግል ቅራኔዎችና ጠቦች በሕግ ይፈታሉ ብለን እናምናለን:: ነገር ግን ሕጉ አድላዊ ነው ብለው የሚያምኑና ዳኞችና ፖሊሶች የአንድ ቡድን ታማኝ አገልጋዮች ናቸው ብለው የሚያምኑ አብዛኛዎች ሰዎች በሚገኙበት ሁኔታ መተማመን ይፈርሳል:: በዚህም ምክንያት የፋኖ ተሰማራ ጥሪ ተበደልን ለሚሉ ሁሉ ሁኔታውን ማረሚያ መስሎ ይታያል:: እንደማያርመው ግን እየየን ነው፤ በዱላ መግዛት የማያዛልቅ መሆኑንም አይተናል፤ በአህጉራችንም በሙሉ እያየን ነው::
ስለዚህም አገዛዙ ራሱን ለማረምና ለመለወጥ ወደሚችል መንግሥት መለወጥ አለበት:: ይህንን ለማድረግ የሚያስፈልገው አገሩ የሁላችንም መሆኑን ከመገንዘብ ጋር በጎ ፈቃድና ቆራጥነት ነው:: ሕዝቡ ቢተላለቅ፣ ሕዝቡ ቢደኸይና አገር ቢዋረድ የሚጠቀም ዜጋ የለም:: ለዚህ ነው የአገዛዙ ሥርዓት መሪዎች በጎ ፈቃድንና ቆራጥነትን ማሳየት ያለባቸው:: ትልቅነት የሚመጣው ዱላን ጥሎ ዱላ ለመምዘዝ የሚዘጋጀውን በበጎ ፈቃድና በቆራጥነት ግንባር ለግንባር በመግጠም ነው:: የግብፁ ሳዳት ስተት ብለው ኢየሩሳሌም ሲገቡ፣ የደቡብ አፍሪካው ደ ክለርክ ማንዴላን ከስር ለቅቀው ተወዳዳሪያቸው ሲያደርጉ ሁለቱም ያሳዩት በጎ ፈቃድና ቆራጥነት ትንሽነት የገዢዎች ባሕርይ በሆነበት አህጉር ትልቅነትን አጎናጸፋቸው:: ከገዢዎቻችን በኩል የሚጠበቀው በጎ ፈቃድንና ቆራጥነትን የሚያሳይ የትልቅነት ተግባር ነው:: ልጆቻቸውና የልጅ ልጆቻቸው ኮርተው የሚኖሩበት አገር መገንባት የሚችሉት በዚህ መንገድ ብቻ ነው:: ከአንድ ሰው ጋር ስለአፍሪካ አምባገነኖች ስንነጋገር በቅርቡ የተፈጸመ የትልቅነትና የትንሽነት መግለጫ ለምሳሌ ጠቀሰልኝ፤ ሞቡቱ ለሠላሳ ዓመታት ያህል ዛይርን ገዝቶ በሰው አገር ሞተና ሃምሳ ሰዎች ያህል ቀበሩት:: አማሆይ ቴሬዛ በሰው አገር ሄደው ለሰው አገር ድሆች ሲሠሩ ኖረው የህንድ መንግሥትና ሕዝብ እንደ አንድ ተወዳጅ መሪ አድርጎ በትልቅ ማዕርግ ቀበራቸው:: ትልቅነትም ሆነ ትንሽነት በሞትም ይከተላል::

ይህንን የትልቅነትንና የታሪክ ሠሪነትን መንገድ መማር የሚችለው ከታሪክ ነው:: ታሪክ ከሚያስተምረን ነገሮች አንዱ ያለፈውን ታሪክ ሁሉ ጥለው አዲስ ታሪክ ከባዶ ሜዳ ላይ ለመጀመር የፈለጉ ሁሉ መጨረሻቸው ውድቀት መሆኑን ነው:: ታሪክን እሠራለሁ በማለት ታሪክን መሥራት አይቻልም:: ታሪክ መሥራት የሚቻለው ለአገርና ለሕዝብ በቀዋሚነት የሚያገለግልና



ለሚቀጥሉት ትውልዶች የብልጽግናና የኀብረት መሠረት በመጣል ነው:: እኔ አውቅላችኋለሁ ማለት ለሌኒንም፣ ለስታሊንም፣ ለማኦም አልበጀም:: ሁሉም ያለፉት ልጆቻቸውና ሕዝቦቻቸው የሚያፍሩባቸውና የሚረግሙዋቸው ሆነው ነው:: በጉልበታቸው ዘመን የተፈሩትን ያህል ከሞቱ በኋላ ተዋርደዋል:: ያ ውርደት የልጆቻቸውና የዘመዶቻቸው ነው፤ እነሱማ ከበድንነት ወደ በድንነት ተሸጋግረዋል:: ዱላ በድን ያደርጋል፤ ዱላ የያዘ ሰው ከዱላው ጋር ብቻ የመነጋገር ዝንባሌ ያድርበታል:: ዱላ ያልያዘ ሰው ጋር መነጋገር ውርደት ይመስለዋል:: ውርደት ስተት ብሎ የሚመጣው ዱላ በቀደደው መንገድ ነው::
ገዢዎቻችን መላ አድርገው ሊይዙት የሚገባቸው ከዱላ ጋር መነጋገርን ሳይሆን ከሰዎች ጋር መነጋገርን መሆን አለበት:: ግፍ እንደክረምት ጎርፍ ነው:: በየቤታችን አካባቢ ስናየው የወረደው ዝናብ ትንሽ ይመስላል:: በያለበት የወረደው ሁሉ ሲጠራቀም ትልቅና ኃይለኛ ጎርፍ ይሆንና ብዙ ጥፋትን ያደርሳል:: ግፍም ሲጠራቀምና የማይችሉት ሸክም ሲሆን የከፋ ጥፋትን ያስከትላል:: ይህ ከመሆኑ በፊት በግፍ መቀጠል የማያዛልቅ መሆኑን ተገንዝቦ የተለየ ሀሳብ ካላቸው ጋር ለመነጋገር በቆራጥነት መወሰን ያስፈልጋል:: ከአብዛኛው ሕዝብ ጋር የተጣላ ሥርዓት በጦርነት ማሸነፍ አይችልም:: መነሻውና መጀመሪያው ይኸ ነው:: ጉልበት ያለውና በጉልበት የሚተማመነው አዲስ መላን ሲቀበል ሌሎችም መላቸውን ለመለወጥ ይገደዳሉ:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጎትና ምኞት ሥልጣኑን በሰላም መረከብ ነው:: ለኢትዮጵያ ሕዝብም ሆነ ለተወሰነ ክፍለ ሕዝብ የቆመ ድርጅት ሁሉ ከዚህ የተለየ ዓላማ ሊኖረው አይችልም::

የተለያዩ የአገር ክፍሎች የአስተዳደር ሥልጣንም ሆነ የመገንጠል ጥያቄ፣ የመሬትም ሆነ የሌላ የኢኮኖሚ መብት በሕዝብ መወሰን አለበት ብለን ከተማመንን ውይይትንና የጉዳዮቹን ከባድነት የምንፈራበት ምንም ምክንያት አይኖርም:: የችግሮቹ ሁሉ መነሻ የሕዝብን የሥልጣን ባለቤትነት መፍራት ነው:: በውድም ሆነ በግድ ሕዝብ የፈለገው ነገር መሆኑ የሚቀር አይደለም:: ይህንን የታሪክ ፍርድ ለመቀበል ከተራ አእምሮ በላይ አይጠይቅም:: የሕዝብን መንፈስና አእምሮ አፍኖ፣ አካሉን ረግጦ በመግዛት ወደ ብልጽግናና ወደ ጥንካሬ እመራዋለሁ ማለት ዘበት ነው:: ወንበሩ ላይ የተቀመጡትም ሆኑ ተቀናቃኞቻቸው አስተሳሰባቸውን ከዚህ በሽታ ማፅዳት አለባቸው:: በቅን መንፈስ መነጋገር የሚቻለው ከዚያ በኋላ ነው::

ሌላም መወገድ ያለበት ችግር አለ:: የአገርንና የሕዝብን ጉዳይ እንደግል ጉዳያቸው የሚመለከቱ ሰዎች ከባድ ስሕተትን ይፈጽማሉ:: የግል ጥላቻና የግል ጠብ በአገር ጉዳይ ውስጥ ቦታ የላቸውም:: የተለያየ ሀሳብ ይዘው በአገር ጉዳይ ላይ የሚነጋገሩ ሰዎች የሥልጣን ተቀናቃኞች እንጂ ጠላቶች አይደሉም:: በመሠረቱ ጠላት የሚባለው ሊያጠፉት የሚፈልጉትን ነው::

የሥልጣን ተቀናቃኞች ዓላማ መጠፋፋት አይደለም፤ ሀሳብንና ሀሳብን በተግባር በማሳየት በሕዝብ ዳኝነትና በሰላም መሸናነፍ ነው። የሕዝብ ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ሰዎች ይህንን ያህል ቅን መንፈስ ማሳየት ይጠበቅባቸዋል። ጠላትነት ሲኮተኩቱ ለየግላቸው ሳይሆን ለሕዝብ፣ የሚያስከትለውም አደጋ ከፍተኛ እንደሆነ መገንዘብ አለባቸው። ለዚህ ነው ከዱላው ይልቅ ወደ መላው ማዘንበል የሚያሻው።

## 4 መደምደሚያ

የግፍ መሣሪያ የሆነውን ዱላ ለመጣል የአእምሮና የመንፈስ ብቃት ከተገኘ መላው የሚገኘው ከመነጋገር ብቻ ነው። ንግግሩ ፍሬአማ እንዲሆን ሥልጣን በዱላ የያዙትና ሥልጣን በዱላ ለመያዝ የሚፈልጉት ሁሉ በቅን መንፈስና በቆራጥነት ከራሳቸው ይበልጥ አገሪቱንና ሕዝቡን አስበልጠው ለትልቅነት በሚያበቃቸው ወኔ ዱላቸውንና ዛቻቸውን ጥለው መቀራረብ አለባቸው። ይህንን ለማድረግ ሁሉም ወገን ሊያምንባቸውና ሊቀበላቸው የሚያስፈልጉ ጉዳዮች አሉ። እነዚህም በቅደም ተከተል ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ናቸው።-

የኢትዮጵያ ሕዝብ የመጨረሻው የበላይ ባለሥልጣን ስለሆነ ያለ ሕዝብ ፈቃድ ምንም ዘለቄታ የሚኖረው ውሳኔ ማድረግ አይቻልም። በሕግ ለሕግ የሚተዳደር ሕዝብ በሰው አይገዛም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የተረጋጋና ዋስትና ያለው ኑሮ ለማካሄድ ሰላም ናፍቆታል፤ ሰላምን ይሻል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከድንቁርናና ከደህነት ለመላቀቅ፤ በሙሉ ኃይሉ ሠርቶ ለማምረትና ወደ ዘመናዊ የብልጽግና ኑሮ ለመግባት ይፈልጋል፤ ገበሬውና ሠራተኛው አምርቶ፣ ነጋዴው ነግዶ፣ ባለሙያው በየሙያው በሙሉ ልብ ሠርቶ ሁሉም የራሱ ባለቤት ሆኖ በሕግ ጥላ ስር የሚኖርበትን ቀን እየጠበቀ ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነቱን በሕግና በሥርዓት ካልተረከበ ሰላም አይኖርም፤ ሰላም ከሌለ እድገትና መሻሻል አይመጣም።

በአለፉት ሀያ አምስት ዓመታት ውስጥ የተገነባው ሲፈርስ፣ የሠራው ሲወቀስ፣ የሚያላግጠው ሲወደስ፣ የተማረው ወይ ሲገደል፣ ወይ ሲታሰር፣ ወይ ሲሰደድ፣ በተለያዩ የዘመኑ ዜና ማሰራጫዎች ሕዝብን ማታለል ልዩ ጥበብ ሲሆን፣ በደርግ ዘመን በመደብ አሁን ደግሞ በጎሠኛነት ሕዝብ ሲታመስ አይተናል፤ እያየንም ነው። በነዚሁ ዓመታት ውስጥ ኢትዮጵያውያን ከመቼውም ጊዜ የበለጠ በችጋርና በስደት የታወቁ ሆኑ። ገና አላቆመም። የኢትዮጵያውያን ኩራትና ክብር ተሙዋጠጠ፤ በቀላሉና በትንሹ ራስን መሸጥና መለወጥ አዲስ ባህል ሆነ። የሚሸጥና የሚለወጥ ለከፉ ቀን እንደማይሆን ሳልተገነዘብን በዓለም ሁሉ የተከበሩና ኢትዮጵያንም ያስከበሩት አፄ ኃይለ ሥላሴ ብቻቸውን ሲሞቱና



የቀብር ሥርዓት እንኳን ሳያገኙ አየን፤ ኮሎኔል መንግሥቱ ብቻቸው መላ ከዱላ የሚሻለው።

በትንሽነት ትልቅ ሥራ ማከናወን አይቻልም። ትልቅ ሆነውልን ተከብረው እንዲያስከብሩን እንፈልጋለን።

## አባሪ

## ለቅንጅት ምክር ቤት የስንብት ደብዳቤ

በሊቀ መንበር ኃይሉ ሻውል በኩል
ለቅንጅት ምክር ቤት አባላት
መጋቢት 29፤ 1997

### ቅንጅትና ምርጫው

ቅንጅቱ ሲመሠረት በአባል ድርጅቶች ሁሉ የታመነበት ዓላማ በዚህ ምርጫ በድል አድራጊነት መውጣት ነበር፤ ቅንጅቱ መንቀሳቀስ ከጀመረመረም በኋላ በአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን የቅንጅት ምልእክተኞች በደረሱባቸው ከተማዎች በሙሉ ቅንጅት በኢትዮጵያ ሕዝብ (በገጠሬውም ሆነ በከተሜው) ላይ የጫረው አዲስ ተስፋ ከተጠበቀው በላይ በጣም ከፍተኛ እንደሆነ ለመገንዘብ ችለናል፤ ዛሬ ቅንጅት ሰፊ የሆነ የሕዝብ ድጋፍ እንዳለው አያጠራጥርም፤ ከሁሉም በላይ ቅንጅት በጫረው ተስፋ ምክንያት ሕዝቡ በአደባባይ ራሱን አጋልጦአል፤ ስለዚህም በቅንጅት ላይ የማሸነፍ ግዴታ ወድቆበታል፤ ይህንን ምርጫ አገዛዙ ቢያሸንፍ በኽዝቡ ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት መገመት ብዙ መመራመርን የሚጠይቅ አይደለም፤ በእኛ ላይ የበለጠ ኃላፊነትን ሊጭንብን የሚገባው ይህ አስከፊ ሁኔታ ነው።

ነገር ግን ቅንጅቱ ከተቋቋመ ጀምሮ የቅንጅትን ድል የማድረገረ ዓላማ የሚጻረሩ ሁለት አዝማሚያዎች ለእኔ በግልጽ ሲታዩኝ ቆይተዋል፤ አሁን ለምርጫው የቀረው አምስት ሳምንታት ያህል ነው፤ ቅንጅት እነዚህን አፍራሽ አዝማሚያዎች ይዞ ከቀጠለ ድል የማድረጉ ዓላማ ቢያንስ የደበዘዘ እንደሚሆን ይታየኛል፤ ቅንጅት ድልን የማጣቱ ውጤት የኢትዮጵያን ሕዝብ ተስፋ ከማስቆረጡ ጋር ተያይዘው ብዙ ከባድ ጥያቄዎች ይነሣሉ፤ የተለያዩ መልሶችም ይሰጣሉ፤ ዛሬ ቅንጅት በግልጽ ተነጋግሮባቸው ሊፈታቸው ያልቻላቸው ቅራኔዎች በዚያን ጊዜ ገሀድ ይወጣሉ፤ በአደባባይ በይፋ መወነጃጀሉ የማይቀር ይሆናል፤ በምርጫው የሚወድቁት ሰዎች ያለጥርጥር ይከፋሉ፤ በምርጫው የቀናቸው ሰዎች ሠራዊት የሌለው ጄኔራሎች ይሆናሉ፤ የዛሬው ሁኔታ በሰኔ በፍጹም ይለወጣል።

ለእኔ እንደሚታየኝ የቅንጅቱ አባሎች በሰኔ የሚፈጠረውን ሁኔታ ዛሬ በዓይነ አእምሮአቸው ማየት ግዴታቸው ይመስለኛል፤ አስቸጋሪ መሆኑ ይገባኛል፤ ግን ይቻላል፤ ቅንጅት በድል አድራጊነት ቢወጣ የሚያስከትለውን በአገሪቱ ሁሉ የሚያስተጋባ እልልታ በቅንጅት አባሎች ላይ ከሚጥልባቸው ከባድ ኃላፊነት ጋር ቀድሞ ማየት የሚሳነን አይመስለኝም፤ ቅንጅቱ ቢሸነፍ ግን በአገሪቱ በሙሉ ብቻ ሳይሆን በውጭም የሚያስተጋባ ኡኡታና በቅንጅት



አባሎች ላይ የሚሰነዘረውን የመረረ ነቀፌታ እንዴት እንደምንጋፈጠው ከአሁኑ ማሰብ ተገቢ ይመስለኛል፤ የአንድ አገር ሕዝብን ተስፋ አጨናግፎ በሰላም መኖር ያስቸግር ይሆናል፤ በሁለቱም አቅጣጫዎች ሊታሰብ ይገባል፤ በሰኔ ለማሰብ ጥቂት ይረፈረዳል፤ ዛሬ ባለንበት ሁኔታ ቅንጅቱ ቢያሸንፍ ምን እንደሚያደርግ የታወቀ ነገር የለም፤ እዚያ ስንደርስ እንወጣዋለን ተብሎ የታለፈ ጉዳይ ነው።

ቅንጅት ለድል እንዳይበቃ የሚፈታተኑት ሁለት አዝማሚያዎች በውስጡ እንዳሉ ይታየኛል፤ አንዱ ሁላችንም በደንብ የምናውቀውና መፍትሔ ልናገኝለት ሞክረን ያቃተን የመኢአድና የኢዴአፓ/መድኅን የማይበርድ ባላንጣነት ነው፤ በሁለቱ መሀከል ያለው ፉክክር ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ቦታ ያለው አይመስልም፤ ትልቁና ዋናው ዓላማ አንዱ ሌላውን በማናቸውም መንገድ መብለጥ ነው፤ እንዲህ ያለ መንፈስ በነገሡበት በመተባበር፣ በመረዳዳትና በአንድነት ምርጫው ለቅንጅት የተመቻ እንዲሆን ለማድረግ አይቻልም። ቅንጅት ያለበት የገንዘብ እጥረት ሳያንሰው ሁለቱ ድርጅቶች ያላቸውን የሰው ኃይል ማቀናጀትና ማስተባበር ባለመቻላቸው ብዙ መራጮች ያመልጡናል የሚል ከባድ ስጋት አለኝ፤ የሁለቱ ቡድኖች ባላንጣነት ከአገር አልፎ በአሜሪካም እንዳለ ያለጥርጥር መናገር ይቻላል፤ ቡድኖቹን ከአሜሪካ ጋር የሚያይዛቸው የገንዘብ ስንሰለት ዓላማ ግልጽ አይደለም፤ ከአገር ዓላማ ጋር የተያያዘ ከሆነ ሰጪዎችም ሆኑ ተቀባዮች በአንድነት መራመዱን የማይፈልጉበት ምክንያት ምን አለ? በአሜሪካ ላሉ የየቡድኑ ደጋፊዎች ከድል በኋላ ለሚሆነው ቃል የገባላቸው አለ?

በተለያየ ሁኔታ የሁለቱ ቡድኖች ባላንጣነት አገርን ሊጎዳ የሚችልበት ደረጃ ላይ ደረሰ ይመስለኛል፤ ባላንጣነቱ የደረሰበትን ደረጃ የሚያመለክተው አንድ የመኢአድ አባልና አንድ የኢዴአፓ አባል በአንድ ላይ ተቀምጠው የቅንጅቱን ተግባር ለመፈጸም የማይችሉ መሆናቸው ነው፤ እንደዚህ ያለ ወደጥላቻ ያመዘነ ስሜት በልብ ቋጥሮ የቅንጅትን ዓላማ ለማሳካት አይቻልም፤ በአንድ በኩል የግል ዓላማ ከድርጅት ዓላማ ጋር፣ በሌላ በኩል የድርጅት ዓላማ ከቅንጅቱ የአገር ዓላማ ጋር እየተጋጨና እየተቃረነ እርስበርስ መዳከምን አንጂ አብሮ በአንድነት መጠናከርን የማያስገኝ እየሆነ ነው፤ ዛሬ ተደባብሶና ተዳፍኖ ያለው ጥላቻና ቂም ነገ ገሀድ ይወጣል፤ የዚህን ስጋት ውጤት የቅንጅት አባሎች በግለሰብም ሆ በድርጅት ደረጃ አስከሰኔ ቆይተን እንየው ካሉ አውቀውም ይሁን ሳያውቁ «ፖሊቲካ ደኅና ሰንበት» ማለታቸው ይሆናል፤ በፖሊቲካው ትግል ውስጥ የቆዩት የሁለቱ ቡድኖች አመራር አካሎች በራሳቸው ላይ ያንዣበበውን የፖሊቲካ ክስረት መገመት ያቅታቸዋል ብሎ ለማመን ያስቸግራል፤ ጥላቻ ችሎታን እንደሚቀንስ የታወቀ ነው።

የቅንጅቱን የሰው ኃይል ማቀናጀት ከባድ ችግር በሆነበት ጊዜ ቢሮን፣ ቁሳቁስንና ገንዘብን በተቀናጀ ሁኔታ ለመጠቀምና ተፈላጊውን ውጤት ለማስገኘት እንዴት ይቻላል? በአጠቃላይ የሁለቱ ትልልቅ ድርጅቶች ፉክክር ቅንጅትን ለተፈለገው ውጤት እንዳያበቃው አደረገ መሆኑን ማየትስ እንዴት ይሳነናል? ጊዜው ሳያልፍ ቆራጥ እርምጃ ተወስዶ መታረምና ቅንጅቱ በእውነት የሚቀናጅበትን መንገድ መቀየስ አስቸኳይ ግዴታችን እንድናደርገው ያሻናል፡፡

ሁለተኛው ችግር የድርጅቶች ሳይሆን የግለሰቦች ነው፤ ግለሰቦቹ በድርጅታቸውም ውስጥ ሆነ በቅንጅቱ ውስጥ ቁልፍ ቦታና የተግባር ተሳትፎ ያላቸው ከሆኑ ተጽእኖአቸው ድርጅታቸውን አልፎ ቅንጅትንም ይነካል፤ አንዳንድ ግለሰቦች ይህንን የ97ን ምርጫ እንደዓላማ ሳይሆን ለሌላ ዓላማ (ለ2002 ምርጫ) መረማመጃ አድርገውይመለከቱታል፤ ስለዚህም ለአንዱ የቅንጅት አባል ዓላማ የሆነው ለሌላው የቅንጅት አባል ስልት ነው፤ የዚህ ውጤት ውዥንብርና መደናበር፣ አለመግባባትም ይሆናል፤ ፓርቲዎች የብዙኃኑን ዓላማ ማራመጃ መሣሪያዎች መሆናቸው ቀርቶ የግለሰቡን ዓላማ ማራመጃ መሣሪያ እንዲሆኑ ማድረግ የፖሊቲካን ትርጉም ይለውጠዋል፤ ወይም ሌኒኒስት ያደርገዋል፡፡

ለእኔ እንደሚመስለኝ ፖሊቲካ የጋራ ዓላማ ይዘው በጋራ ስልት የሚመሩ ሰዎች ተግባር ነው፤ በአንድ የኳስ ቡድን ውስጥ ሦስቱ አጥቂዎች በጨዋታው አናሸንፍም ብለው አቅዋም ከያዙ በተግባር የተለየ ለማድረግ በጣም አስቸጋሪ ነው፤ (አንዱ) ዓላማ ብሎ የሚፍጨረጨርበትን ስልት ብቻ አድርጎ የሚመለከተው ያቀልለዋል፤ በአስተሳሰብ ከቅንጅቱ ጋር አልተቀናጁም ማለት ነው፤ ኢትዮጵያ ተመልሳ በወያኔ/ኢሕአዴግ ቀንበር ስር ከወደቀች የእኛም ውድቀት መሆኑን ያልተገነዘቡና ለ2002 ምርጫ የሚዘጋጁ ሰዎች በመሀከላችን የሉ ይመስለኛል፤ በየዋህነት ከአየነው የዋህነት ይመስለኛል፡፡

ለድርጅታችን ያወጣነው ስም ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ የሚል ነው፤ ታዲያ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የምንመኘውን አንድነት እኛ በውስጣችን ማሳየት የለብንም? ዴሞክራሲ ማለት የተለያዩ አስተያየቶችን በሰላምና በቅንነት ማስተናገድ ከሆነስ በእኛ መሀከል እንዲህ ያለ አሠራርና መንፈስ መለመድ የለበትም?በለስ ቀንቶን ብናሸንፍስ እንዴት ተብሎ ነው አገርን ማስተዳደር የሚችል መንግሥት ማቋቋም የምንችለው? በየሥልጣኑ ሥፍራ ላይ የሚደለደሉትን ሰዎች እንመድብ ሲባል እንደቀላል ነገር እየተመለከትነው እስካሁን አልተቻለም፤ ምክንያቱ መፈራራት መሆኑ ግልጽ ነው፤ ምን ዓይነት የጥላቻና የእርስበርስ መጠላለፍ አስተዳደር ሊመሠረት ነው?

ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች የሉም ብሎ መካዱ መፍትሔ አይሆንም፤ የሉም በማለት ብቻ አናጠፋቸውም፤ መፍትሔው በእውነትና በቁርጠኛነት፣



በንጹሕ ኅሊናና በመተማመን ተነጋግረን የመጨረሻ መፍትሔ ስናገኝላቸው ብቻ ነው፡፡

ትናንት ለየብቻችን ስንፎካከር ያደረብንን ቁጪትና ቂም ዛሬም በአንድ ላይ ሆነን ተሸከመነው መቀጠሉ አውቀንም ይሁን ሳናውቅ ነገ መርዙን በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ለማራገፍ ያቀድን ያስመስላል፤ ያስከብራል ብለን የገባንበት ተግባር ለአሳፋሪ ውርደት ሊዳርገን እየተፈታተነን ነው፤ራሳችንን አሸንፈን ፈተነውን ሳናልፍ ወያኔ/ኢሕአዴግን ለማሸነፍ የምናደርገው ትግል ይሰምርልናል ማለት ከንቱ ምኞት ነው፡፡

በመጨረሻ አንድ ሀሳብ ላቅርብ፤ በሁለት ደረጃዎች የሚገለጥ ነው፤ በመጀመሪያው ደረጃ የቅንጅቱ የምክር ቤት አባላት ከልብ ተነጋግረቀውና ያለፈውን እርግፍ አድርገው ትተው ለወደፊቱ በአንድነት ለቅንጅት ለመሥራት ቃል ኪዳናቸውን ማደስ ያስፈልጋቸዋል፤ በሁለተኛ ደረጃ የቅንጅቱን ዓላማ ሰፋ ላለ መድረክ ለማስተዋወቅና ቃል ኪዳናችንን ለማጠናከር ጉዳዩን ሰፋ ያለ ጉባኤ እንዲወያይበት አድርገን ቅንጅቱ በምርጫው በድል እንዲወጣ ማረጋገጥ አለብን፤ የአራቱም አባል ድርጅቶች የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴዎች በአንድ ላይ ተሰብስበው፣ ተወያይተው አንድ ውሳኔ ላይ እንዲደርሱ ጊዜውና ቦታው ተመቻችቶ እንዲገለጽ ሀሳብ አቀርባለሁ፡፡

ጥላቻን በፍቅር፣ ቂምን በይቅር ባይነት፣ ጥርጣሬን በልበ-ሙሉነትና በመተማመን፣ የግል የሥልጣን ጥምን በአገር ፍቅር ስሜት አሸንፈን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነጻነት አስተማማኝ ምክንያት ለመሆን እግዚአብሔር ልባችንን ለበጎ መንፈስ ይክፈትልን፡፡

ይህ እስከሚሆን ድረስ ከዚህ ቀን ጀምሮ በቅንጅቱ ውስጥ የማልገኝ መሆኑን ስገልጽ በመሪር ሐዘን ነው፡፡

ታዛዥዎ

መስፍን ወልደ ማርያም